


# ጌታን በመዝሙር ማመስገን መልካም ነው

ፍጥረት ሁሉ እንደየባሕርዩ እግዚአብሔርን የሚያመሰግን መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ (መዝ 148)። ሰው እግዚአብሔርን ለማመስገን ያለው የተፈጥሮ ዝንባሌ ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው። ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት በሚሰጡት ብርሃን፥አዝርዕት አትክልት ዕፅዋት በሚያበረክቱት ፍሬ፥ እንስሳት አራዊት አዕዋፋት በሚያሰሙት ድምፅ እግዚአብሔር ይመሰገናል። አዳምና ሔዋን ልጆቻቸውም ለፈጣሪያቸው የሚያቀርቡትን ምስጋና በመዝሙር ይገልጹታል።

የዳዊት መዝሙር፥በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት መጻሕፍት መሃከል በምእመናን ዘንድና በየአብያተ ክርስቲያኑ ተዘውትሮ የሚነበብ፥የሚዘመርና የሚጸለይ መጽሐፍ ነው። ይህም ያለምክንያት አይደለም። በመጀመሪያ፥ እያንዳንዱ ምእመን በሥጋዊ ኑሮውና በመንፈሳዊ ሕይወቱ ከራሱ፥ ከሌላው ሰውና ከፈጣሪው ጋር ስላለው ግንኙነት በአእምሮው የሚያስበው፥በመንፈሱ የሚሰማውና በአካሉ የሚደርስበት ክፉውም ሆነ ደጉ እንደየሁኔታው በመዝሙራቱ ውስጥ ጎልቶ የተጻፈ መሆኑን ይመለከታል። ዳግመኛ፥ ለእግዚአብሔር ሊያቀርበው የሚፈልገው ምስጋና፥ልመና ወይም የንስሐ ጸሎት በመዝሙራቱ ውስጥ እንደየአግባቡ አንድ በአንድ የተዘጋጀለት ሆኖ ያገኘዋል። በመጨረሻ፥ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ደረሰበት መከራ፥ስለ ሞቱና ስለ ትንሣኤው ራሱ ይጠቅሳቸው የነበሩትና በመዝሙራቱ ውስጥ ያሉት ሌሎቹ የትንቢት ቃላት ተሟልተው በትክክል የተፈጸሙ መሆናቸውን ይገነዘባል። በዚህ ሁሉ እጅግ ስለሚረካና ስለሚጽናና፥ደስም ስለሚለው መጽሐፉን ከመውደድና ከማዘውተር ይደርሳል።

አዎን፥ምስጢሩ እየተገለጠና ትንቢቱ እየተፈጸመ፥ ዘላለማዊ መልእክቱም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ከዚህ ዘመን የደረሰው ይህ የመዝሙር መጽሐፍ፥በእርግጥ ሊወደድና ሊዘወተር ይገባዋል።

# የዳዊት መዝሙራት

## መግቢያ

ይህ የምስጋናና የጸሎት መጽሐፍ በምዕራፍ ተለይተው በአምስት ክፍሎች የተመደቡ 150 መዝሙራት ይገኙበታል። በውስጡ ያንዳንድ ገጣሚዎች ድርሰት ታክሎበታል ቢባልም፣ አብዛኛው ዝግጅት፣ ስሙን ለመጽሐፉ መጠሪያ የሰጠው የአንድ ገናና ባለቅኔና መዘምር ሥራ መሆኑ ተረጋግጧል። ይህ ሰው፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺህ ዓመት ግድም የኖረውና ከእረኝነት እስከ ንጉሥነት ባሳለፈው ረዥም ዘመኑ ውስጥ ብዙ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ደርሰውበት የነበረው ነቢዩ ዳዊት ነው። እርሱም በፈጣሪው ላይ ባለው ጽኑ እምነትና ፍቅር ብቻ ሁሉንም አሸንፎ፣ በእግዚአብሔር ለሚተማመኑ ሰዎች እነሆ ታላቅ ምሳሌ ለመሆን በቅቷል፤ ከአምላኩም ዘንድ የዘላለምን ቃል ኪዳን ለመቀበል ታድሏል።

---

## አንደኛ መጽሐፍ

ከመዝሙር 1-41

### መዝሙር 1

1 የክፉ ሰዎችን ምክር የማይከተል፣ በኃ
ጢአተኞች የበደል ሥራ የማይካፈል፣ በእግ
ዚአብሔር ሥራ ከሚቀልዱ ፌዘኞችም ጋር
የማይውል ሰው ምንኛ የተባረከ ነው! 2 እን
ዲህ ያለው ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ
በመፈጸም ይደሰታል። የእግዚአብሔርን
ቃል እንዴት አድርጎ ሊከተል እንደሚችል
ሁልጊዜ በማሰላሰል ቀኑንም ሌሊቱንም ያሳ
ልፋል።

3 የዚህ ሰው ሕይወት በፈሳሽ ውሃ ዳር
እንደ ተተከለችና ጣፋጭ ፍሬዋን ያለማቋ
ረጥ በወራቷ እንደምትሰጥ፣ ቅጠሏም እንደ
ማይረግፍ ዛፍ ይለመልማል። የሚያደርገ
ውም ሁሉ ይባረክለታል።

4 የክፉዎች ሁኔታ ግን እንዲህ አይደ
ለም፤ ከዚህ ፈጽሞ የተለየ ነው። እነርሱ
ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ገለባ ናቸው፤
5 በመጨረሻው የፍርድ ቀንም አይድኑም።
ኃጢአተኞች በዚያን ጊዜ በጻድቃን መካ
ከል ሊቆሙ አይችሉም።

6 እግዚአብሔር የጻድቃንን አሳብና አኗ
ኗር አንድ በአንድ ያውቃል፤ የክፉዎች አሳ
ብና አኗኗር ግን ጨርሶ ይጠፋል።

### መዝሙር 2

1 ስለ ምን አሕዛብ በእግዚአብሔር ላይ
ያምፃሉ? ሕዝቡስ ስለ ምን ከእነርሱ ጋር
በከንቱ ይዶልታሉ? 2 እነሆ የዓለም መንግ
ሥታት መሪዎች በአንድ ዓላማ በኅብረት
ተነሡ፤ ከባለሥልጣኖቻቸውም ጋር ተሰብስ
በው በእግዚአብሔርና በመሲሑ ላይ ሤራ
አደረጉ። 3 «በሉ እንግዲህ፣ እኛን ያሰሩበ
ትን ሰንሰለታቸውን እንበጣጥስ፤ የአገዛዝ ቀን
በራቸውንም ከላያችን አሽቀንጥረን እን
ጣል» ሲሉ ተስማሙ።

4 ዙፋኑ በሰማይ የሆነው አምላክ ግን
በሤራቸው ከንቱነት ያፌዝባቸዋል፤ በማይ
ረባ ዕቅዳቸውም ይዘብትባቸዋል። 5 በዚያን
ጊዜ በቊጣው ይገሥፃቸዋል፤ በመዓቱም
ያሸብራቸዋል።

6 «እኔ የቀባሁትን ንጉሥ በተቀደሰችው
ተራራዬ በጽዮን ላይ አነገሥሁት» ይላቸ
ዋል።

7 ንጉሡም እንዲህ ይላል፡- «እነሆ የእግ
ዚአብሔርን አዋጅ ገልጬ እናገራለሁ።
እርሱ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፡- ‘አንተ
ልጄ ነህ፤ እኔም ዛሬ ወለድሁህ። 8 ለምነኝ፤
በምድር ላይ የሚኖሩትን አሕዛብ ሁሉ የአ
ንተ ዜጎች እንዲሆኑ እሰጥሃለሁ፤ መላው
ዓለም የአንተ ይዞታ ትሆናለች። 9 አንተም
እንደ ብረት በጠነከረ በትረ መንግሥት ታስ
ተዳድራቸዋለህ፤ እንደ ሸክላ ዕቃም ታደቃ
ቸዋለህ።’»

10 ስለዚህ እናንተ የዓለም መንግሥታት
መሪዎች፣ ይህን ማስጠንቀቂያ በማስተዋል
አመዛዝኑት። 11 እግዚአብሔርን በፍርሃት
አገልግሉት፤ በመንቀጥቀጥም 12 በእግሩ ሥር
ወድቃችሁ ስገዱለት፤ አለበለዚያ ቊጣው
ፈጥኖ ይገለጣል፤ እናንተም ሳታስቡት

በድንገት ትሞታላችሁ።
እግዚአብሔርን መጠጊያቸው የሚያደ
ርጉ ሁሉ ግን የተባረኩ ናቸው!

## መዝሙር 3

1 እግዚአብሔር ሆይ ፣ ጠላቶቼ ምንኛ
እንደ በዙ ተመልከት። እኔን ለመጕዳት
በክፋት የተነሡብኝ ባለጋራዎቼ እጅግ
ብዙዎች ናቸው። 2 «አምላኩ አያድነ
ውም» እያሉ ብዙዎች ስለ እኔ ይናገራሉ።
3 አንተ ግን አቤቱ ፣ ጠላቶቼ እንዳያጠቁኝ
ተከላካለህ የምታድነኝ ጋሻዬ ነህ፤ ራሴን
ከደፋሁበት ቀና የምታደርግልኝ መከበሪ
ያዬ አንተ ነህ።
4 ከመጨነቄ የተነሣ ድምፄን ከፍ አድ
ርጌ ወደ እግዚአብሔር ጸለይሁ፤ እርሱም
በተቀደሰ ተራራው ሆኖ ሰማኝ። 5 ከዚህ
በኋላ ተኛሁ፤ የሰላምም እንቅልፍ ወሰደኝ።
እግዚአብሔር ሌሊቱን ሙሉ ጠብቆኛልና
ጠዋት በደኅና ነቅቼ ከመኝታዬ ተነሣሁ።
6 በዐመፅ ተነሥተውብኝ የከበቡኝ ጠላቶቼ
በብዙ ሺ የሚቈጠሩ ቢሆኑም ከእንግዲህ
አልፈራም።
7 አሁንም ፣ «አቤቱ ፈጣሪዬ ሆይ ፣
ተነሥ ፣ አድነኝ» እያልኩ ወደ አንተ እጮሃ
ለሁ። አንተ ከዚህ በፊት የተነሡብኝን ጠላ
ቶቼን ሁሉ ቅስማቸውን ሰብረህ አዋርደህል
ኛል፤ ክፉዎችንም ጕልበታቸውን አቅልጠህ
አድክመህልኛል።
8 የደኅንነት ረድኤት የሚገኘው ከእግዚ
አብሔር ብቻ ነው፤ በረከትህ ምን ጊዜም
ከሕዝብህ አይለይ።

## መዝሙር 4

1 የምታጸድቀኝ አምላክ ሆይ ፣ በምጠራህ
ጊዜ ሁሉ መልስልኝ። ካለሁበት መከራና
ጭንቀት እፎይ የምልበትን ዕረፍት ስጠኝ።
ጸሎቴን ሰምተህ ምሕረትህን አድርግልኝ።
2 እናንት የሰው ልጆች ፣ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላችኋል፤ «እስከ መቼ ራሳችሁን
እያታለላችሁ የሐሰት አምልኮ ስትከተሉ
ትኖራላችሁ? ይህንንም በማድረግ ክብሬን
ወደ ውርደት ስትለውጡ የምትኖሩትስ
እስከ መቼ ነው?»
3 ጌታ ጻድቃንን ለራሱ የመረጣቸው
መሆኑን እወቁ። እኔም ወደ እርሱ ስጮህ
ይሰማኛል።
4 እናንተም የቍጣ ስሜት ባደረባችሁ
ጊዜ ኃጢአትን እንዳትፈጽሙ ተጠንቀቁ፤
በመኝታችሁ ላይ ሳላችሁ ጸጥ ብላችሁ
ልቦናችሁን መርምሩ።
5 በእግዚአብሔር ተማምናችሁ እርሱን
የሚያስደስተውን መሥዋዕት አቅርቡለት።
6 «መልካም የሆነውን ነገር ማን ሊያሳ
የን ይችላል?» ብለው ብዙዎች ይጠይ
ቃሉ። ስለዚህ ጌታ ሆይ ፣ የፊትህን ብርሃን
በእኛ ላይ ግለጸው። 7 የስንዴውና የወይኑ ፣
የዘይቱም ምርት በዝቶ በሚገባላቸው ጊዜ
ሰዎች ከሚሰማቸው ደስታ ይልቅ በልቦናዬ
ውስጥ ያሳደርከው ሐሤት እጅግ ይበል
ጣል። 8 አቤቱ ፣ የሰላም ዋስትና ባለው ሕይ
ወት ውስጥ ስለምታኖረኝ ፣ በምተኛበት ጊዜ
በሰላም አንቀላፋለሁ።

## መዝሙር 5

1 እግዚአብሔር ሆይ ፣ ጸሎቴን ስማ፤ መቃ
ተቴንም ተመልከት። 2 እንድትረዳኝ የም
ጮኸውና የምጸልየው ፈጣሪዬና ንጉሤ
ወደ ሆንከው ወደ አንተ ብቻ ነውና አድም
ጠኝ። 3 በዚህ ጸሎቴ ዘወትር ጧት ጧት
ፍላጎቴን ዘርዝሬ አቀርብልሃለሁ፤ መልስህ
ንም በተስፋ እጠባበቃለሁ፤ አንተም የልመ
ናዬን ድምፅ ትሰማለህ።
4 አቤቱ ፣ የዐመፅ ነገር ደስ የሚልህ አም
ላክ አለመሆንህን አውቃለሁ፤ ክፉ የሆነው
ሁሉ ወደ አንተ ከቶ አይቀርብም። 5 በአ
ንተ ፊት እብሪት ያደረበት ኃጢአተኛ
ሊቆም አይችልም። ጌታ ሆይ ፣ ክፉ አድራጊ
ዎችን ሁሉ ትጠላለህ፤ 6 ሐሰት የሚናገሩ
ትን ታስወግዳቸዋለህ፤ የሰውን ደም ለማፍ
ሰስ የሚጣደፉትንና በአታላይነት የሚኖሩ
ትን ትጸየፋቸዋለህ።
7 እኔ ግን ታላቅ በሆነው መሐሪነትህ
ተማምኜ ወደ ቤትህ እገባለሁ፤ አክብሮት
በተሞላበት ፍርሃትም ወደ መቅደስህ እሰግ
ዳለሁ። 8 ስለዚህ ጌታ ሆይ ፣ ጠላቶቼ ፣ «አሸ
ነፍነው» እንዳይሉ በጽድቅህ ምራኝ። መን
ገዴንም በፊትህ ቀና አድርግልኝ።
9 የጠላቶቼ ልቦና ሰውን በሚያጠፋ
አሳብ የተሞላ ነው፤ ከአፋቸው የምትወጣው
አንዲቷ ቃል እንኳ አትታመንም። ጕሮሮአ
ቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው። ምላሳ
ቸው ከሽፍጥ በቀር እውነትን ከቶ አይናገ
ርም። 10 ስለዚህ እግዚአብሔር ሆይ ፣ በዚህ
ጥፋታቸው ወንጀለኞች መሆናቸው እንዲ
ታወቅ አድርግ። ለሌላው ያዘጋጁት የተን
ኰል ወጥመድ የራሳቸው መጥፊያ ይሁን።
በአንተ ላይ ዐምፀውብሃልና ስለ ሠሩት
ኃጢአት ከፊትህ አርቃቸው።
11 አንተን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ

ግን ደስ ይበላቸው፤የሐሤት መዝሙር ምን
ጊዜም ይዘምሩልህ ፤ አንተም ከለላ ሆነህ
ትጠብቃቸዋለህ። በዚህ ጊዜ ስምህን የሚ
ወዱ ሁሉ በአንተ በማመናቸው ታላቅ
ደስታ ይሰማቸዋል። 12 ጌታ ሆይ፣ጻድቃንን
እንዲህ ትባርካቸዋለህ ፤ ሞገስህም ጋሻ
መከታ ሆኖ እንዲጠብቃቸው ታደርጋለህ።

## መዝሙር 6

1 እግዚአብሔር ሆይ ፣ በቍጣህ አትገሥ
ፀኝ፤በመዓትህም አትቅጣኝ። 2 እነሆ ደክሜ
አለሁና እዘንልኝ ፤ በሽታዬ እስከ አጥንቴ
ደርሶ ሰውነቴ ታውኳልና ጌታ ሆይ፣እባክህ
ፈውሰኝ። 3 «እንዲህ የምሠቃየው እስከ
መቼ ነው? ወደ ፊትስ ምን ሊደርስብኝ
ይሆን?» በሚል ፍርሃት ነፍሴ እጅግ ተጨ
ንቃለችና፣አምላኬ ሆይ፣ማረኝ።
4 እንግዲህ ፈጣሪዬ ሆይ ፣ ቍጣህን መል
ስህ ከዚህ ሥቃይ አውጣኝ ፤ ምን ጊዜም
በማይለወጠው ፍቅርህ አድነኝ። 5 አለዚያ
መሞቴ ነው። የሞተ ሰው ደግሞ አያስታው
ስህም። ለመሆኑ በመቃብር ሆኖ የሚያመስ
ግንህ አለ? 6 አቤቱ ፣ በሕመሜ ምክንያት
ያለማቋረጥ በማቃሰቴ ኃይሌ አለቀ፤ሌሊቱን
ሙሉ ስለማለቅስ መኝታዬ በእንባዬ ረጥቦ፣
ትራሴም ርሶ ያድራል። 7 ለጠላቶቼ ሁሉ
መዘባበቻ በመሆኔ መራራ ኀዘን ተሰማኝ፤
ዓይኖቼም በዚሁ ጠንቅ እየተዳከሙ ሄዱ፤
ማየትም ተሣናቸው።
8 እናንት ክፉ አድራጊዎች ሁሉ ፣ ከእኔ
ራቁ። እነሆ ፈጣሪዬ ልቅሶዬን ሰምቷልና፤
9 «ማረኝ» ብዬ የለመንኩትንም ጌታዬ አዳ
ምጦአል፤አምላኬ ጸሎቴን ተቀብሎልኛል።
10 ስለዚህ ጠላቶቼ ሁሉ በኀፍረት ይሸማ
ቀቁ ፤ ኩምሽሽ ይበሉ ፤ ያልታሰበ ውርደት
አግኝቷቸው ወደ ኋላቸው ይመለሱ።

## መዝሙር 7

1 እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ ፣ በአንተ
ተማምኛለሁና ከሚያሳድዱኝ ሁሉ አድ
ነኝ። 2 ነጣቂ አንበሳ ሊበላው ያሰበውን እን
ስሳ አድፍጦ ይዞ እንደሚገነጣጥለው ሁሉ፣
እኔንም እንዲሁ ሊያደርጉኝ ነውና፣ከእጃቸ
ውም ሊያስጥለኝ የሚችል ማንም ስለሌለ
አቤቱ፣አንተ ድረስልኝ።
3 እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፣በእጄ የፈ
ጸምኩት ወንጀል ቢኖርብኝ፣በርግጥ ይህን
የመሰለ በደል ሠርቼ ከተገኘሁ፣ 4 ከእኔ ጋር
ሰላማዊ በሆነ ሰው ላይ ክፉ አድርጌ ፣
ወይም ባለጋራዬን ያለምክንያት ጐድቼው
እንደ ሆንሁ፣ 5 ጠላቴ ያሳደኝ፤ደርሶም ይያ
ዘኝ ፤ ከክብሬ አዋርዶ ፣ ሕይወቴንም አጐሳ
ቍሎ በትቢያ ላይ ይርገጠኝ።
6 እግዚአብሔር ሆይ ፣ አሁንም በቍጣህ
ተነሥ ፤ የጠላቶቼን የጭካኔ ኃይል መክት
ልኝ፤ አቤቱ ፣ ንቃ ፤ ትክክለኛ ዳኝነትህንም
ስጥ። 7 ሕዝቦች ለጉባኤ በዙሪያህ ይሰብ
ሰቡ ፤ አንተም እጅግ ከፍ ባለው መንበርህ
ላይ ተቀምጠህ ፍረድ። 8 ጌታ እግዚአብ
ሔር ሆይ ፣ ለሕዝብ ሁሉ የምትፈርድና
ከሁሉ በላይ የሆንክ አንተ ነህና ፣ አሁንም
ለእኔ እንደ ጽድቄና እንደ ቅንነቴ ፍረድ
ልኝ። 9 ጻድቅ አምላክ ሆይ፣የሰውን አእም
ሮና ልቦና መረምረህ ስለምታውቅ የክፉዎ
ችን የጭካኔ ሥራ «በቃ» ብለህ አቁም፤የጻ
ድቃንን ሕይወት ግን የተደላደለ አድርግ።
10 አዎን፣ከሁሉ በላይ የሆነው እግዚአብ
ሔር ጋሻዬ ነው ፤ እርሱ ቅን ልቦና ያላቸ
ውን ያድናል። 11 እግዚአብሔር በየዕለቱ
ቍጣውን የማይገልጽ ኃያልና ታጋሽ አም
ላክ ፣ በእውነት የሚፈርድ ጻድቅ ዳኛም
ነው። 12 ማንም ሰው ከክፉ ሥራው ካልተ
መለሰ በስተቀር እርሱ ጌታ ሰይፉን ይስ
ላል ፤ ቀስቱን አጐብጦ አውታሩን ይወጥ
ራል ፤ 13 የሚንበለበሉ ፍላጻዎቹን ያሰና
ዳል፤ለሞት የሚያደርሱ መሣሪያዎቹን ለቅ
ጣት ያዘጋጃል።
14 ክፉ ሰው ተንኰልን በልቡ ይጠነስ
ሳል ፤ ጊዜው ሲያመቸውም ፣ የጥፋት ዕቅዱ
ንና የሐሰት ወጥመዱን ይፋ ያወጣዋል።
15 ዳሩ ግን ፣ እንዲህ ያለው ሰው ለሌላው
በቈፈረው ጕድጓድ ራሱ ይገባበታል ፤
16 ሌላውን ለመጕዳት በተበተበው ደባ ራሱ
ይያዝበታል፤ሌላውን ሊያጠቃበት ባዘጋጀው
ኃይል ራሱ ይጠፋበታል።
17 ስለዚህ በእውነት ለሚፈርደው ጻድቅ
አምላክ ምስጋና አቀርብለታለሁ። ከሁሉ
በላይ ስለ ሆነው የእግዚአብሔር ስም የው
ዳሴ መዝሙር እሰማለሁ።

## መዝሙር 8

1 እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ ፣ ስምህ
በመላው ዓለም ምንኛ የገነነ ነው! ለክብ
ርህ የሚገባው ምስጋና ከሰማያት በላይ
እልፎ እንዲንሰራፋ አደረግህ። 2 ጥላቻንና
ቂምን በማጥፋት ጠላቶችህን ድል ታደርግ
ዘንድ ፣ ልጆችና የሚጠቡ ሕፃናት ከአንደበ
ታቸው ለአንተ የሚገባውን ንጹሕ ምስጋና
እንዲያሰሙ ወሰንክ።
3 የእጅህ ፍጥረት የሆኑትን ሰማያትን ፣

በየመደብካቸው ቦታ ጸንተው የሚገኙት
ንም ጨረቃንና ከዋክብትን በምሽት ቀና
ብዬ በምመለከትበት ጊዜ፥በአንክሮ እንዲህ
እላለሁ፤ 4«ኧረ ለመሆኑ ለሰው ይህን ያህል
የምታስብለትና የምትጠነቀቅለት ከቶ እርሱ
ምንድነው? 5ከመላእክት ጥቂት አሳንስ
ከው፤ ዳሩ ግን የክብርና የምስጋና ዘውድ
አቀዳጀኸው፤ 6በእጆችህ ሥራዎች ላይ
ገዢ አድርገህ ሾምከው። ከፈጠርከው ፍጥ
ረት አንድም ሳይቀር ከእግሩ በታች አድር
ገህ አስገዛህለት። 7ግዛቱም የቤት እንስሶች
ንና የቀንድ ከብቶችን፥የምድር አራዊትንና
8የሰማይ አዕዋፍን፥የባሕር ዓሣዎችንና
በውሃ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ፍጥ
ረቶች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው።»
9እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፥ስምህ
በመላው ዓለም ምንኛ የገነነ ነው!

## መዝሙር 9

1እግዚአብሔር ሆይ፥በፍጹም ልቦናዬ
አመሰግንሃለሁ፤ያደረግሃቸውንም ተአምራት
ሁሉ እናገራለሁ። 2በአንተ ደስ ይለኛል፤
ሐሤትም አደርጋለሁ። ልዑል አምላክ
ሆይ፥ለስምህ የምስጋና መዝሙር አቀርባ
ለሁ።
3ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ፤በፊ
ትህም ተሰነካክለው ይጠፋሉ። 4በጽድቅ
ለመፍረድ እነሆ በዙፋንህ ላይ ተቀምጠህ
መብቴን አስከበርህልኝ፤የምጋደልለት ዓላማ
ዬንም ደግፈህ አጸናህልኝ። 5አሕዛብን ገሠ
ፅካቸው፤ክፉዎችን አጠፋህ፤ስማቸውም ለዘ
ላለም ተረስቶ እንዲቀር አደረግህ። 6በጠላ
ቶቼ ላይ ታላቅ የጦርነት እልቂት ተከታ
ትሎ ደረሰባቸው። ከተሞቻቸውን ከመሠረ
ቶቻቸው ገለባብጠህ ደመሰስክ፤መታሰቢያ
ቸው እንኳ ደብዛው ጠፋ።
7እግዚአብሔር ግን ለዘላለም ነግሦ የሚ
ኖር አምላክ ነው። ፍርዱን ለመስጠት ዙፋ
ኑን ዘርግቷል። 8ዓለምን በጽድቅ ይዳኛል።
አሕዛብንም በትክክለኛ አስተዳደር ይገዛቸ
ዋል። 9እግዚአብሔር ለተጠቁ አምባቸው፥
የችግር ጊዜንም የሚያሳልፉበት መጠጊያ
ቸው ነው። 10ጌታ ሆይ፥ስምህን የሚያውቁ
በአንተ ይተማመናሉ፤አንተም የሚፈልጉህን
ሁሉ በመከራቸው ጊዜ አትለያቸውም።
11እንግዲህ ዙፋኑን በጽዮን ላይ ለዘረ
ጋው ፈጣሪ የምስጋና መዝሙር አቅርቡ፤
ያደረገውን ሁሉ በአሕዛብ መካከል በይፋ
ተናገሩ። 12እርሱ የሰውን ደም የሚበቀልና
ሁሉን የሚያስታውስ አምላክ ነው፤በችግር
የሚሠቃዩትንም ጩኸት ቸል አይልም።
13አሁንም እግዚአብሔር ሆይ፥ጠላቶቼ
የቱን ያህል በጭካኔ እንደሚያሳድዱኝ አይ
ተህ ምሕረትህን አድርግልኝ፤እነሆ ከሞት
አፋፍ ደርሻለሁና ከወደቅሁበት አንሣኝ።
14እኔም ምስጋናዬን በኢየሩሳሌም በሮች
ላይ ቆሜ በገሃድ አቀርብልሃለሁ፤በዚያም
ስለ ማዳንህ ሐሤት አደርጋለሁ።
15አሕዛብ ግን በቈፈሩት ጕድጓድ ራሳ
ቸው ገቡበት፤ሰውረው በዘረጉት ወጥመድ
እግሮቻቸው ተተብትበው ተያዙ። 16እግዚ
አብሔር ክፉዎችን በራሳቸው ሥራ እንዲ
ጠመዱ ያደርጋል። ትክክለኛ ዳኝነቱም
የታወቀ ነው። 17ክፉዎች ወደ ሲኦል ይወ
ርዳሉ፤እግዚአብሔርን የሚዘነጉ አሕዛብም
ፍጻሜአቸው የከፋ ነው። 18ችግረኞች ሁል
ጊዜ እንደ ተረሱ፥በመከራ የሚሠቃዩም
ተስፋ እንደ ቈረጡ አይቀሩም።
19ስለዚህ እግዚአብሔር ሆይ፥ደካማ
ፍጡር የሆነው ሰው «አሸነፍኩ» ብሎ እን
ዳይታበይ ተነሥ፤አሕዛብም በዙፋንህ ፊት
ቀርበው ፍርድህን ይቀበሉ። 20አቤቱ፥አሕ
ዛብን በሚያስፈራ ቅጣትህ አስደንግጣቸው፤
አቅመ ቢስ ሰዎች መሆናቸውንም እንዲያ
ውቁት አድርግ።

## መዝሙር 10

1እግዚአብሔር ሆይ፥በችግር ጊዜ ስለ
ምን ትርቃለህ? ስለ ምንስ ትሰወራለህ?
2ግፈኛ ሰው ከእብሪቱ የተነሣ ደካሞ
ችን ለማጥቃት ከመጣጣርና የተንኰል ዕቅ
ዶችን ከማውጠንጠን አያርፍም፤እነርሱም
በወጥመዱ ውስጥ ይወድቁለታል።
3ግፈኛ ሰው በልቡ የሚያስበውን ክፉ
ምኞት «መልካም ነው» እያለ ይመካበ
ታል። የገንዘብ ፍቅር ያደረባቸውን ሰዎች
ሥራ በማሞገስ እግዚአብሔር የሚጸየፈውን
ድርጊት ያበረታታል። 4በትዕቢቱ ምክንያት
እግዚአብሔርን ከቶ አይፈልገውም፤እንዲያ
ውም የእግዚአብሔር መኖር ለእርሱ እንደ
ማይጠቅመው ስለሚገምት፥በእግዚአብሔር
ማመን በልቡ ውስጥ ቦታ እንዳይኖረው
ለማድረግ ይሞክራል።
5እንዲህ ያለው ሰው ትምክሕት ያደረበ
ትና ከእግዚአብሔር ሕግ የራቀ ቢሆንም፥
ሥራው ለጊዜው ፍሬያማ ይሆንለታል፤የሚ
ቃወሙትንም በንቀት ያፌዝባቸዋል። 6በል
ቡም፥«ከዚህ ኑሮዬ ሊያናውጠኝ የሚችል
አንዳችም ኃይል ከቶ የለም፤ምንም ዓይነት
ችግር ሳያገኘኝ ለመቼውም ደስ ብሎኝ

እኖራለሁ» ብሎ ይተማመናል። 7 ከአንደ
በቱ የሚወጣው ንግግር ሁሉ በእርግማን፥
በውሸትና በዛቻ የተሞላ ነው፤ የሚናገራ
ቸው ቃላት ችግርንና ጭንቀትን የሚያስተ
ጋቡ ናቸው።
8 በየከተማው ሰዋራ ስፍራዎች እያደባና
የሚፈልጋቸውን ሰዎች በምስጢር እየተከ
ታተለ ንጹሐንን ይገድላል። 9 ችፍግ ባለ
ቍጥቋጦ ውስጥ እንደ ተሸሸገ ነጣቂ አን
በሳ፥ በአመቺ ስፍራ አድፍጦ መከላከያ የሌ
ላቸውን በስውር ባዘጋጀው ወጥመድ ይይዛ
ቸዋል። 10 እነርሱም ከሚደርስባቸው መንገ
ላታት የተነሣ አቅም ያንሣቸውና ከጕል
በቱ በታች ይወድቃሉ። 11 በልቡም እንዲህ
ይላል፤ «እግዚአብሔር የምፈጽመውን ግፍ
ጨርሶ አያይም፤ ፊቱን እንደ ሸፈነ ሰው
አይመለከትም።»
12 እግዚአብሔር ሆይ፥ እንግዲህስ
ተነሥ፤ አቤቱ፥ ረዳት የሌላቸውን ሳትረሳ
እጅህን ዘርግተህ እንዲህ ካለው ግፈኛ አድ
ናቸው። 13 ለመሆኑ ግፈኛ ሰው በእግዚአብ
ሔር ላይ ስለ ምን የንቀት ቃል ይናገራል?
«በክፉ ሥራዬ አይፈርድብኝም» ብሎስ
እንደ ምን ያስባል?
14 አሁንም አምላክ ሆይ፥ በግፈኞች ምክ
ንያት የሚደርሰውን መከራና ኀዘን ተመል
ክተህ ፍርድህን በሥልጣንህ ስጥ፤ እነሆ
የሚሠቃዩ ሁሉ ራሳቸውን ለአንተ አደራ
ሰጥተዋል። አሳዳጊ ለሌላቸው የሙት ልጆ
ችም ረዳታቸው አንተ ነህ። 15 ስለዚህ የግፈ
ኛውንና የክፋውን ሰው ክንድ ሰበር። የክ
ፋት ሥራ ደብዛው እንዲጠፋ ለግፈኛው
የሚገባውን የቅጣት ዋጋ ክፈል።
16 እግዚአብሔር ዘላለም የሚኖር ንጉሥ
ስለ ሆነ በእርሱ የማያምኑ ሕዝቦች ሁሉ
ከግዛቱ ፈጽመው ይጠፋሉ።
17 እግዚአብሔር ሆይ፥ በመከራ የተቀጠ
ቀጡ ሕዝቦች ምኞት ምን እንደ ሆነ ታው
ቃለህ፤ ተስፋ በመቍረጥ ፊንታ ይበረታቱ
ዘንድ ጩኸታቸውን አዳምጠህ ፍላጎታቸ
ውን ትፈጽምላቸዋለህ። 18 አሳዳጊ የሌላቸ
ውንና የተጨቈኑትንም ሁሉ ከሚያጠቃ
ቸው ተከላክለህ ታድናቸዋለህ፤ ሟችና
ፈራሽ የሆነ ግፈኛ ሰው ዳግመኛ ተነሥቶ
በጭካኔው እንዳያሸብራቸው ታደርጋለህ።

## መዝሙር 11

1 በሚያድነኝ በእግዚአብሔር ተማምኜ
ሳለሁ እንዴት፥ «ወደ መሸሸጊያህ ተራራ
እንደ ወፍ በረህ ሽሽ!» ትሉኛላችሁ?
2 ክፉዎች፥ ልበ ቅኖችን አድፍጠው ለመ
ውጋት ቀስቶቻቸውን ወጥረዋል፤ ፍላጻቻቸ
ውንም ሊያስፈንጥሩ ደግነዋል። 3 ታዲያ
ሕግና ሥርዓት እንዲህ ሲጠፉ ሲያይ ጻድቅ
ከቶ ምን ሊያደርግ ይችላል?
4 ዙፋኑ በሰማይ የሆነው እግዚአብሔር
ግን በመቅደሱ ሆኖ የሰውን ልጆች ድርጊት
አንድ በአንድ ይመለከታል፤ ዓይኖቹ እያንዳ
ንዱን ሰው በጥልቅ ይመረምራሉ። 5 እግዚ
አብሔር ጻድቁን ሳይቀር ይፈትናል። ክፉዎ
ችንና የግፍ ሥራ የሚወዱትን ግን ፈጽሞ
ይጠላል። 6 በክፉዎች ላይ የከሰል ፍምና
የድኝ ረመጥ ያዘንብባቸዋል፤ ፍጻሜአቸ
ውም ወላፈኑ በሚለበልብ አየር ውስጥ
መሠቃየት ይሆናል።
7 እግዚአብሔር ጻድቅ አምላክ ስለ ሆነ
ትክክለኛ ዳኝነት ይወዳል። ልበ ቅኖችም
ፊቱን ያዩታል።

## መዝሙር 12

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ በአንተ የሚያምኑ
ደጋግ ሰዎችን ማግኘት አልተቻለምና ኧረ
ድረስልን! እምነት የሚጣልባቸው ሁሉ
እነሆ ከሰዎች መካከል ጠፍተዋል። 2 እያን
ዳንዱ ሰው ለሌላው ከመዋሸትና በከንቱ
ውዳሴ በተሸፈነ አነጋገር ሌላውን ከመደ
ለል በስተቀር፥ እውነትን የሚናገር ከቶ
የለም።
3 እግዚአብሔር ሸንጋዮችንና፥ 4 «በንግግ
ራችን እናሸንፋለን፤ በአንደበታችንም የፈለግ
ነውን እንናገርበታለን፤ ስለዚህ ማን አለ
ብን?» የሚሉትን ትዕቢተኞች ሁሉ ያጠ
ፋል። 5 ደግሞም፥ «በደካሞች ላይ ከተጫ
ነው የጭቈና ቀንበርና ችግረኞች ከሚያሰ
ሙት የጣር ጩኸት የተነሣ አሁን እነሣ
ለሁ፤ እነርሱንም ከሚያጠቋቸውና ከሚያሠ
ቃዩዋቸው እጅ አድናቸዋለሁ» ይላል እግ
ዚአብሔር። 6 የእግዚአብሔር ቃል እንከን
እንደማይገኝበት፥ ሰባት ጊዜ በእሳት እንደ
ነጠረ ብር ንጹሕና የታመነ ነው።
7 አቤቱ ፈጣሪያችን፥ እንዲህ የሚያደርግ
ትውልድ በሚነሣበት ጊዜ ዘወትር ከለላ
ሆነህ ጠብቀን። 8 በዚያ ዘመን የነውር ሥራ
በሰዎች ዘንድ የሚያስከብርና ክፉዎች
እንደ ልባቸው የሚዘባነኑበት ይሆናልና።

## መዝሙር 13

1 ፈጣሪዬ ሆይ፥ የምትረሳኝ እስከ መቼ
ነው? ለዘላለም ነውን? ፊትህን እስከ መቼ
ትሰውርብኛለህ? 2 በየቀኑ በልቤ ሳዝን የም

ውለውና በአሳቤም ብዙ ነገሮችን ሳወጣ
ሳወርድ የምኖረው እስከ መቼ ነው? ጠላቴ
በእኔ ላይ የሚበረታው እስከ መቼ ነው?
3 እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፣ እንግዲህ
ወደ እኔ ተመልከት፤ መልስልኝም፤ ዓይኖቼ
በሞት እንዳይከደኑ ብርሃንህን እያዩ እንዲ
ኖሩ አድርግ። 4 አለዚያ ጠላቴ፣ «ይኸዋ!
አሸነፍኩት» ሊል፣ የሚጠሉኝም በእኔ
መውደቅ ደስ ሊላቸው ነው።
5 እኔ ግን ምን ጊዜም በማይለወጠው
ፍቅርህ እተማመናለሁ፤ ልቤም በማዳንህ
ደስ ይለዋል። 6 እግዚአብሔር የቸርነት
ሥራውን ስለሚያበዛልኝ የምስጋና መዝ
ሙር አቀርብለታለሁ።

## መዝሙር 14

1 ሞኝ በልቡ፣ «እግዚአብሔር የለም»
ብሎ ያስባል። እንዲህ ያሉ ሰዎች ሁሉ፣
በአስተሳሰባቸው የተሳሳቱና በተግባራቸው
የረከሱ ናቸው። ከመካከላቸውም በጎ ነገርን
የሚሠራ አንድ እንኳ የለም።
2 እግዚአብሔር ግን፣ ፈጣሪውን የሚፈ
ልግ አስተዋይና አዋቂ ሰው ይገኝ እንደ
ሆነ በማለት ከሰማይ የሰው ልጆች ወደሚኖ
ሩባት ወደ ምድር ተመለከተ። 3 ሁሉም
እርሱን ማምለካቸውን ትተው፣ በአስተሳሰባ
ቸውም አንድ ሳይቀሩ ረክሰው አገኛቸው።
ከመካከላቸውም በጎ ነገርን የሚሠራ የለም፤
አንድ እንኳ የለም።
4 ሰዎች እንጀራን እንደሚበሉ ሁሉ፣ ወገ
ኖቼን የሚዘርፉና እግዚአብሔርን በአምልኮ
የማይጠሩት ክፉ አድራጊዎች እስከዚህ ዕው
ቀት የሌላቸውና ፈጽመው የማያስተውሉ
ናቸውን? 5 እነሆ እግዚአብሔር በጻድቃን
ማኅበር መካከል መገኘቱ ሲገለጽ፣ ክፉ አድ
ራጊዎች በታላቅ ፍርሃትና ድንጋጤ ይዋ
ጣሉ። 6 የችግረኞች ዕቅድ እንዳይቃና ክፉ
ዎች የሚያቀርቡትን ተቃውሞ እግዚአብ
ሔር ለችግረኞች መከታ ሆኖ ይከላከላል።
7 የእስራኤልን ሕዝብ የሚያድን ቤዛ
ከጽዮን ይወጣል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ
ነጻነቱንና መብቱን መልሶ ሲያጐናጽፈው፣
በዚያን ጊዜ የያዕቆብ ልጆች የሆኑት የእስ
ራኤል ሕዝብ እጅግ ደስ ይላቸዋል፤ ሐሤ
ትም ያደርጋሉ።

## መዝሙር 15

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ በመቅደስህ ማን
ይኖራል? በተቀደሰውስ ኰረብታህ ላይ ማን
ሊገኝ ይችላል?
2 ነውር በሌለበት ሕይወት የሚኖር፣ የጽ
ድቅን ሥራ የሚፈጽም፣ ከልቡ እውነተኛ
የሆነውን ቃል የሚናገር፣ 3 በምላሱ ሰብቅ
የማይገኝበት፣ ሌላውን ሰው ለመጉዳት ክፉ
ነገር የማይሠራ፣ በሐሜት የሰውን ስም የማ
ያጠፋ፣ 4 ነውረኛውን የሚጸየፍ፣ እግዚአብ
ሔርን የሚፈሩትን ግን የሚያከብር፣ ጉዳት
የሚያመጣበት እንኳ ቢሆን ቃል ኪዳኑን
የሚጠብቅ፣ 5 ገንዘቡን ያለወለድ የሚያበድ
ርና በንጹሑ ላይ ለመፍረድ ጉቦ የማይቀ
በል ነዋ! እነዚህን ነገሮች የሚያደርግ ሰው
ፈጽሞ አይናወጥም።

## መዝሙር 16

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ በአንተ ተማምኛለ
ሁና ጠብቀኝ።
2 እግዚአብሔርን፣ «አንተ ፈጣሪዬ ነህ፤
ካንተ በቀር ለእኔ የሚሻለኝ ሌላ ምንም
መልካም ነገር የለኝም» አልሁት። 3 ደስታ
ዬን ሁሉ በምድር ላይ ተከብረው ከሚኖሩ
ትና የእርሱ ከሆኑት ቅዱሳን አገኛለሁ።
4 ሌሎችን አማልክት የሚያመልኩ ግን ኀዘ
ናቸው እየበዛ ይሄዳል፤ እኔም የአማልክቱን
ስም በአንደበቴ አልጠራም፤ የደም መሥዋዕ
ታቸውን አላቀርብም።
5 ጌታ ሆይ፣ ለእኔ የሚገባኝን ድርሻዬንና
ፋንታዬን ወስነህ ሰጥተኸኛል፤ ዕጣዬንም
የጸና አድርገህልኛል። 6 የይዞታዬ ድንበር
ለም የሆነውን ቦታ ከልሎ የሚያቅፍ ሆኖል
ኛል። የወረስኩት ርስት በእርግጥ የሚያስደ
ስት ነው።
7 መካሪዬ የሆነውን አምላክ አመሰግነዋ
ለሁ። እርሱ ሌሊት በመኝታዬ እንኳ ሳይ
ቀር ጥበብንና መመሪያን ይሰጠኛል። 8 ፈጣ
ሪዬን ምን ጊዜም በፊቴ እንዳለ አድርጌ እየ
ዋለሁ። እርሱ በቀኜ ሆኖ ስለሚደግፈኝ
አልናወጥም።
9 ስለዚህ ጌታ ሆይ፣ በልቤ እጅግ ደስ
ይለኛል፤ በአንደበቴ እልል እላለሁ። ሰውነ
ቴም የተጠበቀ ሆኖ ያርፋል። 10 ነፍሴን
በሲኦል አትተዋትምና፤ ቅዱስህ በመቃብር
መበስበስን እንዲያይ አታደርግምና።
11 የሕይወትን መንገድ እንዳውቅ አደረ
ግኸኝ፤ ያንተም መገኘት በሚሰጠው ደስታ
ትሞላኛለህ፤ በቀኝህም በመሆን ዘላለማዊ
ደስታ አገኛለሁ።

## መዝሙር 17

1 እግዚአብሔር ሆይ፣ እውነተኛ ልመና
ዬን ስማ፤ ጩኸቴንም አድምጥ። የማቀርብ

ጥሎኝ በመከራ መድከሜን አይተው ጠላ
ቶቼ ደርሰውብኝ ነበር፤እግዚአብሔር ግን
ደገፈኝ። 19 በጭንቀት ከቈየሁበት ጠባብ
ዋሻ አውጥቶ ሰፊ ወደ ሆነው መልካም
ስፍራ አደረሰኝ። በእኔ ደስ ተሰኝቷልና አዳ
ነኝ። 20 እግዚአብሔር እንደ እውነተኛነቴ፥
እጄም ከክፉ ሥራ ንጹሕ እንደ መሆኑ
መጠን ዋጋዬን ከፈለኝ። 21 የእግዚአብሔ
ርን መንገድ ተከትያለሁና፤የማመልከውን
ፈጣሪዬን በመተው ክፉ ነገር አልፈጸም
ኩም። 22 ሕጎቹን ሁሉ በፊቴ እንዳሉ አድ
ርጌ ዘወትር አስታውሳቸዋለሁ፤ትእዛዛቱን
ከመፈጸም ቸል ያልኩበት ጊዜ የለም።
23 በደል የሌለብኝ ከኃጢአት የራቅሁ ሆኜ
በእርሱ ዘንድ ለመገኘት የተቻለኝን አድርጌ
አለሁ። 24 ስለዚህ እግዚአብሔር እንደ እው
ነተኛነቴ፥በእርሱም ፊት እጄ ከክፉ ሥራ
ንጹሕ እንደ መሆኑ መጠን ዋጋዬን ከፈ
ለኝ።

25 ጌታ ሆይ፥ለታማኙ ሰው ታማኝነትህን
ታሳየዋለህ፤ለየዋሁም የዋህነትህን ታሳየዋ
ለህ፤ 26 ለንጹሑም የአንተን ንጽሕና ታሳየ
ዋለህ፤ለአታላዩ ግን አንተን ሊያታልል እን
ደማይችል ታሳየዋለህ። 27 ትሑቱን ታድና
ለህ፤ራሳቸውን የሚያኰሩትን ግን ታዋርዳ
ለህ። 28 የሸፈነኝን ጨለማ አስወግደህ በብር
ሃን እንድኖር የምታደርገኝ ፈጣሪዬ አንተ
ነህና አቤቱ፥ይህን ብርሃን የሚሰጠኝ መብ
ራቴ እንዳይጠፋ ጠብቅልኝ። 29 ለወረራ
የሚመጡብኝን ጦረኞች ልቋቋማቸውና
በፊቴ የሚደነቀረውን ግንብ ዘልዬ ላልፍ
የምችለው በአንተ በፈጣሪዬ እርዳታ ነው።

30 እዩት፥የፈጣሪ መንገዱ ፍጹም ነው፤
ቃሉም እንከን የማይገኝበት ነው። በእርሱ
የሚተማመኑትን ሁሉ ጋሻ ሆኖ ያድናቸ
ዋል። 31 ለመሆኑ ከእግዚአብሔር በቀር
ሌላ አምላክ ማነው? ከእርሱ ከፈጣሪያችን
በቀር ጽኑ አምባ ማን አለ? 32 ኃይልን የሚ
ያስታጥቀኝ፥መንገዴንም ፍጹም የሚያደር
ግልኝ እግዚአብሔር ነው። 33 ገደሉን
አልፌ ከተራራው አናት ላይ በቀላሉ እንድ
ደርስ እግሮቼን እንደ ዋልያ እግሮች እንዲ
ቀለጥፉ ያደርጋቸዋል። 34 እጆቼን በጦርነት
ስልት ያሰለጥናቸዋል፤ለክንዶቼም የነሐሱን
ቀስት የሚያጐብጥ ጕልበት ይሰጣቸዋል።

35 ጌታ ሆይ፥ እንዲህ አድርገህ የድል
ጋሻ አስጨበጥከኝ፤ቀኝ እጅህ አጽንታ ጠበ
ቀችኝ፤ ታላቅነትን ልታጐናጽፈኝና ከውር
ደቴ ልታነሣኝ ጐንበስ አልክ። 36 ሌላው
ቀርቶ ስራመድ ወለም እንዳይለኝ የምጓዝበ
ትን ቀጭን መንገድ አስተካክለህ አስፋህ
ልኝ። 37 ስለዚህ ጠላቶቼን አሳድጄ ደረስኩ
ባቸው፤በሞላ ማለቃቸውን ሳላረጋግጥ ወደ
ኋላዬ አልተመለስኩም። 38 እንደ ገና እንደ
ማይነሡ አድርጌ አደቀቅኋቸው፤ከጫማዬ
በታች እንደ ትቢያ ረገጥኋቸው። 39 አንተ
ለጦርነት የሚያስፈልገኝን ኃይል አስታጠቅ
ኸኝ፤ባላጋራዎቼ ከእግሬ ሥር እንዲወድቁ፥
40 ሊዋጉኝ የሞከሩትም ጠላቶቼ ገና ሲያ
ዩኝ ፊታቸውን አዙረው እንዲሸሹ አደረግሃ
ቸው፤እኔም ተቃዋሚዎቼን ሁሉ አጠፋኋ
ቸው። 41 ጠላቶቼ እርዳታ እንዲደርስላቸው
ጩኸው ነበር፤ ዳሩ ግን አንድም ሊያድና
ቸው የቻለ አልነበረም። እግዚአብሔርም
አልመለሰላቸውም። 42 ነፋስ ጠርጎ እንደሚ
ወስደው ትቢያ አደቀቅኋቸው፤በጐዳና ተረ
ግጦ እንደሚቦካ ጭቃም አደረግኋቸው።

43 ጌታ ሆይ፥ከሕዝብ ዐመፅ አዳንኸኝ፤
በአሕዛብም ላይ መሪ አደረግኸኝ፤የማላው
ቀው ሕዝብ ተገዛልኝ። 44 እነዚህ ሁሉ ስለ
እኔ ገና በዝና ሲሰሙ ታዘዙልኝ፤ ባዕዳን
ዜጎች በፊቴ እየተሽቈጠቈጡና ለጥ እያሉ
እጅ ነሡኝ። 45 ሁሉም የፍርሃት መንፈስ
አድሮባቸው ከየምሽጋቸው በመንቀጥቀጥ
እየወጡ መጡ።

46 እግዚአብሔር ለዘላለም ሕያው ሆኖ
ይኖራል! የማይናወጠው አምባዬ ለሆነው
ለእርሱ ክብር ምስጋና ይድረሰው! የእኔ
መድኅን እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ከፍ
ከፍ ይበል! 47 በክፉት የተነሡብኝን የተበ
ቀለልኝና አሕዛብን ድል አድርጎ ያስገዛልኝ
እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው። 48 ጠላቶ
ቼም ከሚያደርሱብኝ ጥፋት አዳነኝ። ከተ
ቃዋሚዎቼ በላይ ከፍ ያለ መፈራትንና
ክብርን ሰጠኝ፤በኃይላቸው ከሚመኩ ሰዎች
እጅ ከመውደቅም አተረፈኝ።

49 ስለዚህ እግዚአብሔር ሆይ፥በአሕዛብ
መካከል አመሰግንሃለሁ፤ለስምህ የምስጋና
መዝሙር አቀርብልሃለሁ።

50 እርሱ እግዚአብሔር ቀብቶ ላነገሠው
ለዳዊትና ለዘሩ ታላላቅ ድሎችን ሲያጐናጽ
ፍና የማይለወጥ ፍቅሩን ለዘላለም ሲገልጽ
ይኖራል።

## መዝሙር 19

1 ሰማያት የእግዚአብሔርን ገናና ክብር
በይፋ ይናገራሉ፤ጠፈርም የእጆቹን ጥበብ
በአዋጅ ያስረዳል። 2 ሁሉም ያለማቋረጥ
ይህን የመልእክት ቃል ከቀን ወደ ቀን ያስ
ተላልፋሉ ፤ ዕውቀትንም ከሌሊት ወደ

ሌሊት ይገልጣሉ። 3ይህንንም የሚያደር
ጉት በመናገር አይደለም፤ ቋንቋ የላቸው
ምና፤ድምፅ እንኳ አያሰሙም። 4ግን የሚያ
ስተላልፉት መልእክትና የሚገልጡት ዕው
ቀት በምድር ላይ ከዳር እስከ ዳር፣በመላው
ዓለም በአራቱ ማዕዘን ተዳርሶ ይገኛል።
እግዚአብሔር ፀሐይን ፈጥሮ በሰማዩ
መሃል አኖረ። 5ከእልፍኙ ብቅ ብሎ ለሚ
ጠባበቁት ሠርገኞች እንደሚታይ ሙሽራና
እሽቅድድሙን ለማሸነፍ በጋለ ስሜት እን
ደሚገሠገሥ ግንባር ቀደም ሯጭ፣ 6ፀሐ
ይም ጧት ጧት ከምሥራቅ አድማስ
ደምቆ ይወጣል፤መውጫ መግቢያ ጐዳናው
ንም ተከትሎ ይጓዛል፤ ከሙቀቱ ተሸሽጎ
የሚያመልጥ አንድም ፍጡር ሳይኖር በመ
ጨረሻ ከምዕራብ አድማስ ደርሶ ይጠል
ቃል።
7የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ስለ ሆነ
ይህን እንዲያስተውል ሰውን አነቃቅቶ ሕይ
ወት ይሰጠዋል። የእግዚአብሔር ድንጋጌ
ዎች የታመኑ ስለ ሆኑ አላዋቂውን ብልህ
ያደርጉታል። 8የእግዚአብሔር ሥርዓቶች
ቀናዎች ስለ ሆኑ የሰውን ልቦና ደስ ያሰ
ኛሉ። የእግዚአብሔር ትእዛዞች ብርሃን ስለ
ሆኑ የሰው ዓይኖች ሁሉን አጥርተው እንዲ
ያዩ ያደርጋሉ። 9እግዚአብሔርን መፍራት
ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ንጹሕ ምግባር
ነው። የእግዚአብሔር መመሪያዎች ሁለንተ
ናቸው ጽድቅ ስለ ሆነ አለኝታነታቸው የተ
ረጋገጠ ነው። 10እነዚህ ሁሉ እጅግ ከነጠረ
ብዙ የወርቅ ክምችት ይልቅ የተወደዱና
የከበሩ ናቸው። ከማር እንጀራ ላይ ከሚንጠ
ባጠብ ወለላም ይበልጥ የሚጣፍጡ
ናቸው። 11አገልጋይህ በእነርሱ ማስጠንቀቂ
ያነት ራሱን ይጠብቃል፤የሚፈጽማቸውም
በመሆኑ የሚያገኘው ዋጋ ታላቅ ነው።
12ግን በልቦናው ውስጥ ያለው አሳብና
የሚፈጽመው ሥራ ኃጢአት መሆኑን
ለይቶ ለማወቅ የሚችል ማነው? ስለዚህ
ይህን ከመሰለው የተሰወረ ስሕተት አንጻኝ።
13ፈቅጄ የምሠራው ኃጢአት እንዳይኖርብ
ኝና ለኃጢአቱ እንዳልገዛ እኔን አገልጋይህን
ጠብቀኝ። በዚያን ጊዜ ከበደል ነጻ እሆና
ለሁ፤ ሕግህን በመተላለፍ ታላቅ ኃጢአት
ከመሥራትም እድናለሁ።
14እግዚአብሔር ሆይ፣ ለእኔ ዓለቴና
ቤዛዬ ሆነህ የምታድነኝ አንተ ነህና፣በልቦ
ናዬ የማሰላስለው አሳብና በአንደበቴም የም
ናገረው ቃል በፊትህ የሚያስደስት ይሁን
ልኝ።

## መዝሙር 20

1መከራ በገጠመህ ጊዜ እግዚአብሔር
ጸሎትህን ሰምቶ ይመልስልህ። ስሙን የም
ትጠራው የያዕቆብ አምላክ ይጠብቅህ።
2በጽዮን ከሚገኘው መቅደሱ እርዳታውን
ይላክልህ፤ድጋፉንም ይለግስህ። 3መሥዋዕት
ህን ሁሉ ያስብልህ፤የሚቃጠለውን ቊርባን
ህን ይቀበልልህ። 4ልብህ ሊያገኘው የተመ
ኘውን ይስጥህ፤ዕቅዶችህንም ሁሉ ፍሬያማ
ያድርግልህ። 5ድል አድርገህ በምትመለስ
በት ጊዜ እኛ ደግሞ ተሰልፈንና «ሆ!»
እያልን፣በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ስም
ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርገን እንይዛ
ለን። እግዚአብሔር ልመናህን ሁሉ ይፈጽ
ምልህ።
6እነሆ እግዚአብሔር ቀብቶ የሾመውን
እንደሚያድነው አውቃለሁ። አዎን፣የማዳን
ኃይል ያለውን ቀኝ እጁን ከተቀደሰ መኖሪ
ያው ከሰማይ በመላክ ለጸሎቱ መልስ ይሰጠ
ዋል። 7በዘመናዊ ሠረገላዎችና መሣሪያዎች
በደረጁ ጦር ኃይሎቻቸው የሚመኩ ሕዝ
ቦች አሉ፤እኛ ግን የምንተማመነው በአምላ
ካችን በእግዚአብሔር ስም ነው። 8እነርሱ
ወድቀው ሲጠፉ፣እኛ ግን ከወደቅንበት ተነ
ሥተን ጸንተን እንኖራለን።
9እግዚአብሔር ሆይ፣ የሕዝብህ መሪ
አድርገህ የሾምከውን ንጉሥ ድል አቀዳ
ጀው። እኛም በጸሎት በምንጠራህ ጊዜ
ስማን።

## መዝሙር 21

1እግዚአብሔር ሆይ፣ቀብተህ የሾምከው
ንጉሥ በኃይልህ ደስ ይለዋል። በየጊዜው
በምታቀዳጀው ድል የሚሰማው ሐሤት
ምንኛ ታላቅ ነው! 2እነሆ፣የልቡን ፍላጎት
ፈጽመህለታል፤በአንደበቱ የጠየቀህን አላስቀ
ረህበትም።
3በተትረፈረፈ በረከትህ ተቀበልኸው፤
ከንጹሕ ወርቅ የተሠራ ዘውድ በራሱ ላይ
ጫንክለት። 4መልካም ኑሮን ለመነህ፤አን
ተም ረዥም ዕድሜና የዘላለም ሕይወት
ሰጠኸው። 5ከአንተ ባገኛቸው ድሎች ስሙ
የገነነ ሆነ፤ክብርና ግርማ ሞገስ አጐናጸፍ
ከው። 6በእርግጥም ዘላለማዊ በረከትህን ለገ
ስከው፤የአንተ መገኘት በሚሰጠው ፍሥሐ
ደስ አሰኘኸው። 7ይህ ንጉሥ በእግዚአብ
ሔር ስለ ተማመነና ከሁሉ በላይ የሆነው
የፈጣሪው የማይለወጥ ፍቅር ስለማይለየው
ምን ጊዜም አይታወክም።

8ጌታ ሆይ ፥ እጅህን በጠላቶችህ ሁሉ
ላይ ትዘረጋለህ ፤ በቀኝ እጅህም ትይዛቸዋ
ለህ። 9በምትገለጽበት ጊዜ እንደ ጋለ
ምድጃ ታደርጋቸዋለህ። እግዚአብሔር ጠላ
ቶቹን በቍጣው ኃይል ይጨርሳቸዋል፤እሳ
ቱም ትበላቸዋለች። 10የልጅ ልጆቻቸውን
ሳይቀር ከምድር ገጽ ፥ ትውልዳቸውንም
ከሰው ዘር ለይተህ ታጠፋለህ። 11እነርሱ
ግን በአንተ ላይ ሤራ ለመፈጸም ቢዶል
ቱና ፥ የተንኰልን ዕቅድ ለመዘርጋት ቢያው
ጠነጥኑ ፥ ምንም ሊሳካላቸው አይችልም።
12ገና የቀስትህን አውታር ስበህ ስታነጣጥር
ባቸው ፊታቸውን አዙረው ይሸሻሉ።
13እግዚአብሔር ሆይ ፥ በኃይልህ ከፍ
ከፍ በል ፤ እኛም ለኃያልነትህ የምስጋና
መዝሙር እናቀርብልሃለን።

## መዝሙር 22

1አምላኬ! አምላኬ! ስለ ምን ተው
ኸኝ? እኔን ለማዳን ለምን ትዘገያለህ? ከማ
ሰማህስ የሥቃይ ድምፅ ይህን ያህል ለምን
ትርቃለህ? 2አቤቱ ፈጣሪዬ ሆይ ፥ በቀን
ወደ አንተ እጮኻለሁ፤ነገር ግን አትመልስ
ልኝም። በሌሊት እንኳ ዝም አልልም።
3አንተ ግን ቅዱስ ነህ፤በእስራኤል የምስ
ጋና ዙፋን ላይም ተቀምጠሃል ፤ ሕዝቡም
የምስጋና መዝሙራቸውን የሚያቀርቡት
ለአንተ ነው። 4አባቶቻችን በአንተ ተማ
መኑ፤አዎን፥በአንተ ተማመኑ፤አንተም ከመ
ከራ አወጣሃቸው ፤ 5ወደ አንተ በመጮሃ
ቸው ሊድኑ ቻሉ። በአንተ ተማምነዋልና
አላፈሩም።
6እኔ ግን ሰዎች የሚያላግጡብኝ፥በሕዝ
ቡም ዘንድ የተናቅሁና እንደ ሰው ልቈጠር
የማይገባኝ ትል ነኝ። 7የሚያዩኝ ሁሉ ያፌ
ዙብኛል ፤ ራሳቸውንም እየነቀነቁ እንዲህ
የሚል የስድብ ቃላት ያወርዱብኛል ፤
8«'በእግዚአብሔር እተማመናለሁ' ይላል፤
ታዲያ ለምን አሁን አያድነውም? በእርሱ
ደስ የተሰኘ ከሆነ፥እስቲ ከዚህ መከራ ያው
ጣው!»
9አቤቱ፥ከማኅፀን ያወጣኸኝ አንተ ነህ፤
ገና የእናቴን ጡት ስጠባ ሳለሁ እንኳ በአ
ንተ እንድተማመን አደረግኸኝ። 10ከተወለ
ድኩባት ቅጽበት አንሥቶ እምነቴ በአንተ
ላይ ነው ፤ በእናቴ ማኅፀን ውስጥ ከነበርኩ
በት ጊዜ ጀምሮ አምላኬ አንተው ነህ።
11ስለዚህ ፈጣሪዬ ሆይ፥መከራ ሊደርስብኝ
ስለተቃረበና የሚረዳኝም ማንም ስለሌለ ፥
አቤቱ፥ከእኔ አትራቅ።

12እነሆ ብዙ ጠላቶች እንደሚዋጋ
የበሬ መንጋ ከበቡኝ፤እንደ ኃይለኞቹ የባ
ሳን ሰንጋዎችም በዙሪያዬ መጡብኝ።
13ነጣቂ አንበሳ የሚበላውን እንስሳ ለመስ
በር እንደሚያገሣ ሁሉ ፥ እነርሱም አፋቸ
ውን በእኔ ላይ ከፈቱብኝ። 14እኔም በድን
ጋጤ እንደ ውሃ ፈሰስሁ፤አጥንቶቼ ከመገጣ
ጠሚያቸው የተለያዩ መሰለኝ፤ ልቤም በደ
ረቴ ውስጥ እንደ ሰም ቀለጠ። 15ኃይሌ
እንደ ገል ደረቀ ፤ ምላሴም ከላንቃዬ ጋር
ተጣበቀ ፤ ወደ መቃብር እንደ ወረደ ሬሳ
ሆንሁ። 16አቤቱ ፥ ጠላቶቼ እንደ ተናካሽ
ውሾች ከበቡኝ፤ክፉዎች ሰዎች በአንድነት
ሆነው በዙሪያዬ መጡብኝ፤እጆቼንና እግሮ
ቼን ቸነከሩኝ። 17አጥንቶቼ ሁሉ አንድ
በአንድ ይቈጠራሉ፤የሚያዩኝ ሰዎች ሁሉ፥
«እሰይ!» እያሉ እያተኰሩ ተመለከቱኝ።
18ልብሶቼን ተከፋፈሉ። በመደረቢያዬ ላይ
ግን ዕጣ ተጣጣሉ።
19አቤቱ ፥ አንተ ግን ከእኔ አትራቅ ፤
ኃይሌ ሆይ፥እኔን ለመርዳት ፍጠን። 20በሰ
ይፍ ስለት ሊያጠፉኝ ከተዘጋጁት እጅ፥ከተ
ናካሽ ውሾችም ጥርስ የተወደደች ሕይወ
ቴን አትርፍ። 21ከተራቡ አንበሶች አስጥ
ለኝ፤ከተዋጊ የጎሽ መንጋም አድነኝ።
22እኔም ስምህን በወንድሞቼ መካከል
በይፋ እገልጻለሁ፤በጉባኤ ላይ ተነሥቼ የም
ስጋና መዝሙር አቀርብልሃለሁ። 23እናንተ
እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ ፥ ፈጣሪያች
ሁን በመዝሙር አመስግኑት ፤ እናንተ የያዕ
ቆብ ልጆች የሆናችሁ የእስራኤል ሕዝብ፥
ሁላችሁ አክብሩት ፤ 24እርሱ የችግረኛውን
ሥቃይ አልናቀም ፤ አልተጸየፈምም። ችግረ
ኛው «ድረስልኝ» ብሎ ያቀረበለትን የል
መና ጩኸት ሰማ እንጂ ፊቱን ከእርሱ አል
ሸሸገም።
25ጌታ ሆይ፥በታላቁ ጉባኤ ላይ የሚገለ
ጸው ክብሬ የሚመጣው ከአንተ ዘንድ
ነው ፤እኔም በሚፈሩህ ፊት ቃሜ ስእለቴን
እፈጽማለሁ። 26ድኾች በልተው ይጠግ
ባሉ ፤ እግዚአብሔርን የሚሹ ሁሉ እርሱን
በመዝሙር ያመሰግኑታል፤ልቦናቸውም በዘ
ላለም ሕይወት ተሞልቶ ደስ ይላቸዋል።
27በምድር ላይ ከዳርቻዋ እስከ ዳርቻዋ
የሚኖሩ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በየወገናቸው
ያለፈውን በማስታወስ ወደ እግዚአብሔር
አምልኮ ይመለሳሉ ፤ በፊቱም ወድቀው ይሰ
ግዳሉ። 28መንግሥት የእርሱ ናትና፤ሕዝቦ
ችንም በበላይነት የሚያስተዳድር እርሱ
ነውና።

29 በተድላ በደስታ ከሚኖሩት የምድር
ባለጸጎች ጀምሮ ራሳቸውን በሕይወት ለማ
ቈየት እስከማይችሉት ድኾች ድረስ ሁሉም
ያመልኩታል፤ፈራሽ በሰባሽ የሆነው ተንቀ
ሳቃሽ ፍጥረት በሙሉ በፊቱ ይንበረከካል።
30 መጪው ትውልድ ለእግዚአብሔር የሚ
ሆን አገልግሎት ይፈጽማል፤ወደ ፊት የሚ
ነሡት ትውልዶች የእግዚአብሔርን ነገር
ይሰማሉ። 31 እነርሱም እግዚአብሔር ጻድቅ
አምላክ ስለ መሆኑና ስላደረጋቸው ድንቅ
ነገሮች ገና ላልተወለደው ሕዝብ በይፋ
ይተርካሉ።

## መዝሙር 23

1 እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ ስለዚህ
የሚያስፈልገኝ ሁሉ አለኝ። 2 በለመለመ
መስክ ያሰማራኛል፤ ጸጥ ብሎ በሚፈስ
ወንዝ ዳር ይመራኛል። 3 የተጐሳቈለች ነፍ
ሴንም ያድሳል። ስለ ስሙም ሲል ትክክለኛ
ውን መንገድ ያሳየኛል።
4 ጨለማ በወረሰው አስፈሪ ሸለቆ ውስጥ
እንኳ ባልፍ፥ አንተ ከእኔ ጋር ስለ ሆንክ
አደጋ ይደርስብኛል ብዬ አልፈራም። በት
ርህ ስለሚመራኝ፥ ምርኲዝህም ስለሚደግ
ፈኝ እየተጽናናሁ እጓዛለሁ።
5 ጠላቶቼ በይፋ እያዩ ማእድን ታዘጋጅ
ልኛለህ፤በደስታ እንደ ተቀበልከኝም ለማሳ
የት ዘይትን በራሴ ላይ ታፈስልኛለህ፤የምጠ
ጣውንም ነገር ጽዋዬ ሞልቶ እስከሚፈስ
ትሰጠኛለህ። 6 ምሕረትህና ቸርነትህ በሕይ
ወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል። እኔም በእግ
ዚአብሔር ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

## መዝሙር 24

1 ምድርና በእርስዋ ያለው ማንኛውም
ነገር፥ መላዋ ዓለምና በውስጥዋ የሚኖሩት
ሁሉ የእግዚአብሔር ናቸው። 2 እርሱ የም
ድር መሠረቷ በውቅያኖሶች ውሃ ውስጥ
ጠልቆ እንዲጸና አደረገ።
3 ወደ እግዚአብሔር ኰረብታ ማን ይወ
ጣል? በተቀደሰ ስፍራውስ ማን ይቆማል?
4 ከዚህ ለመድረስ የሚቻለው፥እጆቹን ከበ
ደል ሥራ የሚያጠራ፥ልቡን ከክፉ አሳብ
የሚያነጻ፥ነፍሱን ጣዖትን ከማምለክ የሚያ
ርቅና በሐሰት የማይምል ሰው ነው። 5 እን
ዲህ ያለው ሰው ከእግዚአብሔር በረከትን
ይቀበላል፤ መድኅኑ በሆነው ፈጣሪ ከክስና
ወቀሳ ነጻ ይሆናል። 6 እግዚአብሔርን
የሚሹ፥የያዕቆብን ፈጣሪ ፊት ለማየት የሚ
ፈልጉ ደጋግ ሰዎች የሚገኙበት ትውልድ
እንዲህ ያለው ነው።
7 የክብር ንጉሥ እንዲገባ እናንተ የቅ
ጽር በሮች ተከፈቱ፤ እናንተም ከጥንት
ጀምሮ የነበራችሁ የግቢ መዝጊያዎች
ወለል በሉ። 8 ለመሆኑ ይህ የክብር ንጉሥ
ማነው? እርሱማ ብርቱውና ኃያሉ፥በጦርነ
ትም ላይ አሸናፊ የሆነው እግዚአብሔር
ነው። 9 የክብር ንጉሥ እንዲገባ እናንተ የቅ
ጽር በሮች ተከፈቱ፤ እናንተም ከጥንት
ጀምሮ የነበራችሁ የግቢ መዝጊያዎች
ወለል በሉ። 10 ለመሆኑ ይህ የክብር ንጉሥ
ማነው? እርሱማ ሁሉን ቻይ የሆነው አም
ላክ ራሱ እግዚአብሔር ነው።

## መዝሙር 25

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ በነፍሴ እየቃተ
ትኩ ወደ አንተ እጸልያለሁ። 2 ፈጣሪዬ
ሆይ፥በአንተ ተማምኛለሁና በምንም ነገር
አልፈር፤ጠላቶቼም «አሸነፍነው» አይበሉ።
3 ተስፋው በአንተ የሆነ ሰው ሁሉ ከቶ አያ
ፍርም። ይሉኝታ የሌላቸው ከዳተኞች ግን
እነርሱ በኀፍረት ላይ ይወድቃሉ።
4 ጌታ ሆይ፥ እንድጓዝበት የምትፈልገ
ውን ጐዳናህን አሳየኝ፤መንገድህን እንዴት
እንደምከተል አስተምረኝ፤ 5 እውነትህን
እንዳውቅ እያስተማርክ ምራኝ። አንተ ፈጣ
ሪዬና መድኅኔ ስለ ሆንክ፥ ቀኑን ሙሉ
ተስፋ የማደርገው አንተኑ ነው። 6 እግዚአ
ብሔር ሆይ፥ ከጥንት ጀምሮ ለሰው ልጅ
ስታደርግ የኖርከውን ታላቁን ምሕረትህንና
የፍቅርህን ሥራ አስታውስ። 7 በወጣትነቴ
ዘመን ሕግህን በመተላለፍ የሠራሁትን
ኃጢአቴን አታስብብኝ። እግዚአብሔር
ሆይ፥ አንተ ደግ ርኅሩኅ አምላክ ነህና፥
እንደ ፍቅርህ መጠን አስበኝ።
8 እግዚአብሔር በባሕርዩ ርኅሩኅና ቅን
ስለ ሆነ፥ኃጢአተኞች ይድኑ ዘንድ መንገ
ዱን እንዲያውቁ ያስተምራቸዋል። 9 ትሑ
ታንን ቀና በሆነው ጐዳና ይመራቸዋል፤
መንገዱንም ያስተምራቸዋል። 10 ለቃል
ኪዳኑ ታማኞች ሆነው ለሚገኙት፥የእግዚአ
ብሔር መንገዶች ሁሉ ፍቅርንና መተማመ
ንን የሚያጐናጽፉ ናቸው። 11 ጌታ ሆይ፥
ኃጢአቴ ከባድ ቢሆንም፥ስለ ስምህ ብለህ
ይቅር በለኝ።
12 እንግዲህ እግዚአብሔርን የሚፈራ
ሰው ማነው? ለእርሱ የተመረጠለትን መን
ገድ እንዲከተል እግዚአብሔር ዕውቀቱን
ይሰጠዋል፤ 13 ዕድሜውን በተድላ ደስታ
ያሳልፋል፤የልጅ ልጆቹና ዘሮቹ ምድርን

ይወርሳሉ። 14 እግዚአብሔር የሚያምናቸው
እርሱን የሚፈሩትን ነው። የቃል ኪዳኑንም
ምስጢር እንዲያውቁት ይገልጽላቸዋል።
15 እግሮቼን ከተያዙበት ወጥመድ የሚያላቅ
ቃቸው እርሱ ብቻ ስለ ሆነ ዓይኖቼ ምን
ጊዜም የሚመለከቱት ወደ እግዚአብሔር
ነው።

16 አቤቱ ፥ ብቸኛና በችግር የምሠቃይ
ነኝና ፊትህን ወደ እኔ መልሰህ ቸርነትህን
አድርግልኝ። 17 በልቤ ውስጥ ያለው ጭን
ቀት እየባሰ ስለ ሄደ እባክህ ከዚህ ጕስቁል
ናዬ አውጣኝ። 18 ሥቃዬንና መከራዬን
ተመልክተህ ኃጢአቴን ሁሉ አስወግድ
ልኝ። 19 የጠላቶቼ ቍጥር ምን ያህል እንደ
ጨመረና በእኔ ላይ ያላቸው ጥላቻ የቱን
ያህል ከባድ እንደ ሆነ ተመልከት። 20 ሕይ
ወቴን ጠብቀህ ከሞት አትርፈኝ፤ መጠጊያ
እንድትሆነኝ በአንተ ተማምኛለሁና አል
ፈር። 21 ተስፋዬን የጣልኩት በአንተ ላይ
ስለ ሆነ እምነቴና ቅንነቴ እንዲጠብቁኝ
አድርግ።

22 እግዚአብሔር ሆይ ፥ የእስራኤልን
ሕዝብ ከደረሰበት መከራ ሁሉ ቤዛ ሆነህ
አድነው።

## መዝሙር 26

1 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ሕይወቴን በንጽ
ሕና የምመራና ፥ በአንተም ላይ ያለኝ እም
ነት የማያወላውል በመሆኑ ከክስና ወቀሳ
ነጻ አድርገኝ። 2 አቤቱ ፥ ልቦናዬንና ሕሊና
ዬን እየመረመርክ ጨርሰህ ፈትነኝ። 3 ፍቅ
ርህ ምን ጊዜም በፊቴ ነው ፤ በኑሮዬም
እነሆ እውነትህን ያለማቋረጥ እከተላለሁ።
4 በሽንገላ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር አልዋል
ኩም ፤ ከግብዞች ጋር አባሪ ተባባሪ አልሆን
ኩም። 5 ክፉ አድራጊዎች የሚያደርጉትን
ጉባኤ ተጸየፍሁ ፤ ከግፈኞችም ጋር አብሬ
መቀመጥን እምቢ አልሁ። 6 ጌታ ሆይ ፥ እጆ
ቼን ከበደል አንጽቼ ወደ መሠዊያህ ቀረ
ብሁ ፤ 7 ለአንተ የሚገባውን የምስጋና መዝ
ሙር ከፍ ባለ ድምፅ አሰማሁ ፤ ድንቅ ሥራ
ዎችህን በይፋ ተናገርሁ። 8 ፈጣሪዬ ሆይ ፥
የአንተ መኖሪያ ፥ የክብርና የምስጋናህም
መገኛ የሆነውን ቤትህን እወዳለሁ።

9 አቤቱ ፥ ኃጢአተኞችን በሞት በምትቀ
ጣበት ጊዜ ነፍሴን ከእነርሱ ጋር አትውሰ
ዳት ፤ ሕይወቴን የሰውን ደም ከሚያፈሱ
ጋር አታጥፋ። 10 የእነዚህ ሰዎች እጅ የክ
ፋት ዕቅዳቸውን ለመፈጸም የተዘጋጀ ፥ ቀኝ
እጃቸውም በጉቦ የተመላ ነው። 11 እኔ ግን
ሕይወቴን በንጽሕና የምመራ ስለ ሆንሁ
ይቅር ብለህና ቤዛ ሆነህ አድነኝ።

12 እግሮቼ በተደላደለ ስፍራ ጸንተው
ስለ ቆሙ በታላቁ ጉባኤ መካከል ተገኝቼ
ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀርብለታለሁ።

## መዝሙር 27

1 እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኅኔ ስለ
ሆነ የሚያስፈራኝ ማነው? እግዚአብሔር
የሕይወቴ መተማመኛ ምሽግ ስለ ሆነ የሚ
ያስደነግጠኝስ ማነው? 2 ክፉዎች ሰዎች
እኔን በመቃወም ሥጋዬን ሊቦጫጭቁ ፥ ጠላ
ቶቼና ባለጋራዎቼም ሊያጠቁኝ አሰፍስፈው
በሚነሡበት ጊዜ ሁሉም እየተሰነካከሉ
ይወድቃሉ። 3 አንድ ራሱን የቻለ ጦር ቢከ
በኝ እንኳ በልቤ ፍርሃት አይሰማኝም ፤ ጦር
ነት ቢነሣብኝም ፥ በልበ ሙሉነት ጸንቼ እቆ
ማለሁ።

4 እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመን
ሁት። ይህቺም የለመንኩት አንዲት ነገር
ዕድሜዬን ሙሉ በእግዚአብሔር ቤት እየተ
ገኘሁ ፥ የእግዚአብሔርን ግርማ ሞገስ እንዳ
ደንቅና በመቅደሱም ውስጥ እርሱን በመ
ሻት እንድኖር ነው። 5 እርሱ በመከራ ጊዜ
ምንም እንዳይደርስብኝ በመኖሪያው ውስጥ
ሰውሮ ይጠብቀኛል ፤ በመጠለያው ድንኳን
ውስጥ ይሸሽገኛል ፤ በዓለትም ላይ ከፍ አድ
ርጎ ያስቀምጠኛል። 6 እኔም በዚያን ጊዜ
በዙርያዬ ካሉ ጠላቶቼ ይልቅ ገናና ሆኜ
እታያለሁ። ፈጣሪዬ ይህን ስላደረገልኝ በእ
ልልታ ድምፅ በድንኳኑ መሥዋዕት አቀርብ
ለታለሁ ፤ በዜማ መሣሪያዎች እየታጀብሁ
ለጌታ ፥ ለፈጣሪዬ እዘምርለታለሁ።

7 እግዚአብሔር ሆይ ፥ በምጠራህ ጊዜ
ድምፄን ስማ ፤ ምሕረት አድርግልኝና ለጸ
ሎቴ መልስ ስጠኝ። 8 ልቤ አንተን እያሰበ ፥
«የእርሱን ፊት ፈልግ» ስለሚለኝ ፥ አቤቱ ፥
ፊትህን እሻለሁና ፥ 9 ፊትህን ከእኔ አትሸ
ሽግ። ረዳቴ ነህና እኔን ባሪያህን «ወግድ»
ብለህ በቍጣ አትመልሰኝ። አምላኬና መድ
ኅኔ ሆይ ፥ ፊት ነሥተህ አትጣለኝ ፤ ጨርሰ
ህም አትተወኝ። 10 አባቴና እናቴ ቢተዉኝ
እንኳ ፥ አንተ ፈጣሪዬ ፥ «አይዞህ» ብለህ በማ
ጽናናት ትቀበለኛለህ። 11 ስለዚህ ጌታ ሆይ ፥
መንገድህን እንዴት እንደምከተል አስተም
ረኝ። የሚያጠቁኝ ባለጋራዎቼ ያፍሩ ዘንድ
አካሄዴን የቀና አድርገህ ምራኝ ፤ 12 ጠላ
ቶቼ በእኔ ላይ እንዲደርስ ለሚመኙት ውድ
ቀት አትዳርገኝ። እነሆ ሐሰተኞች ምስ
ክሮች የጭካኔ ሥራቸውን ሊፈጽሙብኝ

እየዛቱ በእኔ ላይ ተነሥተውብኛልና።
[13]«እግዚአብሔር በሕያዋን ምድር የሚ
ያደርግልኝን የቸርነት ሥራ አያለሁ» በሚ
ለው እምነቴ የጸናሁ ነኝ። [14]እግዚአብሔር
የሚያደርገውን በተስፋ ተጠባበቅ፤ በርታ!
ልብህ በትዕግሥት ይጽና፤ እግዚአብሔር
የሚያደርገውን በተስፋ ተጠባበቅ።

## መዝሙር 28

[1]እግዚአብሔር ዓለቴ ሆይ፥ ወደ አንተ
እየተጣራሁ ነኝና እንዳልሰማ ሆነህ ቸል
አትበለኝ። ዝም እንዳልኸኝ ብትቀር ግን
ወደ መቃብር እንደሚወርዱት ሙታን እሆ
ናለሁ። [2]አሁንም፥ «ድረስልኝ፥ማረኝ» እያ
ልኩ በሰማይ ወዳለው ቅዱስ መኖሪያህ እጆ
ቼን ዘርግቼ እየጠራሁህ ነኝና ጩኸቴን
ስማ።
[3]አቤቱ፥ ክፉ ሥራ ከሚሠሩ ከግፈኞች
ጋር ደምረህ ወደ ቅጣት አትውሰደኝ፤እነ
ርሱ የተንኰል ዓላማቸውን በሕሊናቸው
ውስጥ ሰውረው የሚኖሩ ናቸው፤ በሰዎች
ዘንድ ግን በአንደበታቸው ሰላማውያን መስ
ለው ይታያሉ። [4]ለዚህ ድርጊታቸውና
ለክፉ ሥራቸው ፍዳቸውን ክፈላቸው፤በእጃ
ቸው ባደረሱት ጥፋት መጠን የሚገባቸውን
የቅጣት ዋጋ እንዲያገኙ አድርግ። [5]ለእግዚ
አብሔር ሥራዎችና በእጆቹ ለፈጸማቸው
ድርጊቶች ምንም ደንታ የላቸውምና። እር
ሱም ምን ጊዜም አንሰራርተው እንደ ገና
ሊቋቋሙ እንደማይችሉ አድርጎ ያፈራርሳ
ቸዋል።
[6]ምሕረት እንዲያደርግልኝ ወደ እርሱ
ያቀረብሁትን ጩኸቴን ሰምቷልና እግዚአ
ብሔር የተመሰገነ ይሁን። [7]እግዚአብሔር
ኃይሌና ጋሻዬ ነው፤በእርሱ ከልቤ ስለምተ
ማመን እርዳታው አልተለየኝም። ስለዚህ
ልቤ በደስታ ይፈነድቃል፤ ምስጋናዬንም
በመዝሙር አቀርብለታለሁ።
[8]እግዚአብሔር ለሚታመኑበት ሕዝቡ
ኃይላቸው ነው፤ እርሱ ለቀባው የሕዝብ
መሪም የመዳኛው ምሽግ ነው።
[9]አቤቱ፥ርስትህ የሆኑ ሕዝብህን አድን፤
ባርካቸውም፤ እረኛ ሆነህ እስከ ዘላለምም
አቅፈህ ደግፈህ ጠብቃቸው።

## መዝሙር 29

[1]እናንት ኃያላን፥ለእግዚአብሔር የምስ
ጋና መዝሙር አሰሙ፤ክብርንና ምስጋናን፥
ኃይልንም ለእግዚአብሔር ስጡ፤ [2]ለስሙ
የሚገባውን ክብርና ምስጋና ለእግዚአብ
ሔር አቅርቡ። የቅድስናው ግርማ ሞገስ
ደምቆ በሚታይበት ስፍራ ለእግዚአብሔር
ስገዱ።
[3]የእግዚአብሔር ቃል በውሆች ላይ
ነው፤ የክብርና የምስጋና አምላክ ነጐድጓ
ዱን በደመና ውስጥ ያስተጋባል። እግዚአብ
ሔር ነጐድጓዱን በውቅያኖሶች ማዕበል ያሰ
ማል። [4]የእግዚአብሔር ቃል ኃያል ነው፤
የእግዚአብሔር ቃል ግርማው ገናና ነው።
[5]የእግዚአብሔር ቃል ዝግባን ይሰብራል፤
እግዚአብሔር የሊባኖስን ዝግባ እንክትክት
አድርጎ ይሰባብረዋል። [6]ሊባኖስን እንደ
እምቦሳ እንዲቦርቅ፥ ስርዮንን እንደ ጎሽ
ኰርማ እንዲዘል ያደርጋል። [7]የእግዚአብ
ሔር ቃል በመብረቅ ብልጭታ ይመታል።
[8]የእግዚአብሔር ቃል በረሃውን ያናውጠ
ዋል፤የቃዴስን ምድረ በዳ ሳይቀር እግዚአ
ብሔር ያናውጣል። [9]የእግዚአብሔር ቃል
ወርካውን እንደ ፈትል ይገምደዋል፤የደኑን
ቊጥቋጦ ገፎ ሴጣ ያደርገዋል። በዚህ ጊዜ
ሁሉም፥ «ምስጋናና ክብር ለእግዚአብሔር
ይሁን» እያሉ ከፍ ባለ ድምፅ በመቅደሱ
ይዘምራሉ።
[10]እግዚአብሔር በሥልጣኑ የጥፋት
ውሃን መቅሠፍት ያመጣ መሆኑን አሳይ
ቷል፤እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ
ፍጥረቱን የሚያስተዳድር የዘላለም ንጉሥ
ነው። [11]እግዚአብሔር ለሚታመኑበት
ሕዝቡ ኃይልን ይሰጣል። እግዚአብሔር ሰላ
ምን በመስጠት ሕዝቡን ይባርካቸዋል።

## መዝሙር 30

[1]እግዚአብሔር ሆይ፥ ከወደቅሁበት
ጥልቅ ጕድጓድ እጄን ይዘህ ስላወጣኸኝና
ጠላቶቼም፥ «እንኳን እንዲህ ሆነ» እያሉ
እንዳይሳለቁብኝ ስላደረግህ፥ ስምህን እያገነ
ንኩ አመሰግንሃለሁ። [2]ፈጣሪዬ እግዚአብ
ሔር ሆይ፥ «እርዳኝ» ብዬ ጠራሁህ፤አን
ተም ፈወስከኝ። [3]ጌታ ሆይ፥ከመሞት አት
ርፈህ፥ወደ መቃብርም ከመውረድ አድነህ
ከሲኦል አወጣኸኝ።
[4]አሁንም ቅዱሳኑ ለእግዚአብሔር
ዘምሩ፤ለስሙ የምስጋና መዝሙር አቅርቡ።
[5]ቊጣው ለአንድ አፍታ ነው፤ቸርነቱ ግን
ዕድሜ ልክ አብሮን ይኖራል፤ሲለቀስ ቢታደ
ርም፥በማለዳ ደስታ ይሆናል።
[6]በደላኝ ጊዜ፥ «እንግዲህ ለዘላለም አል
ናወጥም» አልሁ። [7]ጌታ ሆይ፥በፊትህ ሞገ
ስን ባገኘሁ ጊዜ የሕይወቴን አቋዋም እንደ
ማይነቃነቅ ተራራ የጸና አደረግኸው። ገጽ

ህን በሸሸግህብኝ ጊዜ ግን ተስፋ የሚያስቈ
ርጥ ኀዘን ላይ ወደቅሁ።
8በዚያን ጊዜ፥እግዚአብሔር ሆይ፥ወደ
አንተ ተጣራሁ። ምሕረትህንም እንድታወር
ድልኝ እንዲህ እያልኩ ወደ አንተ ወደ
ጌታ ጮህኩ፤ 9«እኔ ብጠፋ፥ሞቼም ወደ
መቃብር ብወርድ ከቶ ምን ጥቅም አለው?
አፈር ያመሰግንሃልን? የሚተማመኑብህ
አምላክ መሆንህን በማረጋገጥ ስለ አንተ
በይፋ ይናገራልን? 10ፈጣሪዬ ሆይ፥ስማኝ፤
ይቅርታህንም አድርግልኝ። አቤቱ፥አጋዤና
ረዳቴ ሁን።»
11እነሆ ይህን ጸሎቴን ተቀብለህ የልቅሶ
ዬን ጩኸት ወደ እልልታ መዝሙር ለወጥ
ህልኝ፤የኀዘን ልብሴን አውልቀህ የደስታ
ሸማ አጐናጸፍከኝ። 12እግዚአብሔር ሆይ፥
ይህን ስላደረግህልኝ ልቤ ይዘምርልሃል፤
ዝም አይልም። አዎን፥ለዘላለሙ ሳመሰግንህ
እኖራለሁ።

## መዝሙር 31

1እግዚአብሔር ሆይ፥አንተን መጠጊያዬ
ስላደረግሁ ምን ጊዜም አልፈር፤በጽድቅ
ህም ከመከራ አውጣኝ። 2ጆሮህን ወደ እኔ
አዘንብል፤ታተርፈኝም ዘንድ ፈጥነህ ድረስ
ልኝ፤እኔን ለማዳን መጠጊያ አምባዬና ጠን
ካራ ምሽጌ ሁን። 3አምባዬና ምሽጌ አንተ
ስለ ሆንህ፥ስለ ስምህም ስትል እየመራኸኝ
ቀናውን መንገድ አሳየኝ። 4መጠጊያዬ
አንተ ነህና በስውር ከተዘጋጀብኝ ወጥመድ
ጠብቀኝ። 5የእውነት አምላክ እግዚአብ
ሔር ሆይ፥እነሆ ነፍሴን አደራ ብዬ በእጅህ
ስለ ሰጠሁህ ቤዛ ሆነህ አድነኝ።
6ከንቱ የሆኑትን ጣዖቶች በማምለክ የጸ
ኑትን ጠላሁ፤እኔ ግን በእግዚአብሔር ታመ
ንሁ። 7ጌታ ሆይ፥በመከራ መሠቃየቴን ስላ
የህና የነፍሴን ጭንቀት ስላወቅህ በፍቅርህ
ደስ ይለኛል፤ሐሤትም አደርጋለሁ። 8ለጠ
ላት አሳልፈህ አልሰጠኸኝም፤እንዲያውም
በሰፊ መስክ ላይ እንደ ልቤ እንድመላለስ
አስቻልከኝ።
9አሁንም እግዚአብሔር ሆይ፥በጽኑ
መከራ ላይ ነኝና ምሕረትህን አድርግልኝ።
ዓይኖቼ ከልቅሶ፥ነፍሴና ሥጋዬም ከመሪር
ኀዘን የተነሣ ደከሙ። 10ሕይወቴ በጭን
ቀት፥ዕድሜዬም በዋይታ አለቀ። በሥቃዬ
ምክንያት ጕልበቴ እየከዳኝ፥አጥንቶቼም
እየደቀቁ ሄዱ። 11ለጠላቶቼ ሁሉ መዘባበቻ
በመሆኔ፥በጎረቤቶቼ ዘንድ ፈጽሜ ተናቅሁ።
የሚያውቁኝ ሰዎች በመንገድ ላይ ገና
በሩቅ ሲያዩኝ ስለሚሸሹኝ ለወዳጆቼ እንኳ
ማስፈራሪያ ሆንሁ። 12በእነርሱ ዘንድ እንደ
ሞተ ሰው ተረሳሁ፤እንደ ተሰበረ የሸክላ
ዕቃም ተጣልኩ። 13ብዙዎች የሚሰነዝሩብ
ኝን ስድብ ሰማሁ፤የሚያጋጥመኝ የሚያሸ
ብር ነገር ብቻ ነው፤ሰዎች በእኔ ላይ ይዶል
ቱብኛል፤ሕይወቴንም ለማጥፋት ያሤራሉ።
14እኔ ግን እግዚአብሔር ሆይ፥የምተማ
መነው አንተን ብቻ ስለ ሆነ፥«አንተ አም
ላኬ ነህ» እላለሁ። 15ዕድሜዬን ወስነህ
ኑሮዬን የምትመራ አንተ ነህና ከጠላቶቼና
ከሚያሳድዱኝ እጅ አድነኝ። 16የፊትህ
ሞገስ በአገልጋይህ ላይ ይብራ፤በማይለወጠ
ውም ፍቅርህ አድነኝ። 17ጌታ ሆይ፤ጩኸ
ቴን ወደ አንተ ስላሰማሁ አልፈር፤ክፉዎች
ግን ይፈሩ፤በሲኦልም ዝም ይበሉ። 18እነ
ርሱ በጻድቁ ላይ የትዕቢትና የንቀት ቃል
በእብሪት ስለሚናገሩ የሚዋሹበት አንደበታ
ቸው ይዘጋ።
19አቤቱ፥ለሚፈሩህና በአንተ ለሚተማ
መኑብህ ሰዎች በሕዝብ ፊት በግልጽ ለታ
ደርግላቸው ያሰብከው ቸርነትህ ምን ያህል
ታላቅ ነው! 20በሰዎች ተንኰል እንዳይጠ
መዱ መጠለያ ሆነህ ትሸሽጋቸዋለህ፤የአንደ
በት ንትርክ እንኳ እንዳይደርስባቸው በማደ
ሪያህ ውስጥ ተከባክበህ ትጠብቃቸዋለህ።
21እነሆ፥በወራሪዎች በተከበበች ከተማ
ውስጥ ሳለሁ፥ለእኔ ያለውን እጹብ ድንቅ
የሆነ ፍቅሩን በግልጽ አሳይቷልና እግዚአ
ብሔር የተመሰገነ ይሁን። 22በዚያ ድንጋ
ጤዬ ጊዜ ተቻኩዬ፥«ለካ እግዚአብሔር
እንዳያየኝ ከፊቱ የተወገድሁ ሆኛለሁና!»
ብዬ ነበር። አንተ ግን እንድትምረኝ የጮህ
ኩትን ጩኸቴን፥እንድትደርስልኝ የተጣራ
ሁትንም ጥሪዬን ሰማህ።
23እንግዲህ ቅዱሳኑ ሁሉ እግዚአብሔ
ርን ውደዱት። እግዚአብሔር እውነተኞችን
ይጠብቃል፤ለትዕቢተኞች ግን ፍዳቸውን
ይከፍላቸዋል። 24እግዚአብሔርን ተስፋ
የምታደርጉ ሁሉ በርቱ፤ልባችሁም በትዕግ
ሥት ይጽና።

## መዝሙር 32

1እግዚአብሔር ጥፋቱን ይቅር የሚለ
ውና ኃጢአቱን የሚተውለት፥ 2በደሉን
የማይቈጥርበትና በልቡ ሽንገላ የሌለበት
ሰው ምንኛ የተባረከ ነው!
3እኔ ግን ዝም ብዬ ቀኑን ሙሉ በትካዜ
እየተወዛወዝኩ ስለምውል ኀዘኔ እስከ አጥ
ንቴ ደርሶ ሰውነቴ አለቀ። 4በቀንና

በጥላቻ አፋጩብኝ።
17 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ይህን ድርጊታቸ
ውን ዝም ብለህ የምትመለከተው እስከ
መቼ ነው? እንደ ተራቡ አንበሶች ሊገነጣ
ጥሉኝና ይህቺን አንዲት ሕይወቴን ሊያጠ
ፏት ከተዘጋጁት ከእነዚህ ጨካኞች ነፍሴን
አትርፋት። 18 እኔም በአማኞችህ ታላቅ
ጉባኤ መካከል አመሰግንሃለሁ፤ብዙ ሕዝብ
በሚሰበሰብበትም በዓል ላይ የምስጋና መዝ
ሙር አቀርብልሃለሁ።
19 ምንም ሳልበድላቸው የተነሡብኝ
ጠላቶቼ ፥ «እንኳን እንዲህ ሆነ» ብለው
ደስ እንዲላቸው ፥ ያለምክንያት የሚጠሉ
ኝም እንዲጠቃቀሱብኝ አታድርግ። 20 በሰ
ላም የሚኖሩትን ሰዎች በሐሰት ለመክሰስ
ተንኰል ከመሸረብ በስተቀር ከአንደበታ
ቸው መልካም ነገር አይሰማም። 21 አፋቸ
ውን በእኔ ላይ ከፍተው ፥ «እሰይ ፥ እሰይ ፥
ይኸው በገዛ ዓይናችን የደረሰበትን አየን!»
ይላሉ።
22 እግዚአብሔር ሆይ ፥ የደረሰብኝን
ጥቃት ሁሉ ተመልክተኸዋልና እንግዲህስ
ዝም አትበል ፤ አቤቱ ፥ ከእኔ አትራቅ።
23 ንቃ! ስለ እኔ ለመከላከል ተነሥ፤ፈጣሪዬ
እግዚአብሔር ሆይ ፤ ለእኔ ተዋጋልኝ።
24 ጻድቅ አምላክ ነህና ፥ ጌታዬ እግዚአብ
ሔር ሆይ፥ከክስና ወቀሳ ነጻ አድርገኝ፤ጠላ
ቶቼ ፥ «እንኳን እንዲህ ሆነ!» እያሉ ደስ
አይበላቸው። 25 «እሰይ! በእርሱ ላይ የፈለ
ግነው ደረሰ» ወይም «እጃችን ውስጥ
ወደቀ» ብለው እንዲፎክሩብኝ አታድርግ።
26 አቤቱ፥መከራ በሚደርስብኝ ጊዜ፥ «እን
ኳን እንዲህ ሆነ!» እያሉ የሚደሰቱ ሁሉ
ይፈሩ፤ይታወኩ። በእኔ ላይ ራሳቸውን በትዕ
ቢት ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ሁሉ ኀፍረትንና
ውርደትን ይልበሱ። 27 ከክስና ወቀሳ ነጻ
መሆኔን የሚወዱ ግን በደስታና በሐሤት
እልል ይበሉ፤ዘወትር፥ «በአገልጋዩ ደኅን
ነት ደስ የሚለው እግዚአብሔር ገናና
ይሁን!» ይበሉ። 28 አንደበቴ ጽድቅህንና
ታላቅነትህን ይናገራል።

## መዝሙር 36

1 ስለ ኃጢአተኞች ሰዎች ፥ መንፈስ
በልቤ ውስጥ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፦ «በእ
ነርሱ ዘንድ እግዚአብሔርን መፍራት
የለም። 2 በልባቸው ራሳቸውን ከመጠን
በላይ በከንቱ ውዳሴ እየካቡ ስለሚያመጻ
ድቁ ኃጢአታቸውን ለይተው ለማወቅና
ለመጸየፍ ከቶ አይቻላቸውም። 3 ከአንደበታ
ቸው የሚወጣው ቃል ሁሉ ክፋትንና ሐሰ
ትን የተመላ ነው። ከብልህነት አስተሳሰብና
ከመልካም አድራጎት ጨርሰው የተለዩ
ናቸው። 4 ተኝተው ሳለ እንኳ የሚያውጠን
ጥኑት ክፉ ሥራን ብቻ ነው። ራሳቸውን
የሚያዘጋጁት ለኃጢአት ድርጊት እንጂ
ጥፋትን ተቃውመው ለመመለስ አይደ
ለም።»
5 አንተ ግን እግዚአብሔር ሆይ፤ፍቅርህ
እስከ ሰማየ ሰማያት ፥ ታማኝነትህም የሰማ
ይን ደመና የሚያልፍ ነው። 6 ጽድቅህ
እንደ ታላላቆቹ ተራራዎች እጅግ ጎልቶ
ይታያል ፤ ፍርድህ እንደ ውቅያኖስ የጠለቀ
ነው። ጌታ ሆይ፥አንተ የሰውን ልጆችና እን
ስሳትን ጠብቀህ ታኖራለህ። 7 የማይለወጠው
ፍቅርህ በዋጋ ሊተመን የማይቻል ነው።
ታላላቆችም ሆኑ ታናናሾች ሰዎች፥ሁሉም
በክንፎችህ ጥላ ሥር መጠጊያን ያገኛሉ።
8 በቤትህ ውስጥ ሞልቶ ከተትረፈረፈው
ምግብ በልተው ይጠግባሉ። ከተድላህ
ወንዝ መጠጥ ሰጥተህ ታረካቸዋለህ። 9 የሕ
ይወት ምንጭ የሚገኘው ካንተ ዘንድ ነው፤
ብርሃንንም ለማየት የምንችለው በአንተ
ብርሃን ነው።
10 አሁንም ለሚያውቁህ ፍቅርህን ፥ ቅን
ልቦና ላላቸውም ጽድቅህን አታጓድልባ
ቸው። 11 ትዕቢተኞች ሊቃወሙኝ ወደ እኔ
ለመምጣት እግሮቻቸውን አያንሡ፤ክፉዎች
እኔን ለማሳደድ እጆቻቸውን አይሰንዝሩ።
12 ክፉ አድራጊዎች እንዴት ያለ አወዳደቅ
እንደ ደረሰባቸውና እንዳያንሠራሩ ሆነው
እንደ ተጣሉ ተመልከቱ!

## መዝሙር 37

1 ክፉዎች በሚያደርሱት የበደል ድር
ጊት አትበሳጭ ፤ ግፈኞችም በሚፈጽሙት
የጥፋት ሥራ አትቅና። 2 ሁሉም ፈጥነው
እንደ ሣር ይደርቃሉ፤እንደ ቅጠልም ጠው
ልገው ይረግፋሉ።
3 አንተ ግን በእግዚአብሔር ተማምነህ
መልካም ነገር አድርግ ፤ እርሱ በለመለመ
መስክ አሰማርቶ ደስ ብሎህ በሰላም እንድ
ትኖር ያደርግሃል። 4 በእግዚአብሔር ደስ
ይበልህ ፤ እርሱ ልቦናህ የተመኘውን ይሰጥ
ሃል።
5 ዕቅድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፤
በእርሱም ተማመን ፤ እርሱም ዕቅድህን
በሥራ ላይ እንድታውል ይረዳሃል። 6 ጽድ
ቅህ እንደ ጠዋት ጮራ እንዲያበራ፥የዓላማ
ህም ትክክለኛነት እንደ ቀትር ፀሐይ እንዲ

ያንጸባርቅ ያደርግልሃል።
7 በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ በል ፤ እርሱ
የሚያደርገውን በትዕግሥት ተጠባበቅ። የሰ
ዎች ኑሮ ሲቃና ፥ የክፋት ዕቅዶቻቸውንም
በሥራ ላይ ሲያውሉ ስታይ አትበሳጭ።
8 ከመቈጣት ታገሥ ፤ ከመናደድም ተጠ
በቅ ፤ አትበሳጭ ፤ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ
የሚያደርሱት ወደ ክፋት ነው። 9 ክፉዎች
ሰዎች ካሉበት ይወገዳሉ ፤ እግዚአብሔርን
ተስፋ የሚያደርጉ ግን ምድርን ይወርሳሉ።
10 ክፉዎች ለጥቂት ጊዜ ብቻ ፥ «አለን!
አለን!» ይላሉ ፤ ወዲያው ግን ይጠፋሉ ፤ ቢፈ
ለጉ እንኳ አይገኙም። 11 ገሮች ግን ምድ
ርን ይወርሳሉ ፤ በፍጹም ሰላም ደስ ብሏ
ቸው ይኖራሉ።
12 ክፉዎች በጻድቃን ላይ ያሤራሉ ፤ እነ
ርሱን ሲያዩዋቸው በዛቻ ጥርሳቸውን ይነክ
ሱባቸዋል። 13 እግዚአብሔር ግን የክፉዎች
ፍጻሜ የደረሰ መሆኑን አስቀድሞ ስለሚያ
ውቅ ይስቅባቸዋል።
14 ግፈኞች ፥ ድኾችንና ችግረኞችን የባሰ
ለመጣል ፥ በቅንነት መንገድ የሚሄዱትንም
ጨርሰው ለማጥፋት ሰይፋቸውን ይመዛሉ ፤
ቀስታቸውንም ይደግናሉ። 15 ዳሩ ምን ያደ
ርጋል! ሰይፋቸው ተመልሶ የራሳቸውን
ልብ የሚወጋ ፥ ቀስታቸውም ተሰባብሮ የሚ
ወድቅ ይሆናል።
16 ክፉዎች ከሰበሰቡት የደለበ ሀብት
ይልቅ ፥ የጻድቃን አነስተኛ የዕለት ጉርስ
ይሻላል። 17 የክፉዎች ኃይል ተንኰታኩቶ
ይወድቃል ፤ እግዚአብሔር ግን ጻድቃንን
ደግፎ ያጸናቸዋል።
18 ንጹሐን በየዕለቱ ኑሮአቸው የሚፈጽ
ሙት ምግባር በእግዚአብሔር ዘንድ የታ
ወቀ ስለ ሆነ የዘላለም ሕይወት ይወር
ሳሉ። 19 መቅሠፍት በሚመጣበት ጊዜ
አይደናገጡም ፤ በረሃብም ዘመን ምግብ ይኖ
ራቸዋል።
20 ክፉዎች ግን ይጠፋሉ ፤ የእግዚአብ
ሔር ጠላቶች ፥ በክረምት ለምልሞና አብቦ ፥
በበጋ እንደሚደርቀው የሜዳ ሣር ናቸው ፤
ፍጻሜያቸውም እንደ ጢስ በኖ መጥፋት
ይሆናል።
21 ኃጥእን ይበደራሉ ፤ መልሰው አይከፍ
ሉም ፤ ጻድቃን ግን ለጋሶች ናቸው። 22 እግ
ዚአብሔር የሚባርካቸው ሁሉ ምድርን
ይወርሳሉ ፤ እርሱ የሚረግማቸው ግን ይጠ
ፋሉ።
23 እግዚአብሔር የጻድቅን እርምጃ ይቈ
ጣጠራል ፥ በአኗኗሩም ደስ ይለዋል ፤ 24 ይህ
ሰው ቢደናቀፍ እንኳ ጌታ በእጆቹ ስለሚደ
ግፈው ከቶ አይወድቅም።
25 ከልጅነት ይኸው እስከ እርጅና ደርሻ
ለሁ ፤ ዳሩ ግን በዚህ ረዢም ዕድሜዬ ጻድቅ
አጥቶ ተቸግሮ ፥ ልጆቹም ተርበው ምግብ
ሲለምኑ አይቼ አላውቅም። 26 እንዲያውም
እጁ ሰፊ ሆኖ ሲቸርና ያለወለድ ሲያበድር ፥
ልጆቹም በበረከት የተሞሉ ሆነው አይቻ
ለሁ።
27 ስለዚህ ክፋትን ተው ፤ መልካሙንም
ነገር አድርግ ፤ እንዲህ ካደረግህ ምን ጊዜም
ያለሥጋት ተረጋግተህ ትኖራለህ። 28 እግዚ
አብሔር እውነተኞችን ይወዳልና ፤ በእርሱ
የሚተማመኑትን አይተዋቸውም ፤ ለዘላለም
ይጠብቃቸዋል። የክፉዎች ዘሮች ተወግ
ደው ሲጠፉ ፥ 29 ጻድቃን ምድርን ወርሰው
ለዘላለም ይኖሩባታል።
30 ጻድቅ ሰው ከአንደበቱ ጥበብን ያፈል
ቃል ፤ በልሳኑም እውነትን ይናገራል ፤ 31 የፈ
ጣሪው ሕግ በልቡ ውስጥ ስለ ተቀረጸ እግ
ሮቹ አይሰናከሉም።
32 ክፉዎች በጻድቃን ላይ ያደባሉ ፤ ሕይ
ወታቸውን ሳይቀር ለማጥፋት ይከታተሏቸ
ዋል። 33 እግዚአብሔር ግን ጻድቃንን ለክፉ
ዎች አሳልፎ አይሰጣቸውም ፤ ተከሰው አደባ
ባይ ቢያቀርቡዋቸውም እንኳ እንዲፈረድባ
ቸው አያደርግም።
34 እግዚአብሔርን ደጅ ጥኑ ፤ መንገዱንም
ተከተሉ። እርሱ ምድርን ትወርሱ ዘንድ
ከሁሉ ይልቅ ከፍ ከፍ ያደርጋችኋል ፤ ክፉዎ
ችም ተወግደው ሲጠፉ ለማየት ትበቃላ
ችሁ።
35 ጭካኔን የተሞላ ክፉ ሰው በምቹ
መሬት ላይ እንደ ተተከለ ዛፍ ለምልሞና
ተንሰራፍቶ አየሁት። 36 ከጥቂት ጊዜ በኋላ
ብመለከተው ግን በቦታው ጨርሶ የለም ፤
ብፈልገው እንኳ ከቶ ሊገኝ አልቻለም።
37 ዳሩ ግን የንጹሑን ሰው ሁኔታ ሲያስ
ተውሉት ፥ የልበ ቅኑንም ኑሮ ሲያመዛዝ
ኑት ፥ ሰላም ወዳድ ሰው ብሩህ ተስፋ እንዳ
ለው ይታያል። 38 እነሆ ኃጢአተኞች ሁሉ
ፈጽመው ያልቃሉ ፤ ክፉዎችንም ወደ ፊት
የሚጠብቃቸው ዕጣ መወገድና ማለቅ ብቻ
ነው።
39 ጻድቃን የደኅንነትን ቤዛ የሚያገኙት
ከእግዚአብሔር ነው ፤ በመከራቸውም ጊዜ
ምሽጋቸው እርሱ ነው። 40 እርሱን መጠ
ጊያ ስላደረጉት እግዚአብሔር ይረዳቸዋል ፤
ያድናቸዋል ፤ ከክፉዎችም እጅ ያወጣቸ
ዋል።

# መዝሙር 38

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ በቍጣህ አትገሥ
ፀኝ፤ በመዓትህም አትቅጣኝ። 2 እነሆ ፍላጻ
ዎችህ ወግተውኛል፤ የእጅህም በትር አደ
ፍብኛል። 3 ከቍጣህ የተነሣ በሰውነቴ
ውስጥ ጤንነት አይሰማኝም። በኃጢአቴ
ምክንያት አጥንቶቼ ሳይቀሩ ታውከዋል።
4 በደለኛነቴ ከአቅሜ በላይ ሆኖብኛል፤
እንደ ከባድ ሸክም ተጭኖኝ አስጨንቆ
ኛል። 5 በሞኝነት በፈጸምኩት ኃጢአት
ምክንያት የደረሰብኝ ቍስል እያመረቀዘ
የማይሽር ሆነ። 6 ጒስቊልሁ፤ ተዋረድሁ፤
ቀኑን ሙሉ በትካዜ እውላለሁ። 7 በአከር
ካሪዬ ውስጥ ትኩሳትና ውጋት ያሠቃየ
ኛል። መላ ሰውነቴ ጤና የለውም።
8 አቅሜ ደከመ፤ ፈጽሜ ውድቅድቅ
አልሁ። በልቤ ውስጥ መራራ ሥቃይ ስለ
ሚሰማኝ በኀዘን እቃትታለሁ።
9 ጌታ ሆይ፥ ፍላጎቴ በአንተ ፊት
ግልጽ ስለ ሆነ፥ ሁሉንም ታውቀዋለህ፤
የጭንቀት ስሜቴ ካንተ የተሰወረ አይደ
ለም። 10 ልቤ ይሸበራል፤ ጒልበቴ ከዳኝ፤
ዓይኔ እንኳ ማየት ተሳነው። 11 በቍስሌ
ምክንያት ወዳጆቼና ባልንጀሮቼ ሸሹኝ፤
ጎረቤቶቼም ራቁኝ። 12 ሕይወቴን ለማጥ
ፋት የሚፈልጉ ጠላቶቼ ወጥመዳቸውን
ዘረጉብኝ፤ ጒዳት ላይ ሊጥሉኝ የሚያስቡ
ባለጋራዎቼ ስለ እኔ ውድቀት ይማከራሉ፤
ቀኑን ሙሉ የሐሰት ነገር ለመፈጸም
ያሤራሉ።
13 እኔም ምንም እንደማይሰማ ደንቆሮና
አፉን ሊከፍት እንደማይችል ድዳ ሆንሁ።
14 መስማት እንደ ተሳነውና አንዳችም
መልስ መስጠት እንዳቃተው ሰው እስከ
መሆን ደረስሁ።
15 ስለዚህ አቤቱ፥ ፈጣሪዬ እግዚአብሔር
ሆይ፥ አንተን በትዕግሥት እጠብቃለሁ። አን
ተም ልመናዬን ትሰማኛለህ። 16 እኔም፥
«እግሬ በሚሰነካከልበት ጊዜ ጠላቶቼ፥
'እንኳን እንዲህ ሆነ!' በማለት በእኔ ላይ
እንዲታበዩና ደስ እንዲላቸው አታድርግ»
አልሁ።
17 እነሆ ልወድቅ ነው፤ ሥቃዬም አልተ
ወኝም። 18 ኃጢአቴን በማስታወስ ስለ
ተጨነቅሁ በደሌን እናዘዛለሁ። 19 የበረቱ
ብኝ ጠላቶቼ ብዙዎች ናቸው፤ ያለምክንያት
የሚጠሉኝም ቍጥራቸው የበረከተ ነው።
20 በጎ የሆነውን ነገር በመሻቴና በመልካም
አድራጎቴ ፋንታ ክፉውን የሚመልሱልኝ
ሰዎች ስሜን በሐሰት ያጠፋሉ።
21 ፈጣሪዬ ሆይ፥ አትተወኝ፤ አቤቱ፥ ከእኔ
አትራቅ። 22 መድኀኔ እግዚአብሔር ሆይ፥
እኔን ለመርዳት ፈጥነህ ድረስ።

# መዝሙር 39

1 «ኑሮዬን በጥንቃቄ እመራለሁ፤ አንደበ
ቴን ክፉ ከመናገር እጠብቃለሁ፤ ክፉዎች
በአካባቢዬ እስካሉ ድረስ ዝም እላለሁ»
አልሁ። 2 ዳሩ ግን አፌን ዘግቼ ጸጥ በማለ
ቴና መልካም ስለ ሆነው ነገር እንኳ ባለ
መናገሬ እነሆ ሥቃዬ በረታብኝ። 3 ልቤ
እየጋለብኝ ሄደ፤ መከራዬን ባሰላሰልኩ
ቍጥር ሰውነቴ እንደ እሳት የሚነድብኝ
ሆነ። ቢጨንቀኝ በአንደበቴ እንዲህ እያ
ልኩ መናገር ጀመርኩ፤ 4 «እግዚአብሔር
ሆይ፥ የሕይወቴ ፍጻሜ መቼ እንደ ሆነና
የዕድሜዬ ልክ ስንት እንደ ሆነ ግለጽልኝ፤
በዚህ ዓለም የምኖረው ዘመን ፈጥኖ የሚያ
ልፍ መሆኑን ለማወቅ አስችለኝ። 5 አቤቱ፥
የዕድሜዬን መጠን ከጋት የማትበልጥ አደ
ረግሃት፤ በአንተ ዘንድ የዘመኔ ርዝመት
ኢምንት ናት። የያንዳንዱም ሰው ሕይወት
እፍ እንደሚሉት ትንፋሽ ነው። 6 ሰው
ወዲያ ወዲህ የሚንቀሳቀሰው እንዲያው
እንደ ጥላ ነው፤ እየተራወጠ በከንቱ ይባክ
ናል፤ ለማን እንደሚሆን ሳያውቅ ሀብት ያከ
ማቻል።
7 «እኔ ግን፥ ጌታ ሆይ፥ ከአንተ በቀር ሌላ
ማንን ደጅ እጠናለሁ? ተስፋዬ አንተ ብቻ
ነህ። 8 በኃጢአቴ ምክንያት ከሚደርስብኝ
ቅጣት አድነኝ፤ የማይረቡ ሰዎች መሳለቂያ
አታድርገኝ። 9 እኔ ዝም አልኩ፤ አንደበቴን
ከመናገር ገታሁ። ምክንያቱም ይህን ሁሉ
ያደረግህ አንተ ነህ። 10 በእጅህ ካወረድክ
ብኝ ከባድ በትር የተነሣ በጣም ደክሜአለ
ሁና አቤቱ፥ 'በቃህ' ብለህ ቅጣትህን አንሣ
ልኝ። 11 ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው ትገሥጻ
ቸዋለህ፤ ትቀጣቸዋለህ፤ የሰበሰቡትንም
ሀብት፥ ብል እንደ በላው ልብስ አመድ ታደ
ርጋባቸዋለህ። የእያንዳንዱ ሰው ሕይወት
እፍ እንደሚሉት ትንፋሽ ነው።
12 «አሁንም እግዚአብሔር ሆይ፥ ጸሎ
ቴን ስማ! 'ድረስልኝ' እያልኩ የማሰማውን
ጩኸቴን አድምጥ፤ ጆሮህን ወደ ልቅሶዬ
አዘንብል፤ እንደ ቀደሙት አባቶቼ እኔም
እንግዳና በምድር ላይ አላፊ መንገደኛ ስለ
ሆንኩ 13 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቼ ከመሰ
ናበቴ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ደስታን አይ
ዘንድ እባክህ ፋታ ስጠኝ።»

## መዝሙር 40

1 እግዚአብሔርን ያለመሰልቸት ደጅ
ጠናሁት፤እርሱም ጩኸቴን ሰምቶ ፊቱን
ወደ እኔ መለሰልኝ። 2 ማጥና ረግረግ ከሞላ
በት የመከራ ጒድጓድ አወጣኝ፤እግሮቼ በዓ
ለት ላይ እንዲያርፉ አድርጎ የምቆምበትን
ጽኑ ስፍራ አዘጋጀልኝ። 3 ለእርሱ ለፈጣሪያ
ችን ለማቀርበው ምስጋና አዲስ ዝማሬ ከአ
ንደበቴ አፈለቀልኝ። ብዙዎች ይህን አይ
ተው ይፈራሉ፤እምነታቸውንም በእግዚአብ
ሔር ላይ ይጥላሉ።
4 እግዚአብሔርን መተማመኛው ያደረ
ገና የሐሰት አምልኮን የሚፈጽሙ ትዕቢ
ተኞችን እርአያ የማይከተል ሰው የተባ
ረከ ነው። 5 አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፥
ለእኛ ያደረግሃቸው ድንቅ ተአምራትህ
ብዙዎች ናቸው፤ያቀድክልንን በጎ ነገሮች
ዘርዝሮ ለማስረዳት የሚቻለው ማንም
የለም፤እኔ ስለ እነዚህ ነገሮች ልናገር
ብል፥ብዛታቸው ከመጠን በላይ ይሆንብ
ኛል።
6 የእንስሳት ደም የሚፈስበትን መሥዋ
ዕትና የእህሉን ቍርባን አልፈለግህም፤
የሚቃጠለውንና የኃጢአት ማስተስረያ
የሆነውንም ቍርባን አልፈቀድክም፤የሚ
ሰማ ጆሮ፥የሚያስተውል አእምሮ ግን
ሰጠኸኝ። 7 እኔም እንዲህ አልሁ፦ «ስለ
እኔ በመጽሐፍ በተጻፈው መሠረት እነሆ
መጥቻለሁ። 8 አምላኬ ሆይ፥ሕግህ በልቦ
ናዬ ስላለ ፈቃድህን መፈጸም እወዳ
ለሁ።»
9 በሕዝብህ ታላቅ ጉባኤ መካከል
ቆሜ ስለ ጽድቅህ በይፋ እናገራለሁ፤አን
ደበቴን አልዘጋም፤ይህንንም ጌታ ሆይ፥
አንተ ታውቀዋለህ። 10 በልቤ ውስጥ ያለ
ውን ጽድቅህን አልሸሽግም። የምትታመ
ንና የምታድን አንተ መሆንህን እናገራ
ለሁ። ፍቅርህንና እውነትህን ከሕዝብህ
ጉባኤ አልሰውርም።
11 እግዚአብሔር ሆይ፥ምሕረትህን ከእኔ
አትመልስ፤ፍቅርህና እውነትህ ዘወትር ይጠ
ብቁኝ። 12 ስፍር ቍጥር የሌለው ችግር ከበ
ኛል፤ከራስ ጸጒሬ ይልቅ በበዛው ኃጢአቴ
ምክንያት ማየት ተስኖኛል። ልቤም እየከ
ዳኝ ሄደ።
13 አቤቱ፥ጌታ ሆይ፥እኔን ለማዳን ፈቃ
ድህ ይሁን፤ትረዳኝ ዘንድ ፈጥነህ ድረስ
ልኝ። 14 ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ ሁሉ
ይፈሩ፤ይታወኩ፤ውድቀቴን የሚመኙም
ሁሉ እየተዋረዱ ይመለሱ። 15 «እሰይ!
እሰይ! እንኳን እንዲህ ሆነ!» የሚሉኝ
በሚደርስባቸው ኀፍረት ግራ ገብቷቸው
ይገረሙ። 16 የሚፈልጉህ ሁሉ ግን በአንተ
ደስ ይበላቸው፤ሐሤትም ያድርጉ፤ቤዛነት
ህን የሚወዱ ዘወትር፥ «እግዚአብሔር
ገናና ይሁን!» ይበሉ።
17 አቤቱ፥እኔ ድኻ፥ችግረኛም ነኝና
አስበኝ። የምትረዳኝና የምታድነኝ አንተ
ስለ ሆንክ ፈጣሪዬ ሆይ፥ «አለሁልህ»
በለኝ።

## መዝሙር 41

1 ለድኻና ለችግረኛ የሚራራ ሰው የተባ
ረከ ነው። እግዚአብሔር በመከራ ጊዜ ይደ
ርስለታል፤ 2 ይጠብቀዋል፤በሕይወትም ያኖ
ረዋል፤በምድር ላይ ይባርከዋል፤ለጠላቶቹም
አሳልፎ አይሰጠውም። 3 ታሞ ቢተኛ በአል
ጋው ላይ ያጽናናዋል፤ጤናውንም ይመልስ
ለትና ያስነሣዋል።
4 እኔም ፈጣሪዬን፥ «እግዚአብሔር
ሆይ፥ቃልህን ተላልፌ ኃጢአትን ሠርቻለ
ሁና ማረኝ፤ከሕመሜ ፈውሰኝ» አልሁት።
5 ጠላቶቼ ግን፥ «መቼ ይሞትልን ይሆን?
ከነስሙስ ተረስቶ የሚቀረው መቼ ይሆን?»
እያሉ ስለ እኔ በጥላቻ ይናገራሉ። 6 ከእነ
ርሱ መካከል ሊጠይቁኝ የሚመጡ ቢኖ
ሩም እኔን በመደለል በሐሰት ቃል ሊያጽና
ኑኝ ይሞክራሉ፤በልባቸው ግን ስሜን የሚ
ያጠፉበትን ክፉ ነገር ያስባሉ፤ከእኔ እንደ
ተመለሱ ሐሜታቸውን በያለበት ይነዛሉ።
7 ጠላቶቼ ሁሉ በእኔ ላይ በአንድነት
ይንሾካሾኩብኛል፤የሚመኙትም እስከ
መጨረሻው የምጠፋበትን ነገር ብቻ
ነው። 8 «መጥፎ ደዌ ይዞታልና ከተኛበት
አልጋ ከእንግዲህ ወዲያ ፈጽሞ አይነ
ሣም» ይላሉ። 9 አብሮኝ በአንድ ማዕድ
የሚሳተፈው ያመንኩት የልብ ወዳጄ ሳይ
ቀር በእኔ ላይ በባላጋራነት ተነሥቶብ
ኛል።
10 አንተ ግን እግዚአብሔር ሆይ፥ማረኝ፤
ብድራቸውን እከፍላቸው ዘንድ ፈውሰህ
አስነሣኝ። 11 ጠላቶቼ እስካሁን ሊያሸንፉኝ
ስላልቻሉ በፊትህ ሞገስ ያገኘሁ መሆኔን
በዚህ አውቄአለሁ። 12 የልቤን ቅንነት ተመ
ልክተህ ደግፈህ አቆየኸኝ፤ለዘላለምም በፊ
ትህ እኖር ዘንድ አጸናኸኝ።
13 የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ለዘ
ላለም የተመሰገነ ይሁን!
አሜን፤አሁንም አሜን።

# ሁለተኛ መጽሐፍ

ከመዝሙር 42-72

## መዝሙር 42

1 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ዋልያ ከምንጭ
ውሃ ለመጠጣት እንደሚጓጓ ፥ ነፍሴ አንተን
ትናፍቃለች። 2 «ወደ ፈጣሪዬ ሄጄ ሕያው
አምላኬን የማገኘው መቼ ይሆን?» እያለች
ነፍሴ እግዚአብሔርን ለማየት ተጠማች።
3 ደግሞም ሰዎች ፥ «አምላክህ ታዲያ
ወዴት አለ?» እያሉ ሁልጊዜ ስለሚጠይ
ቁኝ ከኀዘን የተነሣ ቀንና ሌሊት የሚፈስ
ሰው እንባዬ ምግቤ ሆነ። 4 ሕዝቡ በታ
ላቅ ጉባኤ ተሰብስቦ ለፈጣሪው ምስጋናን
እያቀረበ ደስታውን በሆታና በእልልታ
የሚገልጽበት በዓል ነበረው። እኔም እፊት
እፊት ሆኜ እየመራሁ ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ እንጓዝ ነበር። አሁን ያንን
ሁሉ ሳስታውስ ልቤ በጽኑ ኀዘን ይታወክ
ብኛል።
5 በዚህ ጊዜ፥ «ነፍሴ ሆይ፥ለምን ትተክ
ዠለሽ? ለምንስ ይህን ያህል ትታወኪብኛ
ለሽ? እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጊ። ፈጣ
ሪዬንና መድኀኔን ገና አመሰግነዋለሁ» እያ
ልሁ እጽናናለሁ።
6 ጌታ ሆይ ፥ ነፍሴ በትካዜ ተጐሳቍላ
ለች፤እኔም ቀድሞ በዮርዳኖስ ምድርና በአ
ርሞንኤም ኰረብታዎች ፥ በሚዛር ተራራም
ያደረግኸውን ቸርነትህን አስታውሳለሁ።
7 አንዱ የወንዝ ጥልቀት በሚያስገመግመው
የፏፏቴዎችህ ድምፅ የሌላውን ወንዝ ጥል
ቀት ይጣራል። ማዕበልህና ሞገድህ እያጥለ
ቀለቀኝ በላዬ አለፈ።
8 እግዚአብሔር ፍቅሩን በቀን ይልካል፤
እኔም ዝማሬውን በሌሊት አሰማዋለሁ፤
ይህ ፥ ለሕይወቴ ፈጣሪ የማቀርበው ጸሎት
ነውና።
9 መጠጊያዬን እግዚአብሔር፥ «ስለ ምን
ረሳኸኝ? በጠላቴ እየተጨቈንኩስ ለምን
በኀዘን ሳለቅስ እኖራለሁ?» አልሁት።
10 የሚጠሉኝ ሁሉ፥ «ታዲያ አምላክህ የት
አለ?» እያሉ ቀኑን ሙሉ ስለሚያሸሟጥ
ጡኝ፥እነሆ እስከ አጥንቶቼ በሚደርስ ጭን
ቀት እሠቃያለሁ።
11 በዚህ ጊዜ፥ «ነፍሴ ሆይ፥ለምን ትተ
ክዠለሽ? ለምንስ ይህን ያህል ትታወኪብኛ
ለሽ? እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጊ፤ፈጣሪ
ዬንና መድኀኔን ገና አመሰግነዋለሁና» እያ
ልሁ እጽናናለሁ።

## መዝሙር 43

1 ፈጣሪዬ ሆይ፥ከክስና ወቀሳ ነጻ አድር
ገኝ፤ስለ ቆምኩለት ዓላማዬም ከጽድቅ የራ
ቀውን ሕዝብ በመቃወም ተከራከርልኝ፤ከሸ
ንጋዮችና ከክፉ ሰዎች አድነኝ።
2 «አምላኬና ጽኑ ምሽጌ ነህ» ብዬ ሳም
ንብህ ፥ ስለ ምን «ወግድ» ብለህ ተውኸኝ?
በጠላቶቼ እየተጨቈንኩስ ለምን በኀዘን ሳለ
ቅስ እኖራለሁ? 3 ማደሪያህ ወደ ሆነው
ቅዱስ ተራራህ መርተው ይወስዱኝ ዘንድ፥
ብርሃንህንና እውነትህን ላክልኝ። 4 ከዚያም
ተድላ ደስታዬ ወደ ሆነው ፈጣሪዬ፥የእር
ሱም መንበር ወደሚገኝበት መቅደስ እደር
ሳለሁ። ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ሆይ፥በበገና
በሚታጀብ መዝሙር አመሰግንሃለሁ።
5 አሁንም ነፍሴ ሆይ ፥ ለምን ትተክዣ
ለሽ? ለምንስ ይህን ያህል ትታወኪብኛ
ለሽ? እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጊ። ፈጣ
ሪዬንና መድኀኔን ገና አመሰግነዋለሁ።

## መዝሙር 44

1 እግዚአብሔር ሆይ ፥ አባቶቻችን በዕድ
ሜያቸው፥ከእነርሱም በፊት በነበረው ዘመን
ያደረገኸውን ሁሉ ነገሩን፤እኛም በጆሮአ
ችን ሰማን። 2 አሕዛብን በክንድህ ኃይል አስ
ወጥተህ ለአባቶቻችን ይህቺን አገር አወረስ
ካቸው፤የተቃወሙዋቸውን የአሕዛብ ወገ
ኖች ድል ነሥተህ በተድላ ደስታ እንዲኖሩ
አደረግሃቸው። 3 ስለ ወደድካቸው በቀኝ
እጅህና በክንድህ ፥ በፊትህም ብርሃን ይህን
ሁሉ አደረግህላቸው እንጂ፥አባቶቻችን ይህ
ቺን አገር ከእጃቸው ለማግባት የቻሉት
በጦር መሣሪያቸው ብዛት አልነበረም፤
ለድል አድራጊነት ያበቃቸውም የክንዳቸው
ኃይል አልነበረም።
4 ለያዕቆብ ልጆች ድልን እንዲጐናጸፉ
የበየንክላቸው አንተ፥ንጉሤና አምላኬ ነህ።
5 በአንተ ኃይል ጠላቶቻችንን ወደ ኋላቸው
እንዲያፈገፍጉ እናደርጋቸዋለን፤የሚያጠቁ
ንን ደግሞ በስምህ ከእግራችን በታች ረግ
ጠን እናዋርዳቸዋለን። 6 እኔ በቀስቴ አልተ
ማመንም፤ሰይፌ ድልን ሊያስገኝልኝ አይቻ
ለውም። 7 በጠላቶቻችን ላይ ድልን እንድን
ጐናጸፍ ፥ ተቃዋሚዎቻችንም በኀፍረት እን
ዲሸማቀቁ ያደረግህ አንተ ነህ። 8 በዘመና
ችን ሁሉ የምንመካው በአንተ በፈጣሪያችን
ነው፤ስምህንም ለዘላለም በመዝሙር ስናመ
ሰግን እንኖራለን።
9 አሁን ግን አቤቱ ፥ «ወግዱ» ብለህ

ተውኸን ፤ አዋረድኸንም። ከሠራዊታችንም
ጋር ወደ ጦር ሜዳ አትወጣም። 10ከጠላቶ
ቻችን ፊት እንድንሸሽ አደረግኸን፤ተጻራሪ
ዎቻችን ዘረፋቸውን ፈጸሙብን። 11 ተኩላ
እንደሚናጠቀው የበግ መንጋ ለጠላቶቻችን
አሳልፈህ ሰጠኸን፤በአሕዛብም መካከል በታ
ተንኸን። 12 ሕዝብህን ከምንም ለማይቈጠር
አነስተኛ ዋጋ ለወጥካቸው።

13በጎረቤት አገሮች በሚኖሩ ሕዝቦች
ዘንድ መሰደቢያ፥በአካባቢያችን ላሉት መሣ
ቂያና መሣለቂያ ፥ 14በአሕዛብም መካከል
መተረቻ አደረግኸን። የሚያዩን ሰዎች ሁሉ
በመዘበት ራሳቸውን ይነቀንቁብናል።

15ዕድሜዬን ሙሉ እንደ ተዋረድሁና
ፊቴን በኀፍረት እንደ ሸፈንሁ እኖራለሁ።
16ይኸውም ቂም በቀሉን ሊወጣብኝ ከቈረ
ጠው ጠላቴና ከሚያሽሟጥጡኝ ሰዎች ስድ
ብና ዘለፋ የተነሣ ነው።

17አቤቱ፥ይህ ሁሉ በእኛ ላይ ቢደርስብ
ንም አንተን ማስታወሳችንንና ለቃል ኪዳ
ንህ ታማኞች መሆናችንን አልተውንም።
18ልባችን አንተን ከማምለክ በቀር ወደ
ሌላ አላዘነበለም ፤ እግሮቻችን መንገድህን
ስተው ወደ ሌላ አቅጣጫ አልሄዱም።
19አንተ ግን እነሆ በመከራ አደቀቅኸን፤
ለተኩላዎች ንጥቂያ ዳረግኸን ፤ በድቅድቅ
ጨለማም ሸፈንኸን።

20የፈጣሪያችንን የእግዚአብሔርን ስም
ረስተን ቢሆን ኖሮ ፥ እጆቻችንንም ወደ
ባዕድ አማልክት አንሥተን ሰግደን ቢሆን
ኖሮ፥ 21በልብ ውስጥ የተሰወረውን መርም
ረህ የምታውቅ አንተ ይህን ሁሉ ገላልጠህ
ታወጣው አልነበረምን? 22ዳሩ ግን ሁል
ጊዜ ስለ አንተ የሞት ጽዋ እንቀበላለን፤
ሊታረዱ እንደ ተዘጋጁ በጎች ተቈጥረናል።

23እግዚአብሔር ሆይ፥እንግዲህስ ንቃ!
ስለ ምን እንደ ተኛ ሰው ዝም ትላለህ?
ተነሥ! ለዘላለም «ወግዱ» ብለህ የተውኸን
ሆነን አንቅር፤ 24ፊትህን ከእኛ ለምን ትሰ
ውራለህ? መሠቃየታችንንና መጨቈናችን
ንስ ለምን ትረሳለህ? 25እነሆ ትቢያ እስከ
መሆንና ሰውነታችን ከመሬቱ ጋር እስከ
መጣበቅ ደርሷል። 26ስለዚህ ተነሥ! እር
ዳን ፤ ከማይለወጠው ፍቅርህ የተነሣ ቤዛ
ሆነህ አድነን።

## መዝሙር 45

1ልቤ መልካም ነገር ያፈልቃል፤እንደበ
ቴም እንደ ብልህ ደራሲ ብዕር ቃሌን ይገ
ልጣል። ለንጉሡ ክብር ያዘጋጀሁትን ቅኔ
እንዲህ እያልኩ አበረክታለሁ፦

2«ንጉሥ ሆይ ፥ እግዚአብሔር የዘላለም
በረከትን የሰጠህ ስለ ሆንክ፥አንተ ከሰዎች
ሁሉ ይልቅ እጅግ የተዋብክ ነህ፤ከንፈሮችህ
እንደ ማር ወለላ ሞገስን ያፈሳሉ። 3ኃያል
ሆይ፥ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ፤በግርማ የተ
ንቈጠቈጠ ልብስ መንግሥትህንም ልበስ።
4እውነትን፥የዋህነትንና ጽድቅን ለመጠበቅ
በግርማ ሠረገላህ ተቀምጠህ በድል አድራጊ
ነት ወደ ፊት ተጓዝ። ቀኝ እጅህ የሚፈጽ
መው የሚያስፈራው ድንቅ ሥራህ ገሃድ
ይውጣ። 5የተሳሉ ፍላጾችህ የንጉሡን
ጠላቶች እየነደፉ ልባቸውን ጠልቀው ይወ
ጓቸው። አሕዛብ ከእግርህ ሥር ይውደቁ።
6አምላክ ሆይ ፥ ዙፋንህ ለዘላለም ይኖራል፤
በትረ መንግሥትህም ለትክክለኛ ፍርድ
የቆመ ይሆናል። 7አንተ ጽድቅን ትወድዳ
ለህ ፤ ክፋትንም ትጠላለህ ፤ ስለዚህ ፈጣሪህ
እግዚአብሔር የደስታ ዘይትን ቀብቶ ከጓደ
ኞችህ በላይ ከፍ አደረገህ። 8የክብር ልብሶ
ችህ መዓዛ የከርቤና የሰንደል ፥ የዝባድም
ሽቱ ነው። በዝሆን ጥርስ ባጌጠው ቤተ
መንግሥትህ አዳራሾች ውስጥ በዜማ መሣሪ
ያዎች ድምፅ ደስ ትሰኛለህ። 9ስለ ክብርህ
በፊትህ ከሚቀርቡት ደናግል መካከል የነገ
ሥታት ሴቶች ልጆች ይገኛሉ፤ንግሥቲቱም
በኦፊር ወርቅ የተንቈጠቈጠ ልብሷን ተጐ
ናጽፋ በቀኝህ ትቆማለች።

10«ልጂ ንግሥት ሆይ፥ጆሮሽን ወደ እኔ
አዘንብለሽ ስሚኝ ፤ የምነግርሽንም አስተ
ውዪ። ወገኖችሽንና የወላጆችሽን ቤት
እርሺ! 11እነሆ ንጉሡ ውበትሽን በታላቅ
አድናቆት ወዶልሻል፤እርሱም ጌታሽ ነውና
አክብሪው። 12የጢሮስ ሴቶች ልጆች ገጸ
በረከታቸውን ይዘው ወደ አንቺ ይመጣሉ፤
ባለጸጎችም ከአንቺ ዘንድ ሞገስን ለማግኘት
ደጅ ይጠናሉ።»

13ንግሥቲቱ በሙሉ ክብሯ አሸብርቃ
በእልፍኟ ውስጥ ትጠባበቃለች። ቀሚሷ
ወርቀ ዘቦ ነው፤ 14በጥልፍ ሥራ ያጌጠ
መጐናጸፊያ ደርባለች። ደናግል ደንገጥሮቿ
አጅበዋትና የእልፍኝ አስከልካዮች እያጋፈ
ሩላት ወደ አንተ ወደ ንጉሡ ለመቅረብ
ትመጣለች። 15ሁሉም ደስታንና ሐሤትን
ተሞልተው ወደ ንጉሡ ቤተ መንግሥት
ይገባሉ።

16ንጉሡም ለንግሥቲቱ እንዲህ ይላ
ታል፦ «በመላው ዓለም ላይ የሕዝብ መሪ
ዎች ሆነው የሚሾሙ ልጆች ለአንቺ በአባ
ቶችሽ ፋንታ ይተኩልሻል። 17እኔም መታ

ሰቢያሽ ሕያው ሆኖ ከትውልድ ወደ ትው
ልድ እንዲተላለፍ፥የዓለም ሕዝቦችም ዘላ
ለም ሲያመሰግኑሽ እንዲኖሩ አደርጋለሁ።»

## መዝሙር 46

1 እግዚአብሔር መጠጊያችንና ኃይላ
ችን፥በመከራም ጊዜ ዘወትር የማይለየን ረዳ
ታችን ነው። 2 ስለዚህ መሬት ብትንቀጠቀ
ጥና ተራሮች ተነቅለው በውቅያኖስ ውስጥ
ቢሰጥሙ አንፈራም። 3 እንደ ነጐድጓድ
የሚጮህና አረፋው የሚዥረፈረፍ ታላቅ
ማዕበል ቢነሣ፥ ጋራዎች ብቅ ጥልቅ እያሉ
ቢናወጡ አንሸበርም።
4 የልዑል እግዚአብሔር ማደሪያ የሆ
ነው መቅደስ የሚገኝባት የእግዚአብሔር
ከተማ አለች፤እርሷንም እንደ መስኖ በደ
ስታ የሚያረካት ወንዝ አለ። 5 እግዚአብ
ሔር በዚች ከተማ ስለሚኖር ፈጥኖ ይረዳ
ታል፤ ምን ጊዜም አትፈርስም። 6 አሕዛብ
እያመፁ ሽብርና ሁከትን ያነሣሉ። እግዚአ
ብሔር ቃሉን ሲያሰማ መንግሥታት ይወድ
ቃሉ፤ምድርም በድንጋጤ ትቀልጣለች።
7 ኃያሉ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው።
የያዕቆብ አምላክ ምሽጋችን ነው።
8 ኑ፥የእግዚአብሔርን ሥራ እዩ! እርሱ
በምድር ላይ ታላቅ ጥፋት እንዳመጣ ተመ
ልከቱ። 9 እነሆ እግዚአብሔር ከዓለም
ዳርቻ እስከ ዳርቻዋ ጦርነት ፈጽሞ የሚወ
ገድበትን ዘመን ያመጣል። በዚያን ጊዜ ቀስ
ትን፥ጦርንና ጋሻን ይሰባብራል፤ ያደቃቸ
ዋል፤በእሳትም ያቀልጣቸዋል። 10 እንዲህም
ይላል፦ «የሰው ልጆች ሁሉ፥ እንግዲህ
እረፉ! እኔ እግዚአብሔር በዚች ዓለም
በሚኖሩ ሕዝቦችና በምድር ላይ ባለው ፍጥ
ረት ዘንድ ገናና ሆኜ የምመለክ የሁሉ
ፈጣሪ መሆኔን እወቁ!»
11 ኃያሉ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፤
የያዕቆብ አምላክ ምሽጋችን ነው።

## መዝሙር 47

1 ሕዝቦች ሁሉ ድምፃችሁን ከፍ አድር
ጋችሁ በደስታና በጭብጨባ ለእግዚአብ
ሔር እልል በሉ! 2 በመላው ምድር ላይ
ታላቁ ንጉሥ የሆነው ልዑል እግዚአብ
ሔር፥ግርማው ምንኛ የሚያስፈራ ነው!
3 እነሆ እርሱ አሕዛብንና ልዩ ልዩ ወገኖ
ችን ድል ነሥቶ እኛ እንድንገዛቸው አደረ
ገን። 4 እርሱ ለወደደውና የያዕቆብ ዘሮች
ለሆነው ሕዝቡ የሚበጀውን ርስት መረጠ
ለት።
5 እግዚአብሔር አምላክ በመለከትና በእ
ልልታ ድምፅ ዐረገ። 6 የምስጋና መዝሙር
ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ለእርሱ ለንጉሣችን
የምስጋና ዝማሬ አሰሙ። አዎን፥ ዘምሩ!
አሁንም ዘምሩ!
7 እግዚአብሔር የመላው ዓለም ንጉሥ
ስለ ሆነ የምስጋና መዝሙር ዘምሩለት።
8 እግዚአብሔር በቅዱስ ዙፋኑ ላይ ተቀ
ምጦ በአሕዛብ ለይ ነግሦአል። 9 የአብርሃ
ም አምላክ እግዚአብሔርን ለማምለክ የአ
ሕዛብ ገዢዎች ተሰብስበዋል፤የዓለም ነገሥ
ታት ሁሉ የእርሱ ናቸውና። እግዚአብሔር
እጅግ የገነነ አምላክ ነው።

## መዝሙር 48

1 እግዚአብሔር ታላቅ ነው፤ በታላቅነ
ቱም መጠን ቅዱስ ተራራው በሚገኝባት
በአምላካችን ከተማ ውስጥ ከፍ ያለ ምስ
ጋና ሊቀርብለት ይገባል። 2 ይህች ተራራ
ውበትና ግርማ ካለው ከፍታዋ ለመላው
ዓለም የደስታ ምንጭ ናት፤በከተማዋ በስተ
ሰሜን በኩል መልካም አቀማመጥ ባለው
ስፍራ ላይ የምትገኘው የጽዮን ተራራ፥ራሷ
የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናት። 3 እግዚአብሔር
በከተማዋ ምሽግ ላይ ሆኖ የሚከላከልላት
እርሱ ራሱ መሆኑን አሳይቷል።
4 የመንግሥታት መሪዎች በኅብረት ሊያ
ጠቋት የመጡበት ጊዜ ነበር። 5 ዳሩ ግን
ቀርበው ሲመለከቷት እጅግ ተገርመውና
ተደናግጠው ተመልሰው ሸሹ፤ 6 ከድንጋጤ
አቸው የተነሣ ብርክ ያዛቸው፤በምጥ ላይ
እንዳለችም ሴት ተጨነቁ። 7 የተርሴስ መር
ከቦች የምሥራቅ ነፋስ ባነሣው ማዕበል
ተሰባብረው እንደሚሰጥሙ፥እነርሱንም እግ
ዚአብሔር አጠፋቸው።
8 እኛም በዚች በአምላካችን መዲና፥በኃ
ያሉ እግዚአብሔር ከተማ «ተደረገ» ሲባል
የሰማነውን ሁሉ እነሆ በዓይናችን አይተን
አረጋገጥን። ፈጣሪያችን ይህችን ከተማውን
ለዘላለም አጽንቶ ይጠብቃታል።
9 አሁንም አቤቱ፥ለእኛ ባለህ ጽኑ ፍቅር
ያደረግህልንን ቸርነት በመቅደስህ ተገኝተን
በተመስጦ እናስታውሳለን። 10 እግዚአብሔር
ሆይ፥ቀኝ እጅህ በጽድቅ ሥራ የተሞላ ስለ
ሆነ እንደ ስምህ ሁሉ ምስጋናህ በዓለም
ላይ ከዳር እስከ ዳር ይደርሳል። 11 በምትሰ
ጠው ትክክለኛ ፍርድ የጽዮን ተራራና የይ
ሁዳ ከተሞች ነዋሪዎች እጅግ ደስ ይላቸ
ዋል፤ሐሤትም ያደርጋሉ።
12 እናንተ ወገኖች፥ በጽዮን አካባቢ

ወዲያ ወዲህ በሉ፤በዙርያዋም ተመላለሱ፤
በግምቦችዋ ላይ የታነጹትን ምሽጎቿን
ቍጠሩ፤ 13 የዲቦቿን ዓይነት አስተውሉ፤
የዘብ ማማዎቿን ልብ አድርጋችሁ ተመል
ከቱ። ይህ ሁሉ ምን ይመስል እንደ ነበር
ለሚቀጥለው ትውልድ ታሪኩን የምታስተላ
ልፉ እናንተ ናችሁና። 14 እንዲህ የሚያደር
ገው ፈጣሪ ለእኛ ለዘላለም አምላካችን፣
እስከ መጨረሻውም መሪያችን ሆኖ ይኖ
ራል።

## መዝሙር 49

1 በዚህ ዓለም የምትኖሩ ሕዝቦች ሁሉ፣
ይህን ስሙ! 2 ዝቅተኞች፣ከፍተኞች፣ሀብታ
ሞችና ድኾች በአንድነት አድምጡ። 3 አን
ደበቴ ጥበብ የተሞላ ቃላትን ይናገራል፤ከል
ቦናዬ የሚፈልቀው አሳብ ማስተዋልን ይለግ
ሳል። 4 ወደ አበው ምሳሌ ጆሮዬን አዘንብላ
ለሁ፤በገና እየደረደርኩ በዜማ ምስጢሬን
እፈታለሁ።

5 ጨካኞች ሸንጋዮች ዙርያዬን የሚከቡ
በት ክፉ ቀን ሲመጣ ስለ ምን እፈራለሁ?
6 እነርሱ በብልጽግናቸው የሚተማመኑና፣
በብዙ ሀብታቸው የሚታበዩ ናቸው።
7 ለሌላ ሰው ሕይወት ቤዛ መሆን ወይም
ለነፍስ የሚገባውን ዋጋ ለእግዚአብሔር
መክፈል የሚችል ሰው ከቶ የለም። 8 ለሕይ
ወት ለውጥ የሚሆነው ዋጋ እጅግ ከፍተኛ
ስለ ሆነ ለዚህ የሚበቃውን ቤዛ መክፈል
ምን ጊዜም አይቻልም፤ 9 አዎን፣ሰው ሳይ
ሞትና በመቃብር ሳይበሰብስ ለዘላለም
ሕያው ሆኖ እንዲኖር ማድረግ ለሰው አይቻ
ለውም።

10 ማንም እንደሚያውቀው፣ ጥበበኞች
ይሞታሉ፤ሰነፎችና ልበ ቢሶችም አብረው
ይጠፋሉ፤ እያንዳንዳቸውም ሀብታቸውን
ለሌላ ጥለው ያልፋሉ። 11 ከእነርሱ በኋላ
መታሰቢያ እንዲሆኗቸው አንዳንድ ቦታዎ
ችን በስማቸው ቢሰይሙም፣የዘላለም ቤታቸ
ውና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ
የሚኖረው መኖሪያቸው መቃብራቸው ብቻ
ሆኖ ይቀራል።

12 ሰው ግን ምንም ያህል ሀብት ቢያከ
ማች፣ከተወሰነለት ዕድሜ ስለማያልፍ እነሆ
ሕይወቱ በሞት ጠፍተው የሚቀሩትን እንስ
ሶች ይመስላል። 13 በገዛ ጥበባቸው የሚተማ
መኑ ሰዎችና የተከታዮቻቸው ፍጻሜ
ይኸው ነው። 14 ዕድላቸው እንደሚታረዱ
በጎች የሞት መኖና የመቃብር ዳረጎት እየ
ሆኑ መቅረት ይሆናል። ሥጋቸው የመሳፍ
ንት መኖሪያ ከመሰለው ቤታቸው ይርቅና
መቃብር ውስጥ ወድቆ ይፈራርሳል። ንጋት
በሆነ ጊዜ ቅን ሰዎች ተነሥተው ይገዟቸ
ዋል።

15 እግዚአብሔር ግን ቤዛዬ ሆኖ ነፍሴን
ከሲኦል ያድናታል፤በርግጥም ወደ እርሱ
ይወስዳታል።

16 አንድ ሰው በሀብቱ እያደገ፣በቤቱም
ተድላ ደስታው እየጨመረ ሲሄድ ስታዩ
አትገረሙ፤ 17 ያ ሰው በሚሞትበት ጊዜ
ከሀብቱ ቅንጣት ነገር እንኳ አይወስድምና፤
ተድላ ደስታውም አይከተለውም። 18 እርሱ
ግን በሕይወት ሳለ ይህን ዘንግቶ፣ራሱን በማ
መጻደቅ፣ ሰዎች በባለጠግነቱ በሚያቀርቡ
ለት ከንቱ ውዳሴ እየተደለለ ይቈያል።
19 በመጨረሻም የሕይወትን ብርሃን ለዘላ
ለም የማያዩት እርሱን የመሰሉት አባቶቹ
ተጠቃለው ወደ ሄዱበት ዓለም ይወርዳል።

20 ሀብቱ የበዛለት፣ ማስተዋል ግን የሌ
ለው ሰው ሕይወቱ ሞቶ የሚቀረውን እን
ስሳ ይመስላል።

## መዝሙር 50

1 የኃያላን አምላክ እግዚአብሔር ቃሉን
አሰማ፤ምድርን ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ
ጠራት። 2 ፍጹም ውበትን ከተቀዳጀችው
ከጽዮን እግዚአብሔር የክብሩን ብርሃን ያሳ
ያል። 3 ፈጣሪያችን ይመጣል፤ ዝም አይ
ልም፤በፊቱ የሚያቃጥል እሳት ይነዳል፤በዙ
ርያው የሚያናውጥ ዓውሎ ነፋስ ይነ
ዳል። 4 የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ለመዳኘት
ከላይ ሰማያትን፣ከታችም ምድርን ለእማኝ
ነት ይጠራል። 5 ደግሞም፣ «ከእኔ ጋር ያደ
ረጉትን ቃል ኪዳን፣መሥዋዕት በማቅረብ
እንዲጠብቁ፣ ለእኔ አገልግሎት የተመረጡ
ትን ቅዱሳን ሰብስቡልኝ» ይላል። 6 ሰማያት
የእግዚአብሔርን ፍጹም ጻድቅነት በይፋ
ይገልጣሉ። እግዚአብሔር ራሱ እውነተኛ
ዳኛ ስለ ሆነ እንዲህ ይላል፡-

7 «ሕዝቤ እስራኤል ሆይ፣በእናንተ ላይ
በግልጽ የምናገረው አለኝና ስሙኝ። ስለ
ፈጸማችሁት በደል እመሰክርባችኋለሁ።
አዎን፣ አምላካችሁማ እኔ እግዚአብሔር
ነኝ። 8 አሁን የምወቅሳችሁ ለምን ቍርባን
አላቀረባችሁልኝም? ለምን መሥዋዕት አል
ሠዋችሁልኝም? ብዬ አይደለም። እነዚህ
ሁሉ ዘወትር ሲፈጸሙ እመለከታለሁ።
9 ከበረታችሁ ኰትታችሁ የምታርዱልኝ
ፍሪዳ ወይም የምትሠዉልኝ ሙክት ለእኔ
አያስፈልገኝም። 10 ምክንያቱም በየዱሩ

የሚኖሩት እንስሳትና በሺህ በሚቈጠሩት
ኰረብታዎች ላይ የተሰማሩት የከብት መን
ጋዎች ሁሉ የእኔ ናቸው። 11 በየተራራው
የሚሰፍሩትን አዕዋፍ እያንዳንዳቸውን አው
ቃቸዋለሁ፤በምድር ላይ በየመስኩ የሚርመ
ሰመሱት ተንቀሳቃሽ ፍጡሮች የእኔ
ናቸው። 12 አልራብም እንጂ፥ብራብ እንኳ፥
'አብሉኝ አጠጡኝ' ብዬ አልነግራችሁም፤
ዓለምና በውስጥዋ ያለው ሁሉ የእኔ ነው።
13 ለመሆኑ ለመሥዋዕት የሚታረደውን የፍ
ሪዳ ሥጋ እበላለሁን? የሙክቱንስ ደም
እጠጣለሁን? 14 ለእኔ ለፈጣሪያችሁ የምስ
ጋና መሥዋዕት አቅርቡልኝ፤ከሁሉ በላይ
ለምሆን ለእኔ ለአምላካችሁ የተሳላችሁትን
ስእለት ፈጽሙ። 15 በዚህ ጊዜ፥መከራ ደር
ሶባችሁ ስትጠሩኝ ወዲያው ደርሼ አድናች
ኋለሁ። እናንተም ታከብሩኛላችሁ።»
16 ክፉዎችን ግን እግዚአብሔር እንዲህ
ይላቸዋል፦ «ሕጌን በቃላችሁ ለማሰማት፥
ስለ ኪዳኔስ ለማስረዳት ምን መብት አላ
ችሁ? 17 ምክሬን ጠላችሁ፤ቃሌንም አቃለላ
ችሁ። 18 ስርቆት ሲፈጽም ከምታዩት ሌባ
ጋር በወንጀሉ ተባበራችሁ፤ ዕድል ፈንታ
ችሁ ከአመንዝሮች ጋር እንዲሆን መረጣ
ችሁ። 19 አንደበታችሁን ለክፋት፥ከንፈራች
ሁንም ለማታለያ መሣሪያ አደረጋችሁ።
20 በወንድሞቻችሁ ላይ ዘወትር ነገር ትሠራ
ላችሁ፤የናታችሁን ልጅ እንኳ ታማላችሁ።
21 ይህን ሁሉ አድራጎታችሁን እያየሁ ዝም
አልኳችሁ፤እኔም ፈጽሜ እንደ እናንተ የሆ
ንኩ መሰላችሁ። አሁን ግን እዘልፋችኋለሁ፤
በፊት ለፊታችሁም እከሳችኋለሁ።
22 «እናንተ እግዚአብሔርን የምትረሱ
ሁሉ፥ ይህን ወቀሳዬን አመዛዝናችሁ ተመ
ለሱ። አለዚያ ከእኔ እጅ ሊያስጥላችሁ የሚ
ችል ማንም ስለሌለ ጨርሼ አጠፋችኋለሁ።
23 ለእኔ የምስጋና መሥዋዕት የሚያቀርብ
ልኝ፥ ያከብረኛል፤ማዳኔንም አሳየው ዘንድ
መንገድ ያዘጋጅልኛል።»

## መዝሙር 51

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ ስለ ጽኑ ፍቅርህ
ስትል ምሕረት አድርግልኝ፤ስለ ታላቁ ርኅ
ራኄህም ስትል መተላለፌን ደምስስልኝ።
2 ከበደሌ ሁሉ እጠበኝ፤ ከኃጢአቴም አን
ጻኝ።
3 እኔ ራሴ ጥፋቴን አውቀዋለሁ፤ኃጢአ
ተኛነቴንም ሁልጊዜ እገነዘባለሁ። 4 አንተን
ብቻ በደልኩ፤በአንተ ዘንድ ክፉ የሆነውን
ሥራ አደረግሁ፤የምታሰማው የወቀሳ ቃል
እውነት ነው፤የምትበይነውም ፍርድ ትክ
ክል ነው። 5 ከተወለድኩበት ጊዜ ጀምሮ
ኃጢአትን ሠራሁ፤በእናቴ ማኅፀን ከመፀነሴ
ጀምሮ ኃጢአተኛ ነኝ። 6 በእርግጥ፥አንተ
የምትፈልገው ከሕሊና የሚመነጨውን
እውነተኛነት ነው፤በውስጥ ሕዋሳቴም ጥበ
ብን እንዳውቅ አስተማርከኝ።
7 አቤቱ፥በስርየት ደም በተነከረ ሂሶጵ
እርጨኝ፤ እኔም እነጻለሁ። እጠበኝ፤እኔም
ከበረዶ ይበልጥ ነጭ እሆናለሁ። 8 ደስታንና
ሐሤትን አሰማኝ፤አንተ ያደቀቅሃቸው አጥን
ቶቼ ሳይቀሩ ደስ ይበላቸው። 9 አቤቱ፥አይ
ተህ እንዳላየ ሆነህ ኃጢአቴን ተውልኝ፤በደ
ሌን ሁሉ ፋቅልኝ።
10 ፈጣሪዬ ሆይ፥ ልቤን ንጹሕ አድርግ
ልኝ፤ውስጤን በማይናወጠው መንፈስ አድ
ስልኝ። 11 «ከፊቴ ወግድ!» ብለህ አትተ
ወኝ፤ ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ አትውሰድ
ብኝ። 12 ለእኔ መድኅኔ በመሆንህ ይሰማኝ
የነበረውን ደስታ መልሰህ አሳድርብኝ።
ይህን በመሰለው ሕይወት ጸንቼ እኖር ዘንድ
ለአንተ የሚታዘዝ መንፈስ ስጠኝ።
13 እኔም ሕግህን ለሚተላለፉት መንገድ
ህን አስተምራቸዋለሁ፤ኃጠአተኞችም በን
ስሐ ወደ አንተ ይመለሳሉ። 14 አምላኬ
ሆይ፥ ከክፉ የምታድነኝ ፈጣሪዬ አንተ
ነህና፥የሰውን ደም በማፍሰስ ከሚመጣ ፍዳ
አውጣኝ። ልሳኔ ለጽድቅ የምስጋና መዝ
ሙር ያሰማል። 15 አቤቱ ፥ ከንፈሮቼን
ክፈት፤አንደበቴም ምስጋናህን በይፋ ይናገ
ራል። 16 በመሥዋዕት ደስ አይልህም፤የሚ
ቃጠል ቍርባን አያስደስትህም። የሚያስደስ
ትህ ቢሆን ኖሮ እኔም ባቀረብኩልህ ነበር።
17 ነገር ግን አንተ የምትወደው መሥዋዕ
ትና የምትቀበለው ቍርባን የተሰበረ ልቦና
ነው። አዎን፥አምላክ ሆይ፥አንተ መንፈሱን
በንስሐ የሰበረውንና ልቡናውን በትሕትና
ያዋረደውን ሰው አትንቅም።
18 አቤቱ፥አንተን ደስ በሚልህ መንገድ
ጽዮንን አበልጽጋት፤ የኢየሩሳሌምንም ግን
ቦች እንደ ገና አድስህ አቁማቸው። 19 እን
ዲህ ሲሆን የሚቀርብልህ መሥዋዕት ሁሉ
የጽድቅ ይሆናል፤የሚቃጠለውም ቍርባን
ያስደስትሃል፤ ያን ጊዜ ሰዎች ፍሪዳውን
ለመሥዋዕት በመሠዊያህ ላይ ያቀርቡል
ሃል።

## መዝሙር 52

1 አንተ ኃያል ሰው፥ ስለ ምን በክፋት
ሥራህ ትመጻደቃለህ? ለምንስ ዕድሜህን

ሙሉ ስትመካ ትኖራለህ? በእግዚአብሔር
ፊት የተዋረድህና የተናቅህ መሆንህን አታ
ውቅምን? 2 አንተ ሽንገላን የምታዘወትር
ሰው፥ እነሆ አንደበትህ እንደ ተሳለ ምላጭ
ሌላውን ሰው ለማጥፋት ያሤራል። 3 ከደግ
ነት ይልቅ ክፋትን፥ እውነትን ከመናገር
ይልቅ ሐሰትን ትወዳለህ። 4 አንተ አንደበተ
ሸንጋይ! በሰው ላይ ጉዳትን ሊያመጡ
የሚችሉ ቃላት በአንተ ዘንድ የተወደዱ
ናቸው።

5 ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም ፈርሶህ
ከምትቀርበት ፍጻሜ ያደርስሃል፤ ድንገት
ሳታስበው ከዚህ ዓለም ነጥቆና ገንጥሎ ያስ
ቀርሃል፤ ፍጡራን በሕይወት ከሚኖሩባት
ምድር ከነሥርህ ይነቃቅልሃል።

6 ጻድቃን የዚህ ሰው ፍጻሜ እንዲህ
መሆኑን ሲመለከቱ እግዚአብሔርን ይፈ
ራሉ። እንዲህ እያሉም ይስቁበታል፥
7 «አዬ ጉድ! ያ ሰው እግዚአብሔርን መተ
ማመኛው ስላላደረገ፥ በሀብቱ ብዛት ስለ
ተመካና ሌሎችን በመጉዳት በሚያገኘው
ጥቅም ላይ ኑሮውን ስለ መሠረተ መጨረ
ሻው እንዲህ ሆነ!»

8 እኔስ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ
እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ ነኝ፤ለዘላለምም
በፈጣሪዬ ጽኑ ፍቅር ተማምኜ እኖራለሁ።
9 አቤቱ፥ስላደረግህልኝ ሁሉ ዘላለም አመሰ
ግንሃለሁ፤ ስምህ መልካም ነውና በስምህ
ተስፋ አደርጋለሁ። በቅዱሳንህ ፊት አመሰ
ግንሃለሁ።

## መዝሙር 53

1 ሞኝ በልቡ፥ «እግዚአብሔር የለም»
ብሎ ያስባል። እንዲህ ያሉ ሰዎች በአስተሳ
ሰባቸው የተሳሳቱና በአኗኗራቸው የረከሱ
ናቸው። ከመካከላቸው በጎ ነገርን የሚሠራ
አንድ እንኳ የለም።

2 እግዚአብሔር ግን ፈጣሪውን የሚፈ
ልግ አስተዋይና አዋቂ ሰው ይገኝ እንደ
ሆነ በማለት ከሰማይ የሰው ልጆች ወደሚኖ
ሩባት ምድር ተመለከተ። 3 ሁሉም እርሱን
ማምለካቸውን ትተው፥ በአስተሳሰባቸውም
አንድ ሳይቀሩ ረክሰው አገኛቸው። ከመካከ
ላቸው በጎ ነገር የሚሠራ የለም፤ አንድ
እንኳ የለም።

4 ሰዎች እንጀራን እንደሚበሉ ሁሉ ወገ
ኖቼን የሚዘርፉና እግዚአብሔርን በአም
ልኮ የማይጠሩ ክፉ አድራጊዎች እስከዚህ
ዕውቀት የሌላቸውና ፈጽመው የማያስተ
ውሉ ናቸውን? 5 የሚያስፈራና የሚያስደነ
ግጥ ነገር ሳይኖር በፍርሃትና ድንጋጤ ይዋ
ጣሉ። አንተን ሊያጠቁህ የሚነሡብህን
ሁሉ አምላክህ አጥንታቸውን ይበታትናል።
ፈጣሪህ ንቋቸዋልና በውርደት ላይ ትጥላቸ
ዋለህ።

6 እነሆ የእስራኤልን ሕዝብ የሚያድን
ቤዛ ከጽዮን ይወጣል። እግዚአብሔር የሕዝ
ቡን ሕይወት መልሶ ሲያደላድለው በዚያን
ጊዜ የያዕቆብ ልጆች የሆኑት የእስራኤል
ሕዝብ እጅግ ደስ ይላቸዋል፤ሐሤትም ያደ
ርጋሉ።

## መዝሙር 54

1 ፈጣሪዬ ሆይ፥ስለ ስምህ አድነኝ፤በኃያ
ልነትህም ከክስና ወቀሳ ነጻ አድርገኝ።
2 አምላኬ ሆይ፥ጸሎቴን ተቀበል፤የማሰማህን
ቃል አድምጥ።

3 እነሆ የማላውቃቸው ጠላቶች ተነሥ
ተው እያጠቁኝ ናቸው፤ስለ እግዚአብሔር
ደንታ የሌላቸው ጨካኞች ሕይወቴን ሊያ
ጠፉ ይፈልጋሉ።

4 እግዚአብሔር የምተማመንበት ረዳቴ
ነው፤ በሕይወት እንድኖር የሚደግፈኝ
እርሱ ፈጣሪዬ ነው።

5 ስሜን በሐሰት በሚያጠፉ ሰዎች ላይ
ክፋታቸው በራሳቸው ይድረስባቸው፤ አን
ተም ፈጣሪዬ በእውነተኛ ፍርድህ አጥፋ
ቸው።

6 እግዚአብሔር ሆይ፥በፍጹም ልቤ የቊ
ርባን መሥዋዕት አቀርብልሃለሁ። ስምህ
መልካም ነውና ስለ ስምህ እየዘመርኩ አመ
ሰግንሃለሁ። 7 ምክንያቱም ከደረሰብኝ
መከራ ሁሉ አውጥተህ አድነኸኛል፤በጠላ
ቶቼ ላይ ድል ማድረጌን በዓይኔ አይቻለሁ።

## መዝሙር 55

1 ፈጣሪዬ ሆይ፥ጸሎቴን አድምጥ፤ልመና
ዬን ቸል አትበል፤ 2 ስማኝ፤መልስልኝም።
እነሆ መንፈሴ በጭንቀት ታውኳል፤ ግራ
ገብቶኝ እቅበዘበዛለሁ፤ 3 የጠላቶቼ የማስፈ
ራሪያ ጩኸትና የክፉ ሰዎች ግልምጫ አይ
ሎብኛል። በቊጣ በሚነሡብኝ ጊዜ
ሥቃይ ያጸኑብኛል፤በጥላቻ ይዘልፉኛል።

4 ልቤ በውስጤ ተጨነቀ፤ «ልሞት
ነው» እያልኩ መንፈሴ ተሸበረ። 5 ፍርሃ
ትና መንቀጥቀጥ ሰውነቴን ወረረኝ፤የሚያስ
በረግግ ስሜት ሁለንተናዬን አለበሰኝ። 6 እን
ዲህም አልሁ፡- «ከዚህ በርሬ ዕረፍት አገኝ
ዘንድ ምነው እንደ ርግብ ክንፍ በኖረኝ?
7 ርቄ ለመሸሽና በምድረ በዳ ውስጥ

'እፎይ!' ብዬ ለመቈየት በቻልሁ ነበር፤
8 ከዓውሎ ነፋስና ከውሽንፍር ወደ ራቀው
የመጠለያ ስፍራዬ ፈጥኜ በደረስሁ ነበር።»
9 እግዚአብሔር ሆይ፥በከተማይቱ ውስጥ
የግፍ ሥራና ሁከት በዝቶ አያለሁና ክፉዎ
ችን አመሰቃቅላቸው፤እርስ በርሳቸውም
እንዳይግባቡ አድርጋቸው። 10 ቀንና ሌሊት
በግንቦቿ ላይ እየተንጠለጠሉ ያደባሉ፤በው
ስጥዋ በቀልና ወንጀል ሰፍኗል። 11 የጥፋት
ኃይሎች በከተማዋ ውስጥ የክፋት ሥራቸ
ውን እያካሄዱ ናቸው፤ማስፈራራትና ማታ
ለል ከጐዳናዎቿ ተለይተው አያውቁም።
12 ጠላቴ ቢዘልፈኝ፥በታገሥኩት ነበር፤
ባለጋራዬ ሊያጠቃኝ ቢነሣብኝ፥ ተሸሽጌ
ባመለጥኩት ነበር። 13 ነገር ግን ይህን ያደረ
ገኝ እኩያዬና ባልንጀራዬ፥የቅርብ ጓደኛ
ዬም የሆነ ሰው ነው። 14 በእግዚአብሔር
ቤት ከሚያመልኩት ሕዝብ ጋር ሁለታች
ንም አብረን በመገኘት ደስ የሚያሰኝ ሕብ
ረት እናደርግ ነበር።
15 የክፋት ማደሪያ በእነርሱ መካከል
ስለ ሆነ፥በጠላቶቼ ላይ በድንገት ሞት ይድ
ረስባቸው፤ ወደ ሲኦል ከነሕይወታቸው
ይውረዱ፤
16 እኔ ግን ወደ ፈጣሪዬ ወደ እግዚአብ
ሔር ተጣራሁ፤እርሱም አዳነኝ። 17 በማታና
በጠዋት፥በቀትርም ጭንቀቴን ለእርሱ አቀረ
ብሁ፤እርሱም ድምፄን ሰማ። 18 የሚቃወ
ሙኝ ብዙዎች ቢሆኑና ጠላቶቼ ጦርነትን
ቢያውጁብኝ፥አንዳችም ጉዳት እንዳያገኘኝ
እርሱ ጠብቆና ቤዛ ሆኖ አዳነኝ። 19 በዘላለ
ማዊው ዙፋን ላይ የተቀመጠው አምላክ
ጭንቀት የደረሰባቸውን ሰዎች ጩኸት ይሰ
ማል፤ከክፋት መንገዳቸው ፈጽመው የማይ
መለሱትንና እግዚአብሔርን የማይፈሩትን
ሰዎች ግን በጽኑ መከራ ያሠቃያቸዋል።
20 ለካስ ጓደኛዬ በባልንጀሮቹ ላይ የሚ
ያምፅና ቃል ኪዳኑን የማይጠብቅ ከዳተኛ
ኖሯል! 21 ንግግሩ እንደ ቅቤ የለሰለሰ፥
በልቡ ግን ጠበኛ ኖሯል! ከአንደበቱ የሚ
ወጡት ቃላት ሰውነትን ከቅባት ይልቅ
የሚያለዝቡ ሲመስሉ፥ ለካስ እንደ ሰይፍ
የተሳሉ ኖረዋል!
22 ጸድቁን ምን ጊዜም ቢሆን እንዲ
ወድቅ አይተወውምና፥ አሳብህን በእግዚ
አብሔር ላይ ጣል፤እርሱም አጽንቶ ይጠ
ብቅሃል። 23 አምላክ ሆይ፥ክፉዎችን ፈር
ሰው በሰበሰው ወደሚቀሩበት የመቃብር
አዘቅት ትጥላቸዋለህ። የሰውን ደም በማፍ
ሰስና በሸንገላ የሚኖሩ ሁሉ የዕድሜያቸ
ውን እኩሌታ እንኳ ሳይቈዩ ይቀሠፋሉ።
እኔ ግን በአንተ እተማመናለሁ።

## መዝሙር 56

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ሰዎች ሊያጠፉኝ
እያሳደዱኝ ናቸውና አቤቱ፥ በምሕረትህ
አድነኝ። ፋታ ሳይሰጡኝ ማጥቃታቸውን
አጽንተውብኛል። 2 ስሜን በሐሰት የሚያ
ጠፉ ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ ያሳድዱኛል፤በት
ዕቢት ተወጥረው የሚያጠቁኝ ብዙዎች
ናቸው።
3 በምፈራበት ጊዜ በአንተ እተማመና
ለሁ። 4 አሁንም ቃሉን በማወድስለት አምላ
ክና ፈጣሪ እተማመናለሁ፤አልፈራም። ደካ
ማና ሟች የሆነው ሰው ከቶ ምን ሊያደር
ገኝ ይችላል?
5 ጠላቶቼ ምን ጊዜም ንግግሬን የሚተረ
ጕሙት በማጣመም ነው፤ዘወትር የሚያሤ
ሩት እኔን ለመጕዳት ነው። 6 አዎን፥ይዶል
ቱብኛል፤ሕይወቴንም ለማጥፋት እያደቡና
እግሬን እየጠበቁ ይከታተሉኛል።
7 ፈጣሪዬ ሆይ፥ አሕዛብን አዋርደህ ጣላ
ቸው እንጂ ከቍጣህ በምንም ሁኔታ አያም
ልጡ። 8 ልቅሶዬን መዝግብልኝ፤የእንባዬን
መጠን በመጽሐፍህ አስፍርልኝ። በእርግጥ
በመዝገብህ ተጽፈው የለምን?
9 «ድረስልኝ» ብዬ ወደ አንተ በምጮህ
በት ጊዜ ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ፤
በዚህም እግዚአብሔር ከጐኔ የቆመ መሆ
ኑን አውቃለሁ። 10 አሁንም ቃሉን በማወ
ድስለት ፈጣሪ፥አዎን፥ቃሉን በማወድስለት
11 በእግዚአብሔር አምላክ እተማመናለሁ፤
አልፈራም። ከቶ ሰው ምን ሊያደርገኝ ይች
ላል?
12 አቤቱ፥ ለአንተ የተሳልኩት ስእለት
አለብኝ፤ ስእለቴም የምስጋና ቍርባን ስለ
ሆነ እነሆ አቀርብልሃለሁ። 13 ምክንያቱም
በሕይወት ብርሃን ውስጥ በእግዚአብሔር
ፊት እመላለስ ዘንድ ነፍሴን ከሞት፥እግሮቼ
ንም ከእንቅፋት አድነሃል።

## መዝሙር 57

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ማረኝ፤የተማመን
ኩት በአንተ ብቻ ነውና ማረኝ። የመጣው
መከራ እስኪያልፍ ድረስ በክንፎችህ ጥላ
ሥር እጠለላለሁ።
2 በጭንቀቴ ጊዜ ከሁሉ በላይ ወደ
ሆነው እግዚአብሔር፥ለእኔ ያሰበውን ቸርነ
ቱን ወደሚፈጽምልኝ አምላክ እጮሃለሁ።
3 ሊያጠፉኝ የሚያሳድዱኝን በመገሠፅ በፍ

ቅሩና በእውነተኛነቱ እርዳታውን ከሰማያት
ልኮ እግዚአብሔር ያድነኛል።
4እነሆ በአንበሶች እንደ ተከበበ፣ ከተራ
ቡና ከሚገነጣጥሉ አራዊት መካከል እንደ
ተዘረረ ሰው ሆኛለሁ። ጠላቶቼ ጥርሳቸው
እንደ ጦርና እንደ ፍላጻ፣ ምላሳቸውም
እንደ ተሳለ ሰይፍ ነው።
5እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ ገናናነትህ
ከሰማያት በላይ ከፍ ይበል፤ ክብርና ምስጋ
ናህ በምድር ላይ ይስፈን።
6አቤቱ፣ ከጽኑ መከራ የተነሣ ሰውነቴ
ጐበጠ፤ ጠላቶቼ እግሮቼን ሊጠልፉ መረብ
ዘረጉብኝ፤ በመንገዴ ላይ ጕድጓድ ቈፈሩ፤
ዳሩ ግን ለእኔ ባሰቡት እነርሱ ራሳቸው
ወደቁበት።
7ጌታ ሆይ፣ አንተን በመተማመን ልቤ
ጽኑ ነው፤ አዎን፣ ልቤ ጽኑ ነው፤ በዜማ መሣ
ሪያ ለአንተ እዘምራለሁ። 8አሁንም ነፍሴ
ሆይ፣ ንቂ! በገናና መሰንቆ አዘጋጂ! እኔም
ጎሕ ሲቀድ ማልጄ እነሣለሁ።
9እግዚአብሔር ሆይ፣ በአሕዛብ መካከል
በዝማሬ አመሰግንሃለሁ፤ በሕዝቦች መካከል
እዘምርልሃለሁ። 10ፍቅርህ እስከ ሰማያት
የሚደርስ ታላቅ ነው፤ ታማኝነትህም እስከ
ጠፈር የመጠቀ ነው።
11እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ ገናናነ
ትህ ከሰማያት በላይ ከፍ ይበል፤ ክብርና
ምስጋናህ በምድር ሁሉ ላይ ይስፈን።

## መዝሙር 58

1እናንት የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣
በእርግጥ እውነትን ትናገራላችሁን? ሕዝቡ
ንስ በቅንነት ታስተዳድራላችሁን? 2መች
እንዲህ ሆነና። እናንተስ በልባችሁ ፍርድ
ለማጣመም ታውጠነጥናላችሁ፤ እጆቻችሁም
በምድር ላይ የግፍ ሥራ ይፈጽማሉ። 3ከፉ
ዎች ገና በእናታቸው ማኅፀን ሳሉ ቀናውን
መንገድ ለመሳትና ሐሰትን ለመናገር የተመ
ደቡ ናቸው፤ እንደ ተወለዱም ወደ ስሕተት
አቅጣጫ ያመራሉ። 4ቊጣቸው እንደ እባ
ብና ጆሮዋን እንደምትደፍን እፉኝት
መርዝ ነው፤ 5ይህቺ እፉኝት፣ አስማተኛ
በምንም ዓይነት ብልሃት ቢያቀነቅንላት
ለመስማት ፈቃደኛ አይደለችም።
6እግዚብሔር አምላክ ሆይ፣ ነጣቂነታ
ቸው እንደ አንበሳ ስለ ሆነ፣ ጥርሳቸውን ሰባ
ብረህ አውልቅ፤ ክራንቻቸውንም ነቅለህ
ጣል። 7ከመሬት ፈስሶ እንደሚሠርግ ውሃ
ደብዛቸው ይጥፋ፤ ቀስታቸውን በሚስቡበት
ጊዜ ፍላጻው ይዶልዱም። 8በጕዞው ቀልጦ
እንደሚያልቅ ቀንዳውጣና የፀሐይን ብርሃን
ሳያይ እንደሚቀር ጭንጋፍ ይሁኑ።
9እሾሁ እንደማይታይ የእሜከላ ዘንግ
ከፋታቸውንና ተንኰላቸውን ሸሽገው በሕ
ይወት እንኖራለን ይላሉ፤ ዳሩ ግን የእግዚአ
ብሔር መቅሠፍት ሳያስቡት ድንገት
መጥቶ ያጠፋቸዋል። 10ጻድቃን የመበቀያ
ፍርድ ስለ ተፈጸመ ደስ ይላቸዋል፤ በክፉ
ዎች የደም ጐርፍ እግሮቻውን ያርሳሉ።
11ሰውም ሁሉ፣ «ለካ ጻድቃን ምንም
ቢሆን ዋጋቸውን አያጡም፤ ለካ በምድር
ላይ የሚፈርድ አምላክ በእርግጥ አለ!»
ይላል።

## መዝሙር 59

1ፈጣሪዬ ሆይ፣ ከጠላቶቼ እጅ አውጣኝ፤
በእኔ ላይ ከተነሡብኝ ተቃዋሚዎቼ ጠብ
ቀኝ። 2ከክፉ አድራጊዎች ሰውረኝ፤ ከነፍሰ
ገዳዮች አድነኝ።
3እግዚአብሔር ሆይ፣ አድብተው እንደ
ሚጠባበቁኝ ተመልከት፤ በእነርሱ ላይ የፈጸ
ምኩት በደል ሳይኖር ጨካኞች ሰዎች ይዶ
ልቱብኛል። 4ምንም ዓይነት ጥፋት አላደረ
ግሁም፤ እነርሱ ግን ሊያጠቁኝ ተዘጋጅተ
ዋል። ስለዚህ ያለሁበትን ሁናቴ ተመልከ
ተህ እኔን ለመርዳት ተነሥ! 5የእስራኤል
አምላክ ኀያሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ሆይ፣
አሕዛብን ሁሉ ለመቅጣት ተነሥ! ለክፉዎ
ችና ለከዳተኞች ምሕረት አታድርግላቸው።
6ማታ ማታ ተመልሰው እየመጡ በከተ
ማዋ ውስጥ ሲያደቡና እንደ ተራቡ ውሾች
ሲያጕረመርሙ ያድራሉ። 7ከአፋቸው ምን
እንደሚተፉ እይ፤ ከከንፈሮቻቸው የሚወ
ጣው ቃል እንደ ሰይፍ ይቈራርጣል። እነር
ሱም፣ «ይህን ንግግራችንን ማን ሊሰማን
ይችላል?» ይላሉ። 8እግዚአብሔር ሆይ፣
አንተ ግን በዚህ አድራጎታቸው ትስቅባቸዋ
ለህ፤ እነርሱን በመሰሉ አሕዛብ ሁሉ ትዘብ
ትባቸዋለህ።
9አለኝታዬ ሆይ፣ አንተ የምታደርግልኝን
ሁሉ እጠባበቃለሁ፤ አቤቱ፣ አንተ ምሽጌ
ነህ። 10አዎን፣ አንተ የምትወደኝ ፈጣሪዬ
ነህ።
እግዚአብሔር በፊቴ እየሄደ ይመራ
ኛል፤ ስሜን በሐሰት በሚያጠፉትም ላይ
እንድሳለቅባቸው ያደርገኛል። 11ጋሻችን
እግዚአብሔር ሆይ፣ ሕዝቤ አንተን እንዳይ
ረሱ ጠላቶቻችን የሆኑትን አሕዛብ ጨርሰህ
አታጥፋቸው፤ ነገር ግን በኀያልነትህ እንዲን
ከራተቱና እንዲዋረዱ አድርግ። 12ከአንደበ

ታቸው በተነገረው የሐሰት ቃል ኃጢአት
ተሠርቷል ፤ ከከንፈራቸውም በወጣው ተን
ኰል በደል ደርሷል ፤ ስለዚህ ትዕቢታቸው
ወጥመድ ሆኖ እንዲይዛቸው አድርግ። ስለ
ሚያሰሙት የእርግማንና የሸፍጥ ንግግር
13 በቍጣህ አንድደህ አጥፋቸው ፤ እንዳልነ
በሩ እስኪሆኑ አቃጥለህ አውድማቸው።
ይህን ስታደርግ አንተ እግዚአብሔር የያዕ
ቆብ ልጆች በሆኑት በእስራኤል ላይ ገዢ
መሆንህ በዓለም ላይ ከዳር እስከ ዳር የታ
ወቀ ይሆናል።
14 ማታ ማታ ተመልሰው እየመጡ በከተ
ማዋ ውስጥ ሲያደቡና እንደ ተራቡ ውሾች
ሲያጕረመርሙ ያድራሉ። 15 ምግባቸውን
ለማግኘት የትም ይዞራሉ ፤ ካልጠገቡም
ይጮሃሉ።
16 እኔ ግን ስለ ኃይልህ እዘምራለሁ ፤ ሲነ
ጋም ስለ ፍቅርህ እዜማለሁ ፤ አንተ ምሽጌ
ነህና ፤ በመከራዬም ጊዜ መጠጊያዬ ነህ።
17 አለኝታዬ ሆይ ፥ ለአንተ የምስጋና መዝ
ሙር አቀርባለሁ። አቤቱ ፥ የምትወደኝ ፈጣ
ሪዬ ሆይ ፥ አንተ ምሽጌ ነህ።

## መዝሙር 60

1 እግዚአብሔር ሆይ ፥ እነሆ በእኛ ላይ
ከመቈጣትህ የተነሣ ፥ «ወግዱ!» ብለህ
ተውከን ፤ አቋማችንን ሁሉ አፈራረስህ።
አሁን ግን አቤቱ ፥ መልሰህ አቋቁመን። 2 አገ
ሪቱን አናወጥካት ፤ ኬላዎቿን ሁሉ ሰባብረህ
ክፍት አደረግሃት ፤ እየራደች ነውና ስብራቶ
ቿን ጠግን። 3 ለሕዝብህ የመከራ ዘመንን
አሳየሃቸው ፤ ጠጥቶ እንደ ሰከረ ሰውም አንገ
ዳገድካቸው።
4 ለሚፈሩህ ግን ልዩ ሰንደቅ ዓላማ አቆ
ምክላቸው ፤ እነርሱም የጠላታቸውን ጦር
በመቃወም ይዘው ያውለበልቡታል።
5 አንተ የምትወዳቸውን እንደምታድናቸው
ይታወቅ ዘንድ አቤቱ ፥ እኛን አድነን ፤ በቀኝ
እጅህም ከልለን። 6 እግዚአብሔር በመቅ
ደሱ ሆኖ እንዲህ ሲል ተናግሯል ፦ «ሴኬ
ምን በድል አድራጊነት ከፍዬ እይዛለሁ ፤
የሱኮትን ሸለቆ ለክቼ እወስዳለሁ። 7 ገለዓድ
የእኔ ነው ፤ ምናሴም የእኔው ነው። ኤፍሬም
ለእኔ የራስ ቍር ነው ፤ ይሁዳም በትረ መንግ
ሥቴ ነው። 8 ሞዓብ መታጠቢያ ገንዳዬ
ነው። በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን እጥላለሁ ፤
በፍልስጥኤምም ላይ የድል አድራጊነት
ድምፄን ከፍ አድርጌ አሰማለሁ።»
9 አቤቱ ፥ ወደ ተመሸገችው ከተማ ማን
ያደርሰኛል? ወደ ኤዶምያስ ማን መርቶ
ይወስደኛል? 10 አምላካችን ሆይ ፥
«ወግዱ!» ብለህ የተውከንና ለጦርነት ከሠ
ራዊታችን ጋር ከመውጣት የቀረኸው አን
ተው አይደለህምን? 11 የሰው እርዳታ ከንቱ
ነውና ጠላቶቻችንን ለመቋቋም የምንችል
በት አቅም ስጠን። 12 በእግዚአብሔር
ኃይል ድል እናደርጋለን ፤ ጠላቶቻችንን ከእ
ግራችን በታች አዋርደን እንረግጣቸዋለን።

## መዝሙር 61

1 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ጩኸቴን ስማ ፤ ጸሎ
ቴንም አድምጥ። 2 እነሆ ከምድር ዳርቻ
እጠራሃለሁ ፤ ልቤ እየደከመ ቢሄድም መጣራ
ቴን አላቋርጥም። ከእኔ ከፍ ወዳለው ዓለት
እደርስ ዘንድ ምራኝ። 3 አንተ መጠጊያዬ ፥
ከጠላቴ መከላከያ ጽኑ ምሽጌም ነህና።
4 በማደሪያህ ለዘላለም እኖር ዘንድ ፥ በክንፎች
ህም ሥር መጠለያ አገኝ ዘንድ እናፍቃለሁ።
5 ፈጣሪዬ ሆይ ፥ ስእለቴን ሰማህ ፤ ስምህን
ለሚፈሩ የምታወርሳቸውን ርስት ለእኔም
ለገስኸኝ።
6 አቤቱ ፥ ለንጉሥ ረጅም ዕድሜን
ስጠው ፤ ዘመኑንም ከትውልድ ወደ ትው
ልድ እያሸጋገርክ አብዛለት። 7 ዙፋኑ በፊ
ትህ ለዘላለም ጸንቶ ይኑር ፤ በፍቅርህና በእው
ነትህ ጠብቀው። 8 ያኔ ለስምህ የሚገባውን
የምስጋና መዝሙር ዘወትር አቀርብልሃ
ለሁ ፤ ስእለቴንም በየዕለቱ እፈጽማለሁ።

## መዝሙር 62

1 ነፍሴ እፎይ ብላ ዕረፍትን የምታገ
ኘው በእግዚአብሔር ብቻ ነው ፤ በቤዛነቱ
የማገኘው ፥ ደኅንነቴም የሚመጣልኝ ከእ
ርሱ ነው። 2 መጠጊያዬና ቤዛ መድኃኒቴ
እርሱ ብቻ ነው ፤ ምሽጌ እርሱ ስለ ሆነ ምን
ጊዜም አልናወጥም።
3 ክፉዎች ግን ፥ ጊዜ የጣለውን ሰው እስከ
መቼ ሲያጠቁት ይኖራሉ? እንደ ዘመመ
ግድግዳና እንደሚወዛወዝ አጥር ሊወድቅ
የደረሰ መሆኑን ሲያዩ ገፍተው ለመጣል
ሁሉም ይረባረቡበታል። 4 ከከፍተኛ ደረ
ጃው ጥለው ለማዋረድ አሳባቸውን ይቈር
ጣሉ። ሐሰትን በመናገር ደስ ይላቸዋል ፤ በአ
ንደበታቸው ይመርቃሉ ፤ በልባቸው ግን
ይረገማሉ።
5 አሁንም ነፍሴ ሆይ ፥ እፎይ ብለሽ ዕረፍ
ትን የምታገኚው በእግዚአብሔር ብቻ
ነው። ተስፋ የማደርገውን ማናቸውንም
ነገር የማገኘው ከእርሱ ነው። 6 መጠጊያ
ዬና ቤዛ መድኃኒቴ እርሱ ብቻ ነው ፤ ምሽጌ

እርሱ ስለ ሆነ አልናወጥም። 7በቤዛነቱ
የማገኘው ደኅንነቴና ክብሬ በእግዚአብሔር
እጅ ነው፤እርሱ ብርቱ ምሽጌና መጠጊያዬ
ነው። 8ሕዝቦች ሆይ፥በማናቸውም ጊዜ
በእርሱ ተማመኑ። እግዚአብሔር መጠጊያ
ችን ስለ ሆነ በየልቦናችሁ ውስጥ ያለውን
ፍላጎታችሁን አንድም ሳታስቀሩ ለእርሱ
አስታውቁት።
9ዝቅተኞች ሰዎች እንደ ትንፋሽ
ናቸው፤ ታላላቆቹም የሐሰት ምስሎችን
ይመስላሉ። ለየብቻ ቢመዘኑ ኢምንት፥በአን
ድነት ቢመዘኑም ክብደታቸው የትንፋሽ
ያህል ነው። 10ሰውን አስጨንቃችሁ በምታ
ገኙት ገንዘብ አትተማመኑ፤በስርቆት በተ
ገኘ ሀብትም ትዕቢት አይደርባችሁ፤ብልጽ
ግናችሁ እያደገ በሚሄድበት ጊዜ ልባችሁ
አይመካ።
11እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ፤እኔ
ደግሞ ሁለት ነገሮችን ሰማሁ። እነርሱም፥
«ኃይል የእግዚአብሔር ነው፤ ምሕረትም
ከእግዚአብሔር ነው» የሚሉ ናቸው።
12አቤቱ፥አንተ ለእያንዳንዱ ሰው እንደየሥ
ራው ዋጋውን በእርግጥ ትከፍለዋለህ።

## መዝሙር 63

1እግዚአብሔር ሆይ፥አንተ አምላኬ ስለ
ሆንክ ከልቤ እሻሃለሁ፤ውሃ በሌለበት በደረ
ቅና በተራቈተ አገር ነፍሴ አንተን ተጠ
ማች፤ ሥጋዬም ናፈቀህ። 2በመቅደስህ
ውስጥ አይቼህ፥ ኃይልህንና ገናናነትህን
ተመልክቻለሁ። 3ፍቅርህ ከሕይወት ይልቅ
የተወደደ ስለ ሆነ በከንፈሮቼ ምስጋናን እያ
ቀረብኩ አከብርሃለሁ። 4በሕይወት እስካ
ለሁ ድረስ በዝማሬ አመሰግንሃለሁ፤እጆቼን
አንሥቼ ስምህን እየጠራሁ እጸልያለሁ።
5ከንፈሮቼ ዝማሬ፥አንደበቴ ምስጋናን ያቀ
ርቡልሃል፤ነፍሴ እጅግ ምርጥ የሆነ ምግብ
ተመግባ የጠገበች ያህል ትረካለች።
6አቤቱ፥በአልጋዬ ላይ ተኝቼ ሳለሁ አስ
ታውስሃለሁ፤ ሌሊቱን ሙሉ ነቅቼ ሳስብህ
አድራለሁ። 7ረዳቴ ስለ ሆንክ ከክንፎችህ
ጥላ ሥር ሆኜ እዘምራለሁ። 8ምን ጊዜም
ከአንተ ስለማልርቅ ቀኝ እጅህ ደግፎ ይይዘ
ኛል።
9ሊገድሉኝ የሚፈልጉ ሁሉ ራሳቸው
ይጠፋሉ፤በነፍሳቸውም ጥልቅ ወደ ሆነው
ሲኦል ይወርዳሉ። 10አሟሟታቸው በሰ
ይፍ፥ ሥጋቸውም የአራዊት እራት ይሆ
ናል።
11ንጉሥ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለ
ዋል፤የእግዚአብሔርን ስም የሚጠሩ ሁሉ
ያመሰግኑታል። የሐሰተኞች አንደበት ግን
ይዘጋል።

## መዝሙር 64

1እግዚአብሔር ሆይ፥ብሶቴን እያቀረብ
ኩልህ ነውና ስማኝ። ሊገድሉኝ ከሚያስፈ
ራሩኝ ጠላቶቼ ዛቻ ሕይወቴን ጠብቅ፤
2ከክፉዎች ሤራና የርግማን ጩኸት ከበዛ
በት የዐመፀኞች ስልፍ ሰውረኝ። 3እነርሱ
ምላሳቸው እንደ ተሳለ ሰይፍ፥የሚሰነዝሩዋ
ቸውም ቃላት እንደ መርዛም ፍላጻዎች
ናቸው። 4ንጹሑን ሰው ሳያስበው ያለፍር
ሃት ሸምቀው ይነድፉታል።
5በክፉ ዕቅዳቸው እርስ በርሳቸው ይበረ
ታታሉ፤ወጥመዳቸውንም በድብቅ ስለሚያዘ
ጋጁበት ዘዴ ይነጋገራሉ። «ይህንንስ ማንም
ሊያይብን አይችልም» ብለው ያስባሉ።
6የሚያውጠነጥኑት የበደል ሥራ ስለ ሆነ፥
«እነሆ ፍጹም የሆነ ዕቅድ አዘጋጀን!»
ይላሉ። የሰው አእምሮውና ልቦናው በእር
ግጥ መሠሪ ነው።
7እግዚአብሔር ግን በፍላጻዎቹ ይነድፋ
ቸዋል፤እነርሱም በድንገት እየተመቱ ይወድ
ቃሉ። 8እግዚአብሔር የደባ ሥራቸው በራሳ
ቸው ላይ ተመልሶ እንዲያጠፋቸው ያደር
ጋል። ፍጻሜያቸውን የሚመለከቱ ሁሉ ራሳ
ቸውን በንቀት ይነቀንቃሉ። 9በዚህ ጊዜ
መላው የሰው ዘር ፍርሃት ያድርበታል፤የእግ
ዚአብሔርን ሥራ በይፋ ይናገራል፤አድራጎ
ቱንም በተመስጦ ይመለከታል።
10ጻድቃን በእግዚአብሔር ደስ ይበላ
ቸው፤እርሱን መጠጊያቸው ያድርጉ። ልባ
ቸው ቅን የሆነ ሁሉ ያመስግኑት።

## መዝሙር 65

1እግዚአብሔር ሆይ፥በጽዮን የምስጋና
መዝሙር ሊቀርብልህ ይገባል። እኛ ስእለ
ታችንን የምንፈጽመው ለአንተ ነው።
2አቤቱ፥ ጸሎትን ወደምትሰማው ወደ
አንተ፥ሰዎች ሁሉ ይቀርባሉ። 3በኃጢአት
ተጥለቅልቀን በነበርንበት ጊዜ፥ስለ በደላችን
ቤዛ ሆነህ አዳንከን። 4አንተ የምትመርጠ
ውና በአደባባይህ እንዲኖር የምታቀርበው
ሰው ምንኛ የተባረከ ነው! እኛም ማደሪያህ
በሆነው በመቅደስህ በሚገኘው መልካም
ነገር ሁሉ ረክተናል።
5መድኅናችን እግዚአብሔር ሆይ፥ዕፁብ
ድንቅ በሆኑት የጽድቅ ሥራዎችህ ለጸሎታ
ችን መልስ ትሰጠናለህ፤በምድር ላይ በዳር

ተወስዶ በኖ እንደሚጠፋ ጢስ አድርጋ
ቸው። ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፥
ክፉዎች ከእግዚአብሔር ፊት እንዲሁ
ይጥፉ።
[3]ጻድቃን ግን በእግዚአብሔር ፊት ደስ
ይበላቸው፤ ሐሤትም ያድርጉ፤ አዎን፥ በደ
ስታ ስሜት ይሞሉ፤ እልል ይበሉ። [4]ለአምላ
ካችን ዘምሩ፤ ለስሙ የምስጋና መዝሙር
አቅርቡለት። ደመናትን ሠረገላዎቹ ያደረገ
ውን፥ ስሙ እግዚአብሔር የሆነውን እርሱን
ላቅ ባለ ምስጋና አወድሱት፤ በፊቱም የደ
ስታ በዓል አድርጉ። [5]በተቀደሰ መኖሪያው
ያለው አምላክ፥ አሳዳጊ ለሌላቸው ልጆች
አባት፥ ባል ለሌላቸው ሴቶች አጋር ነው።
[6]እግዚአብሔር ለብቸኞች፥ቤተሰብ እንዲኖ
ራቸው፥እስረኞች እየዘመሩ ነጻ እንዲወጡ፥
ዐመፀኞች ግን በፀሐይ ሐሩር በተቃጠለ
በረሃ ውስጥ እንዲኖሩ ያደርጋል።
[7]እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥ ሕዝብህን
ለመምራት በወጣህ ጊዜ፥በምድረ በዳ መካ
ከል በተጓዝክ ጊዜ፥ [8]በሲና ተራራ በተገለ
ጥከውና የእስራኤል አምላክ በሆንከው በአ
ንተ በፈጣሪ ፊት ምድር ተንቀጠቀጠች፤
ሰማይም የዝናብ ዶፍ አወረደ። [9]አቤቱ፥
ለሕዝብህ ልታወርሳቸው ላዘጋጀሃትና በች
ግር ለተጠቃችው ምድር የምትለመልምበ
ትን በርካታ የዝናብ በረከት ሰጠሃት።
[10]ሕዝብህም ገብተው ርስት አድርገው ኖሩ
ባት። አቤቱ፥ በሰፊው ልግስናህ፥የድኻውን
ችግር አስወግደህ ኑሮውን አሟላህለት።
[11]እግዚአብሔር ቃሉን በይፋ አስታ
ወቀ፤ የምሥራቹንም ያሠራጨው ሠራዊት
ብዙ ነው። [12]«ነገሥታትና ሠራዊቶቻቸው
ፈጥነው ይሸሻሉ፤ ከቤት የማትወጣዋ ሴት
እንኳ ከምርኮው ትካፈላለች። [13]እግዚአብ
ሔር ለርስቱ በመረጠው ሕዝብ መካከል
የሚኖር ሰው፥ ከብር እንደ ተሠሩ እንደ
ርግብ ክንፎችና በሚያንጸባርቅ ወርቅ እንደ
ተለበጡ ላባዎችዋ ያጌጠ፥ ይሆናል።»
[14]ኃያሉ እግዚአብሔር በዚያች ምድር የነ
በሩትን ነገሥታት፥ በሰልሞን ተራራ ላይ
ተቈልሎ እንደሚቀልጠው የበረዶ ክምር
በታተናቸው።
[15]ሥርጕጥጕጥ የበዛባቸው የባሳን ተራ
ሮች ግርማ ሞገስ የተቀዳጁ ናቸው። [16]እና
ንተ ታላላቅ ተራራዎች! እግዚአብሔር
አምላክ ሊነግሥባትና ለራሱ የዘላለም መኖ
ሪያው ሊያደርጋት ወደ መረጣት ተራራ
በቅንዓት ዓይን አትዂራችሁ ለምን ትመለከ
ታላችሁ? [17]የእግዚአብሔር ሠረገላዎች
እልፍ አእላፍ ናቸው፤እነሆ እግዚአብሔር
ከሲና ተነሥቶ መቅደሱ ወደ ሆነችው ወደ
ጽዮን ተራራ ደርሷል። [18]እግዚአብሔር
አምላክ ሆይ፥ ወደምታድርባት ወደዚያች
ተራራ ባረግህ ጊዜ፥ምርኮኞችን ከኋላህ አስ
ከትለህ፤ ከዐመፀኞች ሳይቀር እጅ መንሻ
ተቀበልህ።
[19]ሸክማችንን ሁሉ ዘወትር ለሚሸከም
ልን፥መድኅናችን ለሆነው ለእርሱ ለአምላካ
ችን ምስጋና ይድረሰው። [20]ፈጣሪያችን
የሚያድን አምላክ ነው፤ ከሞት የማምለጥ
ኃይል የሚገኘው የሁሉ ገዢ ከሆነው ከእግ
ዚአብሔር ነው።
[21]እግዚአብሔር የጠላቶቹን ራስ ራሳቸ
ውን ፥ ከኃጢአታቸው የማይመለሱትንም
ጐፈሬያማ ጭንቅላታቸውን ፈረካክሶ ይጥ
ላል። [22]ለሕዝቡም እንዲህ ይላል፦ «ከባ
ሳን ተራራ አውርጄ፥ ከባሕሩም ጥልቀት
አውጥቼ አመጣችኋለሁ፤ [23]እግሮቻችሁን
በጠላቶቻችሁ የደም ጐርፍ ውስጥ ትነክራ
ላችሁ፤ውሾቻችሁም የሚልሱትን ድርሻቸ
ውን ያገኛሉ።»
[24]ፈጣሪዬ ሆይ፥ለአንተ ክብር የወጣው
አጀብ እነሆ በገሃድ ታየ፤ይህም አጀብ የታ
የው አምላኬና ንጉሤ ወደ መቅደሱ በገባ
በት ቀን ነው። [25]መዘምራኑ ፊት ፊት እያ
ሸበሸቡ ይመራሉ፤ቀጥለውም በዜማ መሣሪ
ያዎች የሚጫወቱት ይጓዛሉ፤ ከእነርሱም
ጋር ከበሮ የሚመቱት ቈነጃጅት ይገኛሉ።
[26]በታላቁ ጉባኤ እግዚአብሔርን አመስግ
ኑት፤ በእስራኤልም ጉባኤ መካከል አወድ
ሱት። [27]አነስተኛው የብንያም ነገድ ሕዝ
ቡን ይመራቸዋል፤በብዛት የተሰበሰቡት የይ
ሁዳ መሳፍንት፥የዛብሎንና የንፍታሌም አለ
ቆች በታላቁ አጀብ መካከል ነበሩ።
[28]እግዚአብሔር ሆይ፥ ኃይልህን ግለጥ።
አቤቱ፥ ከዚህ ቀደም እንዳደረግኸው ብርቱ
ክንድህን አሳይ። [29]በኢየሩሳሌም ወደሚገ
ኘው መቅደስህ፥ነገሥታት ገጸ በረከት ያመ
ጡልሃል። [30]በየሸምበቆው መካከል ተሸ
ሽጎ የተኛውን የእባብ ዝርያና በአሕዛብ
ጥጆች መካከል እንደ ልቡ የሚፈነጨውን
የወይፈን መንጋ ሁሉ ገሥጽ። እያንዳንዳ
ቸው ከነበሩበት ተዋርደው የብር ጥሪታቸ
ውን እያመጡ እንዲገብሩልህ አድርግ፤በጦ
ርነት እልቂት የሚደሰቱትን አሕዛብ በታት
ናቸው። [31]የመንግሥት ልኡካን ከግብጽ
ይመጣሉ፤ኢትዮጵያም ፈጥና እጆቿን ወደ
እግዚአብሔር ትዘረጋለች።
[32]የዓለም መንግሥታት ሆይ፥ እግዚአብ

ሑርን አመስግኑት፤ለጌታ የምስጋና መዝሙ
ርን አቅርቡለት። 33 በምሥራቅ በኩል ወደ
ሰማየ ሰማያት ለወጣና ኃያል ቃሉን እንደ
ነጐድጓድ ለሚያሰማ ለእግዚአብሔር
ዘምሩ። 34 የግርማው ገናናነት በእስራኤል
ላይ፥ኃይሉም በሰማያት የሰፈነውን የእግዚ
አብሔርን ክብር አውጁ። 35 አቤቱ፥ግርማህ
በመቅደስህ የሚያስፈራ ነው። የእስራኤል
አምላክ ኃይልንና ብርታትን ለሕዝቡ ይሰ
ጣል።

እግዚአብሔር ይመስገን።

## መዝሙር 69

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ የውሃ ሙላት
ሊውጠኝ እስከ አንገቴ ደርሶብኛልና አድ
ነኝ። 2 ጥልቀቱ የእግር ማቆሚያ በሌለው
ማጥ ውስጥ ሰጥሜአለሁ፤ ጥልቅ ባሕር
ውስጥ ገብቻለሁ፤ ጐርፉ አጥለቅልቆኛል።
3 «ድረስልኝ» እያልኩ ወደ ፈጣሪዬ በመ
ጮህ ደከምሁ፤ ጉሮሮዬም ደረቀ። የአምላ
ኬን እርዳታ በመጠባበቅ ዓይኖቼ ፈዘዙ።
4 ያለምክንያት የሚጠሉኝ ከራስ ጸጉሬ ይበ
ልጥ በዝተዋል፤እንዲያውም ከመሬት ተነ
ሥተው የሚቃወሙኝና ሊያጠፉኝ የሚፈ
ልጉ ጠላቶቼ እጅግ ብዙ ናቸው። የሰው
ሀብት እንደ ሰረቀ ተቈጥሬ፥ያልወሰድኩትን
እንድከፍል ተገደድሁ።

5 እግዚአብሔር ሆይ፥በስንፍና የፈጸምኩ
ትን ሥራ ሁሉ አንተ ታውቃለህ፤የሠራሁት
በደል ካንተ የተሰወረ አይደለም። 6 አቤቱ፥
ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ፥ አንተን ተስፋ
የሚያደርጉ በእኔ ምክንያት አይዋረዱ። የእ
ስራኤል አምላክ ሆይ፥አንተን የሚሹህ በእኔ
ምክንያት አይፈሩ። 7 በአንተ በማመኔ፥
ሰዎች የሚያደርሱብኝን ንቀትና ኀፍረት
በትዕግሥት ተቀበልኩ። 8 በዘመዶቼ ዘንድ
እንደ ባዕድ፥በእናቴ ልጆች ዘንድ እንደ ባይ
ተዋር ተቈጠርሁ። 9 ስለ ቤትህ ያደረብኝ
ቅንዓት እንደ እሳት አቃጠለኝ፤የሚጠሉህ፥
በአንተ ላይ የሚሰነዝሩት ስድብ በእኔ ላይ
ዐረፈ። 10 ሳለቅስና ስጾም ያላግጡብኛል፤እኔ
ግን ሁሉንም ታግሼ አሳልፈዋለሁ። 11 ራሴን
በማጐሳቈል ማቅ ለብሼና በትካዜ ተቀምጬ
ሲያዩኝ፥ የእኔን ነገር እያነሡና እየጣሉ
መሣቂያ መሣለቂያ ያደርጉኛል። 12 በየአደ
ባባዩ ተቀምጠው የሚውሉ ሁሉ ያፌዙብ
ኛል፤በየመጠጥ ቤት የሚያመሹትም በእኔ
ላይ እየገጠሙ ይዘፍኑብኛል።

13 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥እኔ ግን
ሞገስህን እንደማገኝ በማመን ወደ አንተ
እጸልያለሁ፤ በታላቁ ፍቅርህና በሚያስተማ
ምነው ቤዛነትህ መልስልኝ። 14 በረግረግ
ከመዋጥ አትርፈኝ፤እንዳልሰምጥ ጠብቀኝ፤
በሚጠሉኝ እጅ ከመውደቅ፥ ወደ ጥልቁ
ባሕርም ከመውረድ አድነኝ። 15 አቤቱ፥
የውሃው ሙላት እንዳያጥለቀልቀኝና የረግ
ረጉ ጥልቀት እንዳይውጠኝ፥አዘቅቱም ተደ
ርምሶ እንዳይቀብረኝ እርዳኝ። 16 ጌታ
ሆይ፥ በንጹሕ ፍቅርህ ለጸሎቴ መልስ
ስጠኝ፤በታላቁ ምሕረትህ አስበኝ። 17 ከእኔ
ከአገልጋይህ ፊትህን አትሰውር፤ በመከራ
ላይ ነኝና ፈጥነህ መልስልኝ። 18 ወደ እኔ
ቀርበህ አስጥለኝ፤ለጠላቶቼ መዘባበቻ እንዳ
ልሆን፥አቤቱ፥ቤዛ ሆነህ አድነኝ።

19 የጠላቶቼን አድራጎት ሁሉ በግልጽ
ስለምትመለከት፥ እንዴት አድርገው እንደ
ሚንቁኝ፥እንደሚያዋርዱኝና እንደሚያሳፍ
ሩኝ ታውቃለህ። 20 በእኔ ላይ ያላቸው
ንቀት ልቤን ተስፋ አስቈርጦታል፤አቅመ
ቢስ አድርጎኛል። «የሚያስተዛዝነኝ ሰው
ይኖር ይሆን?» ብዬ ጠበቅሁ፤ነገር ግን አን
ድም የለም። የሚያጽናኑኝን ሰዎች ፈለ
ግሁ፤ ነገር ግን ማንንም አላገኘሁም።
21 በመብሌ ውስጥ ሐሞት ጨመሩበት፤ለጥ
ማቴም ሆምጣጤን ሰጡኝ።

22 በፊታቸው የተዘረጋው ገበታ ፍዳቸ
ውን የሚቀበሉበትና በጥፋታቸው የሚያዙ
በት ወጥመድ ይሁንባቸው። 23 ዓይኖቻቸው
ሊያዩ እንዳይችሉ ይጨልም፤ጀርባቸውም
ለዘላለም የጐበጠ ይሁን። 24 መዓትህን በላያ
ቸው አፍስስ፤ጽኑ ቍጣህ ድንገት ይድረስባ
ቸው። 25 አገራቸው ምድረ በዳ ይሁን፤ቤታ
ቸው ሰው ዝር የማይልበት ወና ሆኖ
ይቅር። 26 አንተ ያቈሰልከውን እነርሱ አሳ
ደዋልና፤ ከአንተ በመጣ ቅጣት ተጐድቶ
የሚሠቃየውን አምተውታልና። 27 በፈጸ
ሙት ወንጀልና በደል ክሰሳቸው፤ በአንተ
ቤዛነት ከሚገኘው ደኅንነት ድርሻ አይኑራ
ቸው። 28 ስማቸው በጻድቃን ስም ዝርዝር
ውስጥ እንዳይገኝ ከሕይወት መጽሐፍ ደም
ስሳቸው።

29 እነሆ እኔ በሥቃይና በጽኑ መከራ ላይ
እገኛለሁና አቤቱ፥ቤዛነትህ ይጠብቀኝ።

30 የፈጣሪዬን ስም በዝማሬ አወድሳለሁ፤
«ክብርና ምስጋና ለአንተ ይሁን» እያልኩ
ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ። 31 ይህም ለመሥዋ
ዕት ከሚቀርብለት በሬ፥ ቀንዱና ሰኰናው
ገና ካልጸና ወይፈን ይልቅ ያስደስተዋል።
32 እግዚአብሔርን የሚሹ ችግረኞች የጌታን
የቸርነት ሥራ ሲያዩ ደስ ይላቸዋል።

አዎን ፥ እናንተ እግዚአብሔርን የምትሹ
ሁሉ ፥ ልባችሁ ይጽናና። 33 እግዚአብሔር
የችግረኞችን ጩኸት ይሰማል፤በምርኮ ያሉ
ትን ሕዝቡንም ቸል አይልም።
34 ሰማይና ምድር፥ውቅያኖሶችና በውስ
ጣቸው የሚንቀሳቀሰው ፍጥረት ሁሉ እር
ሱን ያመስግኑ። 35 እግዚአብሔር ጽዮንን
ያድናታልና፤የይሁዳን ከተሞች እንደ ገና
ይሠራቸዋል። ሕዝቡ ወደነዚህ ከተሞች
ገብተው ይሰፍራሉ፤ርስት አድርገውም ይይ
ዙዋቸዋል። 36 የአገልጋዮቹ ልጆች ጽዮንን
ይወርሳሉ፤ ስሙን የሚወዱ ሁሉ በእርሷ
ውስጥ ይኖራሉ።

## መዝሙር 70

1 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥እኔን ለማ
ዳን ፍጠን፤ እኔን ለመርዳት በቶሎ ድረስ
ልኝ። 2 ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ
ይፈሩ፤ይታወኩ፤የእኔን ውድቀት የሚመኙ
ተዋርደው ይመለሱ። 3 "እሰይ! እሰይ! እን
ኳን እንዲህ ሆነ!" የሚሉኝ አፍረው ተስፋ
ይቊረጡ። 4 አንተን የሚሹህ ሁሉ ግን ደስ
ይበላቸው፤ ሐሤትም ያድርጉ። ቤዛነትህን
የሚወዱ ዘወትር "እግዚአብሔር ገናና
ይሁን!" ይበሉ።
5 እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝና አቤቱ፥ፈጥ
ነህ ድረስልኝ። የምትረዳኝና የምታድነኝ
አንተ ነህና፥ጌታ ሆይ፥አትዘግይብኝ።

## መዝሙር 71

1 እግዚአብሔር ሆይ፥አንተን ተማጽኜለ
ሁና ምን ጊዜም በኀፍረት ላይ እንዳልወ
ድቅ እርዳኝ። 2 በጽድቅህ አስጥለኝ፤ከመ
ከራ አውጣኝ፤ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፤
አድነኝም። 3 ችግር በገጠመኝ ጊዜ ሁሉ
ተጠግቼ የምድንበት ተገን ሁነኝ፤መጠጊያ
ዬና ምሽጌ አንተ ነህና በትእዛዝህ አድነኝ።
4 ፈጣሪዬ ሆይ፥በክፉዎች እጅ እንዳልወ
ድቅ፥ ግፈኞችና ጨካኞችም እንዳይዙኝ
ጠብቀኝ።
5 የሁሉ ገዢ እግዚአብሔር ሆይ፥ከልጅ
ነቴ ጀምረህ ተስፋዬና መተማመኛዬ አን
ተው ነበርክ። 6 ከተወለድኩበት ጊዜ አን
ሥቶ እምነቴን በአንተ ላይ ጣልኩ፤ከእናቴ
ማኅፀን በደኅና ያወጣኸኝ አንተ ነህ። ስለ
ዚህ ዘወትር ሳወድስህ እኖራለሁ።
7 እነሆ በብዙዎች ዘንድ እንደ ጉድ የም
ታይ ከመሆን ደርሻለሁ፤ አንተ ግን ጽኑ
መጠጊያዬ ነህ። 8 ዕፁብ ድንቅ ስለ ሆነው
ክብርህ ቀኑን ሙሉ በይፋ እናገራለሁ፤አን
ደበቴም በውዳሴህ ተሞልቶ ይውላል።
9 አቤቱ፥በእርጅናዬ ዘመን ጨርሰህ አት
ጣለኝ፤ ጒልበቴ ሲደክምብኝ አትተወኝ።
10 ጠላቶቼ ነገር ይሠሩብኛል፤ ሊገድሉኝ
የሚከታተሉኝ በአንድነት ይዶልቱብኛል።
11 እንዲህም ይላሉ፦ "እግዚአብሔር ትቶ
ታል፤የሚያስጥለው ማንም የለምና፥አሳዳ
ችሁ ያዙት።" 12 አቤቱ፥ ፈጣሪዬ ሆይ፥
ከእኔ አትራቅ፤እኔን ለመርዳት ፈጥነህ ድረስ
ልኝ። 13 ከሳሾቼ በኀፍረት ተጐሳቊለው
ይጥፉ፤ሊጐዱኝ የሚፈልጉ ተንቀው ውርደ
ትን እንደ ሸማ ይልበሱ።
14 እኔ ግን ምን ጊዜም ባለ ተስፋ ስለ
ሆንኩ ምስጋናዬን እጥፍ ድርብ አድርጌ
አቀርብልሃለሁ። 15 ይህን ያህላል ብዬ ልገ
ምተው የማልችለውን የጽድቅህን ሥራና
የቤዛነትህን ነገር አንደበቴ ቀኑን ሙሉ ሲና
ገር ይውላል። 16 የሁሉ ገዢ እግዚአብሔር
ሆይ፥እነሆ ኀይል ስለ ተሞሉ ሥራዎችህ
በይፋ እናገራለሁ፤የአንተ ብቻ ስለ ሆነው
ጽድቅህ አዋጅ አሰማለሁ። 17 አቤቱ፥ከልጅ
ነቴ ጀምረህ አስተማርከኝ፤እኔም እስከዚች
ቀን ድረስ ስለ አንተ ድንቅ ሥራዎች በግ
ልጽ እናገራለሁ። 18 አምላክ ሆይ፥ኀይልህን
ለሚቀጥለው ትውልድ፥ ኀያልነትህን ወደ
ፊት ለሚመጡት ሁሉ ገልጬ እስካስታ
ውቅ ድረስ፥ ባረጅና ባፈጅም ቸል ብለህ
አትተወኝ።
19 ጌታ ሆይ፥ ጽድቅህ እስከ ሰማየ ሰማ
ያት ይደርሳል፤ ታላላቅ ነገሮችን ያደረግህ
አንተ ነህ። አቤቱ፥ አንተን የሚመስልህ
ማነው? 20 ቊጥሩ የበዛና መራራ የሆነ
መከራ እንዲደርስብኝ ብታደርግም፥ ከአዘ
ቅት እንደ ገና አውጥተህ ኑሮዬን መልሰህ
ታደላድልልኛለህ፤ 21 በክብር ላይ ክብርን
ትጨምርልኛለህ፤መልሰህም ታጽናናኛለህ።
22 እግዚአብሔር ሆይ፥ ስለ ታማኝነትህ
በገናዬን እየደረደርኩ በዜማ አመሰግንሃ
ለሁ። የእስራኤል ቅዱስ አምላክ ሆይ፥በመ
ሰንቆ ቃና እየታጀብሁ በዝማሬ አመሰግንሃ
ለሁ። 23 ቤዛ ሆነህ ላዳንኸኝ ለአንተ፥ምስጋ
ናዬን በመዝሙር በማቀርብበት ጊዜ ከንፈ
ሮቼ የእልልታ ድምፅ ያሰማሉ። 24 ጉዳት
ሊያደርሱብኝ የፈለጉ ሁሉ ፥ በኀፍረትና
በሁከት ውስጥ ስለ ወደቁ ልሳኔ ያለማቋረጥ
ስለ ጽድቅ ሥራዎችህ ይናገራል።

## መዝሙር 72

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ትክክለኛ ዳኝነት
ህን ለንጉሥ፥ ጽድቅህን ለንጉሥ ልጅ

ትን ምክንያት ለመረዳት በምሞክርበት ጊዜ
የሕሊና ጭንቀት ተሰማኝ። 17ወደ እግዚአ
ብሔር መቅደስ ገብቼ ወደ ፊት የሚደርስባ
ቸው ነገር እስኪገለጽልኝ ድረስ ከተሰማኝ
ጭንቀት መገላገል አልቻልኩም። በመጨ
ረሻ ግን ፍጻሜአቸው ምን እንደሚሆን ተረ
ዳሁ።
18አዎን፥አንተ በሚያዳልጥ ስፍራ ላይ
አቆምካቸው ፤ ለውድቀትም ዳረግሃቸው።
19በታላቅ ድንጋጤ ተውጠው በድንገት
መጥፋታቸው የሚያስገርም ነው! 20ጌታ
ሆይ፥ከእንቅልፉ ለሚነቃ ሰው፥በሕልሙ
ያየው ነገር ሁሉ ቅዠት ሆኖ እንደሚቀር፥
አንተም ለመፍረድ በምትነሣበት ጊዜ እንደ
ከንቱ ነገር ትንቃቸዋለህ።
21 ልቤ በኀዘን ተሞልቶ መንፈሴ በተመ
ረረ ጊዜ፥ 22ስሜት እንደሌለውና ምንም
እንደማያውቅ ሰው ሆንኩ፤በፊትህ እንደ
ዱር እንስሳ ሆኜ ታየሁ። 23ይሁን እንጂ፥
እኔ ምን ጊዜም ከአንተ አልተለየሁም፤አን
ተም አልተውከኝም። 24በምክርህ ትመራኛ
ለህ፤የኋላ ኋላም ወደ ገናናው ክብርህ ታስገ
ባኛለህ። 25በሰማይ ከአንተ በቀር ማን አለ
ኝታ አለኝ? ከአንተ ጋር ከሆንኩ በምድር
ላይ የምመኘው ሌላ ነገር ከቶ የለም።
26በሥጋዬና በልቦናዬ እደክም ይሆናል፤
እግዚአብሔር ግን ለልቤ ኀይልን ይሰጣል፤
እርሱ የዘላለም ፈንታዬ ነው።
27እነሆ፥ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉ፤አን
ተን የሚክዱትን ሁሉ እንዳልነበሩ ታደርጋ
ቸዋለህ። 28ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር
መቅረብ ይሻለኛል። የሁሉ ገዢ የሆነውን
እግዚአብሔርን መጠጊያዬ አድርጌዋለሁ።
ስለ ሥራዎቹ ሁሉ እመሰክራለሁ።

## መዝሙር 74

1እግዚአብሔር ሆይ፥ለምን «ወግዱ»
ብለህ ለዘላለም ተውኸን? በግጦሽ በምታሰ
ማራቸው በጎችህስ ላይ ቊጣኽ ለምን እየ
ጋለ ይሄዳል? 2በቀደመው ዘመን የዋጀኸ
ውን ሕዝብ አስብ፤ለራስህ መርጠህና ቤዛ
ሆነህ ያዳንኸውን ነገድ፥መኖሪያህ የሆነች
ውንም የጽዮንን ተራራ አስታውስ።
3እነሆ በመቅደስህ ላይ ጠላት ታላቅ
ጥፋት አደረሰ። የጥፋቱ ቋሚ ምስክር በሆ
ነው ፍርስራሽ መካከል እርምጃህን እየመረ
ጥክ እስቲ ጐብኘው። 4ከእኛ ጋር ፊት
ለፊት በተገናኙህበት ስፍራ ጠላቶችህ ደነፉ
በት፤ዓርማቸው የሆነውን ምልክታቸውንም
አቆሙበት። 5አድራጎታቸው ጥቅጥቅ ያለ
ውን ደን ለመመንጠር መጥረቢያቸውን እን
ዳዘጋጁ ዛፍ ቈራጮች ነው። 6ከእንጨት
ተፈልፍሎ የተሠራውን ጌጣ ጌጥ ሁሉ በም
ሳራቸውና በመዶሻቸው ሰባብረው ጣሉት።
7ቤተ መቅደስህን አመድ እስኪሆን አጋ
ዩት፤ቅዱስ ስምህ የሚጠራበትን መኖሪያ
ስፍራ አረከሱት። 8በልባቸውም፥ «እስከ
መጨረሻው አንኮታኩተን እናጠፋቸዋለን»
ብለው በመነሣት፥በአገሪቱ ውስጥ የእግዚአ
ብሔር አምልኮ የሚፈጸምባቸውን ስፍራ
ዎች ሁሉ አቃጠሉ።
9ይህ ሁሉ ሲሆን ከአንተ ምንም ዓይነት
የተአምራት ምልክት አልተሰጠንም፤ከነቢያ
ትም አንድም የቀረ አልተገኘም፤ይህ ሁኔታ
እስከ መቼ እንደሚቈይ የሚያውቅ ከመካከ
ላችን አንድም የለም። 10እግዚአብሔር
ሆይ፥ ጠላት በአንተ ላይ እንዲህ እያፌዘ
የሚናገረው እስከ መቼ ነው? ተቃዋሚህስ
ስምህን ለዘላለም እያዋረደ ሊኖር ነውን?
11እጅህን፥ያውም ኀይለኛ የሆነውን ቀኝ
እጅህን አጣምረህ የምትመለከተው ስለ ምን
ድነው? አሁንም ከለበስከው መጐናጸፊያህ
ውስጥ ብቅ አድርገውና ሰንዝረህ አጥፋ
ቸው።
12እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥ አንተ
ግን ከጥንት ጀምሮ ንጉሤ ነህ፤ቤዛነትህን
በምድር ላይ አወረድህ። 13በኀይልህ ባሕ
ሩን ከሁለት የከፈልክ አንተ ነህ፤በውሃው
ውስጥ ያለውን የዓሣ ነባሪውን ራስ ሰበርህ።
14ሌዋታን የተባለውን ታላቅ የባሕር ውስጥ
አውሬ ራሶች ቀጠቀጥህ፤ለኢትዮጵያ ሰዎ
ችም ምግባቸውን ሰጠሃቸው። 15ምንጮ
ችን የምታፈልቅ፥ወንዞችን የምታፈስና ጅረ
ቶችን የምታደርቅ አንተ ነህ። 16ቀኑም
ሌሊቱም ያንተ ነው፤ፀሐይንና ጨረቃን
አንተ ፈጠርካቸው። 17የምድርን ድንበሮች
ሁሉ ከልለህ የወሰንክ፥ክረምትና በጋን የሠ
ራህ አንተ ነህ።
18ጌታ ሆይ፥ ጠላት በአንተ እንዴት
አድርጎ እንዳፌዘ አስብ፤አላዋቂዎች ስምህን
እንዴት እንዳዋረዱ አስታውስ። 19የርግብ
ህን ሕይወት ለአራዊት አሳልፈህ አትስጥ፤
በመከራ የሚሠቃየውን የሕዝብህን ሕይወት
ለምን ጊዜውም አትርሳ። 20ጨለማ በሰፈነ
ባት በዚች አገር የግፍ ሥራ ስለ በዛ ቃል
ኪዳንህን አስታውስ። 21የተጨቈኑ፥አፍረ
ውና ተዋርደው እንዲያፈገፍጉ አታድርግ።
ድኾችና ችግረኞች ስምህን ያመስግኑ።
22አሁንም እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥
ተነሥ! ዓላማህ እንዳይደፈር ተከላከል።

ሞኞች ቀኑን ሙሉ በአንተ ላይ ያፌዙትን
አትርሳ። 23 የተቃዋሚዎችህን ድንፋታና
እየበረታ የሚሄደውን የጠላቶችህን ሁካታ
ችል አትበል።

## መዝሙር 75

1 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥ ለአንተ
ምስጋናችንን እናቀርባለን፤ ስምህ ቅርብ
ነውና እናመሰግንሃለን፤ ሰዎች፥ ድንቅ ስለ
ሆኑ ሥራዎችህ ይናገራሉ።
2 አንተም እንዲህ አልህ፦ «አመቺውን
ጊዜ መርጬ በቅንነት የምፈርድ እኔ ነኝ።
3 ምድር ከነሕዝቦቿ በምትናወጥበት ጊዜ
ምሰሶዎቿን አጽንቼ የምይዝም እኔ ነኝ።
4 እብሪተኛውን፥ ‘እንግዲህ አትደንፋ’ ግፈ
ኛውንም፥ ‘ያለኔ ሥልጣን ያለው የለም
አትበል፤ 5 እግዚአብሔርን በመቃወም በሰ
ማያት ላይ የሥልጣን ዛቻህን አታሳይ፤አንገ
ትህን መዘህ በድፍረት አትናገር’ እለዋ
ለሁ።»
6 ሥልጣን ከምሥራቅ ሆነ ከምዕራብ
ወይም እንዲሁ ዝም ብሎ ከምድረ በዳ አይ
ገኝም። 7 ነገር ግን ሁሉን የሚያስተዳድር
እግዚአብሔር ነው፤አንዱን ያዋርዳል፤ሌላ
ውን ከፍ ያደርጋል። 8 ፈልቶ በወጣለት
በቊጣው ወይን የተሞላ ጽዋ እግዚአብሔር
በእጁ ይዟል፤በምድር ላይ ለሚኖሩ ግፈ
ኞች ሁሉ ከጽዋው እየቀዳ ይሰጣቸዋል፤እነ
ርሱም አምቡላውን ሳይቀር ጨልጠው ይጠ
ጡታል።
9 እኔ ግን ይህንን ለዘላለም አስታውቃ
ለሁ። ለያዕቆብ አምላክ የምስጋና መዝሙር
አሰማለሁ። 10 የግፈኞችን ኃይል አዋርዳ
ለሁ፤ የጻድቃን ሥልጣን ግን ከፍ ከፍ
ይላል።

## መዝሙር 76

1 እግዚአብሔር በይሁዳ ነገድ ዘንድ የታ
ወቀ ነው፤ስሙም በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ
በታላቅነት ይጠራል። 2 ቤተ መቅደሱ በኢየ
ሩሳሌም ከተማ፥ ማደሪያ ስፍራው በጽዮን
ተራራ ነው። 3 በዚያም ተወርዋሪ ፍላጻዎ
ችን፥ ጋሻዎችንና ሰይፎችን፥ ሌላውንም
የጦር መሣሪያ ሁሉ ይሰባብራል።
4 ጌታ ሆይ፥አንተ በሚያንጸባርቅ ብርሃን
አሸብርቀሃል፤ግርማህ የዱር አራዊት ከሞሉ
ባቸው ተራራዎች ይልቅ የሚያስፈራ ነው።
5 በፊትህ ጀግኖች ኃይላቸውን ተገፈው
ወደቁ፤የሞት ጽዋቸውንም ተቀበሉ፤ከጦረ
ኞች አንዳቸው እንኳ እጃቸውን ማንሣት
አልቻሉም። 6 የያዕቆብ አምላክ ሆይ፥በተግ
ሣፅህ ፈረሱ ከነሠረገላው ተንኮታኩቶ
ወደቀ። 7 መፈራት ያለብህ አንተ ብቻ ነህ።
በተቈጣህ ጊዜ በፊትህ ከቶ ማን ሊቆም
ይችላል? 8 በሰማያት ሆነህ ፍርድህን አሰ
ማህ፤ዓለምም በፍርሃት ተውጦ ዝም አለ።
9 አቤቱ፥በምድር ላይ በመከራ የሚሠቃዩ
ትን ሁሉ ታድን ዘንድ ልትፈርድ በተነሣህ
ጊዜ፥ 10 በሰዎች ላይ የምታወርደው መዓ
ትና ቊጣህ የሚያስመሰግንህ መሆኑ እር
ግጥ ነው፤ከመቅሠፍትህ የሚተርፉት ራሳቸ
ውን ተቈጣጥረው በሥርዓት ይኖራሉ።
11 ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር ስእለ
ትን ተሳሉ፤ያንንም ፈጽሙ፤የጎረቤት አገ
ሮች ሁሉ መፈራት ለሚገባው ለእርሱ፥ገጸ
በረከት ያቅርቡለት። 12 እርሱ የገዢዎችን
መንፈስ ይሰባብራል፤በምድር ነገሥታትም
ዘንድ የተፈራ ይሆናል።

## መዝሙር 77

1 «ድረስልኝ» ብዬ ወደ እግዚአብሔር
ጮህኩ፤ እንዲሰማኝ ወደ እግዚአብሔር
ጩኸቴን አሰማሁ። 2 መከራ ስለ ደረሰብኝ
እግዚአብሔርን ፈለግሁት፤ያለመታከት እጆ
ቼን በሌሊት ወደ እርሱ ዘረጋሁ፤ ነፍሴ
መጽናናት አልቻለችም።
3 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥ አንተን
እያሰብኩ በትካዜ እወዛወዛለሁ። በተመስጦ
ብዙ ነገሮችን አሰላስላለሁ፤መንፈሴ እያደረ
እየደከመ ሄደ። 4 ሌሊቱን ሙሉ ዓይኖቼን
አፍጥጬ እንዳድር አደረግኸኝ፤ መጸለይ
እንኳ ፈጽሞ አቃተኝ። 5 የቀድሞው ዘመን
በአሳቤ ትዝ አለኝ። 6 በሌሊት የማሰማውን
ዝማሬ አስታወስኩ፤ በዚህ ጊዜ ልቤ ተመ
ሰጠ፤ መንፈሴም እንዲህ እያለ ይጠይቅ
ጀመር፦ 7 «ለመሆኑ እግዚአብሔር እኛን
‘ወግዱልኝ’ ብሎ ለዘላለም መተዉ ነውን?
ሞገሱን ዳግመኛ ፈጽሞ ላያሳየን ነውን?
8 ያ ምን ጊዜም የማይለወጠው ፍቅሩስ ተለ
ይቶን ሊቀር ነውን? የተስፋውንስ ቃል
ለመቼውም መሻሩ ነውን? 9 በውኑ እግዚአ
ብሔር መሐሪ አምላክ መሆኑን ረሳውን?
ርኅራኄውንስ በቊጣው አገደውን?» 10 ዳግ
መኛም በአሳቤ፥ «ከሁሉ በላይ የሆነው
አምላክ በብርቱ ክንዱ ኃይሉን ወደ ገለጠባ
ቸው ዘመናት መለስ እላለሁ» አልኩ።
11 አዎን፥ሥራህን አስታውሳለሁ፤ጌታ ሆይ፥
ከብዙ ዓመታት በፊት የፈጸምካቸውን ተአ
ምራትህን አስባቸዋለሁ፤ 12 ሥራዎችህን
ሁሉ በተመስጦ አሰላስላቸዋለሁ፤ ታላላቅ

የኃይል ድርጊቶችህን አጤናቸዋለሁ።
13 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ መንገዶ
ችህ የተቀደሱ ናቸው። እንደ ፈጣሪያችን
እንደ አንተ ያለ እጅግ ገናና አምላክ ከቶ
ማነው? 14 አንተ ተአምራት የምታደርግ
አምላክ ነህ፤ በሕዝቦች መካከል ኃይልህን
ታሳያለህ። 15 የያዕቆብና የዮሴፍ ተወላጆች
የሆኑትን ሕዝብህን በኃያሉ ክንድህ ቤዛ
ሆነህ አዳንካቸው።
16 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ ባሕሩ
ገና በሩቅ ሲያይህ ፈርቶ ተሸማቀቀ፤ እስከ
መጨረሻ ጥልቀቱ ድረስ ተናወጠ። 17 ደመ
ናዎች ዶፍ አዘነቡ፤ ሰማዩም የነጐድጓድን
ድምፅ አስተጋባ፤ ፍላጻዎችህ እንደ ብል
ጭታ በየአቅጣጫው ተወረወሩ። 18 ነጐድጓ
ድህ ከዓውሎ ነፋስ ጋር ተቀላቅሎ ተሰማ፤
መብረቅህ በዓለም ላይ ቦግ ብሎ አበራ፤
ምድርም ተንቀጠቀጠች፤ ተናወጠችም።
19 ዱካህ የማይታይ ቢሆንም መንገድህ በባ
ሕሩ ውስጥ፣ ጐዳናህም በውቅያኖሶቹ መካ
ከል ያስኬዳል።
20 ሕዝብህን በሙሴና በአሮን እጅ እንደ
እረኛ መራሃቸው።

## መዝሙር 78

1 ሕዝቤ ሆይ፣ የማስተምራችሁን ስሙኝ፤
ከአንደበቴ የሚወጡትን ቃላት አዳምጡ።
2 ንግግሬን በምሳሌ እጀምራለሁ፤ ከጥንት
ጀምሮ የተሰወሩትን ነገሮች ገልጬ አወጣ
ለሁ፤ 3 እነርሱም አባቶቻችን የነገሩን፣
እኛም የሰማናቸውና የምናውቃቸው ነገ
ሮች ናቸው። 4 እነዚህን ነገሮች ከልጆቻ
ቸው አንደብቅም። እግዚአብሔር ሊመሰገን
ባቸው የሚገባውን ሥራዎቹን፣ ኃይሉንና
ድንቅ ተአምራቶቹን ለሚቀጥለው ትውልድ
እንነግራለን። 5 የያዕቆብ ልጆች የሚተዳደሩ
በትን ሥርዓት ደነገገ፤ የእስራኤል ሕዝብ
የሚመራበትን ሕግ አወጣ፤ ይህንንም ሕግ
አባቶቻችን ለልጆቻቸው እንዲያስተምሯ
ቸው አዘዛቸው። 6 የሚቀጥለው ትውልድና
ገና ያልተወለዱት ልጆች ሳይቀሩ እንዲያ
ውቁትና እነርሱ ደግሞ በተራቸው ለልጆቻ
ቸው እንዲነግሯቸው ወሰነ። 7 በዚህ ጊዜ
እያንዳንዱ ትውልድ እምነቱን በእግዚአብ
ሔር ላይ ይጥላል፤ የፈጸመውንም ሥራ አይ
ረሳም፤ ትእዛዛቱን ይጠብቃል እንጂ። 8 እንደ
ቀደሙት አባቶቻቸው ልባቸው በእግዚአብ
ሔር ዘንድ ያልታመነና መንፈሳቸው ለእ
ርሱ ታማኝነት የሌለው እምቢተኛና ዐመ
ፀኛ ትውልድ አይሆኑም።
9 የኤፍሬም ነገድ፣ በቀስት መሣሪያ ደር
ጅተው ሳሉ ለውጊያ በተሰለፉበት ቀን ሳይ
ዋጉ ሸሹ። 10 ይህም ሊሆን የቻለው፣ የእግ
ዚአብሔርን ቃል ኪዳን ስላልጠበቁና
በሕጉ ጸንተው መኖርን እምቢ ስላሉ
ነበር። 11 እርሱ የሠራውንና ያሳያቸውን
አስደናቂ ሥራዎቹን ረሱ። 12 አባቶቻቸው
በግብጽ ምድርና በጣኔዎስ በረሃ ሳሉ ዓይና
ቸው እያየ ተአምራትን አደረገ። 13 ባሕሩን
ከሁለት ከፍሎ በመካከሉ አሳለፋቸው፤ ወሃ
ውን ገድቦ እንደ ግድግዳ አቆመላቸው።
14 ቀን ቀን በደመና፣ ሌሊትም በእሳት ብር
ሃን እየመራ መንገዱን አሳያቸው። 15 የም
ድረ በዳውን ዓለት ሰንጥቆ፤ እንደ ጅረት
የሚፈስ ውሃ ሰጣቸው። 16 ከቋጥኝ ምንጮ
ችን እያፈለቀ ውሃው እንደ ጅረት እንዲወ
ርድ አደረገ።
17 እነርሱ ግን ይህን ባደረገላቸውና
ከሁሉ በላይ በሆነው አምላክ ላይ የሚፈጽ
ሙትን በደልና ዐመፅ በዚያው በምድረ በዳ
እያሉ ቀጠሉ። 18 የተመኙትን የምግብ ዓይ
ነት እንዲሰጣቸው በመጠየቅ እግዚአብሔ
ርን ተፈታተኑት። 19 እንዲህም እያሉ ያሳ
ጡት ጀመር፦ «ለመሆኑ እግዚአብሔር
በዚህ በረሃ ገበታን ዘርግቶ ምግብን ሊያቀ
ርብ ይችላልን? 20 እርግጥ ዓለቱን በመታው
ጊዜ ውሃው ዥረር ብሎ ፈሰሶ ነበር፤ ምን
ጮም እንደ ዥረት ወርዶ ነበር። ይሁን
እንጂ መብል ሊሰጠን ይችላልን? ለሕዝቡ
የሚያስፈልገውን ሥጋ ሊያቀርብ ከቶ ይቻ
ለዋልን?»
21 እግዚአብሔር ይህን ሐሜታቸውን
ሲሰማ እጅግ ተቈጣ፤ የመዓቱ እሳት በያዕ
ቆብ ልጆች በእስራኤል ሕዝብ ላይ ነደደባ
ቸው። 22 ይህም የሆነው የሚያስፈልጋቸ
ውን በሚሰጣቸው በእግዚአብሔር ስላላመ
ኑና በእርሱም የማዳን ኃይል ስላልተማመኑ
ነበር። 23 እርሱ ግን ለደመና ትእዛዙን
ሰጥቶ የሰማያት በሮች እንዲከፈቱ አደረገ።
24 ሕዝቡ ይበሉ ዘንድ መና አዘነበላቸው፤
የሰማይ ምግብ ሰጣቸው፤ 25 ሰዎችም የመላ
እክትን እንጀራ በሉ። ለመብላት የሚችሉ
ትን የምግብ ዓይነት ሁሉ አቀረበላቸው።
26 የምሥራቅን ነፋስ ከፍቶ ስለ ለቀቀውና
የደቡቡን ነፋስ በኃይሉ እየመራ ስላመ
ጣው፣ 27 እነሆ ሥጋን እንደ አፈር፣ የሚበ
ርሩ ወፎችን እንደ ባሕር አሸዋ አብዝቶ
በላያቸው አዘነበ፤ 28 በሰፈራቸው መካከልና
በድንኳኖቻቸው ዙርያ እንዲፈስስ አደረ
ገው። 29 የጎመጁትን ምግብ ስለ ሰጣቸው

ከመጠን በላይ እስኪጠግቡ በሉ። 30 ዳሩ
ግን ምግቡን ገና ከፊታቸው ሳያነሡት፥እን
ዲያውም የጎረሱትን በአፋቸው እንደ ያዙ፥
31 የእግዚአብሔር ቍጣ ወረደባቸው። ከመ
ካከላቸው እጅግ ኀበዞች የሆኑትን በሞት
ቀጣቸው፤የእስራኤል ወጣቶች ተቀሠፉ።
32 እነርሱ ግን፥ይህ ሁሉ የቅጣት መቅሠ
ፍት እየወረደባቸው እግዚአብሔርን መበደ
ላቸውን አላቋረጡም፤ ይህን ሁሉ ድንቅ
ተአምራቱን እያሳያቸው አላመኑበትም።
33 ስለዚህ ዕድሜያቸው በከንቱ፥ ዘመናቸ
ውም በሽብር እንዲያልቅ አደረገ። 34 እግዚ
አብሔር በቀጣቸው ጊዜ፥በጭንቀት እንደ
ገና ወደ እርሱ መለስ ብለው ፈለጉት።
35 እግዚአብሔር መጠጊያቸው፥ከሁሉ በላይ
የሆነው አምላክ ቤዛቸው መሆኑንም አስታ
ወሱ። 36 በአንደበታቸው አቈላመጡት፤
ሐሰት በተመላ ንግግር ሸንገሉት። 37 ልባ
ቸው ግን የሸፈተና ለቃል ኪዳኑም ያልታ
መነ ነበር። 38 እግዚአብሔር ግን መሐሪ
ነውና ኃጢአታቸውን ሁሉ ይቅር አላቸው
እንጂ በበደላቸው ምክንያት አላጠፋቸ
ውም። ቍጣውን በየጊዜው እየገታ መለ
ሰው፤የመዓቱም መቅሠፍት በሙሉ እንዲወ
ርድ አላደረገም። 39 ሥጋ ለባሾችና እንዴ
ካለፈ እንደማይመለስ የነፋስ ሽውታ መሆና
ቸውን አሰበ።

40 በምድረ በዳ ሳሉ ስንት ጊዜ በእርሱ
ላይ ዐመፁ! ስንት ጊዜስ አሳዘኑት! 41 ደግ
መው ደጋግመው እግዚአብሔርን ተፈታተ
ኑት ፤ የእስራኤልን ቅዱስ አምላክ አበሳ
ጩት። 42 ተጨቍነው ከነበሩበት ሲያወጣ
ቸው ያሳየውን ኃይሉን አላስታወሱም።
43 የተአምራት ምልክቶቹን በግብጽ
ምድር ፥ ድንቅ ሥራዎቹን በጣኔዎስ በረሃ
በገሃድ ያሳየበት ወቅት ትዝ አላላቸውም።
44 በዚያን ጊዜ የግብጻውያንን ወንዞች ወደ
ደም ለወጠ፤ ስለዚህ ግብጻውያን ከፈሳሽ
ውሆቻቸው ሊጠጡ ከቶ አልቻሉም።
45 እየነደፉ የሚጨርሷቸውን የዝንብ መንጋ
ዎችና ታላቅ ጥፋት የሚያደርሱባቸውን
እንቍራሪቶች ላከባቸው። 46 ለመከር የደረሰ
ውን አዝመራቸውን ለኵብኵባ፥ለፍሬ የደ
ረሰ ሰብላቸውን ለአንበጣ ሰጠባቸው።
47 የወይን አትክልታቸውን በበረዶ፥የፍሬ
ዛፎቻቸውን በውርጭ አጠፋባቸው። 48 የጋ
ማና የቀንድ ከብቶቻቸውን ለበረዶ ውሽንፍ
ርና ለመብረቅ ዳረጋቸው። 49 ጽኑ ቍጣው
ንና መዓቱን፥ንዴቱንና ቅጣቱን እንዲያወር
ዱባቸው የመቅሠፍት መላእክቱን ላከባ
ቸው። 50 ለቍጣው መንገድ ስለ ከፈተ፥
በመቅሠፍት እንዲያልቁ አደረጋቸው እንጂ
ከሞት አላተረፋቸውም። 51 በካም ቤተሰብ
ውስጥ የመጀመሪያ ፍሬ የሆኑትን የግብጻ
ውያንን በኵር ልጆች ሁሉ ገደለ።

52 ሕዝቡን ግን እንደ መንጋ አወጣ
ቸው ፤ በምድረ በዳ መካከል እንደ በግ
መራቸው። 53 መንገዱን እያሳየ በጕዞአ
ቸው ላይ ስለ ጠበቃቸው ምንም አልፈ
ሩም፤ ጠላቶቻቸውን ግን በባሕር አስጥሞ
አስቀራቸው። 54 እንዲህ አድርጎ በቀኝ
እጁ ወደ ያዛትና ተራራማ ወደ ሆነችው
ወደ ተቀደሰችው ምድሩ ድንበር አደረሳ
ቸው። 55 ምድሪቱን ይዘው የነበሩትን አሕ
ዛብ አስወጥቶ አባረረላቸው፤አገራቸውንም
አከፋፍሎና ርስት አድርጎ ሰጣቸው። የእ
ስራኤልን ነገዶች እነሆ ባለ ቦታ ሆነውና
የየራሳቸውን ቤት ሠርተው የሚኖሩ
ሕዝብ ለመሆን አበቃቸው።

56 እነርሱ ግን አሁንም እግዚአብሔርን
ተፈታተኑት፤ከሁሉ በላይ በሆነው አምላክ
ላይ ዐመፁ፤ ሕጉንና ሥርዓቱን አፈረሱ።
57 አባቶቻቸውን በመምሰል የማይታመኑና
እምነተ ቢሶች ሆኑ፤እንደማያስተማምን ስን
ኩል ቀስት የእግዚአብሔርን ዓላማ ሳቱ።
58 በየኰረብታው ላይ በሚፈጽሙት የባዕድ
አምልኮ አስቈጡት፤በሚሰግዱላቸው ጣዖቶ
ቻቸው አስቀኑት።

59 እግዚአብሔር ይህን አድራጎታቸውን
ሲያይ እጅግ ተቈጣ፤የእስራኤልን ሕዝብ
«ወግዱ» ብሎ ከፊቱ አገለላቸው። 60 በእኛ
በሕዝቦቹ መካከል በሴሎ የተከላትን የማደ
ሪያውን ድንኳን ተዋት። 61 የክብሩና የኃ
ይሉ መገለጫ የሆነችውን የቃል ኪዳን
ታቦት በጠላት እጅ እንድትማረክ አደረ
ጋት። 62 የራሱ በሆነት ሕዝብ ላይ እጅግ
በመቈጣቱ ለሰይፍ አሳልፎ ሰጣቸው።
63 ጐልማሶቻቸው በጦርነት እሳት እየተማ
ገዱ ስላለቁ፥የሴቶች ልጆቻቸው የሠርግ
ዘፈን ሁሉ ቀረ። 64 ካህናቶቻቸው ተሰየፉ፤
ሚስቶቻቸው ሊያለቅሱላቸው እንኳ አልቻ
ሉም።

65 በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ከእንቅልፉ
እንደሚነቃ ሰው ተነሣ፤የመጠጥ ኃይል
እንደ ለቀቀውም ጕበዝ ብድግ አለ። 66 ጠላ
ቶቹን ወግቶ መለሳቸው፤በዘላለም ውርደት
ላይ ጣላቸው። 67 በዚያን ጊዜ የዮሴፍን
ተወላጆች አልፈለገም፤የኤፍሬምንም ነገድ
አልመረጠም፤ 68 እርሱ ከነገድ የመረጠው
ይሁዳን፥ከተራራ የወደደው ጽዮንን ነበር።

69 በዚያም ቤተ መቅደሱን እንደ ሰማይ
አጽንቶ ሠራት፤በምድር ላይ ለዘላለም መሠ
ረታት። 70 ዳዊትን ለእርሱ አገልጋይነት
መረጠው፤ከበጎች ጒረኖ አውጥቶ ወሰደው፤
71 ከበጎች ጠባቂነት አንሥቶ ለያዕቆብ ልጆ
ችና የራሱ ለሆኑት የእስራኤል ሕዝብ
እረኛ ይሆን ዘንድ ሾመው። 72 ዳዊትም
ሕዝቡን በቅን ልቦና ጠበቃቸው፤በብልህ
አስተዳደር መራቸው።

## መዝሙር 79

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ አሕዛብ፥ ርስትህ
የሆነችውን አገር ወረሩ፤ቤተ መቅደስህን
አረከሱ፤ ኢየሩሳሌምን የፍርስራሽ ክምር
አደረጓት። 2 የአገልጋዮችህን ሬሳ ለሰማይ
አዕዋፍ፥የቅዱሳንህን አስከሬን ለምድር አራ
ዊት ምግብ አድርገው ሰጡ። 3 በኢየሩሳሌ
ምና በአካባቢዋ ሁሉ የሰውን ደም እንደ
ጐርፍ አፈሰሱ፤ሙታንን የሚቀብር ጠፋ።
4 እኛም በጎረቤቶቻችንና በዙሪያችን ባሉ
አገሮች ዘንድ ለነቀፌታ፥ ለንቀትና ለሣቅ
ለሥላቅ ተጋለጥን።

5 ጌታ ሆይ፥ይህ የሚሆነው እስከ መቼ
ነው? ቊጣህ ለዘላለም ነውን? ቅንዓትህ
እንደ እሳት እስከ መቼ ሲነድብን ይኖ
ራል? 6 አቤቱ፥የአንተን አምላክነት በማያ
ምኑ አሕዛብና ስምህን በማይጠሩ መንግ
ሥታት ላይ ቊጣህን አውርድባቸው።
7 የያዕቆብ ዘር የሆነውን ሕዝብህን በጭ
ካኔ ጨርሰውታል፤አገሩንም አውድመውታ
ልና።

8 ስለ አባቶቻችን በደል እኛን ተጠያቂዎ
ችና ፍዳ ከፋዮች አታድርገን። ተስፋ በሚ
ያስቈርጥ መከራ ላይ እንገኛለንና ምሕረትህ
ፈጥኖ ይድረስልን፤ያድነንም። 9 መድኅናችን
እግዚአብሔር ሆይ፥ ስለ ገናናው ስምህ
ክብር ስትል እርዳን፤ስለ ስምህ ስትል ኃጢ
አታችንን ይቅር ብለህ ከዚህ መከራ አው
ጣን። 10 አሕዛብ፥ «አምላካቸው ወዴት
ነው?» ስለ ምን ይበሉ? እንደ ጐርፍ የፈሰ
ሰውን የአገልጋዮችህን ደም የምትበቀል
አምላክ መሆንህን በአሕዛብ መካከል በገ
ሃድ አሳውቅ። 11 የእስረኞች የሥቃይ
ጩኸት ከፊትህ ይድረስ፤ይሙት በቃ የተፈ
ረደባቸውን በክንድህ ኃይል ሕይወታቸውን
አትርፍ። 12 ጌታ ሆይ፥በአንተ ላይ የተዘባበ
ቱትን መዘባበት ሰባት እጥፍ አድርገህ ክፈ
ላቸው።

13 እኛ በለመለመ መስክህ ላይ እንደም
ታሰማራቸው በጎችህ የምትጠብቀን ሕዝ
ብህ፥ለዘላለም እናመሰግንሃለን። ከትውልድ
ወደ ትውልድ ምስጋናህን ስንናገር እንኖራ
ለን።

## መዝሙር 80

1 የዮሴፍን ወገኖች እንደ መንጋ የምት
መራ የእስራኤል እረኛ ሆይ፥ስማን። ኪሩ
ቤል በሚሸከሙት ዙፋንህ ላይ የምትቀመ
ጠው አምላክ፥ ብርሃንህ ይገለጥ። 2 በኤፍ
ሬም፥በብንያምና በምናሴ ወገኖች ፊት በኃ
ይልህ ተነሥ፤መጥተህ አድነን።

3 አምላክ ሆይ፥ ሕይወታችንን አድስ፤
መዳን እንችል ዘንድ ፊትህን በላያችን
አብራ።

4 ኃያሉ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥
በሕዝብህ ጸሎት ላይ ቊጣህ የሚቈየው
እስከ መቼ ነው? 5 የልቅሶ እንጀራ መገብሃ
ቸው፤ እንባቸውንም በጽዋ አጠጣሃቸው።
6 ለጎረቤቶቻችን ነገር መቈስቈሻ አደረግ
ኸን፤ጠላቶቻችን ያፌዙብናል።

7 ኃያሉ አምላክ ሆይ፥ ሕይወታችንን
አድስ፤መዳን እንችል ዘንድ ፊትህን በላያ
ችን አብራ።

8 እኛ እኮ ከግብጽ አምጥተህ፥አሕዛብን
ከዚች ምድር አስወጥተህ፥የተከልካት የወ
ይን ተክልህ ነን። 9 ለእርሷ መሬቱን መንጥ
ረህ አለሰለስክላት፤ሥርም ሰደደች፤ቅጠሏም
አገሩን ሞላው። 10 ተራሮች በጥላዋ፥ግዙ
ፎች ዝግባዎች በቅርንጫፎቿ ተሸፈኑ።
11 ሐረጓን እስከ ታላቁ ባሕር፥ ጫፎቿን
እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ዘረጋች።

12 አላፊ አግዳሚው ፍሬዋን እየለቀመ
እንዲበላ ስለ ምን ቅጥሩዋን አፈራረስክ?
13 ከርከሮ ከዱር እየወጣ ረጋግጦ አበላሻት፤
የሜዳ እንስሶችም ተሰማሩባት።

14 ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ፥ወደ እኛ
ተመለስ፤በሰማይ ሆነህ ወደ ታች ተመል
ከት ፤ የወይን ተክልህን ተከባከባት።
15 ሥሯን ቀኝ እጅህ ተከለው፤ ከእርሷም
ወንድ ልጅን ለራስህ አስነሣህ።

16 እነሆ የወይን ተክልህ ተቈርጣለች፤
በእሳትም ተቃጥላለች፤በተግሣጽህ ሕዝብህ
ይጠፋሉ። 17 እጅህ በቀኝህ ባለው ሰው ላይ
ይረፍ፤ እርሱ፥ ለራስህ ያስነሣኸው የሰው
ልጅ ነው። 18 ከዚያ በኋላ አንተን ትተን
ወደ ሌላ አምልኮ አንሄድም። አቤቱ፥ሕያ
ዋን አድርገን፤እኛም ስምህን እንጠራለን።

19 ኃያሉ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥
ሕይወታችንን አድስ፤ለመዳን እንችል ዘንድ
ፊትህን በላያችን አብራ።

## መዝሙር 81

1ኃይላችን ለሆነው እግዚአብሔር በደ
ስታ ዘምሩ፤ለያዕቆብ አምላክ እልል በሉ።
2በዜማ መሣሪያዎች አቀንቅኑ፤ ከበሮውን
ምቱ፤ ቃናው የሚመስጠውን በገናና መሰ
ንቆ ተጫወቱ። 3ጨረቃ በምትወለድበትና
በዓላችንን በምናከብርበት በአዲሱ ወር መግ
ቢያ ቀንደ መለከቱን ንፉ። 4ይህ ሥርዓት
የእስራኤል ሕዝብ ይጠብቁት ዘንድ የያዕ
ቆብ አምላክ በአዋጅ የሰጣቸው ትእዛዝ
ነው። 5ይህንንም ሥርዓት፥የማናውቀውን
ቋንቋ በሰማንባት በግብጽ አገር ላይ መቅሠ
ፍቱን ባወረደበት ጊዜ ለዮሴፍ ወገኖች
ሕግ አድርጎ አቆመላቸው።

6እርሱም እንዲህ አለ፦ «ሸክማችሁን
ከትከሻችሁ ላይ አውርጄ ጣልኩ፤ እጆቻ
ችሁ የባዕድ ቅርጫት ከማንጠልጠል ነጻ
ሆኑ። 7በመከራ ስትሠቃዩ ወደ እኔ ጮሃ
ችሁ፤እኔም አዳንኳችሁ፤በነጐድጓድ ድምፅ
ከደመና ውስጥ መልስ ሰጠኋችሁ፤ መሪባ
ከሚባለው የውሃ ምንጭ ስትደርሱም ፈተን
ኳችሁ።

8«ሕዝቤ እስራኤል ሆይ፥ስሙኝ። እነሆ
ማስጠንቀቂያዬን አዳምጡ። 9ባዕዳን አማል
ክት በመካከላችሁ አይኑሩ፤ ለሌላ አምላክ
አትስገዱ። 10ከግብጽ ያወጣኋችሁ እግዚአ
ብሔር አምላካችሁ እኔ ነኝ፤ አፋችሁን
ሞልታችሁ የምትጠይቁኝን ሁሉ እኔ እፈጽ
መዋለሁ።

11«ሕዝቤ እስራኤል ግን አላዳመጡ
ኝም፤አልታዘዙኝም። 12ስለዚህ፥የራሳቸውን
ምኞት ተከትለው ይሄዱ ዘንድ በእምቢተኛ
ነታቸው እንዲቀጥሉ ተውኳቸው።

13«ሕዝቤ እስራኤል ሰምተውኝና መን
ገዴን ተከትለው ቢሆን ኖሮ፥ 14ፈጥኜ በጠ
ላቶቻቸው ላይ እጄን ባነሣሁባቸውና ድል
ባደረግሁላቸው ነበር! 15እግዚአብሔርን
የሚጠሉ፥የኋላ ኋላ በፊቱ እየተሽቈጠቈጡ
ይወድቃሉ፤ቅጣታቸውም ለዘላለም ሲፈጸም
ባቸው ይኖራል። 16እናንተ ግን ምርጥ የስ
ንዴ ምርት እየተመገባችሁ ትጠግባላችሁ፤
የጣዝማ ማርም እየበላችሁ ትረካላችሁ።»

## መዝሙር 82

1እግዚአብሔር በታላቁ ጉባኤ ላይ ይቀ
መጣል፤እንደ አማልክት በሚከበሩ ባለሥል
ጣኖች መካከል የፍርድ ቃሉን እንዲህ ሲል
ይሰጣል፦ 2«ሐሰተኞችን ስትደግፉ፥ለግፈ
ኞችም ስታደሉ የምትኖሩት እስከ መቼ
ነው? 3ከዚህ ይልቅ ለደካሞችና ለሙት
ልጆች ተከራከሩላቸው፤የድኾችንና የጭቊ
ኖችን መብት አስጠብቁላቸው። 4ደካሞቹ
ንና ችግረኞቹን ከግፈኞች እጅ አስጥላችሁ
አድኗቸው።

5«እነርሱ ምንም ነገር አያውቁም፤የሚ
ያስተውሉት ምንም ነገር የለም፤እንዲያው
በጨለማ ውስጥ በዳበሳ እንደሚሄድ ሰው
ናቸው። የዚች ዓለም ኅብረተ ሰብ ሥርዓት
ሁሉ ተናግቷልና።

6«እኔ ግን፥ 'እናንት አማልክት ናችሁ፤
ሁላችሁም የልዑል እግዚአብሔር ልጆች
ናችሁ' ብዬ ነበር። 7ለካስ፥እንደ ማንኛ
ውም ሰው ትሞታላችሁ፤ከባለሥልጣኖችም
እንደ አንዱ ትሻራላችሁና» አልሁ።

8አሁንም እግዚአብሔር ሆይ፥ ተነሥ፤
በምድር ላይ ፍርድህን ስጥ። አሕዛብ ሁሉ
የአንተ ርስት ናቸውና።

## መዝሙር 83

1አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፥ለጸሎ
ታችን መልስ ስጠን፤ፈጥነህ ድረስልን እንጂ
ፈጽመህ ዝም አትበለን። 2ጠላቶችህ ምን
ያህል በእብሪት ተነሣሥተው እንደሚራ
ወጡ፥ እንዴትስ አድርገው አንገታቸውን
መዘው በድፍረት እንደሚደነፉ ተመል
ከት። 3በሕዝብህ ላይ በተንኰል ይዶል
ታሉ፤አንተ በምትሳሳላቸው ላይ ያሤራሉ።
4«ኑ! እስራኤል የሚባል ስም ለዘላለም
ተረስቶ እንዲቀር ይህን ሕዝብ እናጥ
ፋው!» ይላሉ።

5በዚህ ሤራ አንድ አሳብ ሆነው ተባ
በሩ፤ በአንተም ላይ ተማምለው አደሙ።
6ኤዶማውያን የሚኖሩባቸው ከተሞች፥እስ
ማኤላውያን፥የሞዓብ ወገኖችና የአጋር ተወ
ላጆች፥ 7የጌባል፥ የአሞንና የአማሌቅ
ምድር ነዋሪዎች፥ፍልስጥኤማውያንና የጢ
ሮስ ሰዎች፥ 8አሦራውያን እንኳ ሳይቀሩ
ለሎጥ ልጆች ደጀን በመሆን ከጠላቶችህ
ጋር አባሪ ተባባሪ ሆኑ።

9አቤቱ፥ የእነዚህ ፍጻሜ፥ በምድያማው
ያን ላይ እንዳደረግኸው፥ በቂሶንም ወንዝ
እንደ ተገደሉት እንደ ሲሣራና እንደ ኢያ
ቢስ ይሁን። 10በእንዶር ጦርነት ላይ ፈጽ
መው እንዳለቁት፥ ዓፅማቸው በምድር ላይ
እንደ ጥራጊ ተጥሎ እንደ ቀሩት አድርጋ
ቸው። 11በመኳንንቶቻቸው፥ የሔሬብና
የዜብ፥ በመሳፍንቶቻቸውም፥የዛብሄልና የስ
ልማና እልቂት ይድረስባቸው። 12እነርሱ፥
«እግዚአብሔር ለሕዝቡ መሰማሪያ ያዘጋጀ

ውን አገር ወስደን እንይዛለን» ብለው ፎከ
ረው ነበር።
13 ፈጣሪዬ ሆይ፥ በነፋስ ተጠርጎ እንደ
ሚወሰድ ትቢያና ገለባ አድርጋቸው።
14 የሰደድ እሳት ደኑን ፈጽሞ እንደሚበላ
ውና የምንጣሮ ነበልባል የተራራውን ቊጥ
ቋጦ አቃጥሎ እንደሚጨርሰው፥ 15 አንተም
እንዲሁ እነርሱን በቊጣህ ውሽንፍር አሳዳ
ቸው፤ በመቅሠፍትህ ዶፍ አስደንግጣቸው።
16 እግዚአብሔር ሆይ፥ ሰዎች የአንተን ስም
መጥራት ይፈልጉ ዘንድ፥ ጠላቶችህ ፊታቸ
ውን በኀፍረት እስኪሸፍኑ ድረስ አዋርዳ
ቸው። 17 ለዘላለም እንዲፈሩና እንዲዘኑ
ኖረው፥ በመጨረሻ በውርደት ተጐሳቊለው
ይጥፉ። 18 ስምህ እግዚአብሔር የሆነው
ጌታ፥ ብቻህን በመላዋ ምድር ከሁሉ በላይ
መሆንህን ይወቁ።

## መዝሙር 84

1 ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ፥ ማደሪያህ
የሆነው ቤተ መቅደስህ ምንኛ ውብ ነው?
2 በእግዚአብሔር አደባባዮች ለመገኘት
ነፍሴ እጅግ ትናፍቃለች፤ ልቤናዬና ሥጋዬ
ሕያው እግዚአብሔርን በመፈለግ ይጮ
ሃሉ።
3 ንጉሤና አምላኬ ኃያሉ እግዚአብሔር
ሆይ፥ በመሠዊያህ አቅራቢያ ድንቢጥ እንኳ
የምትሰፍርበትን ቤት፥ ጨረባም ራሷን የም
ታስጠጋበትንና ጫጩቶቿን የምትፈለፍልበ
ትን ጐጆ ለመሥራት ቦታ አላት። 4 በቤተ
መቅደስህ እያገለገሉ የሚኖሩ የተባረኩ
ናቸው፤ ለዘላለምም ያመሰግኑሃል። 5 በአንተ
ኃይል የሚተማመኑና ዘወትር ልባቸውን
ወደ አንተ የሚያዘነብሉ የተባረኩ ናቸው።
6 በልቅሶ ሸለቆ መካከል በሚያልፉበት
ጊዜ፥ በዚያ ምንጮች የበዙባትና ኩሬዎች
በበልግ ዝናብ የሞሉባት ስፍራ ያገኛሉ።
7 ከጽዮን አምላክ ፊት ደርሰው እስኪታዩ
ድረስ፥ ኃይላቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨ
መረ ይሄዳል።
8 ኃያሉ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥
ጸሎቴን ስማ። የያዕቆብ አምላክ ሆይ፥ ወደ
እኔ አድምጥ። 9 አቤቱ፥ ቀብተህ ያነገሥከ
ውን መሪ በፍቅር ዓይን እየው፤ ጋሻችን ስለ
ሆነ ተመልከተው፤ ጠብቀውም።
10 በሌላ ስፍራ ሺህ ቀኖች ከምኖር፥ በአ
ደባባይህ አንዲት ቀን ብውል ይሻለኛል።
በክፉዎች ቤት መንግሥት ውስጥ ከምኖር፥
በአምላኬ ቤት የበሩ ጠባቂ መሆንን እመር
ጣለሁ። 11 እግዚአብሔር አምላክ ብርሃናች
ንና መከታችን ነው፤ እርሱ ሞገስንና ክብርን
ይሰጠናል። ነውር የሌለበትን መንገድ ተከ
ትለው ለሚኖሩትም፥ መልካም የሆነውን
ነገር ሁሉ አይነፍጋቸውም።
12 ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ፥ በአንተ
የሚተማመን ሰው የተባረከ ነው።

## መዝሙር 85

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ ርስትህ ለሆነችው
አገር ሞገስህን አሳየህ፤ የያዕቆብ ልጆች ለሆ
ኑት ሕዝብህ ብልጽግናቸውን መለስህ።
2 በደላቸውን ይቅር አልክ፤ ኃጢአታቸውን
ሁሉ ሸፈንክላቸው። 3 መዓትህን በሙሉ
አራቅህላቸው፤ ከጽኑ ቊጣህ ተመለስክ።
4 መድኃኒታችን እግዚአብሔር ሆይ፥
ሕይወታችንን አድስ፤ በእኛ ላይ ያለህን
ቅሬታ ተውልን። 5 በውኑ ለዘላለም እንደ
ተቈጣኸን ልትቀር ነውን? ወይስ ቊጣህን
ከትውልድ ወደ ትውልድ ልታራዝመው
ነውን? 6 ሕዝብህ በአንተ ደስ ይለው ዘንድ
ዳግመኛስ መንፈሳዊ መነቃቃትን አትሰጠን
ምን? 7 እግዚአብሔር ሆይ፥ የማይለወጠውን
ፍቅርህን አሳየን፤ ቤዛነትህንም አድለን።
8 እግዚአብሔር አምላክ የሚለውን አዳ
ምጣለሁ። ሕዝቡ ወደ ቀድሞው አላዋቂነ
ታቸው ካልተመለሱ፥ በቅዱሳኑ ዘንድ ሰላ
ምን ለማውረድ የተስፋ ቃሉን ሰጥቷል።
9 ገናና ክብሩ በምድራችን ላይ ሰፍኖ ይኖር
ዘንድ፥ ቤዛነቱ ለሚፈሩት ሁሉ በእርግጥ
ቅርብ ነው።
10 ፍቅርና ታማኝነት ተገናኙ፤ ጽድቅና
ሰላምም ተሳሳሙ። 11 ታማኝነት ከምድር
ፈልቃ ወጣች፤ ጽድቅ ከሰማይ ወደ ታች
ተመለከተች። 12 እግዚአብሔር መልካም
የሆነውን ነገር አለጥርጥር ይሰጣል፤ ምድራ
ችንም አዝመራዋን ታበረክታለች።
13 ጽድቅ በፊቱ ቀድማ ትሄዳለች፤ የሚጓዝበ
ትንም መንገድ ታዘጋጅለች።

## መዝሙር 86

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ ድኻና ችግረኛ
ነኝና ስማኝ፤ መልስልኝም። 2 ፍጹም ታማ
ኝህ ነኝና ሕይወቴን ጠብቅ፤ አንተ ፈጣሪዬ
ነህና በአንተ የተማመንኩትን እኔን አገልጋ
ይህን አድነኝ። 3 አቤቱ፥ ያለማቋረጥ ወደ
አንተ እየተጣራሁ ነኝና ማረኝ። 4 ጌታ
ሆይ፥ ነፍሴ ወደ አንተ አዘንብላለችና ለእኔ
ለአገልጋይህ ደስታን ስጠኝ።
5 እግዚአብሔር ሆይ፥ ለሚጠሩህ ሁሉ
ፍቅርህ የበዛ፥ ቸርና ይቅር ባይ ነህ።

6አቤቱ ፥ ጸሎቴን ስማ፤ «ማረኝ» ብዬ ወደ
አንተ የማቀርበውን የልመና ጩኸት አድ
ምጥ። 7መከራ በሚደርስብኝ ጊዜ ወደ
አንተ እጣራለሁ፤አንተም ትመልስልኛለህ።
8እግዚአብሔር ሆይ ፥ ከአማልክት መካ
ከል አንተን የሚመስል ከቶ ማንም የለም፤
ከአንተ ሥራዎች ጋር ሊወዳደር የሚችል
ሌላ ሥራ ጨርሶ የለም። 9አቤቱ ፥ አንተ
የፈጠርካቸው አሕዛብ ሁሉ ከአንተ ዘንድ
ይቀርባሉ፤በፊትህ ይሰግዳሉ፤ለስምህም ክብ
ርና ምስጋናን ያቀርባሉ። 10አንተ ገናና
ነህና ፤ ድንቅ ተአምራትም ታደርጋለህና።
አንተ ብቻህን እውነተኛው አምላክ ነህ።
11እግዚአብሔር ሆይ ፥ መንገድህን አስተ
ምረኝ፤እኔም እውነተኛ የሆነውን ቃልህን
ተከትዬ እኖራለሁ። ስምህን እፈራ ዘንድ
በአንተ አምልኮ ብቻ የጸና ልቦና ስጠኝ።
12ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ሆይ ፥ በፍጹም
ልቤ አመሰግንሃለሁ ፤ ስምህንም ለዘላለም
ሳወድስ እኖራለሁ። 13ለእኔ ያለህ ፍቅር
ታላቅ ስለ ሆነ ነፍሴን ወደ ሲኦል ከመው
ረድ አዳንካት።
14እግዚአብሔር ሆይ ፥ እብሪተኞች እያ
ጠቁኝ ናቸው፤ስለ አንተ ደንታ የሌላቸው
ጨካኞች ሕይወቴን ሊያጠፉ ይከታተሉ
ኛል። 15አንተ ግን ጌታ ሆይ ፥ ርኅሩኅና
ለጋስ፥ለቍጣ የማትቸኵል፥ፍቅርህና ታማኝ
ነትህ እጅግ የበዛ አምላክ ነህ። 16አሁንም
ወደ እኔ መለስ በል፤ማረኝም፤በእኔ በአገል
ጋይህ ላይ ኀይልህን አሳድርብኝ፤የሴት አገ
ልጋይህን ልጅ እኔን አድነኝ። 17እግዚአብ
ሔር ሆይ ፥ ለእኔ ያለህን ቸርነት ጠላቶቼ
አይተው ያፍሩ ዘንድ ምልክት አሳየኝ ፤
አንተ ረድተኸኛልና፤አጽናንተኸኛልም።

## መዝሙር 87

1እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን በተቀደ
ሰችው ተራራ ላይ መሠረተ። 2ከያዕቆብ
ልጆች የመኖሪያ ሕንፃዎች ይበልጥ፥እርሱ
የጽዮንን ደጃፎች ወደደ። 3አንቺ የእግዚአ
ብሔር ከተማ ሆይ፥ክብርና ገናናነት የተሞ
ላባቸው ቃላት ስለ አንቺ እንዲህ ተብለው
ተነግረዋል፦ 4«ረዓብንና ባቢሎንን፥ከሚያ
ውቁኝ ወገኖች መካከል እመዘግባቸዋለሁ፤
ፍልስጥኤምና ጢሮስ ፥ እንዲሁም የኢትዮ
ጵያ ሕዝብ ‘የጽዮን ተወላጆች ናችሁ’ ይባ
ላሉ።»
5በእርግጥም ሰው በውስጧ ስለ ተወ
ለደ ፥ ሁሉም ጽዮንን «እናታችን» ብለው
ይጠሯታል፤እርሷንም ከሁሉ በላይ የሆነው
እግዚአብሔር ራሱ መሥርቶ ያቋቁማታል።
6እግዚአብሔር የያንዳንዱን ሰው ስም በወገ
ኖቹ መጽሐፍ ውስጥ በሚመዘግብበት
ጊዜ ፥ «ይህኛውም በጽዮን የተወለደ ነው»
የሚለውን ቃል ይጽፍለታል።
7በዚህ ጊዜ ሁሉም ፥ «የደስታችን
ምንጭ አንቺ ጽዮን ነሽ» እያሉ ይዘም
ራሉ።

## መዝሙር 88

1ቤዛዬና አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ ፥
ቀንና ሌሊት በፊትህ አለቅሳለሁ። 2ጸሎቴ
ከአንተ ዘንድ ይድረስ፤ጆሮህን ወደ ልመናዬ
አዘንብል።
3እነሆ ነፍሴ በመከራ ስለ ተጨነቀች
ሕይወቴ የሲኦልን ሥቃይ ለመቀበል ተቃር
ባለች። 4ወደ መቃብር ከወረዱት መካከል
እንደ አንዱ ተቈጠርሁ ፤ ጕልበቱ ተሟጦ
እንዳለቀ ሰው ሆንሁ። 5ሬሳቸው በመቃ
ብር የተጋደመውንና ከክብካቤህ ተለይተው
ለምን ጊዜውም የማታስባቸውን ሙታን
መሰልሁ።
6አዎን ፥ ድቅድቅ ጨለማ በዋጠውና
ጥልቀቱ መጨረሻ በሌለው አዘቅት ውስጥ
ጣልኸኝ። 7የመዓትህ ክብደት ተጫነኝ፤
የመቅሠፍትህ ማዕበል ሁለንተናዬን አጥለቀ
ለቀው። 8እጅግ ቅርቤ ከሆኑ ወዳጆቼ ለየ
ኸኝ ፤ እንዲጠየፉኝም አደረግህ ፤ መውጫ
መግቢያም አሳጣኸኝ። 9ዓይኖቼ ከመራራ
ልቅሶ የተነሣ ፈዘዙ።
እግዚአብሔር ሆይ ፤ በየቀኑ ወደ አንተ
እጣራለሁ ፥ እጆቼንም ወደ አንተ እዘረጋ
ለሁ። 10ድንቅ ሥራዎችህን ለሙታን ታሳያ
ለህን? የሞቱትስ ተነሥተው ያመሰግኑሃ
ልን? 11ፍቅርህ በመቃብር ላሉት፥ታማኝነ
ትህስ በዘላለም ጥፋት ውስጥ ለወደቁት ይነ
ገራልን? 12ተአምራትህስ በጨለማው
ስፍራ ይታወቃልን? ወይስ የጽድቅ ድርጊ
ቶችህ ሁሉም ነገር ተረስቶ በሚቀርበት
ዓለም ይታወሳሉን?
13እኔ ግን፥ጌታ ሆይ፥ «ድረስልኝ» ብዬ
ወደ አንተ እጮኻለሁ፤በማለዳ ጸሎቴን በፊ
ትህ አቀርባለሁ። 14አቤቱ ፥ ስለ ምን
«ወግድ» ብለህ ትተወኛለህ? ፊትህንስ
ከእኔ ለምን ትሰውራለህ? 15ከልጅነቴ
ጀምሬ በመከራ ስለ ተሠቃየሁ እነሆ
ልሞት ተቃርቤያለሁ። በሚያስደነግጠው
ቍጣህም ስለ ተሸበርኩ ተስፋ ከመቍረጥ
ደርሻለሁ። 16መዓትህ በላዬ አለፈ፤አስፈሪ
ግርማህ አንኮታኩቶ ጣለኝ። 17እነዚህ መከ

ራዎች ዕድሜዬን ሙሉ እንደ ውሃ ሙላት
ዙርያዬን ከበቡኝ፤አጥለቅልቀውም ዋጡኝ።
18 ጓደኞቼንና የምወዳቸውን ሁሉ ከእኔ ነጥ
ለህ ወሰድክብኝ፤የቅርብ ባልንጀራዬ ጨለማ
ብቻ ሆነ።

## መዝሙር 89

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ስለ ታላቁ ፍቅርህ
ለዘላለም እዘምርልሃለሁ ፤ ስለ እውነተኛ
አምላክነትህም ከአንደበቴ ከትውልድ ወደ
ትውልድ እያስረዳሁ ዝናህ እንዲታወቅ ሳደ
ርግ እኖራለሁ። 2 ፍቅርህ ለዘላለም ጸንቶ
የሚኖር፥ታማኝነትህም እንደ ሰማያት የማ
ይናወጥ መሆኑን በይፋ እናገራለሁ።
3 እግዚአብሔር ራሱ እንዲህ ብሏልና፦
«እኔ ከመረጥኩትና አገልጋዬ ከሆነው ከዳ
ዊት ጋር ቃል ኪዳን አድርጌአለሁ፤ለእር
ሱም እንዲህ ስል ምዬለታለሁ፦ 4 ‘የትው
ልድ ሐረግህን ለዘላለም እመሠርታለሁ፤
ዙፋንህም ለልጅ ልጅ እየተላለፈ ጸንቶ እን
ዲኖር አደርጋለሁ።’»
5 እግዚአብሔር ሆይ፥የሰማይ ሠራዊት
ተአምራትህንና ታማኝነትህን በቅዱሳን
ጉባኤ መካከል ያወድሳሉ። 6 በላይ በሰማይ
ከእግዚአብሔር ጋር ሊተካከል የሚችል
ከቶ ማን አለ? ከሰማይ ሠራዊት መካከልስ
እግዚአብሔርን የሚመስለው ማነው? 7 በቅ
ዱሳን ሸንጎ እግዚአብሔር አምላክ በታላቅ
ፍርሃት ይከበራል፤የእርሱ ግርማ ሞገስ በዙ
ርያው ካሉት ሁሉ ይበልጣል። 8 ኃያሉ
አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥አንተን የሚመ
ስልህ ማነው? ጌታ ሆይ፥አንተ ኃያል ነህ፤
ታማኝነትህን በሚያረጋግጡ ሥራዎችህ
ተከበሃል።
9 የውቅያኖሱን መናወጥ የምታዝ አንተ
ነህ፤ሞገዱ ሲነሣ ጸጥ ታደርገዋለህ። 10 ተሰ
ይፈው ከወደቁት መካከል ረዓብን እንደ
አንዱ አድርገህ አንኮታኮትከው፤ጠላቶችህን
በብርቱ ክንድህ በታተንካቸው። 11 ሰማያት
የአንተ ናቸው፤ምድርም የአንተ ናት፤ዓለም
ንና በውስጥዋ ያሉትን ሁሉ አንተ ፈጠ
ርህ። 12 ሰሜንና ደቡብን መሠረትህ፤ታቦርና
አርሞንኤም ስለ ስምህ ደስ ብሏቸው ይዘም
ራሉ። 13 ክንድህ ኃያል ነው፤እጅህ ብርቱ
ነው፤ቀኝ እጅህም በገናናነት የከበረ ነው።
14 ጽድቅና ፍትሕ የዙፋንህ መሠረቶች
ናቸው፤ፍቅርና እምነት በፊትህ ይሄዳሉ።
15 እግዚአብሔር ሆይ፥የአንተን ነገር በእል
ልታ መቀበልን ያወቁ፥በአንተም ብርሃን
መሄድን የለመዱ የተባረኩ ናቸው። 16 ዕድ
ሜያቸውን ሙሉ በስምህ እጅግ ደስ ይላቸ
ዋል፤በጽድቅህም ላቅ እያሉ ይሄዳሉ፤
17 ክብራቸውና ኃይላቸው አንተ ነህ። በሞ
ገስህ ሥልጣናችንን ከፍ ከፍ ታደርጋለህ።
18 በእርግጥ ጋሻችን የሆነው ንጉሣችን፥ለእ
ስራኤል ቅዱስ አምላክ ገንዘቡ ነው።
19 አንድ ጊዜ፥ለታመኑ ነቢያትህ በራእይ
እንዲህ ብለህ ተናገርክ፦ «ኃይሌን በአንድ
ጦረኛ ላይ አሳደርሁ፤ከሕዝቡ መካከል አን
ዱን ጐልማሳ ከፍ ከፍ አደረግሁ። 20 አገል
ጋዬን ዳዊትን አገኘሁ፤እርሱንም ቅዱሱን
ዘይት ቀባሁት። 21 እጄ አጽንቶ ይጠብቀ
ዋል፤ክንዴም ያጠነክረዋል። 22 በእርሱ ላይ
ገዢ ሆኖ የሚያስገብረው ጠላት ከቶ አይነ
ሣበትም፤ማንም ግፈኛ ሰው እርሱን ሊጨ
ቊነው አይችልም። 23 ጠላቶቹን በፊቱ
አጠፋለሁ ፤ ተቃዋሚዎቹንም እጥልለታ
ለሁ። 24 እውነተኛው ፍቅሬ ከእርሱ ጋር
ይሆናል፤ስለ ስሜም ሥልጣኑ እየገነነ ይሄ
ዳል። 25 እጁን በታላቁ ባሕር ላይ፥ቀኙንም
በኤፍራጥስ ወንዞች ላይ እንዲያኖር አደርገ
ዋለሁ። 26 ‘አንተ አባቴ፥አምላኬና ጽኑ
መድኅኔ ነህ’ ይለኛል። 27 እኔ ደግሞ፥
‘በምድር ላይ ካሉት ነገሥታት ይልቅ
እጅግ ገናና የምትሆን የበኵር ልጄ ነህ’
ብዬ ከፍተኛውን ሹመት እሰጠዋለሁ።
28 ለእርሱ ያለኝን ፍቅር ለዘላለም አጽንቼ
እጠብቃለሁ፤ከእርሱ ጋር ያደረግሁት ቃል
ኪዳን ምን ጊዜም አይሻርም። 29 የትው
ልድ ሐረጉን ለዘላለም እመሠርታለሁ፤ዙፋ
ኑም እንደ ሰማያት ጸንቶ ይኖራል።
30 «ልጆቹ ሕጌን ቢተዉ፥ሥርዓቴንም
ባይከተሉ፥ 31 ድንጋጌዎቼን ቢተላለፉና
ትእዛዞቼን ቢጥሉ፥ 32 ስለ ኃጢአታቸው
በበትር፥ስለ በደላቸውም በአለንጋ እየገረ
ፍኩ እቀጣቸዋለሁ። 33 ፍቅሬን ግን ከእ
ርሱ አላርቅም ፤ ታማኝነቴንም አልነፍገ
ውም፤ 34 ቃል ኪዳኔን አልሽርም፤የተናገር
ሁትን ቃሌን አላጥፍም። 35 አንድ ጊዜ በቅ
ድስናዬ ስለ ማልሁ፥ለዳዊት አልዋሸውም።
36 አዎን፥የትውልድ ሐረጉ ለዘላለም አይቋ
ረጥም፤ዙፋኑም በፊቴ እንደ ፀሐይ ጸንቶ
ይኖራል፤ 37 በጠፈር ላይ ታማኝ ምስክር
እንደ ሆነችው እንደ ጨረቃ ለዘላለም ጸንቶ
ይኖራል።»
38 ነገር ግን የቀባኸውን «ወግድ» ብለህ
ተውኸው፤ናቅኸው፤እጅግ አድርገህ ተቈጣ
ኸው። 39 ከአገልጋይህ ጋር የገባኸውን ቃል
ኪዳን ችል አልክ፤ዘውዱን በትቢያ ላይ
ጥለህ አረከስኸው። 40 ቅጥሩን ሁሉ ነዳድ

ለሀ ፥ ምሽጎቹንም አፈራርሰሀ ጣልከ።
41 አላፊ አግዳሚው ሁሉ ዘረፈው፤በጎረቤቶ
ቹም ዘንድ መዘባበቻ ሆነ። 42 የጠላቶቹን
ቀኝ እጅ አበረታሀ፤የሚጠሉት ሁሉ በደ
ስታ እንዲፈነድቁ አደረግሃቸው። 43 የሰይ
ፋን ስለት አደነዝከ፤በውጊያም ላይ አልደገ
ፍከውም። 44 ያሸበረቀ ክብሩን ነሣኸው፤
ዙፋኑን አሽቀንጥረሀ ከትቢያ ጋር ደባለቅ
ኸው። 45 የወጣትነት ዘመኑን አሳጠርከበት፤
የኀፍረትን ሽማ አከናነብከው።

46 እግዚአብሔር ሆይ ፥ እንዲህ የሚሆ
ነው እስከ መቼ ነው? ራስህን ለዘላለም
ሰውረሀ ልትቀር ነውን? መዓትህ እንደ
እሳት የሚነደው እስከ መቼ ነው? 47 የእኔ
ሕይወት አጭርና ፈጥና የምታልፍ መሆ
ኗን አስብ። በውኑ የሰውን ልጅ ሁሉ የፈጠ
ርከው ለከንቱ ነውን? 48 ለመሆኑ ፥ ሞትን
ሳያይ ሕያው ሆኖ መኖር፥ራሱንም ከመቃ
ብር ኃይል ማዳን የሚችል ከቶ ማን አለ?

49 እግዚአብሔር ሆይ፥በታማኝነትህ ለዳ
ዊት ቃል ኪዳን እንድትገባለት ያነሣሣሀ ያ
የቀድሞው ፍቅርሀ የታለ? 50 ጌታ ሆይ፥እኔ
አገልጋይሀ ማፌዣ እንደ ሆንኩና አሕዛብ
የሚያወርዱብኝን ሽሙጥ በልቤ ታግሼ
እንደ ተቀበልኩ አስብ። 51 አቤቱ ፥ አንተ
ቀብተሀ ያነገሥከው ንጉሥ በሚሠራው
ሥራ ላይ ጠላቶችሀ የሚያወርዱትን ሽሙ
ጥና ፌዝ አስታውስ።

52 እግዚአብሔር ለዘላለም የተመሰገነ
ይሁን።

አሜን! አሁንም አሜን!

# አራተኛ መጽሐፍ

ከመዝሙር 90-106

## መዝሙር 90

1 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ትውልድ አልፎ
ትውልድ በተተካባቸው ዘመናት ሁሉ
አንተ መጠጊያ ሆንከን። 2 ተራሮች ገዝፈው
ሳይታዩ ፥ ምድርንና መላውን ዓለም ሳትፈ
ጥር የነበርሀ፥መጀመሪያና መጨረሻ የሌለሀ
አንተ ዘላለማዊ አምላክ ነሀ።

3 «የሰው ልጆች ሆይ ፥ ወደ አፈር ተመ
ለሱ» እያልክ ሰዎችን ወደ መሬት ትመል
ሳቸዋለሀ። 4 በአንተ ዘንድ ሺህ ዓመት ትና
ንት እንዳለፈች አንዲት ቀን ፥ ወይም ነቅ
ተው እንዳደሩባት አንዲት ሌሊት ነው።
5 ሰዎችን ሞት እንደ እንቅልፍ አሸልቦ እን
ዲወስዳቸው ታደርጋለሀ። ሰዎች ሲባሉ
ፈልቶ እንደሚያድር ሣር ናቸው። 6 ሣሩ ፥
ሲነጋ ቱግ ብሎ በቅሎ ይታያል፤ሲመሽ
ጠውልጎና ደርቆ ይረግፋል።

7 አቤቱ፥በቍጣሀ ተቃጥለን፥በመዓትሀም
ተደናግጠን አለቅን። 8 የፈጸምነውን በደል
በፊትሀ አኖርሀ ፤ የተሰወረ ኃጢአታችንን
በብርሃንሀ እንዲታይ አደረግኸው። 9 በመቅ
ሠፍትሀ እየተሠቃየን መላ ዘመናችንን እና
ሳልፈዋለን፤ዕድሜያችንን በዋይታ እንጨርሰ
ዋለን። 10 ዕድሜያችን ሰባ ዓመት ነው፤ቢበ
ዛም ከሰማንያ አይበልጥም፤እርሱም በመከ
ራና በኀዘን የተመላ ስለ ሆነ ፈጥኖ ያል
ፋል፤እኛም እንዳልነበርን እንሆናለን።

11 የቍጣሀን ኃይል ማን ያውቀዋል?
መዓትሀ እንደሚያስፈራው ግርማሀ ታላቅ
ነው። 12 አቤቱ ፥ ዕድሜያችን አጭር መሆ
ኑን እንድንረዳ አድርገን ፤ ብልሀ ልቦናም
እንድናገኝ እርዳን።

13 እግዚአብሔር ሆይ፥እዘንልን፤የምትዘገ
የው እስከ መቼ ነው? አቤቱ፥ለእኛ ለአገል
ጋዮችሀ ራራልን። 14 በዘመናችን ሁሉ ደስ
ብሎን በእልልታ ስንዘምርልሀ እንኖር
ዘንድ ፥ በማይለወጠው ፍቅርሀ ቸርነትሀን
በማለዳ አሳየን። 15 መከራን ባመጣህብን
ዓመታት ፋንታ ፥ በተሠቃየንባቸው ዘመናት
መጠን ደስ እንዲለን አድርግ። 16 ሥራዎ
ችሀ ለእኛ ለአገልጋዮችሀ ፥ የሚያሸበርቀው
ክብርሀ ለልጆቻችን ይታዩ።

17 የፈጣሪያችን የእግዚአብሔር ሞገስ
ይደርብን። አቤቱ፥የእጆቻችንን ሥራ ባርከ
ልን፤አዎን፥የእጆቻችንን ሥራ አጽናልን።

## መዝሙር 91

1 ከሁሉ በላይ የሆነውንና ኃያሉን አም
ላክ መጠጊያው አድርጎ የሚኖር ሰው፥የሕ
ይወቱ ዋስትና የሚያስተማምን በመሆኑ ፥
2 «እግዚአብሔር መጠጊያዬና ምሽጌ ፥ የም
ተማመንበት ፈጣሪዬም ነው» ብሎ ይመሰ
ክራል።

3 አዎን ፥ አዳኝ ከሚዘረጋው ወጥመድና
ሰውን ከሚጨርስ ቸነፈር እግዚአብሔር
ያድንሃል። 4 በላባዎቹ ይሸፍንሃል፤ከክንፎቹ
በታች ከለላን ታገኛለሀ፤የእርሱ ታማኝነት
ጋሻና ምሽግ ሆኖ ይከላከልልሃል። 5 ሌሊት
የሚያስደነግጥ ነገር ፥ በቀን የሚወረወር
ፍላጻ፥ 6 በጨለማ እያደባ የሚጥል ቸነፈር፥
በቀትር እየወጋ የሚያጠፋ መቅሠፍትና
አደጋ ከቶ አያስፈራሀም። 7 በአንድ ጐንሀ
አንድ ሺህ ፥ በቀኝሀ በኩል ደግሞ እልፍ
ተጻራሪዎችሀ ይወድቃሉ ፤ አንተን ግን
ምንም ነገር አይነካህም። 8 አንተ ግን በክፉ

ዎች ላይ የሚወርደውን ቅጣት በዓይንህ
ታያለህ፤በማስተዋልም ትመለከታለህ።
9ከሁሉ በላይ የሆነውንና ለእኔ መጠጊያ
የሆነኝን አምላክ ከለላህ ያደረግኸው እንደ
ሆነ፥ 10ምንም ጉዳት አይነካህም፤በቤተሰ
ብህም ላይ አደጋ አይደርስም። 11በምትሄ
ድበት ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን
ያዛቸዋል፤ 12እነርሱም አቅፈው ደግፈው
በመያዝ እግርህ በድንጋይ እንዳይሰናከል
ይጠብቁሃል። 13በተኲላውና በእፉኝቱ ላይ
ትራመዳለህ፤ታላቁን አንበሳና ዘንዶ ትረግጠ
ዋለህ።
14እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ «ይወ
ደኛልና ከክፉ ነገር አድነዋለሁ፤ስሜን የሚ
ጠራውን እንደማድን አምኗልና እጠብቀዋ
ለሁ። 15ይጠራኛል፤እኔም እመልስለታለሁ፤
በመከራው ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ፤
ከክፉ ነገር እጠብቀዋለሁ፤አከብረዋለሁ።
16ረዥም ዕድሜ ሰጥቼ አስደስተዋለሁ፤ቤዛ
ነቱንም አሳየዋለሁ።»

## መዝሙር 92

1ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ መል
ካም ነው። ከሁሉ በላይ የሆንከ አምላክ
ሆይ፥ለስምህ በዜማ መሣሪያዎች መዘመር፥
2ስለ ፍቅርህ በማለዳ፥ስለ ታማኝነትህም
በሌሊት መመስከር፥ 3አሥር አውታር
ባለው በገናና ጣዕሙ በሚመስጥ መሰንቆ
መዘመር ተገቢ ነው።
4ጌታ ሆይ፥ባደረግኸው የቸርነት ሥራህ
አስደስተኸኛልና እነሆ፥በእጆችህ ሥራ
እልል እያልኩ እዘምራለሁ። 5አቤቱ፥
ሥራህ እንዴት ታላቅ ነው? አሳብህስ
ምንኛ ጥልቅ ነው! 6አእምሮ የሌለው ሰው
የማያስተውለው፥ አላዋቂዎችም የማይገነዘ
ቡት አንድ ነገር አለ፦ 7ይኸውም፥ግፈኞች
ለጊዜው እንደ ሣር ቱግ ብለው ቢበቅሉ፥
ክፉ አድራጊዎችም ለምልመው ቢታዩ፥
በመጨረሻ ለዘላለም መጥፋታቸውን ነው።
8እግዚአብሔር ሆይ፥አንተ ግን ለዘላለም
በገናናነትህ ጸንተህ ትኖራለህ። 9አዎን፥ጌታ
ሆይ፥ጠላቶችህ በእርግጥ ይጠፋሉ፤ክፉ አድ
ራጊዎች ሁሉ ይበተናሉ። 10ሥልጣኔን
እንደ ጎሽ ጉልበት አበረታህ፤በረከትህንም
እንደ ዘይት በላዬ አፈሰስክ። 11ዓይኖቼ የተ
ቃዋሚዎቼን መሸነፍ አዩ፤ጆሮዎቼም የጠ
ላቶቼን ጭንቀት ሰሙ።
12ጻድቃን እንደ ዘንባባ ዛፍ ለምልመው
ይንሰራፋሉ፤እንደ ሊባኖስ ዝግባም መለል
ብለው ያድጋሉ። 13በፈጣሪያችን መቅደስ
ውስጥ ስለ ተተከሉ አደባባዩን ያለብሳሉ።
14ዕድሜያቸው ቢረዝም ፍሬ ከመስጠት
አያቋርጡም፤ለጋነታቸውና ልምላሜያቸው
አይለወጥም። 15ይህም፥እግዚአብሔር ቅን
አምላክ፥ለሚጠጉት ጽኑ መጠጊያ መሆኑ
ንና በእርሱ ዘንድ ፈጽሞ ክፋት አለመኖ
ሩን ያረጋግጣል።

## መዝሙር 93

1እግዚአብሔር መንገሡን ገለጠ፤እነሆ፥
ግርማ ያለውን ልብስ መንግሥቱን ተጐናጽ
ፏል፤ኃይሉንም ታጥቋል። ዓለምን በጽኑ
እጁ ስለ መሠረታት ከቶ አትናወጥም።
2እግዚአብሔር ሆይ፥ ዙፋንህ ከጥንት
ጀምሮ ጸንቶ የሚኖር ነው፤አንተም መጀመ
ሪያና መጨረሻ የሌለህ ዘላለማዊ አምላክ
ነህ። 3አቤቱ፥ውቅያኖሶች ተንቀሳቀሱ፤ድም
ፃቸውንም ከፍ ከፍ አደረጉ፤በማዕበላቸው
ጩኸታቸውን አጒልተው አሰሙ። 4እንደ
ነጐድጓድ ከሚጮህ ከታላቅ ፏፏቴና ከባ
ሕር ሞገድ ይበልጥ በሰማይ የሚኖረው እግ
ዚአብሔር ኃያል ነው።
5አቤቱ፥ ሕጎችህ የጸኑ ናቸው፤ ፍጹሜ
ለሌለው ዘመን ቅድስና የቤትህ ጌጥ ሆኖ
ይኖራል።

## መዝሙር 94

1እግዚአብሔር ሆይ፥አንተ የበቀል አም
ላክ ነህ። የምትበቀል አምላክ ስለ ሆንክ
በብርሃንህ ተገለጥ። 2በምድር ላይ የምትፈ
ርድ ዳኛ ሆይ፥ተነሥ! ለትዕቢተኞች የሚገ
ባቸውን ቅጣት ስጣቸው። 3አቤቱ፥ግፈኞች
በሥራቸው ሲኰሩና ሲደነፉ የሚኖሩት
ከቶ እስከ መቼ ነው?
4ከአንደበታቸው የእብሪት ቃል ይጐር
ፋል፤ክፉ አድራጊዎች ሁሉ በትዕቢት ተወ
ጥረዋል። 5አቤቱ፥ሕዝብህን ሰጥ ለጥ አድር
ገው ገዙት፤የአንተ በሆኑትም ላይ የጭቈና
ቀንበራቸውን ጫኑባቸው። 6መበለቶችን፥
የሙት ልጆችንና ባይተዋሩን ይገድላሉ።
7«እግዚአብሔር አያየንም፤የያዕቆብ አም
ላክ ደንታ የለውም» ይላሉ።
8ከሕዝቡ መካከል እናንተ አእምሮ የሌ
ላችሁ ልብ አድርጉ። እናንተ አላዋቂዎች፥
ለመሆኑ መቼ ነው አስተዋዮች የምትሆ
ኑት? 9በውኑ ጆሮን የተከለ አይሰማምን?
ዓይንን የፈጠረስ አያይምን? 10አሕዛብን
እየገሠፀ በሥርዓት የሚገዛቸው አይቀጣ
ምን? የሰውን ልጅ የሚያስተምር እርሱ
ዕውቀት የለውምን? 11እግዚአብሔር የሰው

አሳብ ከንቱ መሆኑን ያውቃል።
12 እግዚአብሔር ሆይ ፣ አንተ እየቀጣሀ
በሥርዓት የምታኖረውና ሕግህን የምታስተ
ምረው ሰው የተባረከ ነው። 13 ግፈኞች
የሚቀበሩበት ጕድጓድ እስኪቈፈር ድረስ
በመከራ ዘመን ከክፉ ነገር ሰውረህ ታሳርፈ
ዋለህ። 14 እግዚአብሔር ሕዝቡን «ወግዱ»
ብሎ አይተዋቸውም ፤ የእርሱ የሆኑትን
እንደ ጣላቸው አይቀርም። 15 ፍርድ በጽ
ድቅ መሠረት ላይ እንደ ገና የምትቆምበት
ጊዜ ይመጣል፤በልቦናቸው ቅን የሆኑ ሁሉ
ይከተሏታል።
16 ግፈኞችን ለመቃወም የሚነሣልኝ
ማነው? ክፉ አድራጊዎችን ለመከራከር
የሚቆምልኝስ ማነው? 17 እግዚአብሔር
ባይረዳኝ ኖሮ በሞት ዝምታ ተውጬ በቀ
ረሁ ነበር። 18 እግዚአብሔር ሆይ ፣ «እግ
ሬን አዳለጠኝ» ባልሁ ጊዜ ፍቅርህ ደገ
ፈኝ። 19 ከፍተኛ ሥጋት በተሰማኝ ጊዜ የአ
ንተ ማጽናናት ለነፍሴ ደስታን አጐናጸ
ፉት።
20 በአዋጅ በሚያወጣቸው ድንጋጌዎች
በሕዝቡ ላይ ሥቃይ የሚያደርስ ግፈኛ
መንግሥት ከአንተ ጋር ኅብረት ሊኖረው
ይችላልን? 21 ክፉዎች ወገን ለይተው በጻድ
ቃን ላይ ይነሣሉ፤ንጹሑን ይሙት ብለው
ይፈርዱበታል። 22 እግዚአብሔር ግን ለእኔ
ምሽጌ ሆነልኝ፤ መጠጊያ አግኝቼ የምድን
በት ምሽጌ አምላኬ ነው። 23 እርሱ ለግፈ
ኞች ከኃጢአታቸው የተነሣ የሚገባቸውን
ፍዳ ይከፍላቸዋል፤ስለ ክፋታቸውም ያጠፋ
ቸዋል። አዎን ፣ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር
ያጠፋቸዋል።

## መዝሙር 95

1 ኑ ፣ ለእግዚአብሔር በደስታ እንዘምር፤
የደኅንነታችን ዓለት ለሆነው አምላክ እልል
እንበል። 2 የምስጋና በረከት ይዘን ከፊቱ
እንቅረብ፤በዜማ መሣሪያዎች ታጅበን በዝ
ማሬ እናወድሰው። 3 እግዚአብሔር ከአማል
ክት ሁሉ በላይ የሆነ ታላቅ አምላክና ገናና
ንጉሥ ነው። 4 የምድር ጥልቅ መሠረቶች
በእጁ ውስጥ ናቸው፤የተራራ ጫፎችም የእ
ርሱ ናቸው። 5 ባሕርን እርሱ ፈጥሮታልና
የእርሱ ነው፤የብሱንም በእጆቹ ሠርቶታል።
6 ኑ ፣ ለእርሱ እየሰገድን እናምልከው፤በፈ
ጣሪያችን በእግዚአብሔር ፊት እንንበርከ
ከክ። 7 እርሱ አምላካችን ነው፤እኛም በለ
መለመ መስኩ ያሰማራን ሕዝቦቹ ፣ በእርሱ
እረኝነት የምንጠበቅ መንጎቹ ነን።
እናንተም ዛሬ ድምፁን ስትሰሙ ፣ 8 አባ
ቶቻችሁ በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ መሪባ
በተባለው የክርክር ውሃ፣ማሣህ በተባለውም
የፈተና ስፍራ እንዳደረጉት ሁሉ ልባችሁን
አታደንድኑ። 9 እነርሱ አስቀድሜ ያደረግሁ
ትን ሁሉ ያዩ ሆነው ሳሉ በዚያ በረሃ ፈተ
ኑኝ፤ ተፈታተኑኝ። 10 እኔም በዚያች ትው
ልድ ላይ ቍጣዬን ለአርባ ዓመታት አጸ
ናሁ። «ይህ ሕዝብ ልቡ ወደ ስሕተት የሚ
ያዘነብል ነው ፤ የእኔንም መንገድ አላወ
ቁም» አልሁ። 11 ስለዚህ በቍጣዬ ሳለሁ
እንዲህ ብዬ ማልሁ፦ «ያዘጋጀሁላቸውን
ዕረፍት ወደሚያገኙባት ምድር ፈጽሞ አይ
ገቡም።»

## መዝሙር 96

1 አዲስ ቅኔ እየተቀኛችሁ እግዚአብሔ
ርን በዝማሬ አመስግኑት፤በምድር ያላችሁ
ሁሉ ፣ ለእግዚአብሔር ዘምሩ። 2 ለእግዚአብ
ሔር የምስጋና መዝሙር አቅርቡ፤ ስሙን
በዝማሬ አወድሱ፤ቤዛ ሆኖ የሚያድን ስለ
መሆኑ ፣ ከዕለት ወደ ዕለት ሳታሰልሱ መስ
ክሩ። 3 ገናና ክብሩን ለአሕዛብ፣ድንቅ ተአ
ምራቱን ለሕዝቦች በገሃድ ተናገሩ። 4 እግዚ
አብሔር ታላቅና ብቻውን ምስጋና ሊቀርብ
ለት የሚገባው፣ከአማልክት ሁሉ በላይ የመ
ፈራት ግርማ ያለው አምላክ ነው። 5 የአሕ
ዛብ አማልክት ሁሉ ጣዖታት ናቸው፤እግዚ
አብሔር ግን ሰማያትን የፈጠረ አምላክ
ነው። 6 ክብርና ግርማ ሞገስ ከፊቱ ያንጸባር
ቃል ፤ ኃይልና ገናናነት ከመቅደሱ ይፈል
ቃል።
7 የአሕዛብ ወገኖች ሁሉ ፣ ለእግዚአብ
ሔር የሚገባውን አድርጉ፤ክብርና ምስጋና፣
ኃይልም የእግዚአብሔር ነው በሉ። 8 ለእግ
ዚአብሔር ስም የሚገባውን ክብርና ምስ
ጋና ስጡ ፤ ቍርባን ይዛችሁ ለአምልኮት
ወደ አደባባዩ ግቡ። 9 በቅድስናው ክብር
ላሸበረቀው ለእግዚአብሔር ስገዱለት ፤
መላዋ ምድርም በፊቱ ትንቀጥቀጥ።
10 «እግዚአብሔር ንጉሥ ነው» እያላ
ችሁ በአሕዛብ መካከል ለፍፉ። ዓለምን
አጽንቶ መሥርቷታልና አትናወጥም።
እርሱ ለሕዝቦች ትክክለኛ ፍርድ ይሰጣ
ልና። 11 ሰማያት ደስ ይበላቸው፤ምድርም
ሐሤት ታድርግ፤ውቅያኖሱ ይናወጥ፤በው
ስጡ ያለው ሁሉ ድምፁን ያሰማ፤ 12 ሜዳ
ውና በላዩ ያለው ማናቸውም ፍጥረት በደ
ስታ ይፈንድቅ። በዚያን ጊዜ በዱር የሚገ
ኙት ዛፎች ሁሉ ደስ ብሏቸው ይዘምራሉ፤

13 አዎን፥በእግዚአብሔር ፊት ይዘምራሉ።
እርሱ ይመጣል፤በምድር ላይ ፍርዱን ለመ
ስጠት ይመጣል። በዓለም ላይ በጽድቅ፥በሕ
ዝቦችም ላይ በእውነት ይፈርዳል።

## መዝሙር 97

1 እግዚአብሔር በመንገሡ በምድር ላይ
ያሉ ሁሉ ሐሤትን ያድርጉ፤ሩቅ ብለው
በሚገኙ ደሴቶች ላይ የሚኖሩ ሁሉ ደስ
ይበላቸው።
2 ደመናና ጭጋግ ከበውታል፤ጽድቅና
ፍትሕ የዙፋኑ መሠረት ናቸው። 3 እሳት
ከፊት ፊቱ ይሄዳል፤በዙርያው ያሉትንም
ጠላቶቹን አቃጥሎ ያጠፋል። 4 መብረቁ
ለዓለም በአንድ ጊዜ ያበራል፤ ምድርም
ይህን አይታ ትንቀጠቀጣለች። 5 የመላዋ
ምድር ጌታ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት
ተራሮች እንደ ሰም ይቀልጣሉ። 6 ሰማያት
ጽድቁን ያውጃሉ፤ ሕዝቦች ሁሉ የክብሩን
ገናናነት ያያሉ።
7 ለተቀረጸ ምስል የሚሰግዱ ፥ በጣዖት
የሚመኩ ሁሉ ያፍራሉ። አማልክት ሁሉ
ለእግዚአብሔር ስገዱለት።
8 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ጽዮን ፍርድህን
ሰማች፤እጅግም ደስ አላት፤የይሁዳ ከተሞች
ሐሤት አደረጉ። 9 ጌታ ሆይ ፥ በመላዋ
ምድር አንተ ልዑል ነህ፤አንተ ከአማልክት
በላይ ገናና ነህ።
10 እግዚአብሔርን የሚወዱ ሁሉ ክፉ
ትን ይጥሉ፤በእርሱ የሚተማመኑትን ሕይ
ወት እርሱ ይጠብቃልና፤ ከግፈኛም እጅ
ያስጥላቸዋል። 11 በጻድቃን ላይ ብርሃን
ይወርዳል፤ ልበ ቅኖች በደስታ ይሞላሉ።
12 ጻድቃን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ፤
ቅዱስ ስሙንም አወድሱ።

## መዝሙር 98

1 ለእግዚአብሔር አዲስ ቅኔ እየተቀኛ
ችሁ በዝማሬ አመስግኑት። እርሱ ድንቅ
ነገሮችን አድርጓልና፤ ቀኝ እጁ ፥ የተቀደሰ
ክንዱም የቤዛነት ሥራዎችን አከናውኗ
ልና። 2 እግዚአብሔር ቤዛ ሆኖ የማዳኑ
ነገር እንዲታወቅ አደረገ፤ጽድቁንም ለአሕ
ዛብ ገለጠ። 3 ለእስራኤል ዘር ያለውን ፍቅ
ርና ታማኝነት አስታወሰ፤ በምድር ላይ
ከዳር እስከ ዳር የሚኖር ፍጥረት ሁሉ የእ
ግዚአብሔር የአምላካችንን ቤዛነት አየ።
4 በምድር የምትኖሩ ሁሉ፥ደስ ብሏችሁ
ለእግዚአብሔር እልል በሉ፤በዜማ መሣሪያ
ዎች እየታጀባችሁ በከፍተኛ ድምፅ ዘምሩ፤
5 በገና እየደረደራችሁ ለእግዚአብሔር
ዘምሩ፤ 6 በእንቢልታና በመለከት ድምፅ እየ
ታጀባችሁ በንጉሡ በእግዚአብሔር ፊት
በደስታ እልል በሉ።
7 ውቅያኖሱና በውስጡ ያለው ማናቸ
ውም ነገር፥ዓለምና በእርሱ የሚኖረው ፍጥ
ረት ሁሉ የደስታ ድምፁን ያስተጋባ።
8 ወንዞች ያጨብጭቡ፤ ተራሮችም በአንድ
ነት ሆነው በደስታ ይዘምሩ፤ 9 እግዚአብ
ሔር በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣል።
እርሱ ዓለምን በጽድቅ ይዳኛታል፤ ለሕዝ
ቡም ትክክለኛ ፍርድ ይሰጣል።

## መዝሙር 99

1 እግዚአብሔር በመንገሡ አሕዛብ ይን
ቀጥቀጡ። ኪሩቤል በተሸከሙት ዙፋኑ
ላይ ተቀምጧልና ምድር ትናወጥ። 2 እግዚ
አብሔር በጽዮን ታላቅ ነው፤በአሕዛብም
ሁሉ ላይ ገናና ነው። 3 «ቅዱስ ነው»
እያሉ ታላቅና ግሩም ስምህን ሁሉም ያወ
ድሱ።
4 እግዚአብሔር በንጉሥነቱ ኃያል ነው፤
እርሱ ትክክለኛ ዳኝነትን ይወዳል። አቤቱ፥
አንተ እውነተኛን ፍርድ መሠረትህ፤ትክክ
ልና ቅን የሆነውን ነገር ለያዕቆብ ዘር አደረ
ግህ። 5 አምላካችን እግዚአብሔርን “ገናና
ነህ” በሉት፤ቅዱስ ነውና ከእግሩ መረገጫ
ሥር እየወደቃችሁ ስገዱለት።
6 ሙሴና አሮን ካህናቱ ነበሩ፤ሳሙኤል
ስሙን ከጠሩት መካከል አንዱ ነበር።
ሁሉም እግዚአብሔርን ጠሩት፤ እርሱም
መለሰላቸው፤ 7 በደመና ዓምድ ተናገራ
ቸው፤እነርሱም የሰጣቸውን ሕግና ትእዛዝ
ጠበቁ።
8 ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሆይ፥እነርሱ
ሲጠሩህ መለስክላቸው፤በጥፋታቸው ብትቀ
ጣቸውም አንተ ለእስራኤል ሕዝብ ይቅር
ባይ አምላክ ነበርክ።
9 እግዚአብሔር አምላካችንን ፥ “ገናና
ነህ” በሉት ፤ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር
ቅዱስ ነውና በተቀደሰ ተራራው ላይ አም
ልኩት።

## መዝሙር 100

1 በምድር ያላችሁ ሁሉ፥ለእግዚአብሔር
በደስታ እልል በሉ። 2 እግዚአብሔርን
በሙሉ ልብ አገልግሉት፤የሚያስደስት ዜማ
እያሰማችሁ እፊቱ ቅረቡ።
3 እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ መሆ
ኑን ዕወቁ። የፈጠረን እርሱ ነው፤እኛም

የእርሱ ነን። አዎን፥እኛ ሕዝቦቹ፥በለመ
ለመ መስኩ የሚያሰማራን በጎቹ ነን።
4 የምስጋና በረከት ይዛችሁ፥ዝማሬም
እያሰማችሁ ወደ መቅደሱ አደባባዮች ግቡ፤
በዚያም ለእርሱ ምስጋና፥ለስሙም ዝማሬ
አቅርቡ። 5 እግዚአብሔር ቸር ነው፤ፍቅሩ
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤ታማኝነቱም ከት
ውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል።

## መዝሙር 101

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ስለ ፍቅርህና ስለ
ፍርድህ እዘምራለሁ፤አዎን፥በዜማ አወድስሃ
ለሁ። 2 ነውር የሌለበት ሕይወት ለመኖር
እጥራለሁ። አቤቱ፥ወደ እኔ የምትመጣው
መቼ ነው? በቤቴ ውስጥ በንጹሕ ሕሊና
እኖራለሁ። 3 ለክፉ ነገር አልበገርም።
እምነት የሌላቸውን ሰዎች አድራጎት
እጸየፋለሁ፤እነርሱም ወደ እኔ አይጠጉም።
4 ልበ ጠማማ የሆኑ ከእኔ ይርቃሉ፤ከክፋት
ጋር አግባብ አይኖረኝም። 5 ባልንጀራውን
ሲያማ የማገኘውን ዝም አሰኘዋለሁ፤ሌላ
ውን ሰው በንቀት የሚመለከተውንና ትዕቢ
ተኛ ልቡና ያለውን ልታገሠው አልችልም።
6 በአገሬቱ ውስጥ እምነት ያላቸውን
ሰዎች ዓይኖቼ ይጠብቃሉ፤እነርሱም ከእኔ
ጋር ይኖራሉ። በኑሮው ነውር የሌለበት
ሰው አገልጋዬ ይሆናል፤ 7 ሸንገላን የሚያዘ
ወትር በቤቴ አይኖርም፤ሐሰት የሚናገርም
እኔ ባለሁበት አይቆምም። 8 በአገሬቱ ውስጥ
ያሉትን ወንጀለኞች ሁሉ በየዕለቱ አጠፋቸ
ዋለሁ፤ማንኛውንም ክፉ አድራጊ ከእግዚአ
ብሔር ከተማ አስወጣዋለሁ።

## መዝሙር 102

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ጸሎቴን ስማ፤
«ድረስልኝ» ብዬ የማሰማው ጩኸቴ በአ
ንተ ዘንድ ተደማጭነትን ያግኝ። 2 በመከ
ራዬ ጊዜ ፊትህን ከእኔ አትሰውር። ጆሮህን
ወደ እኔ አዘንብል፤ስጠራህ ፈጥነህ መልስ
ልኝ።
3 ዕድሜዬ እንደ ጢስ ተኖ አለቀ፤አጥን
ቶቼ እንደ ፍም ነደዱ። 4 ልቤ እንደ ጠወ
ለገ ሣር ሆነ፤ምግብ መብላት እንኳ ተሳ
ነኝ። 5 ከሥቃዬ ጽናት የተነሣ ስለማቃስት
ሰውነቴ አልቆ ቆዳዬና አጥንቴ ብቻ ቀረ።
6 በምድረ በዳ እንደሚንከራተት አሞራና
በፈራረሱ ቤቶች መካከል እንደሚኖር
ጉጉት ሆንሁ። 7 ያለእንቅልፍ አድራለሁ፤
ከጣራ ጫፍ ላይ እንደ ተቀመጠች ብቸኛ
ወፍ ሆንሁ። 8 ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ ሲዘል
ፉኝ ይውላሉ፤በእኔ የሚያምርሩ ሁሉ
ስሜን መራገሚያ አደረጉት። 9 አመዱን
እንደ እህል ቃምሁት፤መጠጡን ከእንባዬ
ጋር ደባልቄ ጠጣሁት። 10 ከታላቁ ቊጣህ
የተነሣ ብድግ አድርገህ ጥለኸኛል። 11 ዕድ
ሜዬ እንደ ጥላ ያልፋል፤እንደ ሣር ጠው
ልጌ እረግፋለሁ።
12 እግዚአብሔር ሆይ፥አንተ በዙፋንህ
ላይ ለዘላለም ትቀመጣለህ፤ዝናህም ከትው
ልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል። 13 ተነሥ
ተህ ጽዮንን በርኅራኄ ዓይን ትመለከታታ
ለህ፤ለእርሷ ሞገስን የምታሳይበት ጊዜው
አሁን ነው፤የወሰንከው ዘመን ደርሷል።
14 ድንጋዮቿ በአገልጋዮችህ ዘንድ የተወ
ደዱ ናቸው፤ትቢያዋ እንኳ ያሳሳቸዋል።
15 አሕዛብ፥የእግዚአብሔር ስም ሲጠራ ይፈ
ራሉ፤አዎን፥የምድር ነገሥታት ሁሉ ለገናና
ነትህ አክብሮታቸውን ይሰጣሉ። 16 እግዚአ
ብሔር ጽዮንን እንደ ገና ይሠራታል፤ገናና
ክብሩም ይገለጻል። 17 ለችግረኞች ጸሎት
መልስ ይሰጣል፤ልመናቸውን አይንቅም።
18 ገና ያልተፈጠረ ሕዝብ እግዚአብሔ
ርን ያመሰግን ዘንድ ይህ ቃል ለሚመጣው
ትውልድ ይጻፍ፦ 19 «እግዚአብሔር ከላይ
ካለው መቅደሱ ወደ ታች ተመለከተ፤በሰማ
ያት ሆኖ ምድርን አየ፤ 20 የእስረኞችን
ጩኸት ይሰማ ዘንድ፥ይሙት በቃ የተፈረደ
ባቸውንም ነጻ ይለቅ ዘንድ።» 21 የእግዚአብ
ሔር ስም በጽዮን፥ምስጋናውም በኢየሩሳ
ሌም ይታወጃል፤ 22 ሕዝቦችና መንግሥታት
እግዚአብሔርን በጉባኤ ለማምለክ ይሰበሰ
ባሉ።
23 ገና ሳላረጅ ጉልበቴ እንዲደክም አደ
ረገ፤ዕድሜዬን አሳጠረ። 24 በዚህ ጊዜ እን
ዲህ አልሁ፦ «ፈጣሪዬ ሆይ፥በዕድሜዬ
እኩሌታ አትውሰደኝ፤አንተ ለዘላለም ነዋሪ
ነህ። 25 በመጀመሪያ የምድርን መሠረት
አኖርህ፤ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው።
26 እነርሱ ይጠፋሉ፤አንተ ግን ጸንተህ ትኖ
ራለህ። ሁሉም እንደ ሸማ ያረጃሉ፤አሮጌው
ልብስ ተጥሎ አዲስ እንደሚቀየር፥ወዲያ
ትጥላቸዋለህ። 27 አንተ ግን መቼም መች
አትለወጥም፤ዓመታትህ ፍጻሜ የላቸውም።
28 ያገልጋዮችህ ልጆች አንተ ባለህበት ይኖ
ራሉ፤ዘሮቻቸው ከፊትህ አይለዩም።

## መዝሙር 103

1 ነፍሴ ሆይ፥እግዚአብሔርን አመስግኚ፤
የውስጥ ሕዋሳቶቼ ሁሉ ቅዱስ ስሙን አወ
ድሱ። 2 ነፍሴ ሆይ፥እግዚአብሔርን አመስ

ይሰማራል፤ተግባሩንም እስከ ምሽቱ ድረስ
ሲያከናውን ይውላል።
24 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ሥራህ ምንኛ
ብዙ ነው! ሁሉን በጥበብ አደረግህ፤ምድር
በፍጡራንህ የተሞላች ናት። 25 እነሆ፥ውቅ
ያኖስ በምላትና በስፋት ተንጣሎ ይታያል፤
በውስጡም ስፍር ቍጥር የሌላቸውን ታላላ
ቅና ታናናሽ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት ይዟል።
26 በላዩ መርከቦች ወዲያና ወዲህ ይጓዛሉ፤
በውስጡም አንተ የፈጠርከው ታላቁ ዓሣ
ነባሪ ይምቦጫረቃል።
27 እነዚህ ሁሉ፥ምግባቸውን በየጊዜያቱ
ትሰጣቸው ዘንድ ወደ አንተ በተስፋ ይመለ
ከታሉ። 28 የምትሰጣቸውንም ሰብስበው
ያከማቻሉ፤እጅህን በምትዘረጋበት ጊዜ ከአ
ንተ በሚያገኙት መልካም ነገር ይጠግባሉ።
29 ፊትህን ስትሰውርባቸው ግን ይደናገ
ጣሉ ፤ እስትንፋሳቸውን ስትነሣቸው ይሞ
ታሉ፤ወደ አፈርም ይመለሳሉ። 30 መንፈስ
ህን በምትልክበት ጊዜ ይፈጠራሉ። እንዲህ
እያደረግህ የምድርን ገጽ ታድሳለህ።
31 የእግዚአብሔር ገናናነት ለዘላለም
ይኑር ፤ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ደስ ይበ
ለው። 32 እግዚአብሔር ምድርን ይመለከ
ታል ፤ እርሷም ትንቀጠቀጣለች ፤ ተራሮችን
ይዳስሳል፤እነርሱም ይጨሳሉ።
33 ዕድሜዬን ሙሉ ለእግዚአብሔር እየ
ተቀኘሁ እዘምራለሁ ፤ በሕይወት እስካለሁ
ድረስ ለፈጣሪዬ የምስጋና መዝሙር አሰማ
ለሁ። 34 መዝሙሬና ምስጋናዬ የሚያስደስ
ተው ይሁን፤እርሱ የደስታዬ ሁሉ ምንጭ
ነው። 35 ኃጢአተኞች ግን ከምድር ይጥፉ፤
ክፉዎችም ከሕይወት ይወገዱ።
ነፍሴ ሆይ፥እግዚአብሔርን አመስግኚ።
ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 105

1 ሃሌ ሉያ!
ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቅርቡ ፤
ስሙን ጥሩ ፤ ያደረገውንም በአሕዛብ መካ
ከል ተናገሩ። 2 ለእርሱ ዘምሩ፤በዝማሬ ምስ
ጋና አቅርቡለት፤የፈጸማቸውን ድንቅ ሥራ
ዎቹን ሁሉ አስታውቁ። 3 ቅዱስ ስሙን
በመጥራታችሁ ታላቅ ክብር ይሰማችሁ፤እግ
ዚአብሔርን የምትሹ ሁሉ፥ደስ ይበላችሁ።
4 ወደ እግዚአብሔርና ወደ ኃይሉ ተመል
ከቱ፤ዘወትር ፊቱን ለማየት ፈልጉ። 5 ያደረ
ጋቸውን ድንቅ ሥራዎችና ተአምራቱን ፥
በይፋ የሰጣቸውንም ፍርዶች አስታውሱ ፤
6 እናንት የአገልጋዩ የአብርሃም ዘሮች ፥
እርሱ የመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች ሆይ ፥
ይህን አትርሱ።
7 እርሱ እግዚአብሔር አምላካችን ነው፤
ፍርዱም በመላዋ ምድር ላይ የሰፈነ ነው።
8 ቃል ኪዳኑን ለዘላለም፥የትእዛዙንም ቃል
ለሺህ ትውልዶች ያስባል። 9 ከአብርሃም
ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳንና ለይስሐቅ የማ
ለውን መሐላ፥ 10 ለያዕቆብም ሕግ አድርጎ
ያጸናውን ፥ ለእስራኤል የሰጠውን የዘላለም
ቃል ኪዳን አይዘነጋም። 11 «ርስት አድር
ገህ የምትካፈለው ድርሻህ ይሆን ዘንድ የከነ
ዓንን ምድር እሰጥሃለሁ» ብሏል።
12 ይህም የሆነው፥ስደተኞች ሳሉ፥ቍጥ
ራቸውም ጥቂት ፥ በእርግጥ ጥቂት ሳለ
ነበር። 13 በዚያን ጊዜ ከሕዝብ ወደ ሕዝብ፥
ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላው ይንከራተቱ
ነበር። 14 ከእነዚህ አንዳቸውም ግፍ እንዲ
ፈጽሙባቸው አላደረገም ፤ እነርሱን ለመጠ
በቅ ሲል ነገሥታትን ገሠፀ። 15 እንዲህም
አለ፡- «የቀባኋቸውን አትንኩ ፤ ነቢያቴንም
አትጕዱ።»
16 ግን በምድራቸው ላይ ረሃብን
አመጣ ፤ የምግብ ክምችታቸውንም አጠፋ።
17 ከእነርሱ ቀደም አድርጎ አንድ ሰው ላከ፤
እርሱም እንደ ባሪያ የተሸጠው ዮሴፍ
ነበረ። 18 እዚያም እግሮቹ እስኪላላጡ
ድረስ በእግር ብረት ታሠረ፤በአንገቱም የብ
ረት ማነቆ አገቡበት። 19 ይህም ሁሉ የደረ
ሰበት የተናገረው እስኪፈጸምና የእርሱም
እውነተኛነት በእግዚአብሔር ቃል እስኪረ
ጋገጥ ድረስ ነበር። 20 በዚያን ጊዜ ንጉሡ
ልኮ አስፈታው ፤ ነጻነቱንም አጐናጸፈው።
21 የቤተ መንግሥቱ አስተዳዳሪ፥በንብረቱም
ሁሉ ላይ አዛዥ አድርጎ ሾመው፤ 22 መሳፍ
ንቱን እንደ ፈቃዱ ይመራቸው ዘንድ፥ለአ
ማካሪዎቹም ጥበብን ያስተምራቸው ዘንድ
ሥልጣንን ሰጠው።
23 ከዚያም እስራኤል፥እርሱም ያዕቆብ፥
ተወላጆቹን በሙሉ ይዞ ወደ ግብጽ ገባ፤
በካም አገር ስደተኛ ሆኖ ኖረ። 24 እግዚአ
ብሔር ሕዝቡን እንዲበዙ ባረካቸው፤በሚቃ
ወሟቸው ዘንድ ቍጥራቸው ከመጠን
አልፎ እንዲታይ አደረገ። 25 እነዚህን የእር
ሱን ሕዝብ ፥ ተቃዋሚዎቻቸው እንዲጠሏ
ቸው ፥ በአገልጋዮቹም ላይ ሤራን እንዲጠነ
ስሱ አደረጋቸው። 26 አገልጋዩን ሙሴን ፥
የመረጠውንም አሮንን አስነሣ። 27 እነር
ሱም ተአምራታዊ ምልክቶቹን በመካከላ
ቸው፥ድንቅ ሥራዎቹን በካም አገር አሳዩ።
28 እግዚአብሔር ጨለማን ሰደደ፤አገሪቱም

በጨለማ እንድትዋጥ አደረገ። ግብጻውያን
ግን ትእዛዙን ላለመቀበል ወሰኑ። 29 ስለዚህ
ውሃቻቸውን ወደ ደም ለወጠባቸው፤ዓሦቻቸ
ውም ሁሉ ሞቱ። 30 ምድራቸውን በእንቍ
ራሪት ሞላው፤እስከ ገገርዎቻቸው መኝታ
ቤት ድረስ ዘልቆ ገባ። 31 ዳግመኛ ሲናገር፥
የዝንብ መንጋ መጣ፤የእሳት እራትም መላ
ውን አገር ወረረው። 32 ዝናባቸውን ከበረ
ዶና ከመብረቅ ጋር ቀላቅሎ በምድራቸው
ላይ አወረደው። 33 የወይን አትክልታቸው
ንና የፍሬ ዛፎቻቸውን ከፋኛ መታባቸው፤
በአገራቸው ያለውን ደን ሁሉ አጠፋ።
34 እንደ ገና ሲናገር፥አንበጣና ስፍር ቍጥር
የሌለው ኵብኵባ መጣ፤ 35 በምድራቸው
ላይ የበቀለውን ማንኛውንም የለመለመ ነገ
ርና መሬታቸው ያፈራውን ሰብል ሁሉ
ሙጥጥ አድርጎ በላው። 36 ከዚያም በአገራ
ቸው የተወለደውን በኵር ሁሉ ቀሠፈ፤የጉ
ብዝናቸው ፍሬ የሆነውን ሁሉ ገደለ።
37 የእስራኤልን ሕዝብ ግን በወርቅና
በብር ሀብት አበልጽጎ አወጣቸው፤ከወገኖቻ
ቸው መካከል አንድም በሕመምና በድካም
የተጐዳ አልነበረም። 38 እስራኤላውያን፥
ግብጻውያንን እጅግ አስደንግጠዋቸው ነበ
ርና፥አገራቸውን ለቀውላቸው በመሄዳቸው
ደስ አላቸው። 39 የእስራኤልን ሕዝብ ይከ
ልል ዘንድ ደመናውን ዘረጋ፤በሌሊትም ያበ
ራላቸው ዘንድ የእሳት ዓምድ አቆመላ
ቸው። 40 ሕዝቡ በጠየቁት ጊዜ ድርጭት
አቀረበላቸው፤የሰማይ እንጀራም አውርዶ
አጠገባቸው። 41 ዐለቱን ሰንጠቀ፤ውሃም
ዠረር ብሎ ፈለቀላቸው፤በዚያ በረሃ ውስጥ
እንደ ወንዝ ፈሰሰላቸው። 42 እርሱ ለአገል
ጋዩ ለአብርሃም የሰጠውን ቅዱስ ቃል
ኪዳን አስታወሰ። 43 የእርሱ የሆነውን
ሕዝብ በታላቅ ደስታ፥ለእርሱ የተመረጡ
ትን ሁሉ በእልልታ እንዲወጡ አድርጓቸ
ዋል። 44 የአሕዛብን አገሮች ሰጣቸው፤
ሌሎች የደከሙበትን እነርሱ ለመውረስ
በቁ፤ 45 ትእዛዛቱን ይጠብቁ፥ሕጉንም ይፈ
ጽሙ ዘንድ ይህን አደረገ።

ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 106

1 ሃሌ ሉያ!
እግዚአብሔር ቸር ነውና ምስጋና አቅር
ቡለት፤ፍቅሩ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
2 እግዚአብሔር በኀያልነቱ ያደረጋቸውን
ሥራዎች በይፋ መናገር፥ምስጋናውንስ
አሟልቶ መግለጽ የሚቻለው ማነው? 3 ትክ
ክለኛ ዳኝነት እንዳይዛነፍ የሚጥሩና ቀና
የሆነውን ከመሥራት የማይቦዝኑ የተባረኩ
ናቸው።
4 እግዚአብሔር ሆይ፥ሕዝብህ በፊትህ
ሞገስን ሲያገኙ እኔንም አስበኝ፤በምታድና
ቸው ጊዜ ለእኔም ድረስልኝ፤ 5 በዚያን ጊዜ
አንተ ለመረጥካቸው ያዘጋጀህላቸውን
ተድላ አገኛለሁ፤የሕዝብህን ደስታ እካፈላ
ለሁ፤ለአንተ የሚገባውን ውዳሴ በሚያቀር
ቡበትም ጊዜ አብሬአቸው ምስጋና አቀርባ
ለሁ።
6 አቤቱ፥አባቶቻችን እንዳደረጉት እኛም
ኃጢአት ሠራን፤አጠፋን፤የከፋት ድርጊቶ
ችን ፈጸምን። 7 አባቶቻችን በግብጽ ሳሉ
ያሳየሃቸውን የተአምራትህን ነገር አላስታወ
ሱም፤ያደረግህላቸውን እያሌ የቸርነት ሥራ
ዎች አላሰቡም። ገና ከኤርትራ ባሕር ሳይ
ርቁ አመፁብህ። 8 አንተ ግን ስለ ስምህ
ስትል ኀያል የሆነውን ሥልጣንህን ትገልጽ
ዘንድ አዳንካቸው። 9 የኤርትራን ባሕር ገሠ
ፅከው፤እርሱም ደረቀ፤በምድረ በዳ መካከል
እንደሚሄዱ፥ጥልቁን አቋርጠው እንዲሻገሩ
መራሃቸው። 10 ከሚጠሏቸው ሰዎች እጅ
አዳንሃቸው፤ከጠላቶቻቸውም እጅ አወጣሃ
ቸው። 11 የሚያሳድዷቸውን ተቃዋሚዎቻ
ቸውን ባሕሩ አጥለቅልቆ አሰጠማቸው፤አን
ዳቸው እንኳ አልተረፉም። 12 ከዚያ በኋላ
ሕዝቡ በተስፋ ቃልህ አመኑ፤ለአንተ የሚገ
ባውንም ምስጋና በዝማሬ አሰሙ።
13 ዳሩ ግን እግዚአብሔር ያደረገላቸውን
ሁሉ ወዲያው ረሱ፤ምክሩን በትዕግሥት
አልተከተሉም። 14 በምድረ በዳ እያሉ በእ
ጕል ምኞት ተሸነፉ፤በዚያ ጠፍ በረሃ እግ
ዚአብሔርን ተፈታተኑት። 15 ስለዚህ የጠየ
ቁትን ሰጣቸው፤ከዚያ ጋር ግን የሚያጠፋ
ደዌን ሰደደባቸው። 16 በሰፈር ሳሉ በሙሴና
እግዚአብሔር በቀደሰው በአሮን ላይ በቅ
ናት ተነሡባቸው። 17 በዚህ ምክንያት
ምድር ተከፍታ ዳታንን ዋጠችው፤አቤሮን
ንም ከነወገኖቹ ቀበረችው። 18 እሳት በተከ
ታዮቻቸው መካከል ተንቦገቦገ፤ነበልባሉም
ክፋዎችን አቃጥሎ ጨረሳቸው።
19 በኰሬብ የጥጃ ምስል ሠሩ፤ቀልጦ
ለተሠራው ጣዖት ሰገዱ። 20 ሣር ለሚበላ
የጥጃ ምስል ክብራቸውን ለወጡ። 21 ያዳና
ቸውን እግዚአብሔርን፥በግብጽ ታላላቅ
ድንቅ ሥራዎች ያደረገውን አምላክ ዘነ
ጉት፤ 22 በካም አገር ያሳየውን ተአምራት፥
በኤርትራም ባሕር የፈጸመውን አስገራሚ
ድርጊት ረሱ። 23 ከዚህ በኋላ፥ «እንግዲህስ

አጠፋቸዋለሁ» ብሎ እስከ መናገር ደረሰ፤
ዳሩ ግን እግዚአብሔር ራሱ የመረጠው
ሙሴ የቍጣው መቅሠፍት እንዳያጠፋቸው
በጸቡ መካከል ከፊቱ ባይቆም ኖሮ፥ ባለቀ
ነበር።
24 ከዚያም የሚገቡባትን መልካሚቱን
አገር ናቁ፤የሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላመ
ኑም። 25 በየድንኳናቸው ሆነው አጕረመ
ረሙ፤ ለእግዚአብሔር አልታዘዝ አሉ።
26 ስለዚህ እጁን አንሥቶ ማለ፤በምድረ በዳ
ወድቀው እንዲቀሩ፥ 27 ዘሮቻቸውም በም
ድር ላይ በአሕዛብ መካከል በየአህጕሩ ተበ
ትነው እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው መሆኑን
ገለጸ።
28 እነርሱ ግን ብዔል ፌጎርን በማምለክ
ተባበሩ፤ሕይወት ለሌላቸው አማልክት የቀ
ረበውን መሥዋዕት በሉ። 29 ይህን በመሰ
ለው ክፉ ሥራቸው እግዚአብሔርን አስቈ
ጡት፤በመካከላቸውም ቸነፈር ገባ። 30 ፊን
ሐስ ተነሥቶ ተገቢውን ፍርድ ሰጠ፤ቸነፈ
ሩም ተገታ። 31 ይህም አድራጎቱ ወደ ፊት
በሚነሡት ትውልዶች ዘንድ ጽድቅ ሆኖ
ሲቈጠርለት ይኖራል።
32 በመሪባ ውሃ አካባቢ ሳሉ እግዚአብ
ሔርን አስቈጡት፤ በእነርሱም ምክንያት
ሙሴ ተቸገረ፤ 33 በእግዚአብሔር መንፈስ
ላይ ስላመፁ ሙሴ የብስጭት ቃል ተናገረ።
34 እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አሕዛብን
ሳያጠፏቸው ቀሩ፤ 35 ይባስ ብለው ከእነርሱ
ጋር ተቀላቅለው፥ ባህላቸውን ባህል አድር
ገው ይኖሩ ጀመር። 36 ወጥመድ የሆኑባቸ
ውን የአሕዛብ ጣዖቶች አመለኩ። 37 ወንዶ
ችና ሴቶች ልጆቻቸውን ለአጋንንት ሠዉ።
38 ለከነዓን ጣዖታት ወንዶችና ሴቶች ልጆቻ
ቸውን መሥዋዕት አድርገው በማቅረባቸው
ንጹሕ ደም አፈሰሱ፤አገሪቱም በደሙ ረከ
ሰች። 39 በፈጸሙት ድርጊታቸው ራሳቸውን
አስነወሩ፤ በገዛ ሥራቸው በእግዚአብሔር
ፊት ረከሱ።
40 ስለዚህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ
ተቈጣ፤ወገኑ የሆነውን ይህን ሕዝብ ተጸየ
ፈው። 41 ለአሕዛብ አሳልፎ ሰጣቸው፤የሚ
ጠሏቸው ገዟቸው። 42 ጠላቶቻቸው ግፍ
ፈጸሙባቸው፤በሥልጣናቸውም አንበረከኳ
ቸው። 43 እግዚአብሔር ከሚደርስባቸው
ነገር ብዙ ጊዜ አዳናቸው። ዳሩ ግን አሻፈ
ረን ብለው በእርሱ ላይ ስላመፁ በኃጢአታ
ቸው ምክንያት ተዋርደው ቀሩ።
44 እርሱ ግን ጩኸታቸውን ሲሰማ ጭን
ቀታቸውን ተመለከተ፤ 45 ለእነርሱ ሲል ቃል
ኪዳኑን አሰበ፤ከፍቅሩ ብዛት የተነሣ ከቍ
ጣው መለስ አለ። 46 በምርኮኛነት የያዙዋ
ቸው ሁሉ እንዲራሩላቸው አደረገ።
47 አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፥ አድ
ነን። ውለታህን በማሰብ ለቅዱስ ስምህ ምስ
ጋና እናቀርብ ዘንድ፥ ከአሕዛብ መካከል
አውጥተህ እንደ ገና ሰብስበን።
48 ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር
ከዘላለም እስከ ዘላለም ምስጋና ይሁን።
ሕዝቡም ሁሉ «አሜን!» ይበሉ።
ሃሌ ሉያ።

# አምስተኛ መጽሐፍ

ከመዝሙር 107-150

## መዝሙር 107

1 እግዚአብሔር ቸር ነውና፥ፍቅሩም ለዘ
ላለም ጸንቶ ይኖራልና፥ ምስጋና አቅርቡ
ለት። 2 እግዚአብሔር ቤዛ የሆናቸው፥ከሚ
ጠሏቸውም እጅ ያዳናቸው፥ 3 ከምሥራቅና
ከምዕራብ፥ከሰሜንና ከደቡብ ከየአህጕሩ የሰ
በሰባቸው ሁሉ ምስጋና ያቅርቡለት።
4 አንዳንዶቹ ጠፍ በሆነ ምድረ በዳ ተን
ከራተቱ፤ቋሚ መኖሪያ መሥራት ወደሚች
ሉበት ከተማ የሚያደርሳቸውን መንገድ
ማግኘት አልቻሉም። 5 ተራቡ፤ተጠሙ፤ተስ
ፋቸውም እየመነመነ ሄደ። 6 ከመከራቸው
ጽናት የተነሣ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ።
እርሱም ከጭንቀታቸው አዳናቸው፤ 7 ቋሚ
መኖሪያ መሥራት ወደሚችሉበት ከተማ
ሰተት ባለ መንገድ እየመራ ወሰዳቸው።
8 አሁንም ስለማይለወጠው ፍቅሩና ለሰው
ልጆች ስላደረጋቸው ድንቅ ሥራዎቹ ምስ
ጋና ለእግዚአብሔር ያቅርቡ። 9 እርሱ የተ
ጠሙትን በመልካም ነገር ያረካል፤የተራቡ
ትንም ያጠግባል።
10 አንዳንዶቹ በብረት ሰንሰለት እየተሠ
ቃዩ፥ በጨለማና በሞት ጥላ ሥር የተቀ
መጡ እስረኞች ሆኑ። 11 በእግዚአብሔር
ቃል ላይ ዐመፁ፤ ከሁሉ በላይ የሆነውን
አምላክ ምክር ናቁ። 12 ስለዚህ መራራ
ለሆነ የጣር ኑሮ ዳረጋቸው፤ ተሰነካከለው
ቢወድቁም ደግፎ የሚያነሣቸው አልነበ
ረም። 13 ከመከራቸው ጽናት የተነሣ ወደ
እግዚአብሔር ጮኹ። እርሱም ከጭንቀ
ታቸው አዳናቸው፤ 14 ከነበሩበት ጨለማና
የሞት ጥላ አወጣቸው፤ ሰንሰለታቸውንም
ሰባብሮ ጣለላቸው። 15 ስለማይለወጠው ፍቅ
ሩና ለሰው ልጆች ስላደረጋቸው ድንቅ
ሥራዎቹ ምስጋና ለእግዚአብሔር ያቅርቡ፤

¹⁶እርሱ የእስር ቤቶችን የናስ መዝጊያዎች
ይሰባብራል፤የብረት አጥራቸውንም ቈራርጦ
ይጥላል።
¹⁷አንዳንዶቹ በዐመፅ መንገዳቸው ምክ
ንያት የማይረቡ ሆነው ቀሩ፤ከበደላቸውም
የተነሣ በመከራ ተሠቃዩ፤ ¹⁸ምግብ አስጠ
ልቷቸው ከሞት አፋፍ ደረሱ። ¹⁹ከመከራ
ቸው ጽናት የተነሣ ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ። እርሱም ከጭንቃቸው አዳናቸው፤
²⁰ቃሉን ወደ እነርሱ ልኮ ፈወሳቸው፤ወደ
መቃብርም ከመውረድ አተረፋቸው።
²¹ስለማይለወጠው ፍቅሩና ለሰው ልጆች
ስላደረጋቸው ድንቅ ሥራዎቹ ምስጋና ለእ
ግዚአብሔር ያቅርቡ። ²²የምስጋና መሥዋ
ዕት ይሠዉለት፤የደስታ ዝማሬ እየዘመሩ
ስለ ሥራው ይናገሩለት።
²³የቀሩትም በመርከብ እየሆኑ በባሕር
ይጓዙ ጀመር፤በውቅያኖሶች ላይ የሚመላ
ለሱ ነጋዴዎች ሆኑ፤ ²⁴በጥልቁ ባሕር
ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍጥረትና
አስደናቂ ሥራዎቹን አዩ። ²⁵እርሱ በተና
ገረ ጊዜ፥ዓውሎ ነፋሱ ተቀሰቀሰ ባሕሩ
ተናወጠ፤ሞገዱንም ከፍ አድርጎ አነሣው።
²⁶መርከባቸውን ወደ ላይ እስከ ሰማያት
እያወጣ፥ወደ ታችም ወደ ጥልቁ ባሕር
እያወረደ አስጨነቃቸው፤ልባቸውም በድን
ጋጤ ቀለጠ። ²⁷ምድርና ሰማዩ ዞረባቸው፤
እንደ ሰከረ ሰው ተንገደገዱ፤የሚያደርጉት
ንም አጡ። ²⁸ከመከራቸው ጽናት የተነሣ
ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤እርሱም ከጭን
ቃቸው አወጣቸው። ²⁹ማዕበሉን ጸጥ አደ
ረገው፤የባሕሩም ሞገድ ቀጥ አለ።
³⁰ባሕሩ እየተረጋጋ በመሄዱ ደስ አላ
ቸው፤እግዚአብሔርም ወደ ተመኙት
ወደብ መርቶ አደረሳቸው። ³¹ስለማይለወ
ጠው ፍቅሩና ለሰው ልጆች ስላደረጋቸው
ድንቅ ሥራዎቹ ምስጋና ለእግዚአብሔር
ያቅርቡ፤ ³²በሕዝቡ ጉባኤ መካከል ገናና
ነቱን ይመስክሩለት፤በመማክርቱም ሸንጎ
ላይ ያወድሱት።
³³እርሱ፥ወንዞችና ወራጅ ምንጮች የበ
ዙበትን አገር ወደ በረሃነት እስኪለወጥ
ድረስ አደረቀው፤ ³⁴ፍሬያማ የሆነውንም
ለም መሬት ጠፍ አድርጎ ወደ ጨውነት
ለወጠው። ይህም ሊደርስ የቻለው፥ነዋሪ
ዎቹ በፈጸሙት ክፋት ምክንያት ነበር።
³⁵ደግሞ በበረሃው፥ሐይቅ እንጣለለበት፤የደ
ረቀውን ምድር ወራጅ ምንጭ የበረከተበት
አደረገው። ³⁶የተራቡትን ወደዚያ አመጣ
ቸው፤እነርሱም የሚቀመጡባትን ከተማ
ቈረቈሩ። ³⁷በዚያ የእርሻ ማሳዎችን አዘጋ
ጅተው ዘር ዘሩ፤አትክልት ተከሉ፤በመከር
ጊዜ ሰብሉንና ፍሬውን ሰበሰቡ። ³⁸እርሱ
ባርኳቸዋልና ዘራቸው እጅግ በረከተ፤የከብ
ቶቻቸውንም ቍጥር አላሳነሰባቸውም።
³⁹ከዚያ በኋላ ከደረሰባቸው ጭቈናና
እልቂት፥ከኀዘን ጽናትም የተነሣ ቍጥራ
ቸው አነሰ፤ተዋረዱም። ⁴⁰ትምክሕተኞች
መኳንንት እንዲናቁ የሚያደርግ አምላክ
በጠፍ በረሃ ውስጥ አንከራተታቸው።
⁴¹ችግረኞችን ግን ከመከራቸው አውጥቶ
ከፍ አደረጋቸው፤ቤተሰቦቻቸውንም እንደ
መንጋ አበዛላቸው። ⁴²ልበ ቅኖች ይህን
አይተው እጅግ ደስ ይላቸዋል፤ክፉዎች
ሁሉ ግን አፋቸውን ዘግተው ዝም
ይላሉ።
⁴³ብልህ የሆነ፥እነዚህን ነገሮች ልብ
አድርጎ ይመልከት፤ የእግዚአብሔርንም
ታላቅ ፍቅር አመዛዝኖ ይረዳ።

## መዝሙር 108

¹እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥አንተን
በመተማመን ልቤ ጽኑ ነው፤በፍጹም ነፍሴ
እቀኝልሃለሁ፤እዘምርልሃለሁም። ²በገናና
መሰንቆ ሆይ፥ንቁ! እኔም ጐሕ ሲቀድ
ማልጄ እነሣለሁ። ³እግዚአብሔር ሆይ፥በአ
ሕዛብ መካከል አወድስሃለሁ፤በሕዝቦችም
መካከል ስለ አንተ እዘምራለሁ። ⁴ፍቅርህ
ከሰማያት ይልቅ ከፍ ያለና ታላቅ ነው፤
ታማኝነትህም እስከ ሰማይ ይደርሳል። ⁵እግ
ዚአብሔር አምላክ ሆይ፥ገናናነትህ ከሰማ
ያት በላይ ከፍ ይበል፤ክብርና ምስጋናህ
በምድር ሁሉ ላይ ይስፈን። ⁶አሁንም የም
ትወዳቸው ይድኑ ዘንድ፥በቀኝ እጅህ ጋሻና
መከታ ሆነህ እርዳን።
⁷እግዚአብሔር አምላክ በመቅደሱ ሆኖ
እንዲህ ሲል ተናግሯል፦ «ሴኬምን በድል
አድራጊነት ከፍዬ እይዛለሁ፤የሱኮትን ሸለቆ
ለክቼ እወስዳለሁ። ⁸ገለዓድ የእኔ ነው፤ምና
ሴም የእኔው ነው። ኤፍሬም ለእኔ የራስ
ቍር ነው፤ይሁዳ በትረ መንግሥቴ ነው።
⁹ሞዓብ መታጠቢያ ገንዳዬ ነው። በኤዶም
ያስ ላይ ጫማዬን እጥላለሁ፤በፍልስጥኤም
ላይ የድል አድራጊነት ድምፄን አሰማ
ለሁ።»
¹⁰አቤቱ፥ወደ ተመሸገችው ከተማ ማን
ያደርሰኛል? ወደ ኤዶምያስስ ማን መርቶ
ይወስደኛል? ¹¹አምላካችን ሆይ፥
«ወግዱ» ብለህ የተውከንና ከሠራዊታችን
ጋር ለጦርነት ከመውጣት የቀረኸው

አንተው አይደለህምን? 12 የሰው እርዳታ
ከንቱ ነውና ጠላቶቻችንን ለመቋቋም የምን
ችልበትን አቅም ስጠን። 13 በእግዚአብሔር
ኃይል ድል እናደርጋለን፤እርሱ ጠላቶቻችንን
ከእግሩ በታች ጥሎ ይረግጣቸዋል።

## መዝሙር 109

1 በውዳሴ የማመሰግንህ እግዚአብሔር
አምላክ ሆይ ፥ ዝም እንዳልክ አትቅር።
2 ክፉዎችና ተንኰለኞች እኔን በሐሰት ለመ
ወንጀል እንደበታቸውን ከፍተዋልና፤ 3 በጥ
ላቻ ቃላት እያዋከቡ ያለምክንያት ያጠቁ
ኛል ፤ 4 ለወዳጅነቴ የመለሱልኝ ውለታ
ክስና ወቀሳ ሆነ። እኔ ግን በጸሎት የምተጋ
ሰው ነኝ። 5 ላደረግሁላቸው ደግነት ክፉ
ትን፥ላሳየኋቸው ፍቅር ጥላቻን ከፈሉኝ።
6 ስለዚህ፥እንዲህ ያለ ሰው የእጁን ያገኝ
ዘንድ ክፉ ዳኛ ሹምበት፤ከሳሽ የሆነውም
ሰይጣን ይፋረደው ፤ 7 በሚከሰስበት ጉዳይ
ጥፋተኛ ሆኖ ይገኝ። የራሱ ጸሎት ከኃጢ
አት ይቈጠርበት። 8 ዕድሜው ይጠር፤ሹመ
ቱን ሌላ ይውሰድበት። 9 ልጆቹ አሳዳጊ የሌ
ላቸው ይሁኑ፤ሚስቱም መበለት ሆና ትቅ
ር ፤ 10 ልጆቹ ከኑሮአቸው ተፈናቅለው
የሚንከራተቱ ለማኞች ይሁኑ። 11 ያበደረው
ባለገንዘብ ቤት ንብረቱን በዕዳ ይያዝበት።
የድካሙን ፍሬ ባይተዋሮች ይዝረፉት።
12 ለእርሱ የደግነት ሥራ የሚያደርግለት፥
አሳዳጊ ለሌላቸው ልጆቹም የሚያዝንላቸው
አይኑር። 13 ዘርማንዘሩ ይጥፋ፤ስሙም ከሚ
ቀጥለው ትውልድ መዝገብ ይደምሰስ።
14 የቀደሙት አባቶቹ በደል በእግዚአብሔር
ፊት ይታወስ፤ የእናቱም ኃጢአት ይቅር
አይባል። 15 የሁሉም መታሰቢያ ከዚህ
ዓለም ይጠፋ ዘንድ ኃጢአታቸው በፊትህ
ሲታሰብ ይኑር።
16 እርሱ የደግነት ሥራ ለመሥራት
ምን ጊዜም አስቦ ስለማያውቅ፥ድኻውንና
ችግረኛውን፥እንዲሁም ተስፋ የቈረጠውን
እስከ ሞት ድረስ ሊያጠቃ ያሳድዳል።
17 እርግማኑ በእርሱ ላይ ይድረስበትና!
የእርግማን ቃል መናገር ይወዳል፤በረከት
ከእርሱ ይራቅና! የበረከት ቃል መስጠት
ደስ አይለውም። 18 መርገምን እንደ
ልብስ አጥልቋታል ፤ እርሷም ሰውነቱን
እንደ ውሃ አርሳዋለች ፤ እንደ ቅባትም
እስከ አጥንቱ ዘልቃለች። 19 እንደ ለበሳት
ነጠላና ከወገቡ ዙርያ እንደማትለይ
ቀበቶ ትሁንለት።
20 ይህ ሁሉ ፥ ስለ እኔ ክፉ ለሚናገሩት
ለከሳሾቼ እግዚአብሔር የሚከፍላቸው ዋጋ
ይሁን። 21 የሁሉ ገዢ የሆንከው እግዚአብ
ሔር ሆይ፥አንተ ግን ስለ ስምህ ብለህ ለእኔ
በጎ አስተያየት ይኑርህ፤በፍቅርህም መልካ
ምነት አድነኝ።
22 እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝ። ልቤም በው
ስጤ ቈስሏል። 23 እንደሚያልፍ የማታ
ጥላ ፥ ተራግፎ እንደ ወደቀ አንበጣም
ሆንሁ። 24 አብዝቼ በመጾም ጒልበቴ
ደከመ ፤ ሰውነቴ ከሳ ፤ ጠወለገ። 25 ከሳሾቼ
የንቀታቸው ምክንያት አደረጉኝ ፤ ባዩኝ
ቍጥር ራሳቸውን ይነቀንቃሉ።
26 እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፥እርዳኝ፤
በፍቅርህ አድነኝ። 27 አቤቱ ፥ ይህንን አን
ተው ራስህ በሥልጣንህ ያደረግኸው መሆ
ኑን ይወቁ። 28 እነርሱ ይራገሙ፤አንተ ግን
ትባርካለህ። ሌላውን በሚያጠቁበት ጊዜ
በኀፍረት ላይ ይወድቃሉ። አገልጋይህ ግን
እጅግ ደስ ይለዋል። 29 ከሳሾቼ ውርደትን
ለብሰዋል ፤ ኀፍረትንም እንደ መጐናጸፊያ
አጣፍተዋል።
30 እግዚአብሔርን በአንደበቴ እጅግ ከፍ
አድርጌ አመሰግነዋለሁ ፤ በታላቅ የሕዝብ
ጉባኤም ላይ አወድሰዋለሁ። 31 ችግረኛውን
በሕይወቱ ከፈረዱበት እጅ ያድነው ዘንድ
እርሱ በቀኙ ይቆማል።

## መዝሙር 110

1 ጌታ፥ጌታዬን፥ «ጠላቶችህን የእግሮችህ
ብርኩማ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀ
መጥ» አለው።
2 ኃያል የሆነውን በትረ መንግሥትህን
እግዚአብሔር ከጽዮን ይዘረጋል ፤ አንተም
በጠላቶችህ መካከል ገዢ ትሆናለህ።
3 ኃይልህን በምትገልጽበት የውጊያ ቀን
ሠራዊትህ በልበ ሙሉነት አብረውህ ይሰለ
ፋሉ። አንተም በቅዱስ ግርማህ አጊጠህ
ትታያለህ። ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ
ወልጄሃለሁና የጒልማሳነትህን ጠል ትቀበ
ላለህ።
4 «አንተ ፥ በመልከ ጼዴቅ ሥርዓት የዘላ
ለም ካህን ነህ» ሲል እግዚአብሔር ማለ፤
ቃሉንም አይለውጥም።
5 እግዚአብሔር በቀኝህ ነው ፤ በቍጣ
ውም ቀን ነገሥታትን ያደቃቸዋል። 6 በመ
ላው ዓለም ባሉ ገዢዎች ላይ ድልን በመቀ
ዳጀት በምድራቸው፥ሬሳ በሬሳ ላይ እንዲከ
መር አድርጎ በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል።

አንተው አይደለህምን? 12የሰው እርዳታ
ከንቱ ነውና ጠላቶቻችንን ለመቋቋም የምን
ችልበትን አቅም ስጠን። 13በእግዚአብሔር
ኃይል ድል እናደርጋለን፤እርሱ ጠላቶቻችንን
ከእግሩ በታች ጥሎ ይረግጣቸዋል።

## መዝሙር 109

1በውዳሴ የማመሰግንህ እግዚአብሔር
አምላክ ሆይ፥ ዝም እንዳልክ አትቅር።
2ክፉዎችና ተንኰለኞች እኔን በሐሰት ለመ
ወንጀል አንደበታቸውን ከፍተዋልና፤ 3በጥ
ላቻ ቃላት እያዋከቡ ያለምክንያት ያጠቁ
ኛል፤ 4ለወዳጅነቴ የመለሱልኝ ውለታ
ክስና ወቀሳ ሆነ። እኔ ግን በጸሎት የምተጋ
ሰው ነኝ። 5ላደረግሁላቸው ደግነት ክፉ
ትን፥ላሳየኋቸው ፍቅር ጥላቻን ከፈሉኝ።
6ስለዚህ፥እንዲህ ያለ ሰው የእጁን ያገኝ
ዘንድ ክፉ ዳኛ ሹምበት፤ከሳሽ የሆነውም
ሰይጣን ይፋረደው፤ 7በሚከሰስበት ጉዳይ
ጥፋተኛ ሆኖ ይገኝ። የራሱ ጸሎት ከኃጢ
አት ይቈጠርበት። 8ዕድሜው ይጠር፤ሹመ
ቱን ሌላ ይውሰድበት። 9ልጆቹ አሳዳጊ የሌ
ላቸው ይሁኑ፤ሚስቱም መበለት ሆና ትቀ
ገር፤ 10ልጆቹ ከኑሮአቸው ተፈናቅለው
የሚንከራተቱ ለማኞች ይሁኑ። 11ያበደረው
ባለገንዘብ ቤት ንብረቱን በዕዳ ይያዝበት።
የድካሙን ፍሬ ባይተዋሮች ይዝረፉት።
12ለእርሱ የደግነት ሥራ የሚያደርግለት፥
አሳዳጊ ለሌላቸው ልጆቹም የሚያዝንላቸው
አይኑር። 13ዘርማንዘሩ ይጥፋ፤ስሙም ከሚ
ቀጥለው ትውልድ መዝገብ ይደምሰስ።
14የቀደሙት አባቶቹ በደል በእግዚአብሔር
ፊት ይታወስ፤የእናቱም ኃጢአት ይቅር
አይባል። 15የሁሉም መታሰቢያ ከዚህ
ዓለም ይጠፋ ዘንድ ኃጢአታቸው በፊትህ
ሲታሰብ ይኑር።
16እርሱ የደግነት ሥራ ለመሥራት
ምን ጊዜም አስቦ ስለማያውቅ፥ድኻውንና
ችግረኛውን፥እንዲሁም ተስፋ የቈረጠውን
እስከ ሞት ድረስ ሊያጠቃ ያሳድዳል።
17እርግማኑ በእርሱ ላይ ይድረስበትና!
የእርግማን ቃል መናገር ይወዳል፤በረከት
ከእርሱ ይራቅና! የበረከት ቃል መስጠት
ደስ አይለውም። 18መርገምን እንደ
ልብስ አጥልቋታል፤ እርሷም ሰውነቱን
እንደ ውሃ አርሳዋለች፤ እንደ ቅባትም
እስከ አጥንቱ ዘልቃለች። 19እንደ ለበሳት
ነጠላና ከወገቡ ዙርያ እንደማትለይ
ቀበቶ ትሁንለት።
20ይህ ሁሉ፥ስለ እኔ ክፉ ለሚናገሩት
ለከሳሾቼ እግዚአብሔር የሚከፍላቸው ዋጋ
ይሁን። 21የሁሉ ገዢ የሆንከው እግዚአብ
ሔር ሆይ፥አንተ ግን ስለ ስምህ ብለህ ለእኔ
በጎ አስተያየት ይኑርህ፤በፍቅርህም መልካ
ምነት አድነኝ።
22እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝ። ልቤም በው
ስጤ ቈስሏል። 23እንደሚያልፍ የማታ
ጥላ፥ ተራግፌ እንደ ወደቀ አንበጣም
ሆንሁ። 24አብዝቼ በመጾም ጒልበቴ
ደከመ፤ ሰውነቴ ከሳ፤ ጠወለገ። 25ከሳሾቼ
የንቀታቸው ምክንያት አደረጉኝ፤ ባዩኝ
ቊጥር ራሳቸውን ይነቀንቃሉ።
26እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፥እርዳኝ፤
በፍቅርህ አድነኝ። 27አቤቱ፥ ይህንን አን
ተው ራስህ በሥልጣንህ ያደረግኸው መሆ
ኑን ይወቁ። 28እነርሱ ይራገማሉ፤አንተ ግን
ትባርካለህ። ሌላውን በሚያጠቁበት ጊዜ
በኀፍረት ላይ ይወድቃሉ። አገልጋይህ ግን
እጅግ ደስ ይለዋል። 29ከሳሾቼ ውርደትን
ለብሰዋል፤ ኀፍረትንም እንደ መጐናጸፊያ
አጣፍተዋል።
30እግዚአብሔርን በአንደበቴ እጅግ ከፍ
አድርጌ አመሰግነዋለሁ፤ በታላቅ የሕዝብ
ጉባኤም ላይ አወድሰዋለሁ። 31ችግረኛውን
በሕይወቱ ከፈረዱበት እጅ ያድነው ዘንድ
እርሱ በቀኙ ይቆማል።

## መዝሙር 110

1ጌታ፥ጌታዬን፥ «ጠላቶችህን የእግሮችህ
ብርኩማ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀ
መጥ» አለው።
2ኃያል የሆነውን በትረ መንግሥትህን
እግዚአብሔር ከጽዮን ይዘረጋል፤አንተም
በጠላቶችህ መካከል ገዢ ትሆናለህ።
3ኃይልህን በምትገልጽበት የውጊያ ቀን
ሠራዊትህ በልበ ሙሉነት አብረውህ ይሰለ
ፋሉ። አንተም በቅዱስ ግርማህ አጊጠህ
ትታያለህ። ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ
ወልጄሃለሁና የጒልማሳነትህን ጠል ትቀበ
ላለህ።
4«አንተ፥በመልከ ጼዴቅ ሥርዓት የዘላ
ለም ካህን ነህ» ሲል እግዚአብሔር ማለ፤
ቃሉንም አይለውጥም።
5እግዚአብሔር በቀኝህ ነው፤ በቍጣ
ውም ቀን ነገሥታትን ያደቃቸዋል። 6በመ
ላው ዓለም ባሉ ገዢዎች ላይ ድልን በመቀ
ዳጀት በምድራቸው፥ሬሳ በሬሳ ላይ እንዲከ
መር አድርጎ በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል።

7እርሱ ግን በመንገዱ ዳር ከሚፈሰው ውሃ
ይጠጣል፤ ራሱንም በብርታት ቀና ያደር
ጋል።

## መዝሙር 111

1ሃሌ ሉያ!
በቅኖች ሸንጎና በጉባኤ መካከል በሙሉ
ልቤ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።
2የእግዚአብሔር ሥራ እጅግ ታላቅ
ነው፤በሥራው ደስ የሚሰኙ ሁሉ በተመ
ስጦ ያሰላስሉታል። 3ድርጊቶቹ ገናናነትና
ግርማ የተመላባቸው ናቸው። ጽድቁም
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። 4ተአምራቱ እን
ዲታወሱ አደረገ። እግዚአብሔር ቸርና
ርኅሩኅ ነው። 5ለሚፈሩት ምግብን ይሰጣ
ቸዋል። ቃል ኪዳኑን ለዘላለም ያስባል።
6የአሕዛብን አገር ለሕዝቡ በማውረስ የሥ
ራውን ኃያልነት አሳየ። 7የእጆቹ ሥራ
ዎች የታመኑና የተስተካከሉ፥ መመሪያዎ
ቹም እንከን የማይገኝባቸው ናቸው።
8በእውነትና በቅንነት የተከናወኑ ስለ ሆኑ
ዛሬም፥ዘወትርም፥ለምን ጊዜውም አይናወ
ጡም። 9እርሱ፥ ለሕዝቡ ቤዛ የሚሆን
መድኅን ላከ። ስሙ ቅዱስና ግሩም የሆ
ነው ጌታ፥ኪዳኑ ለዘላለም ጸንቶ እንዲኖር
ደነገገ።
10የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን
መፍራት ነው። የእግዚአብሔርን መመሪያ
ዎች የሚከተሉ ሁሉ አስተዋዮች ናቸው።
የዘላለም ምስጋና ለእርሱ ብቻ ይገባዋል።

## መዝሙር 112

1ሃሌ ሉያ!
እግዚአብሔርን የሚፈራ፥ በትእዛዛቱም
እጅግ ደስ የሚለው ሰው የተባረከ ነው።
2ልጆቹ በምድር ላይ ኃያላን ይሆናሉ፤
የቅን ሰው ዘሩ የተባረከ ነው። 3ቤቱ በክብ
ርና በብልጽግና ይሞላል። ጻድቅነቱም ለዘ
ላለም ጸንቶ ይኖራል። 4ቅንና ደግ፥ ርኅሩ
ኅና ጻድቅ ለሆነ ሰው በጨለማ ውስጥ
እንኳ የብርሃን ጐሕ ይቀድለታል። 5ያለወ
ለድ የሚያበድርና ሥራውን በትክክለኛነት
የሚመራ ሰው፥ መልካም የሆነውን ሁሉ
ያገኛል፤ 6ከቶ በምንም ነገር አይናወጥም።
ጻድቅ ሰው ለዘላለም ሲታወስ ይኖራል።
7ክፉ ወሬ አያሸብረውም፤በእግዚአብሔር
ስለሚተማመን ልቡ የጸና ነው። 8ልቡ
የጸና ስለ ሆነ ፍርሃት የለበትም፤በመጨረ
ሻም ጠላቶቹን በድል አድራጊነት ይመለከ
ታቸዋል። 9ስጦታውን በሰፊ እጁ ለድኾች
ይቸራል። ጽድቁ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤
ሥልጣኑም በክብር ከፍ ይላል።
10ክፉ ሰው ይህን አይቶ ይበሳጫል፤ጥር
ሱን ያፋጫል፤በንዴት እንጀቱ ያራል። የክ
ፉዎች ምኞት ግን ከንቱ ሆኖ ይቀራል።

## መዝሙር 113

1ሃሌ ሉያ!
የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆይ፥ ጌታን
አወድሱት ፤ የእግዚአብሔርን ስም አመስ
ግኑ። 2የእግዚአብሔር ስም ዛሬም፥ለዘላለ
ምም የተመሰገነ ይሁን። 3ከፀሐይ መውጫ
ጀምሮ እስከ መግቢያው ድረስ የእግዚአብ
ሔር ስም ሲወደስ ይኖራል።
4እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ
ገናና፥ክብርና ምስጋናውም ከሰማያት በላይ
ከፍ ያለ ነው። 5በሰማይ ዙፋኑ ላይ የተቀ
መጠውን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን የሚ
መስለው ከቶ ማነው? 6እርሱ በሰማይና
በምድር የሚሆነውን ይመለከት ዘንድ
ራሱን በትሕትና ዝቅ ያደርጋል።
7ድኻውን ከትቢያ፥ ችግረኛውንም ከአ
መድ ጥራጊ ላይ አንሥቶ ከፍ ያደርገዋል።
8ከመሳፍንትና በሕዝቡ ላይ ከተሾሙ ታላ
ላቅ ባለሥልጣኖች ጋር አብሮ በማዕርግ ያስ
ቀምጠዋል። 9መኻን ሴት የልጆች እናት
ሆና በቤቷ ተደስታ ተደላድላ እንድትኖር
ያደርጋታል።
ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 114

1የያዕቆብ ዘር የሆኑት የእስራኤል
ሕዝብ ከግብጽ አገርና ባዕድ ቋንቋ ከሚና
ገር ወገን ተለይተው በወጡ ጊዜ፥ 2የይሁዳ
ነገድ የእግዚአብሔር መቅደስ ሆነ፤ እስራ
ኤል ደግሞ የእርሱ ግዛት ሆነ።
3የኤርትራ ባሕር ገና ከሩቅ ሲያያቸው
ሸሸ፤የዮርዳኖስም ወንዝ ወደ ኋላው ተመ
ለሰ፤ 4ተራሮች እንደ እምቦሳ፥ኰረብቶችም
እንደ ጠቦት ፈነደቁ።
5የኤርትራ ባሕር ሆይ፥ እንዲያ የሸሸ
ኸው፥ አንተም የዮርዳኖስ ወንዝ ሆይ፥ወደ
ኋላህ የተመለስኸው ከቶ ስለ ምንድነው?
6እናንት ተራሮች እንደ እምቦሳ፥ እናንት
ኰረብቶችስ እንደ ጠቦት የፈነደቃችሁት
ኸረ ስለ ምንድነው?
7ምድር ሆይ፥በያዕቆብ አምላክ በእግዚ
አብሔር መገለጥ ተንቀጥቀጪ! 8ዓለቱን

ወደ ኵሬነት ፥ ጽኑ የሆነውን ቋጥኝ ወደ
ውሃ ምንጭነት የለወጠ እርሱ ነውና።

## መዝሙር 115

1 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ለእኛ ሳይሆን
አቤቱ ፥ ለእኛ ሳይሆን ፥ ነገር ግን ስለ ፍቅር
ህና ስለ ታማኝነትህ ፥ ክብርና ምስጋና ለስ
ምህ ይሁን።
2 አሕዛብ፥ «አምላካቸው ወዴት ነው?»
ለምን ይበሉ! 3 የእኛ አምላክ በሰማያት
ይኖራል። እርሱ የፈለገውን ማንኛውንም
ነገር ያደርጋል። 4 ጣዖቶቻቸው ግን በሰው
እጅ የተሠሩ ወርቅና ብር ናቸው። 5 አፍ
አላቸው ፥ አይናገሩም ፤ ዓይን አላቸው ፥ አያ
ዩም ፤ 6 ጆሮ አላቸው ፥ አይሰሙም ፤ አፍንጫ
አላቸው ፥ አያሸቱም፤ 7 እጅ አላቸው ፤ አይዳስ
ሱም ፤ እግር አላቸው ፥ አይሄዱም ፤ ጉሮሮአቸ
ውም ድምፅ ማሰማት አይችልም። 8 ጣዖቶ
ቹን የቀረጿቸውና እንዲሁም በእነርሱ የሚ
ተማመኑ ሁሉ እንደ ጣዖቶቹ ከንቱ
ናቸው።
9 የእስራኤል ወገኖች ሆይ ፥ እናንተ በእግ
ዚአብሔር ተማመኑ ፤ እርሱ ረዳታችሁና
ጋሻችሁ ነው። 10 የአሮን ወገኖች ሆይ ፥ በእ
ግዚአብሔር ተማመኑ ፤ እርሱ ረዳታችሁና
ጋሻችሁ ነው። 11 እናንተ ጌታን የምትፈሩ
ሁሉ ፥ በእግዚአብሔር ተማመኑ ፤ እርሱ ረዳ
ታችሁና ጋሻችሁ ነው።
12 እግዚአብሔር ያስበናል ፤ ይባርከና
ልም። እርሱ የእስራኤልን ወገን ይባርካል፤
እርሱ የአሮንን ወገን ይባርካል። 13 እርሱ
የሚፈሩትን ሁሉ ፥ ትልቁንም ትንሹንም ሳያ
በላልጥ ይባርካል።
14 እግዚአብሔር እናንተንና ልጆቻችሁን
ባርኮ ቍጥራችሁ እንዲበዛ ያድርግ። 15 ሰማ
ይንና ምድርን በፈጠረ አምላክ የተባረካ
ችሁ ሁኑ።
16 ከሰማያት በላይ ያለው ሰማይ የእግዚ
አብሔር ነው ፤ ምድርን ግን ለሰው ልጅ
ሰጠ። 17 እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት ፥
ዝምታ ወደ ሰፈነበት ፍጻሜ የወረዱት
ሙታን አይደሉም ፤ 18 እግዚአብሔርን
እጅግ ከፍ አድርገን ዛሬም ለዘላለም የምና
መሰግነው እኛ ሕያዋን ነን።
ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 116

1 እግዚአብሔር ምሕረቱን እንዲያደርግ
ልኝ ያሰማሁትን የልመናዬን ድምፅ አዳ
ምጧልና እወደዋለሁ። 2 ጆሮውን ወደ
እኔ ዘንበል አድርጎልኛልና በሕይወት
እስካለሁ ድረስ ጸሎቴን ለእርሱ አቀርባ
ለሁ።
3 እነሆ ፥ የሞት ገመድ በአንገቴ ተተብ
ትቦ በጣር ተይዣለሁ፤የመቃብር አስጨናቂ
ነት አንዣበበብኝ ፤ በመከራና በኀዘን ተሸነ
ፍሁ። 4 ከዚያም ፥ «አቤቱ ፥ አድነኝ!» ብዬ
የጌታን ስም ጠራሁ።
5 እግዚአብሔር ቸርና ጻድቅ ነው። ፈጣ
ሪያችን ፍጹም ርኅሩኅ ነው። 6 እግዚአብ
ሔር ትሑት ልቦና ያለውን ይጠብቃል።
ታላቅ ችግር በገጠመኝ ጊዜ እርሱ አዳነኝ።
7 አሁንም ነፍሴ ሆይ ፥ ዕረፊ ፤ እግዚአብሔር
ለአንቺ መልካም አድርጎልሻል።
8 አቤቱ ፥ አንተ ነፍሴን ከሞት ፥ ዓይኖቼን
ከእንባ ፥ እግሮቼንም ከመሰናከል አድነሃል።
9 በሕያዋን አገር ሆኜ በፊትህ እንድመላለስ
አድርገኸኛል። 10 «በታላቅ ሥቃይ ላይ እገ
ኛለሁ» ብዬ በተናገርሁበት ጊዜ እንኳ
እምነቴን ጠብቄአለሁ። 11 ከመከራዬ የተ
ነሣ ተስፋ ቈርጬ ሳለሁ ፥ «ሰዎች ሁሉ
ሐሰተኞች ናቸው» አልሁ።
12 እግዚአብሔር ለዋለልኝ ቸርነቱ ፥ ወሮ
ታውን እንዴት አድርጌ ልከፍለው እችላ
ለሁ? 13 በእርሱ ቤዛነት የሚገኘውን የደኅ
ንነት ጽዋ አነሣለሁ ፤ የእግዚአብሔርንም
ስም እጠራለሁ። 14 ለእግዚአብሔር የተሳል
ኩትን ስእለቴን በሕዝቡ ሁሉ ፊት እፈጽማ
ለሁ። 15 የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር
ዘንድ የከበረ ነው።
16 እግዚአብሔር ሆይ ፥ እኔ አገልጋይህ
ነኝ፤የታሰርኩበትን ሰንሰለት ፈተህ ነጻ ያደ
ረግኸኝ እኔ የገረድህ ልጅ ፥ በእውነት አገል
ጋይህ ነኝ። 17 የምስጋና መሥዋዕት እሠዋ
ልሃለሁ ፤ ስምህንም እጠራለሁ። 18 ለእግዚአ
ብሔር የተሳልኩትን ስእለቴን በሕዝቡ
ሁሉ ፊት አደርሳለሁ። 19 ኢየሩሳሌም
ሆይ ፥ ማእከልሽ በሆነው በእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ አደባባይ ስእለቴን እፈጽመዋ
ለሁ።
ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 117

1 አሕዛብ ሁላችሁ ፥ እግዚአብሔርን አወ
ድሱት። ሕዝቦች ሁሉ ፥ እርሱን ከፍ አድር
ጋችሁ አመስግኑት። 2 እርሱ ለእኛ ያለው
ፍቅር ታላቅ ነውና ፤ የእግዚአብሔር መታ
መን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራልና።
ሃሌ ሉያ!

# መዝሙር 118

1 ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቅርቡለት፤
እርሱ ቸር ነው፤ፍቅሩም ለዘላለም ጸንቶ
ይኖራል።
2 የእስራኤል ሕዝብ፥ «ፍቅሩ ለዘላለም
ጸንቶ ይኖራል» ብላችሁ ዘምሩ። 3 የአሮን
ወገኖች፥ «ፍቅሩ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል»
ብላችሁ አስተምሩ። 4 እግዚአብሔርን የም
ትፈሩ ሁሉ፥ «ፍቅሩ ለዘላለም ጸንቶ ይኖ
ራል» ብላችሁ ተናገሩ።
5 በተጨነቅሁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ጮህኩ፤እርሱም እኔን ከጭንቀቴ በማው
ጣት ጸሎቴን ሰማኝ። 6 እግዚአብሔር ከእኔ
ጋር ስለ ሆነ አልፈራም። ሰው ከቶ ምን
ሊያደርገኝ ይችላል? 7 እግዚአብሔር ከእኔ
ጋር ነው፤ረዳቴም ነው። ስለዚህ ጠላቶቼን
በድል አድራጊነት ቆሜ እመለከታቸዋለሁ።
8 በሰው ከመተማመን፥ እግዚአብሔርን
መማጸን ይበልጣል። 9 ሥልጣን ባላቸው
ሰዎች ከመመካት፥ እግዚአብሔርን ተስፋ
ማድረግ ይሻላል።
10 አሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ፤እኔ ግን በእግዚ
አብሔር ስም አስወገድኳቸው። 11 በያቅጣ
ጫው ከበውኝ ነበር፤እኔ ግን በእግዚአብ
ሔር ስም አሸነፍኳቸው። 12 እንደ ንብ
መንጋ ወርረው ከበቡኝ፤ዳሩ ግን በእሳት
ውስጥ እንደ ተማገደ እሾህ ነደዱ፤እኔም
በእግዚአብሔር ስም አጠፋኋቸው። 13 ወደ
ኋላዬ እያፈገፈግሁ ድል ልሆን ጥቂት ቀር
ቶኝ ነበር፤እግዚአብሔር ግን ደጀን ሆኖ
ረዳኝ። 14 እግዚአብሔር ኃይሌና ዝማሬዬ፥
ቤዛ መድኃኒቴም ነው።
15 የእልልታ ድምፅና የድል አድራጊነት
ሆታ በጻድቃን ሰፈር በማስተጋባት እንዲህ
ሲል ይሰማል፦ «የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ
የሚያስገርሙ ሥራዎችን ፈጸመ፤ 16 የእግዚ
አብሔር ቀኝ እጅ ከፍ ከፍ አለ፤የእግዚአብ
ሔር ቀኝ እጅ የሚያስገርሙ ሥራዎችን
ፈጸመ!»
17 እኔ እኖራለሁ፤ ከቶም አልሞትም።
እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ በይፋ እናገ
ራለሁ። 18 እግዚአብሔር በብርቱ የመከራ
አለንጋ ቀጣኝ፤ለሞት ግን አሳልፎ አልሰጠ
ኝም።
19 ምስጋናዬን ለእግዚአብሔር ከፊቱ
ሆኜ አቀርብለት ዘንድ የጽድቅን ደጆች
ክፈቱልኝ። 20 ጻድቃን የሚገቡባት የእግዚ
አብሔር ደጅ ይህቺ ናት። 21 አቤቱ፥ልመና
ዬን ሰምተኸኛልና ምስጋና አቀርብልሃለሁ፤
አንተ ቤዛ ሆነህ አድነኸኛል።
22 ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማዕዘን
ራስ ሆነ። 23 እነሆ እግዚአብሔር ይህን
ማድረጉ ምንኛ የሚያስደንቅ ሥራ ነው!
24 ይህች ዕለት እግዚአብሔር በተለይ የሠ
ራት ቀን ናት፤ስለዚህ በእርስዋ እጅግ ደስ
ይበለን፤ሐሤትም እናድርግ።
25 አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፥ አድነን፤
የምንሠራውንም አሳካልን። 26 በእግዚአብ
ሔር ስም የሚመጣው እርሱ ቡሩክ ነው።
እኛም በቤተ መቅደስህ ሆነን፥ «ቡሩክ
ነህ» እንልሃለን። 27 እግዚአብሔር እውነ
ተኛ አምላክ ነው፤ብርሃኑ በእኛ ላይ እንዲ
ያበራ አደረገልን። ስለዚህ የዛፍ ቅርንጫፎ
ችን ይዛችሁ፥ መሠዊያው እስከሚገኝበት
ድረስ በመሄድ በዓሉን በሥነ ሥርዓት አክ
ብሩ።
28 አቤቱ፥ አንተ ፈጣሪዬ ነህና ምስጋና
አቀርብልሃለሁ፤ አንተ አምላኬ ነህና፥
«ገናና ሁን» እያልኩ ከፍ ከፍ አደርግሃ
ለሁ።
29 ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርቡለት፤
እርሱ ቸር ነው፤ፍቅሩም ለዘላለም ጸንቶ
ይኖራል።

# መዝሙር 119

## አሌፍ

1 በአኗኗራቸው ነውር የሌለባቸው፥የእግ
ዚአብሔርን ሕግ የሚከተሉ የተባረኩ
ናቸው። 2 ሥርዓቶቹን የሚጠብቁና በፍጹም
ልባቸው እርሱን የሚሹት የተባረኩ ናቸው።
3 ክፉ የሆነውን ነገር ከቶ አያደርጉም፤በእግ
ዚአብሔር መንገድ ይሄዳሉ እንጂ። 4 አቤቱ፥
አንተ ሊፈጸሙ የሚገባቸውን መመሪያዎች
ሰጠህ። 5 ድንጋጌዎችህን በማክበር ምነው
ጸንቼ ለመኖር የምችል በሆንኩ! 6 እንዲህ
ከሆነ፥ትእዛዛትህን ሁሉ ሳሰላስላቸው የማፍ
ርበት ምክንያት አይኖርም። 7 እውነተኛ
የሆነውን ሕግህን ስለማውቅ በቅን ልቦና
አመሰግንሃለሁ። 8 ድንጋጌዎችህን አክብሬ
ስለምፈጽም ፈጽመህ አትተወኝ።

## ቤት

9 ጐልማሳ ከነውር ንጹሕ ሆኖ ለመኖር
የሚችለው እንዴት ነው? ቃልህን ተከትሎ
ለመኖር ፈቃደኛ ሲሆን ነዋ! 10 አቤቱ፥በፍ
ጹም ልቤ አንተን እሻሃለሁና ከትእዛዛትህ
ወጥቼ እንድሳሳት አታድርገኝ። 11 በአንተ
ላይ በደል ከመፈጸም እርቅ ዘንድ ቃልህን

በልቤ ውስጥ ሰውሬ አኖርሁ። 12አሁንም
እግዚአብሔር ሆይ፥አንተ ቡሩክ ነህና ድን
ጋጌዎችህን አስተምረኝ። 13በቃልህ የተሰ
ጡትን ሕጎች ሁሉ እኔም እየመላለስሁ እደ
ግማቸዋለሁ። 14ብዙ ሀብት ያገኘ ሰው
ታላቅ ደስታ እንደሚሰማው ሁሉ፥እኔም
ሥርዓቶችህን በመከተል እጅግ ደስ ይለ
ኛል። 15መመሪያዎችህን በተመስጦ አሰላስ
ላቸዋለሁ፤መንገዶችህን በማስተዋል እመረ
ምራቸዋለሁ። 16በድንጋጌዎችህ እደሰታ
ለሁ፤ቃልህንም ችል አልልም።

## ጋሜል

17ለእኔ ለአገልጋይህ መልካሙን አድርግ
ልኝ፤እኔም እኖራለሁ፤ለቃልህ እታዘዛለሁ።
18በሕግህ ውስጥ ያሉትን አስደናቂ ምስጢ
ሮች ለመረዳት እችል ዘንድ ዓይነ ልቡናዬን
ክፈትልኝ። 19እኔ በዚህ ዓለም እንግዳ ነኝና
ትእዛዛትህን አትሰውርብኝ። 20ነፍሴ ሕግ
ህን እጅግ አድርጋ ትናፍቃለች። 21ከትእዛዛ
ትህ ወጥተው በስሕተት ጐዳና የሚራመዱ
ትን የተረገሙ እብሪተኞች ትዘልፋቸዋለህ።
22ሥርዓቶችህን ጠብቄአለሁና ንቀትና ውር
ደትን ከእኔ ዘንድ አርቅልኝ። 23መሳፍንቱ
ተባብረው ቢያሙኝ እንኳ፥እኔ አገልጋይህ
ድንጋጌዎችህን ከማሰላሰል ወደ ኋላ አል
ልም። 24ሥርዓቶችህ ከልብ ያስደስቱኛል፤
አማካሪ ሆነው ያገለግሉኛል።

## ዳሌጥ

25እነሆ፥እኔ ከትቢያ ጋር እስክጣበቅ
ድረስ ተዋርጃለሁና በቃልህ ሕይወቴን
አድስ። 26ያኗኗሬን ነገር ዘርዝሬ አመለከት
ሁህ፤አንተም መልስ ሰጠኸኝ። አቤቱ፥ድን
ጋጌዎችህን አስተምረኝ። 27የመመሪያዎች
ህን ምስጢር እንዳስተውል አድርገኝ፤እኔም
ተአምራትህን ለማሰላሰል የበቃሁ እሆና
ለሁ። 28ነፍሴ በኀዘን ደክማለችና እንደ
ቃልህ አጠንክረኝ። 29በሽንገላ ከመኖር
ጠብቀኝ፤ ሕግህንም እንድፈጽም እርዳኝ።
30የእውነትን መንገድ ለመከተል መርጫ
ለሁ፤ ልቡናዬን በሕግህ ላይ አሳርፌአለሁ።
31እግዚአብሔር ሆይ፥በሥርዓቶችህ ጸንቼ
እገኛለሁና አታሳፍረኝ። 32ለልቡናዬ ነጻነት
ሰጥተኸኛልና፥በትእዛዛትህ መንገድ በሙሉ
ልቤ እጓዛለሁ።

## ሔ

33እግዚአብሔር ሆይ፥ ድንጋጌዎችህን
እከተል ዘንድ አስተምረኝ፤ እኔም እስከ
መጨረሻው እጠብቃቸዋለሁ። 34ሕግህን
እፈጽም ዘንድ ማስተዋልን ስጠኝ፤በፍጹም
ልቤም እጠብቀዋለሁ። 35በትእዛዛትህ መን
ገድ እሄድ ዘንድ ምራኝ፤በዚያ ተድላ ደስ
ታን አገኛለሁና። 36ልቡናዬ ወደ ግል
ጥቅም ሳይሆን ወደ ሥርዓቶችህ እንዲያዘነ
ብል አድርግ። 37ዓይኖቼን የማይረባ ነገር
ከማየት መልሳቸው። በቃልህ ሕያው አድር
ገኝ። 38ሌሎች አይተው ይፈሩህ ዘንድ
ለእኔ ለአገልጋይህ የሰጠኸውን የተስፋ ቃል
ፈጽም። 39ሕጎችህ መልካም ናቸውና ከም
ፈራው ውርደት አድነኝ። 40መመሪያዎች
ህን ከልብ ስለምናፍቃቸው አቤቱ፥ሕይወ
ቴን በጽድቅህ አድስ።

## ዋው

41እግዚአብሔር ሆይ፥የማይለወጠውን
ፍቅርህን አሳየኝ፤እንደ ተስፋ ቃልህም ቤዛ
ሆነህ አድነኝ። 42እኔም በቃልህ እንደ
መተማመኔ መጠን ለሚያፌዙብኝ መልስ
ልሰጣቸው እችላለሁ። 43እምነቴን በሕግህ
ላይ ጥያለሁና የእውነትን ቃል ከአንደበቴ
አታርቅብኝ። 44ዘወትር፥ለዘላለምም ለሕ
ግህ እታዘዛለሁ። 45መመሪያዎችህን ልከ
ተል የምፈልግ በመሆኔ እነሆ እንደ ልቤ
በነጻነት እኖራለሁ። 46ስለ ሥርዓቶችህ በነ
ገሥታት ፊት ሳላፍር እመሰክራለሁ።
47ትእዛዛትህን ስለምወዳቸው በእነርሱ ደስ
ታን አገኛለሁ። 48የምወዳቸውን ትእዛዛት
ህን አከብራለሁ፤ ሥርዓቶችህንም አሰላስላ
ለሁ።

## ዛይ

49ለእኔ ለአገልጋይህ ተስፋ ሰጥተኸኛ
ልና አቤቱ፥ቃልህን አትዘንጋ። 50በመከ
ራዬ ጊዜ የሚያጽናናኝ፥ «በሰጠኸኝ የተ
ስፋ ቃል ሕይወቴን ታድስልኛለህ» የሚ
ለው እምነቴ ነው። 51እብሪተኞች ያለመ
ጠን ቢሣለቁብኝም እኔ ግን ከሕግህ ዝንፍ
አልልም። 52እግዚአብሔር ሆይ፥ከጥንት
ጀምሮ ጸንቶ የቈየውን ሕግህን አስታውሳ
ለሁ፤ በእርሱም መጽናናትን አገኛለሁ።
53ሕግህን በተዉ በክፉዎች አድራጎት
ምክንያት በብስጭት ላይ ወደቅሁ።
54በደረስኩበት ስፍራ ሁሉ የምዘምረው
ስለ ድንጋጌዎችህ ነው። 55እግዚአብሔር
ሆይ፥በሌሊት ሳይቀር ስምህን አስታውሳ
ለሁ፤ ሕግህንም እጠብቃለሁ። 56መመሪያ
ዎችህን ተከትዬ መፈጸም የዕለት ተግባሬ
ሆኖልኛል።

## ሔት

57 እግዚአብሔር ሆይ ፥ አንተ ለእኔ ድር
ሻዬ ነህ ፤ እኔም ለቃልህ ልታዘዝ ቃል ገብቻ
ለሁ ። 58 ፊትህን ለማየት በፍጹም ልቤ ፈለ
ግሁ ፤ በተስፋ ቃልህ ቸርነትህን አድርግ
ልኝ ። 59 አኗኗሬን ካመዛዘንኩ በኋላ አካሄ
ዴን ወደ ሥርዓቶችህ አቃናሁ ። 60 ትእዛዛ
ትህን ለመፈጸም እፋጠናለሁ እንጂ አልዘገ
ይም ። 61 ክፉዎች በገመድ ቢተበትቡኝ
እንኳ ፥ ሕግህን ከቶ አልረሳም ። 62 ጽድቅ
ስለ ሆነው ሕግህ ምስጋናዬን አቀርብልህ
ዘንድ በእኩለ ሌሊት እነሣለሁ ። 63 ለሚፈሩ
ህና መመሪያዎችህን ለሚከተሉ ሁሉ እኔ
ባልንጀራቸው ነኝ ። 64 ጌታ ሆይ ፥ ምድር
በፍቅርህ ተሞልታለች ፤ ድንጋጌዎችህን አስ
ተምረኝ ።

## ጤት

65 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ለእኔ ለአገልጋይህ
እንደ ቃልህ መልካሙን ነገር አድርግልኝ ።
66 በትእዛዛትህ ስለማምን ፥ እነርሱን የማስተ
ውልበትን ዕውቀትና የማመዛዝንበትን ትክ
ክለኛ ዳኝነት አስተምረኝ ። 67 መከራ ላይ
ከመውደቄ በፊት በስሕተት መንገድ እሄድ
ነበር ፤ አሁን ግን ለቃልህ እታዘዛለሁ ።
68 አንተ ቸር ነህ ፤ የምታደርገውም የቸርነት
ሥራ ነው ። አቤቱ ፥ ስለ ድንጋጌዎችህ አስተ
ምረኝ ። 69 እብሪተኞች ስሜን በሐሰት ቢያ
ጐድፉትም እኔ ግን መመሪያዎችህን በፍ
ጹም ልቤ እጠብቃለሁ ። 70 የእነርሱ ልብ
ፈጽሞ የደነደነ ነው ፤ እኔን ግን ሕግህ ከልብ
ያስደስተኛል ። 71 በመከራ መጨነቄ ጠቅሞ
ኛል ፤ ድንጋጌዎችህን ለመማር አብቅቶኛል ።
72 በብዙ ሺህ ከሚቈጠር የብርና የወርቅ
ሀብት ይልቅ በቃልህ የተነገረው ሕግ ለእኔ
የበለጠ ዋጋ አለው ።

## ዮድ

73 እጆችህ የሠሩኝና የቀረጹኝ ስለ ሆኑ
አቤቱ ፥ ትእዛዛትህን ዐውቅ ዘንድ ማስተዋ
ልን ስጠኝ ። 74 እምነቴን በቃልህ ላይ ጥያለ
ሁና የሚፈሩህ ሁሉ እኔን በሚያዩበት ጊዜ
ደስ ይበላቸው ። 75 እግዚአብሔር ሆይ ፥
ሕግህ ጽድቅ መሆኑን ዐውቃለሁ ፤ በመከራ
የምትቀጣኝም ከታማኝነትህ የተነሣ ነው ።
76 ለእኔ ለአገልጋይህ በሰጠኸኝ የተስፋ ቃል
መሠረት የማይለወጠው ፍቅርህ አጽናኜ
ይሁን ። 77 ሕግህ ተድላ ደስታዬ ነውና በሕ
ይወት እኖር ዘንድ ቸርነትህ ከእኔ አይለይ ።
78 እብሪተኞች በእኔ ላይ ያለምክንያት በሚ
ያደርሱብኝ ጥቃት ይፈሩ ፤ እኔ ግን መመሪያ
ዎችህን አሰላስላለሁ ። 79 አንተን የሚፈሩና
ሥርዓቶችህን አስተውለው የተረዱ ሁሉ
እኔን ይቅረቡ ። 80 በኀፍረት ላይ እንዳልወ
ድቅ በድንጋጌዎችህ ልቤ ንጹሕ ይሁን ።

## ካፍ

81 ቤዛነትህን ከመናፈቅ የተነሣ ነፍሴ
ዛለች ፤ እኔ ግን አሁንም በቃልህ ላይ እምነ
ቴን እንደ ጣልሁ ነኝ ። 82 የተስፋ ቃልህን
በመጠባበቅ ዓይኖቼ ፈዘዙ ፤ «ለመሆኑ የም
ታጽናናኝ መቼ ነው?» አልሁ ። 83 በጢስ
የሚታጠን የማር ስልቻ ብመስልም ድንጋጌ
ዎችህን አልረሳሁም ። 84 የሚያሳድዱኝን
የምትቀጣቸው መቼ ነው? አገልጋይህስ
ፍርድህን በመጠባበቅ የምቈየው እስከ መቼ
ነው? 85 እብሪተኞች ሕግህን በመቃረን እኔ
የምወድቅበትን ስውር ጕድጓድ ይቈፍ
ራሉ ። 86 ትእዛዛትህ ሁሉ እምነት የሚጣል
ባቸው ናቸው ። እነሆ ፥ ሰዎች ያለምክንያት
እያሳደዱኝ ነውና እርዳኝ ። 87 ከምድር ገጽ
ሊያጠፉኝ ምንም ያህል አልቀራቸውም ፤
እኔ ግን መመሪያዎችህን መከተሌን አልተ
ውሁም ። 88 አቤቱ ፥ በፍቅርህ ሕይወቴን
ተከባክበህ ጠብቅ ፤ እኔም በቃልህ ለገለጽካ
ቸው ሥርዓቶችህ እታዘዛለሁ ።

## ላሜድ

89 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ቃልህ ዘላለማዊ
ነው ፤ በሰማያትም ጸንቶ ያለ ነው ። 90 ታማኝ
ነትህ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ
ይኖራል ። አንተ ምድርን መሠረትሃት ፤ እርስ
ዋም ጸንታ ትኖራለች ። 91 ሕግህ እስከ ዛሬ
ጸንቶ ይገኛል ፤ ሁሉም ነገር አንተን እንዲያ
ገለግል የተዘጋጀ ነው ። 92 ሕግህ ተድላ ደስ
ታዬ ባይሆንኝ ኖሮ ከመከራዬ የተነሣ ሞቼ
በቀረሁ ነበር ። 93 በመመሪያዎችህ ሕይወ
ቴን አድስሀልኛልና ፥ እነርሱን ምን ጊዜም
አልረሳም ። 94 የአንተ ነኝና አድነኝ ፤ መመሪ
ያዎችህንም ስፈልጋቸው ኖሬአለሁ ።
95 ክፉዎች ሊያጠፉኝ አድብተው እየተጠባ
በቁኝ ናቸው ፤ እኔ ግን ሥርዓቶችህን አሰላስ
ላቸዋለሁ ። 96 የማንኛውም ነገር ፍጹምነት
ዳር ድንበር እንዳለው ተገንዝቤአለሁ ፤ የአ
ንተ ትእዛዛት ግን ወሰን የላቸውም ።

## ሜም

97 አቤቱ ፥ ሕግህን ምንኛ እወደዋለሁ!
ቀኑን ሙሉ እርሱን ሳሰላስል እውላለሁ ።

98 ትእዛዛትህ ምን ጊዜም ከአእምሮዬ ስለማ
ይለዩ ከጠላቶቼ ይበልጥ አስተዋይ አድርገ
ውኛል። 99 ሥርዓቶችህን ስለማሰላሰላቸው
ከአስተማሪዎቼ ሁሉ የበለጠ አስተዋይ ለመ
ሆን በቅቻለሁ። 100 ለመመሪያዎችህ ስለም
ታዘዝ ከሽማግሌዎች ይልቅ ብልህ ሆኛ
ለሁ። 101 ለቃልህ እታዘዝ ዘንድ እግሮቼን
ከማንኛውም ክፉ መንገድ አርቄአለሁ።
102 አንተ ስላስተማርኸኝ ከሕግህ ዝንፍ አላ
ልኩም። 103 የተስፋ ቃልህ ምንኛ ይጥመ
ኛል! ከማር ወለላ ይልቅ ይጣፍጠኛል።
104 ከመመሪያዎችህ ማስተዋልን አግኝቻ
ለሁ፤ከዚህ የተነሣ የጥፋትን መንገድ ሁሉ
ጠላሁ።

## ኖን

105 ቃልህ ለእግሬ ፋና ፣ ለመንገዴም
መብራት ነው። 106 ጽድቅ የሆነውን ሕግ
ህን ለመከተል ምያለሁ፤መሐላዬንም አጽን
ቻለሁ። 107 እግዚአብሔር ሆይ፣እጅግ ተሠ
ቃይቻለሁና እንደ ቃልህ ሕይወቴን አድስ።
108 ጌታ ሆይ ፣ እንደበቴ የሚያቀርብልህን
ምስጋና ተቀበል ፤ ሕግህንም አስተምረኝ።
109 ነፍሴ ምን ጊዜም በእጅህ ስለ ሆነች
ሕግህን ከቶ አልረሳም። 110 ክፉዎች በእኔ
ላይ ወጥመዳቸውን አዘጋጅተዋል፤እኔ ግን
ከመመሪያዎችህ ዝንፍ አላልኩም።
111 ሥርዓቶችህ የዘላለም ውርሴ ሆነው ይኖ
ራሉ ፤ እነርሱም የልቤ ደስታ ናቸው።
112 ድንጋጌዎችህን እስከ መጨረሻው ለመ
ጠበቅ ልቦናዬ ተዘጋጅቷል።

## ሳምኬት

113 አሳባቸው መንታ የሆኑ ሰዎችን
ጠላሁ ፤ ሕግህን ግን ወደድሁ። 114 አንተ
መጠጊያዬና ጋሻዬ ነህ፤እምነቴን በቃልህ
ላይ ጥያለሁ። 115 እናንት ክፉ አድራጊ
ዎች ፣ የፈጣሪዬ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት
እፈጽም ዘንድ ከእኔ ራቁ! 116 በተስፋ
ቃልህ ጠብቀኝ፤እኔም እኖራለሁ። አቤቱ፣
ለአንተ ባለኝ እምነት አልፈር። 117 ደግ
ፈኝ፤እኔም እድናለሁ፤ድንጋጌዎችህን በጥ
ሞና አሰላስላለሁ። 118 ከድንጋጌዎችህ
ርቀው የሚሳሳቱትን ሁሉ «ወግዱ!» ብለህ
መለስሃቸው፤የመሸንገል ድካማቸው ከንቱ
ነው። 119 በምድር ላይ የሚኖሩ ክፉዎችን
ሁሉ እንደ ጥራጊ ታስወግዳቸዋለህ፤ስለዚህ
ሥርዓቶችህን እወዳቸዋለሁ። 120 አንተን
በመፍራት ሥጋዬ ይንቀጠቀጣል፤ፍርድህም
ያስደነግጠኛል።

## ዔ

121 ጽድቅና ቅን የሆነውን ነገር አድርጌ
አለሁና በሚጨቍኑኝ እጅ እንድሠቃይ
አትተወኝ። 122 የእኔን የአገልጋይህን ደኅን
ነት አጽና፤እብሪተኞች እንዲጨቍኑኝ አት
ፍቀድላቸው። 123 ቤዛነትህን ፣ ያን በጽድቅ
የሰጠኸኝን የተስፋ ቃልህን በመጠባበቅ ዓይ
ኖቼ ፈዘዙ። 124 ለእኔ ለአገልጋይህ የምታደ
ርግልኝ ሁሉ በፍቅርህ መጠን ይሁን፤ድንጋ
ጌዎችህንም አስተምረኝ። 125 እኔ አገልጋ
ይህ ነኝና ሥርዓቶችህን አስተውላቸው
ዘንድ የአእምሮ ብስለት ለግሰኝ። 126 እግዚ
አብሔር ሆይ ፣ ሰዎች ሕግህን እየሻሩ ስለ
ሆነ ኃይልህን የምታሳይበት ጊዜው አሁን
መሆኑን ይወቁ። 127 ትእዛዛትህን ከወርቅና
ከዕንቁ ይልቅ ስለምወዳቸው ፣ 128 መመሪያ
ዎችህን ሁሉ አመዛዝኜ ቀና ሆነው ስላገኘ
ኋቸው ፣ ከማንኛውም ጠማማ መንገድ
ራቅሁ።

## ፌ

129 ሥርዓቶችህ አስደናቂዎች ስለ ሆኑ
ለእነርሱ እታዘዛለሁ። 130 የቃሎችህ ትር
ጓሜ ብርሃንን ይሰጣል፤በአእምሮአቸው ላል
በሰሉትም ማስተዋልን ያድላል። 131 ለትእዛ
ዛትህ ካለኝ ጽኑ ናፍቆት የተነሣ በጉጉት፣
አፉን ከፍቶ እንደሚያለከልክ ሰው ሆንሁ።
132 ስምህን ለሚወዱ ምን ጊዜም እንደምታ
ደርገው ሁሉ ፣ አሁንም አቤቱ ፣ ወደ እኔ
ተመለስ፤ማረኝም። 133 አረማመዴን በቃልህ
አቅናልኝ፤ኃጢአት አይግዛኝ። 134 ለመመሪ
ያዎችህ እታዘዝ ዘንድ ከሰዎች ጭቈና አድ
ነኝ። 135 ፊትህ በእኔ በአገልጋይህ ላይ
ያብራ ፤ ድንጋጌዎችህንም አስተምረኝ።
136 ሕግህ በሰዎች ዘንድ ባለመከበሩ እንባዬ
እንደ ጐርፍ ፈሰሰ።

## ጻዴ

137 እግዚአብሔር ሆይ ፣ አንተ ጻድቅ
ነህ ፤ ሕግህም የቀና ነው። 138 ሥርዓቶችህ
ጽድቅ ስለ ሆኑ እምነት የሚጣልባቸው
ናቸው። 139 ጠላቶቼ ቃልህን ስለሚያቃ
ልሉ ለአንተ ካለኝ ቅንዓት የተነሣ ተቃጠ
ልኩ። 140 የተስፋ ቃሎችህ ተፈትነው የነ
ጠሩ ናቸው ፤ እኔ አገልጋይህም እወዳቸዋ
ለሁ። 141 የተዋረድሁና የተናቅሁ ብሆንም
መመሪያዎችህን ከቶ አልረሳቸውም።
142 ጽድቅህ ዘላለማዊ ፣ ሕግህም እውነተኛ
ነው። 143 መከራና ኀዘን ተደራርበውብ

ኛል፤ትእዛዛትህ ግን ተድላ ደስታዬ ሆነው
ያጽናኑኛል። 144 ሥርዓቶችህ ለዘላለም ቅን
እንደ ሆኑ ይኖራሉ። አቤቱ ፥ በሕይወት
እኖር ዘንድ እነርሱን የማስተውልበትን አእ
ምሮ ስጠኝ።

## ቆፍ

145 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ከልቤ እየጠራ
ሁህ ነኝና መልስልኝ፤እኔም ለድንጋጌዎ
ችህ እታዘዛለሁ። 146 ወደ አንተ እየጮህኩ
የማቀርብልህን ጥሪ ሰምተህ አድነኝ፤እኔም
ሥርዓቶችህን እጠብቃለሁ። 147 ጐሕ ሳይ
ቀድ ተነሥቼ «ድረስልኝ» እያልሁ እጣራ
ለሁ ፤ እምነቴን በቃልህ ላይ ጥያለሁ።
148 የሰጠሃቸውን የተስፋ ቃሎች ለማሰላ
ሰል እችል ዘንድ ሌሊቱን በሙሉ እንደ
ነቃሁ አድራለሁ። 149 በፍቅርህ መጠን
የልመናዬን ቃል ስማ፤እንደ ሕግህም ሕይ
ወቴን አድስ። 150 የክፋትን ሥራ ለመፈ
ጸም ሤራ የሚያውጠነጥኑ ሁሉ ለእኔ ቅር
ቦቼ፥ከሕግህ ግን የራቁ ናቸው። 151 እግዚ
አብሔር ሆይ፥አንተ ግን ቅርብ ነህ፤ትእዛዛ
ትህም ሁሉ እውነት ናቸው። 152 ሥርዓቶ
ችህ ለዘላለም የጸኑ ሆነው እንዲኖሩ የመሠ
ረትሃቸው መሆናቸውን ከረዥም ጊዜ
በፊት ዐወቅሁ።

## ሬስ

153 ሕግህን አልረሳሁምና ሥቃዬን ተመ
ልከተህ አድነኝ። 154 ስለ ቆምኩለት ዓላማ
ተከላከልልኝ ፤ እኔንም አድነኝ ፤ በተስፋ
ቃልህ ሕይወቴን አድስ። 155 ክፉዎች ድን
ጋጌዎችህን መከተል ስለማይፈልጉ ፥ ቤዛነ
ትህ ከእነርሱ የራቀ ነው። 156 እግዚአብ
ሔር ሆይ ፥ ርኅራኄህ ታላቅ ነውና በሕግህ
ሕይወቴን አድስ። 157 የሚያሳድዱኝ ጠላ
ቶቼ ብዙዎች ቢሆኑም ከሥርዓቶችህ ፈቀቅ
አላልሁም። 158 ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች
ለቃልህ ስለማይታዘዙ በመጸየፍ እመለከታ
ቸዋለሁ። 159 መመሪያዎችህን የቱን ያህል
እንደምወዳቸው አይተህ አቤቱ ፥ በፍቅርህ
መጠን ሕይወቴን ጠብቀህ አቈይ። 160 ቃሎ
ችህ ሁሉ እውነት፥የጽድቅ ሕጎችህም የዘላ
ለም ናቸው።

## ሳን

161 ገዢዎች ያለምክንያት ያሳድዱኛል፤
ልቤ ግን ቃልህን ሲሰማ በፍርሃት ይንቀጠ
ቀጣል። 162 ታላቅ ምርኮ እንዳገኘ ሰው
በተስፋ ቃልህ እጅግ ደስ ይለኛል። 163 የሐ
ሰትን ነገር እጠላለሁ ፤ እጸየፋለሁ ፤ ሕግህን
ግን እወዳለሁ። 164 ጽድቅ ስለ ሆነው ሕግህ
በቀን ሰባት ጊዜ አወድስሃለሁ። 165 ሕግህን
የሚወዱ ፍጹም ሰላም ያገኛሉ ፤ ሊያደናቅ
ፋቸውም የሚችል አንዳች ነገር የለም።
166 እግዚአብሔር ሆይ፥ቤዛነትህን እጠባበቃ
ለሁ፤ትእዛዛትህንም እፈጽማለሁ። 167 ለሥር
ዓቶችህ እጅግ ከፍ ያለ ፍቅር ስላለኝ አክ
ብሬ እፈጽማቸዋለሁ። 168 የኑሮ ዓላማዎቼ
ሁሉ በአንተ ዘንድ በግልጽ የታወቁ ስለ
ሆኑ ለመመሪያዎችህና ለሥርዓቶችህ እታዘዛ
ለሁ።

## ታው

169 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ጸሎቴ ከፊትህ
ይድረስ፤እንደ ቃልህም ማስተዋልን ስጠኝ።
170 ልመናዬ ከፊትህ ይቅረብ፤እንደ ተስፋ
ቃልህም ከችግሬ አውጣኝ። 171 ድንጋጌዎ
ችህን ስለምታስተምረኝ ከከንፈሮቼ የውዳሴ
ቃል ተትረፍርፎ ፈሰሰ። 172 ትእዛዛትህ
ሁሉ ጽድቅ በመሆናቸው አንደበቴ ስለ
ቃልህ ይዘምር። 173 መመሪያዎችህን መር
ጫለሁና እጅህ እኔን ለመርዳት የተዘጋጀ
ይሁን። 174 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ቤዛነትህን
ናፍቄአለሁ ፤ ሕግህ ተድላ ደስታዬ ነው።
175 አወድስህ ዘንድ በሕይወት ልኑር ፤ ሕግ
ህም በኑሮዬ ይደግፈኝ። 176 እንደ ጠፋ በግ
ስለ ባዘንኩ እኔን አገልጋይህን ፈልገኝ፤ትእዛ
ዛትህን አልረሳሁምና።

# መዝሙር 120

1 በመከራዬ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራ
ሁት፤እርሱም መለሰልኝ። 2 አቤቱ፥በአንደበ
ታቸው ከሚዋሹና በንግግራቸው ከሚያታ
ልሉ ሰዎች አድነኝ።
3 አንተ የሚሸነግል ምላስ ያለህ ሰው ፥
እግዚአብሔር ምን ያደርግህ ይሆን? ከዚህስ
የባሰ ምን ነገር ያመጣብህ ይሆን? 4 በጦረኛ
የሰላ ፍላጻና በሚንቀለቀል የግራር ፍም
ይቀጣሃል።
5 መቀመጫዬን በሜሴክ ስላደረግሁና
በቄዳር መንደር ስለምኖር ወዮልኝ! 6 ሰላ
ምን በሚጠሉ መካከል ለረዥም ጊዜ ኖሬአ
ለሁ። 7 እኔ የሰላም ሰው ነኝ፤እኔ ስለ ሰላም
ስናገር ፥ እነርሱ ጦርነት ደጋፊ ሆነው ይገ
ኛሉ።

# መዝሙር 121

1 «እርዳታ የማገኘው ከወዴት ይሆን?»
እያልኩ ዓይኖቼን ወደ ተራራዎች አቅንቼ

እመለከታለሁ። 2እርዳታ የማገኘው ሰማይ
ንና ምድርን ከፈጠረው ከእግዚአብሔር
ነው።
3እርሱ፥ እግርህ እንዲንሸራተት አያደር
ግም፤ ጠባቂህ የሆነው አምላክ አያንቀላ
ፋም። 4አዎን፥ የእስራኤል ሕዝብ ጠባቂ
አያንቀላፋም፤አይተኛም።
5እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፤ እግዚአብ
ሔር በቀኝህ ይቆምልሃል፤ 6በቀን ፀሐይ
አያቃጥልህም፤ሌሊት በጨረቃ ጉዳት አያገ
ኝህም።
7እግዚአብሔር ከጉዳት ሁሉ ይጠብቅ
ሃል፤ እርሱ ሕይወትህን ይጠብቃል።
8አመጣጥህንና አካሄድህን በውጪም በቤ
ትም ይጠብቃል፤ዛሬም፥ዘወትርም፥ለዘላለ
ሙም።

## መዝሙር 122

1ሰዎች፥ «ወደ እግዚአብሔር ቤት እን
ሂድ!» ባሉኝ ጊዜ እጅግ ደስ አለኝ። 2ኢየ
ሩሳሌም ሆይ፥ እግሮቻችን በበርሽ ደጃፍ
ላይ ቆመዋል።
3ኢየሩሳሌም፥ ተገጥግጣ እንደ ታነፀች
ከተማ ናት። 4የእግዚአብሔር ወገን የሆኑት
ነገዶች ወደ እርሷ ይወጣሉ፤እዚያም ለእስ
ራኤል የተሰጠውን ሥርዓት ተከትለው የእ
ግዚአብሔርን ስም ያወድሳሉ። 5ሕዝቡን
ለመዳኘት የዳዊት ቤት የፍርድ ዙፋኖች
በዚያ ተዘርግተዋል።
6ለኢየሩሳሌም ሰላም እንዲህ እያላችሁ
ጸልዩ፦ «አንቺን የሚወዱ ሁሉ ደኅንነታ
ቸው የተረጋገጠ ይሁን። 7በቅጥሮችሽ
ክልል ውስጥ ሰላም፥በአዳራሾችሽም ጸጥታ
ይስፈን።» 8ስለ ወንድሞቼና ስለ ባልንጀ
ሮቼ ስል፥ «ሰላም ይኑርሽ» እላለሁ። 9ለፈ
ጣሪያችን ለእግዚአብሔር ቤት ስል ብልጽ
ግናሽን እሻለሁ።

## መዝሙር 123

1አቤቱ፥ ዙፋንህ በሰማይ ወደ ሆነው
ወደ አንተ ዓይኖቼን አቅንቼ እመለከታ
ለሁ። 2አሽከር የጌታውን እጅ እንደሚመለ
ከት፥ ገረድም የእመቤትዋን እጅ እንደምት
መለከት፥ ምሕረቱን እስኪያደርግልን ድረስ
ዓይኖቻችን ወደ ፈጣሪያችን ወደ እግዚአብ
ሔር ይመለከታሉ።
3እግዚአብሔር ሆይ፥ ማረን፤ ብዙ ውር
ደት ታግሠን አሳልፈናልና ይቅር በለን።
4የትዕቢተኞችን ሽሙጥ፥ የእብሪተኞችንም
ንቀት ታግሠን ቈይተናል።

## መዝሙር 124

1የእስራኤል ሕዝብ እንዲህ ይበል፦
«እግዚአብሔር አጋራችን ባይሆን ኖሮ፥
2ሰዎች ሊያጠቁን በተነሡብን ጊዜ እግዚአ
ብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ፥ 3ቍጣ
ቸው በላያችን በነደደ ጊዜ ከነነፍሳችን በዋ
ጡን ነበር፤ 4የውሃ ሙላት ባሰጠመን
ነበር፤ ኃይለኛ ወራጅ ውሃ ባጥለቀለቀን
ነበር፤ 5የሚያስገመግመው ጐርፍ ጠራርጎ
ይዞን በሄደ ነበር።»
6በጥርሳቸው ዘነጣጥለው እንዳይጥሉን
ያደረገ አምላክ ይመስገን። 7ከአዳኝ ወጥ
መድ ሾልካ እንደምትወጣ ወፍ አመለጥን።
አዎን፥ወጥመዱ ተሰበረ፤እኛም አመለጥን።
8እርዳታ የምናገኘው ሰማይንና ምድርን
በፈጠረ በእግዚአብሔር ስም ነው።

## መዝሙር 125

1በእግዚአብሔር የሚታመኑ፥እንደማት
ናወጠውና ለዘላለም ጸንታ እንደምትኖረው
የጽዮን ተራራ ናቸው። 2ኢየሩሳሌምን ተራ
ሮች እንደ ከበቧት ሁሉ፥እግዚአብሔርም
በሕዝቡ ዙርያ ሆኖ ዛሬም ለዘላለሙም
ይጠብቃቸዋል።
3ለጻድቃን መኖሪያ እንድትሆን በተመደ
በችው አገር ላይ የኃጢአተኞች በትረ መንግ
ሥት ጸንቶ አይቈይም። አለበለዚያ ጻድቃን
እጃቸውን ከፉ ነገር ለማድረግ ያነሣሉ።
4እግዚአብሔር ሆይ፥ ለደጋጎችና ቅን
ልቦና ላላቸው ሰዎች መልካሙን ነገር አድ
ርግላቸው። 5ወደ ጠማማ መንገድ የሚያመ
ሩትን ግን እግዚአብሔር ከክፉ አድራጊ
ዎች ጋር ይቀጣቸዋል።
ሰላም ለእስራኤል ሕዝብ ይሁን።

## መዝሙር 126

1ተማርከው የተሰደዱትን፥እግዚአብሔር
ወደ ጽዮን መልሶ ሲያመጣቸው ነገሩ
ሕልም እንጂ እውነት አልመሰለንም።
2በዚያን ጊዜ አፋችን በሣቅ፥ አንደበታች
ንም በደስታ ዝማሬ ተሞላ። በአሕዛብ
ዘንድ፥ «እግዚአብሔር ታላቅ ነገር አደረገላ
ቸው» ተብሎ ተነገረ። 3አዎን፥እግዚአብ
ሔር እጅግ የሚያስደስት ታላቅ ነገር አድር
ጎልናል።
4እግዚአብሔር ሆይ፥በነጌብ በረሃ ያሉ
ወንዞች ዝናብ ሲጥል እንደሚሞሉ የእኛ
ንም የቀድሞ ኑሮ መልሰህ የተሟላ አድርግ
ልን። 5በለቅሶ የሚዘሩ፥የደስታ መዝሙር

ረጹ ፥ ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ናቸው።
16 አፍ አላቸው መናገር አይችሉም ፤ ዓይን
አላቸው ፥ ማየት አይችሉም ፤ 17 ጆሮ አላ
ቸው ፥ መስማት አይችሉም ፤ በአፋቸው
ውስጥ እስትንፋስ እንኳ የለም። 18 እነዚህን
ጣዖቶች የሚሠሩና በእነርሱ የሚተማመኑ
ሁሉ እንደ ሥሯቸው ጣዖቶች ናቸው።
19 የእስራኤል ወገኖች ሆይ ፥ እግዚአብሔ
ርን አወድሱ ፤ የአሮን ወገኖች ሆይ ፥ እግዚአ
ብሔርን አወድሱ ፤ 20 የሌዊ ወገኖች ሆይ ፥
እግዚአብሔርን አወድሱ ፤ እርሱን የምትፈሩ
ሁሉ ፥ እግዚአብሔርን አወድሱ። 21 በኢየሩሳ
ሌም ለሚኖረው አምላክ ለእግዚአብሔር
ከጽዮን ምስጋና ይድረሰው።
ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 136

1 ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርቡ ፤ እርሱ
ቸር ነውና።
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
2 ለአማልክት አምላክ ምስጋና አቅርቡ ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
3 ለጌቶች ጌታ ምስጋና አቅርቡ ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
4 እርሱ ብቻውን ታላላቅ ተአምራት ለሚያ
ደርገው ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
5 ሰማያትን በጥበቡ ለሠራ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
6 ምድርን በውሃ ላይ ለዘረጋ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
7 ታላላቅ ብርሃናትን ለፈጠረ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
8 ፀሐይ በቀን እንዲሠለጥን ላደረገ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
9 ጨረቃና ከዋክብት በሌሊት እንዲሠለጥኑ
ለወሰነ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
10 የግብጽን በኵሮች ሁሉ ለቀሠፈ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
11 የእስራኤልን ሕዝብ ከመካከላቸው ለይቶ
ላወጣ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
12 በኃያል እጁና በተዘረጋ ክንዱ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
13 የኤርትራን ባሕር ከሁለት ለከፈለ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
14 የእስራኤልን ሕዝብ በመካከሉ መርቶ
ላሳለፈ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
15 ፈርዖንንና ሠራዊቱን በኤርትራ ባሕር
ውስጥ ላሰጠመ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
16 ሕዝቡን በምድረ በዳ መካከል ለመራ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
17 ታላላቅ ነገሥታትን እየመታ ለጣለ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
18 ኃያላን ነገሥታትን ለገደለ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
19 የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
20 የባሳንን ንጉሥ ዐግን ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
21 አገራቸውን ርስት አድርጎ ለሰጠባቸው ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
22 ለአገልጋዮቹ ለእስራኤል ሕዝብ ላወረሳ
ቸው ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
23 ተዋርደን ሳለን ላሰበን ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
24 ከጠላቶቻችን እጅ ነጻ ላወጣን ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
25 ለፍጥረት ሁሉ የዕለት ምግቡን ለሚሰጥ ፥
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
26 ለሰማይ አምላክ ምስጋና አቅርቡለት።
ምሕረቱ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።

## መዝሙር 137

1 ተማርከን ሳለን በባቢሎን ወንዞች ዳር
ተቀምጠን ጽዮንን እስታውሰናት አለቀስን።
2 በገናዎቻችንን በአኻያ ዛፎች ላይ ሰቅለን
አኖርን። 3 የሚያስጨንቁን ማራኪዎቻችን
ግን ፥ «እስቲ ከጽዮን ዝማሬዎች አንዱን
አሰሙን» እያሉ የደስታ ዝማሬ እንድንዘም
ርላቸው አጥብቀው ወተወቱን።
4 ለመሆኑ በባዕድ አገር ሆነን የእግዚአብ
ሔርን ዝማሬ እንዴት አድርገን እንዘምራ
ለን? 5 አሁንም ኢየሩሳሌም ሆይ ፥ ብረሳሽ
ቀኝ እጄ ይዛልብኝ። 6 ባላስብሽና አንቺን
ከደስታዬ ሁሉ በላይ ባላደርግሽ ምላሴ ከት
ናጋዬ ጋር ይጣበቅ።
7 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ኢየሩሳሌም በጠ
ላት እጅ በወደቀችበት ቀን ኤዶማውያን ፥
«አፍርሷት! ከሥር ከመሠረቷ አፍርሷት!»
እያሉ ያስተጋቡትን ጩኸት አትዘንጋ።
8 ጨርሰሽ እንድትጠፊ የተፈረደብሽ
አንቺ ባቢሎን ፥ በእኛ ላይ የፈጸምሽውን
ግፍና በደል የሚበቀል ፥ 9 ልጆችሽንም ይዞ
በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው እርሱ የተመ
ሰገነ ነው።

## መዝሙር 138

1 እግዚአብሔር ሆይ ፥ ከልቤ አወድስሃ
ለሁ ፤ በአማልክት ፊት ቆሜ ውዳሴህን
በዜማ አሰማለሁ። 2 ስለ ፍቅርህና ስለ ታማ
ኝነትህ ቅዱስ በሆነው ቤተ መቅደስህ ፊት
ለፊት እሰግድልሃለሁ ፤ ስምህንም አወድሳ
ለሁ ፤ አንተ ስምህንና ቃልህን ከሁሉ በላይ
ገናና አድርገሃልና። 3 በጠራሁህ ጊዜ መለስ
ህልኝ፤ደፋርና ልበ ጽኑም አደረግኸኝ።
4 እግዚአብሔር ሆይ ፥ በዚህ ዓለም ያሉ
ነገሥታት ሁሉ ቃልህን በሚሰሙበት ጊዜ
ያወድሱህ። 5 አዎን፥የእግዚአብሔር ክብርና
ምስጋና ታላቅ ነውና የእግዚአብሔርን መን
ገድ እያሞገሱ ይዘምሩ።
6 እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ቢሆንም
ዝቅተኛውን ከመመልከት ቸል አይልም ፤
ትዕቢተኛውን ግን ከሩቅ ያውቀዋል።
7 አቤቱ ፥ በመከራ መካከል ባልፍ እንኳ
አንተ ሕይወቴን ትጠብቃለህ። በጠላቶቼ
ቍጣ ላይ እጅህን ትዘረጋለህ ፤ በቀኝህም
ታድነኛለህ። 8 እግዚአብሔር ያሰበልኝን
ይፈጽምልኛል። አቤቱ ፥ ፍቅርህ ለዘላለም
ጸንቶ የሚኖር ነውና የእጅህ ሥራ የሆኑትን
ፍጥረቶችህን ቸል አትበላቸው።

## መዝሙር 139

1 እግዚአብሔር ሆይ ፥ መረመርኸኝ ፤ ዐወ
ቅኸኝም። 2 የምቀመጥበትንና የምነሣበትን
ጊዜ ታውቃለህ ፤ የልቤን አሳብ ከሩቅ ጠል
ቀህ ትገነዘበዋለህ። 3 የምሄድበትንና የማርፍ
በትን ለይተህ ታስተውላለህ፤መንገዶቼ ሁሉ
በአንተ ዘንድ የታወቁ ናቸው። 4 እግዚአብ
ሔር ሆይ ፥ አንድ ቃል ከመናገሬ በፊት ፥
አንተ አስቀድመህ አሳቤን ታውቀዋለህ።
5 እነሆ አንተ ፥ እጅህን በላዬ አሳርፈህ
ከኋላም ከፊትም ከለልከኝ። 6 ዕውቀትህ
እጅግ የሚደንቅ ፥ ከአእምሮዬም እጅግ የሚ
ልቅ ይሆንብኛል።
7 ከመንፈስህ ወዴት ልሄድ እችላለሁ?
ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? 8 ወደ ሰማያት
ብወጣ ፥ በዚያ አንተ አለህ። ወደ ጥልቅ ባሕ
ርም ብወርድ ፥ አንተ ከዚያ ነህ። 9 ጐሕ
ሲቀድ እንደሚነሣ ንስር በርሬ ራቅ ካለው
የውቅያኖስ ዳርቻ ባርፍ ፥ 10 በዚያ እንኳ
እጅህ ይመራኛል ፤ ቀኝ እጅህም አጥብቆ
ይይዘኛል።
11 «በእርግጥ ጨለማ ይሰውረኛል»
ብል ፥ ሌሊቱ በዙርያዬ ብርሃን ይሆንብ
ኛል። 12 በአንተ ዘንድ ማታ አይጨልም
ምና ፤ ሌሊትም እንደ ቀን ያበራል ፤ ጨለማ
በአንተ ዘንድ ብርሃን ነውና።
13 አቤቱ ፥ አንተ ውሳጣዊ አካሌን ፈጥረ
ሃል ፤ በእናቴ ማኅፀን በጥበብ አገጣጥመህ
ሠራኸኝ። 14 ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአ
ለሁና አወድስሃለሁ ፤ ሥራህ ዕፁብ ድንቅ
መሆኑን ደኅና አድርጌ ዐውቃለሁ። 15 በእ
ናቴ ማኅፀን በስውር በተፀንስኩበት ጊዜ ፥
አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም። አካሌ
በምድር ውስጥ እርስ በርሱ በሚገጣጠም
በት ጊዜ ፥ 16 ገና ቅርጽ ያላገኘውን ሰውነ
ቴን ዓይኖችህ አዩ። ለዕድሜዬ ከወሰንካ
ቸው ዓመታት አንዱ እንኳ ሳይጀመር ዘመ
ኖቼ በሙሉ አስቀድመው በመጽሐፍህ
ተመዝግበዋል።
17 ፈጣሪዬ ሆይ ፥ አሳቦችህ በእኔ ዘንድ
ምንኛ ውዶችና የተከበሩ ናቸው! መጠናቸ
ውስ ምን ያህል የሰፋ ነው! 18 ብቈጥራ
ቸው ከምድር አሸዋ የበዙ ይሆናሉ።
አቤቱ፥ተኝቼ በምነቃበት ጊዜ ከአንተ ጋር
ነኝ።
19 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥በእርግጥ
አንተ ክፉዎችን ትገድላቸዋለህ። ስለዚህ
ደም የሚያፈሱ ሰዎች ከእኔ ይወገዱ!
20 ስለ አንተ በክፉ መንፈስ ይናገራሉና ፤
ተቃዋሚዎችህ ስምህን ያጐድፋሉ። 21 እግ
ዚአብሔር ሆይ፥የሚጠሉህን እኔ አልጠላኋ
ቸውምን? በአንተ ላይ ያመፁትንስ አልተጸ
የፍኋቸውምን? 22 እነርሱን ፍጹም በሆነ
ጥላቻ እመለከታቸዋለሁ፤ጠላቶቼም አድርጌ
እቈጥራቸዋለሁ።
23 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ፥ መርም
ረኝ ፤ ልቤንም ድረስበት ፤ ፈትነኝ ፤ አሳቤንም
ዕወቅ። 24 በውስጤ ክፋት እንዳለብኝ ተመ
ልክተህ በዘላለማዊው መንገድ ምራኝ።

## መዝሙር 140

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ከክፉ ሰዎች አስጥ
ለኝ ፤ ከጠበኞችም ጠብቀኝ ፤ 2 በልባቸው
ውስጥ የተንኰል ዕቅድ ያውጠነጥናሉና፤በየ
ዕለቱም ጦርነት ለመቀስቀስ ያስፈስፋሉና።
3 አንደበታቸው እንደ እባብ ምላስ የሰላ
ነው ፤ ከከንፈሮቻቸው የሚወጣው የእፉኝት
መርዝ ነው።
4 አቤቱ ፥ በክፉዎች እጅ እንዳልወድቅ
ጠብቀኝ፤እግሮቼን ጠልፈው ለመጣል ከሚ
ያደቡ ጠበኞች ሰዎች ከልለኝ። 5 ትዕቢተ
ኞች ወጥመዳቸውን በስውር አዘጋጅተውብ
ኛል ፤ መረባቸውን ዘርግተውብኛል ፤ በመንገ
ዴም አሽክላቸውን ጠምደውብኛል።

6 እግዚአብሔር ሆይ፥አንተን፥ «ፈጣሪዬ
ነህ» አልሁህ። አሁንም፥ማረኝ ብዬ የማቀር
ብልህን ልመና ስማኝ። 7 የሁሉ ገዢ የሆንህ
እግዚአብሔር ሆይ፥በውጊያ ላይ ጋሻ ሆነህ
የምትጠብቀኝ ጽኑ አዳኜ አንተ ነህና፥
8 አቤቱ፥ ክፉዎች በትዕቢት እንዳይወጠሩ
የተመኙትን አትስጣቸው፤ ዕቅዳቸውንም
አታሳካላቸው።

9 ዙርያዬን ያከበቡኝ ሁሉ፥ በአንደበታ
ቸው ተናግረው ያመጡት መከራ በየራሳ
ቸው ላይ ይውረድባቸው። 10 የእሳት ፍም
በላያቸው ይፍሰስባቸው፤ ለምን ጊዜውም
ተመልሰው እንዳይነሡ በእሳቱ ነበልባልና
ማጥ በበዛበት አዘቅት ውስጥ ይውደቁ።
11 የሰው ስም አጥፊዎች በአገሪቱ ውስጥ
ደልቷቸው አይኑሩ። ጠበኞችን ጥፋታቸው
እየተከታተለ ከውድቀት ያድርሳቸው።

12 እግዚአብሔር ለተጠቁት ትክክለኛ
ፍርድ እንደሚሰጥና ለችግረኞች መብታቸ
ውን እንደሚያስጠብቅ ዐውቃለሁ። 13 በእር
ግጥ ጻድቃን ስምህን ያወድሳሉ፤ ቅኖችም
በፊትህ ይኖራሉ።

## መዝሙር 141

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ወደ አንተ እጮኻለ
ሁና ፈጥነህ ድረስልኝ። ወደ አንተ በምጣ
ራበት ጊዜ ጩኸቴን ስማ። 2 ጸሎቴ እንደ
ዕጣን ሽታ ከፊትህ ይቅረብ፤ እጆቼን አን
ሥቼ የማቀርብልህ ምስጋና እንደ ምሽት
መሥዋዕት ይሁን።

3 አቤቱ፥ለአንደበቴ ዘብ አቁም፤ለከንፈሮ
ቼም ጠባቂ አድርግ። 4 ከዐመፀኞች ጋር በበ
ደል ሥራ እንዳልመሳጠር፥ልቤም በክፋት
እንዳይማረክ፥ ከድግሣቸውም እንዳልሳተፍ
አድርግ።

5 ጻድቅ ሰው ይቅጣኝ፤ እንደ ምሕረት
እቈጥረዋለሁ፤ ይገሥፀኝ፤ በራሴ ላይ እንደ
ፈሰሰ ቅባት ይሆንልኛል፤አልቀባውም አል
ልም።

ጸሎቴ ግን ምን ጊዜም በክፉ አድራጊ
ዎች ላይ ነው፤ 6 ገዢዎቻቸው ከገደል
አፋፍ ተወርውረው ይጣላሉ፤የተናገርኩት
ቃል ሳይፈጸም ስለማይቀር ለክፉዎች ትም
ሀርት ይሆናቸዋል። 7 እንዲህም ይላሉ፦
«ገበሬ ሲያርስ መሬቱን እየገመሰ ጓሉን
እንደሚያፈራርሰው ሁሉ፥ አጥንታችን እን
ዲሁ በመቃብር አፍ ላይ ተበትኖ ቀረ።»

8 የሁሉ ገዢ የሆንክ እግዚአብሔር
ሆይ፥እኔ ዓይኖቼን ወደ አንተ አቅንቼ እመ
ለከታለሁ፤አንተን ተማፅኛለሁና ለሞት አሳ
ልፈህ አትስጠኝ። 9 ክፉ አድራጊዎች እኔን
ለመጣል ካዘጋጁት ወጥመድ፥ ከዘረጉትም
አሽክላ አድነኝ። 10 እኔ በደኅና ሳልፍ፥ክፉ
ዎች ግን በዘረጉት መረባቸው ውስጥ ይው
ደቁ።

## መዝሙር 142

1 ልመናዬን ወደ እግዚአብሔር በጩ
ኸት አቀረብኩ፤እግዚአብሔር እንዲምረኝ
ድምፄን ከፍ አድርጌ አሰማሁ። 2 ብሶቴን
በፊቱ ዘርዝሬ እገልጻለሁ፤ ችግሬን አንድ
በአንድ እነግረዋለሁ።

3 መንፈሴ እየደከመ በሚሄድበት ጊዜ
መንገዴን የምታውቅ አንተ ነህ፤እነሆ በመ
ንገዴ ላይ ሰዎች ወጥመዳቸውን ሰውረውብ
ኛል። 4 ወደ ቀኝ አየሁ፤ ተመለከትሁ፤አይ
ዞህ የሚለኝ አንድም አላገኘሁም። መጠ
ጊያ የሚሆነኝ አጣሁ፤ለሕይወቴ የሚጠነቀ
ቅላት ማንም የለም።

5 እግዚአብሔር ሆይ፥ ወደ አንተ እጮኻ
ለሁ፤ እንዲህም እላለሁ፦ «አንተ መጠጊ
ያዬ፥ በሕያዋንም ምድር ዕድል ፈንታዬ
ነህ።» 6 ተስፋ በሚያስቈርጥ ችግር ላይ
ነኝና ልመናዬን ስማ፤የሚያሳድዱኝ እጅግ
ስለ በረቱብኝ አልቻልኳቸውምና ከእጃቸው
አስጥለኝ። 7 ስምህን አወድስ ዘንድ ከእስ
ራቴ ፈትህ ነጻ አውጣኝ። ለእኔ ከፈጸምከው
ቸርነትህ የተነሣ ጻድቃን በዙርያዬ ይሰበሰ
ባሉና።

## መዝሙር 143

1 እግዚአብሔር ሆይ፥ ጸሎቴን ስማ፤
ማረኝ ብዬ የማቀርብልህን ልመናዬን አድ
ምጥ፤ስለ ታማኝነትህና ስለ ጽድቅህ ስትል
እኔን ለማዳን ድረስልኝ። 2 አቤቱ፥እኔን አገ
ልጋይህን ወደ ፍርድ አደባባይ አውጥተህ
አታጋልጠኝ፤ በአንተ ፊት ጻድቅ የሆነ
ሕያው ፍጡር የለምና።

3 ጠላት እያሳደደኝ ነው፤ከመሬት እስከ
ደባለቅ አጕሳቈለኝ። ቀደም ብለው እንደ
ሞቱት በጨለማ ውስጥ እንድኖር አድርጎ
ኛል። 4 ስለዚህ መንፈሴ እየደከመ ሄደ፤
ልቤም ተስፋ ቈረጠ።

5 የድሮውን ዘመን አስታወስኩ፤ሥራዎች
ህን ሁሉ አሰላሰልኩ፤የእጆችህን ሥራ አጤ
ናለሁ። 6 እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ፤ ውሃ
እንደ ጠማት እንደ ቈላ መሬት ነፍሴ አን
ተን ተጠማች።

7 አቤቱ፥ፈጥነህ መልስልኝ፤መንፈሴ አን
ተን ከመናፈቁ የተነሣ ደከመ። ፊትህን

ከእኔ አትሰውር ፤ ወደ መቃብር እንደ ወረ
ዱት ሙታን እልሁን። 8የማለዳው ጉሕ
የማይለወጠውን ፍቅርህን ያሰማኝ ፤ በአንተ
ተማጽኛለሁና ፣ ነፍሴ ወደ አንተ ስላዘነበለች
ልከተለው የሚገባኝን መንገድ አሳየኝ።
9አንተን የሙጥኝ ብያለሁና አቤቱ ፣ ከጠላ
ቶቼ አስጥለኝ። 10የአንተን ፈቃድ እንድፈ
ጽም አስተምረኝ ፤ አንተ ፈጣሪዬ ነህና ፤
ቅዱስ መንፈስህ በጽድቅ ጐዳና ይምራኝ።
11እግዚአብሔር ሆይ ፣ ስለ ስምህ ብለህ
ሕይወቴን ጠብቅ ፤ ስለ ጽድቅህ ከመከራ
አውጣኝ። 12በማይለወጠው ፍቅርህ ጠላቶ
ቼን ዝም አሰኛቸው ፤ ተቃዋሚዎቼንም
ሁሉ አጥፋቸው ፤ እኔ አገልጋይህ ነኝና።

## መዝሙር 144

1እጆቼን ለጦርነት ፣ ጣቶቼንም ለውጊያ
ለሚያሠለጥናቸው ፣ መከታዬ ለሆነው ለእግ
ዚአብሔር ምስጋና ይሁን። 2የሚወደኝ
ፈጣሪዬ መጠጊያዬ ፣ መከላከያዬና መድኀኔ ፣
ሕዝቦችን ሰጥ ለጥ አድርጎ የሚያስገዛልኝ
የምተማመንበት ጋሻዬ እርሱ ነው።
3አቤቱ ፣ ይህን ያህል ትጠነቀቅለት
ዘንድ ፣ ይህን ያህልስ ታስብለት ዘንድ የሰው
ልጅ ከቶ ምንድን ነው? 4ሰው እንደ እስት
ንፋስ ነው ፤ ዕድሜውም እንደ ጥላ ፈጥኖ
ያልፋል።
5እግዚአብሔር ሆይ ፣ ሰማያትን ዝቅ አድ
ርግና ከመኖሪያህ ውረድ ፤ ይጨሱ ዘንድ
ተራሮችን ዳስሳቸው። 6መብረቆችን በፊትህ
ላክና ጠላቶችህን ይበታትኗቸው ፤ ፍላጻዎች
ህን እየወረወርክ ተከታትለህ አጥፋቸው።
7እጅህን ከሰማይ ዘርጋ ፤ በውቅያኖስ ውስጥ
ከመስጠምና በባዕዳን ከመገዛት አድነኝ ፤ አስ
ጥለኝም። 8አንደበታቸው በሽንገላ ፣ ቀኝ እጃ
ቸውም በሸፍጥ የተሞላ ነውና።
9እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ፣ አዲስ ቅኔ
ተቀኝቼ ፣ አሥር አውታር ያለውን በገና እየ
ደረደርኩ እዘምርልሃለሁ። 10ለነገሥታት
ድልን ለሚያጐናጽፍና አገልጋዩን ዳዊትን
ከተሠነዘረበት ሰይፍ ላዳነ ለእግዚአብሔር
በዜማ ምስጋና አቀርባለሁ።
11አንደበታቸው በሽንገላ ፣ ቀኝ እጃቸ
ውም በሸፍጥ ከተሞላ ከባዕዳን ሥልጣን
አድነኝ ፤ አስጥለኝም።
12ወንዶች ልጆቻችን በጐልማስነታቸው
መልካም እንክብካቤ እንደ ተደረገላቸው
አትክልት ፣ ሴቶች ልጆቻችንም ለቤተ መንግ
ሥት ጌጥ እንደ ተቀረጹ ዓምዶች ይሆ
ናሉ። 13ጐተራዎቻችን በእህል ይሞላሉ ፤
በጎቻችን በብዙ ሺህ በመራባት ፣ ማሰማሪያ
መስኮቻችንን ያለብሳሉ ፤ 14በሬዎቻችን
ከባድ ጭነት በመሸከም ያገለግላሉ። ቅጥሮ
ቻችን አይደፈሩም ፤ በምርኮ መወሰድም አይ
ኖርም ፤ በጐዳናዎቻችን ላይ የዋይታ ድምፅ
አይሰማም።
15ይህ እውን የሆነለት ሕዝብ የተባረከ
ነው ፤ እግዚአብሔር አምላኩ የሆነ ሕዝብ
የተባረከ ነው።

## መዝሙር 145

1ፈጣሪዬ አምላኬ ፣ ከፍ ከፍ አደርግሃ
ለሁ ፤ ስምህንም ለዘላለም ሳወድስ እኖራ
ለሁ። 2በየዕለቱ አወድስሃለሁ ፤ ስምህን ለዘላ
ለም ከፍ አድርጌ አመሰግናለሁ።
3እግዚአብሔር ታላቅ ነው ፤ ብቻውን
መወደስ የሚገባው ነው ፤ የታላቅነቱን
መጠን ከቶ ማንም ሊለካው አይችልም።
4ትውልዶች ሥራዎችህንና ኀይልህን እንዱ
ለሌላው በማስተላለፍ እያወደሱና እያሞገሱ
ይተርካሉ። 5ገናና ስለ ሆነው ስለ ግርማህ
ያሸበረቀ ክብር ይናገራሉ ፤ እኔም ድንቅ
ሥራዎችህን አሰላስላለሁ። 6እነርሱ ግሩም
ስለ ሆኑት ሥራዎችህ ኀይል ያስረዳሉ ፤
እኔም ስለ ታላላቅ ድርጊቶችህ በይፋ እናገ
ራለሁ። 7እነርሱ ስለ ሰፊው ቸርነትህ የመ
ታሰቢያ በዓል ያደርጋሉ ፤ ስለ ጽድቅህም
በደስታ ይዘምራሉ።
8እግዚአብሔር ለጋስና ርኅሩኅ ፣ ለቍጣ
የዘገየ ፣ ፍቅሩ ግን የበዛ ነው። 9እግዚአብ
ሔር ለሁሉ ቸር ነው ፤ ለፍጥረቱ ሁሉ ርኅ
ሩኅ ነው። 10አቤቱ ፣ አንተ የፈጠርኸው
ነገር ሁሉ ያወድስሃል ፤ ቅዱሳንህም ፣ «ብሩክ
ነህ» እያሉ ያመሰግኑሃል። 11የመንግሥት
ህን ገናና ክብር ፣ ኀያልነትህንም ይናገራሉ ፤
12በኀያልነትህ የፈጸምካቸውን ሥራዎችና
የመንግሥትህን ያሸበረቀ ገናና ክብር ለሰ
ዎች ሁሉ ያስታውቃሉ። 13መንግሥትህ
የዘላለም መንግሥት ናት ፤ ግዛትህም ከትው
ልድ ወደ ትውልድ ጸንቶ ይኖራል።
እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ሁሉ ለመፈ
ጸም የታመነ ነው ፤ የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ
ይወዳል። 14እግዚአብሔር ሊወድቁ የሚንገ
ዳገዱትን ይደግፋቸዋል ፤ በውርደት ያጐነበ
ሱትንም ቀና አድርጎ ያነሣቸዋል። 15የፍጥ
ረት ሁሉ ዓይን ወደ አንተ ይመለከታል ፤ አን
ተም በተገቢው ጊዜ ምግባቸውን ትሰጣቸዋ
ለህ። 16እጅህን ዘርግተህ ሕይወት ያለውን
የያንዳንዱን ፍጥረት ፍላጎት ታረካለህ።
17እግዚአብሔር በሚያደርገው ነገር

ሁሉ ጻድቅና ለፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ርኅ
ሩኅ ነው። 18እግዚአብሔር ለሚጠሩት
ሁሉ፥ አዎን፥ በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ
ቅርብ ነው። 19ለሚፈሩት፥ ፍላጎታቸውን
ያሟላላቸዋል፤ጸሎታቸውን ሰምቶ ያድናቸ
ዋል። 20እግዚአብሔር የሚወዱትን ሁሉ
ይጠብቃቸዋል ፤ ክፉዎችን ግን ሁሉንም
ያጠፋቸዋል።
21አንደበቴ የእግዚአብሔርን ውዳሴ
ይናገራል፤ፍጡር ሁሉ ቅዱስ ስሙን ለዘላ
ለም ያወድሰው።

## መዝሙር 146

1ሃሌ ሉያ!
ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን አወድሺ።
2ዕድሜዬን ሙሉ እግዚአብሔርን ሳወድ
ሰው እኖራለሁ ፤ በሕይወት በምኖርበት
ዘመን ሁሉ ፈጣሪዬን በዜማ አመሰግነዋ
ለሁ።
3ማዳን በማይችሉ ሟች በሆኑ ባለሥል
ጣኖች አትተማመኑ። 4ነፍሳቸው በምትለይ
በት ጊዜ ወደ አፈርነት ይመለሳሉ፤በሞታቸ
ውም ዕለት ዕቅዳቸው ሁሉ እንዳልነበረ
ይሆናል።
5የያዕቆብ አምላክ ረዳቱ የሆነለት፥ተስ
ፋውንም በፈጣሪው በእግዚአብሔር ላይ
የጣለ ሰው የተባረከ ነው። 6እግዚአብሔር
ለዘላለም የታመነ ሆኖ የሚኖር፥የሰማይና
የምድር ፥ የውቅያኖሶችና በውስጣቸው
ያለው ሁሉ ፈጣሪ ነው። 7እርሱ የተጠቁ
ትን በዓላማቸው ይደግፋቸዋል ፤ ለተራቡ
ትም ምግብ ይሰጣቸዋል። እግዚአብሔር
እስረኞችን ነጻ ያወጣቸዋል ፤ 8እግዚአብ
ሔር የዕውራንን ዓይን ያበራል ፤ እግዚአብ
ሔር የተዋረዱትን ከፍ ያደርጋቸዋል፤እግዚ
አብሔር ጻድቃንን ይወዳቸዋል፤ 9እግዚአብ
ሔር ስደተኞችን ይጠብቃቸዋል ፤ የሙት
ልጆችንና መበለቶችን ተከባክቦ ያኖራቸ
ዋል። የክፉዎችን መንገድ ግን ያጠፋል።
10ጽዮን ሆይ፥ አምላክሽ እግዚአብሔር
ትውልዶችን ሁሉ ሲገዛ የሚኖር የዘላለም
ንጉሥ ነው።
ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 147

1ሃሌ ሉያ!
ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን በዝማሬ
ማመስገን ምንኛ መልካም ነው! እርሱን
ማወደስ ምንኛ የሚያስደስትና የሚገባ
ነው!
2እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ያንጻታል፤
በምርኮ የተበተኑትንም እስራኤላውያን ይሰ
በስባቸዋል። 3በኃዘን ቅስማቸው የተሰበረ
ውን ይፈውሳል፤ቍስላቸውንም ይጠግናል።
4የከዋክብትን ብዛት ይወስናል፤እያንዳን
ዳቸውን በየስማቸው ለይቶ ይጠራቸዋል።
5ጌታችን እግዚአብሔር ታላቅ ፥ በሥልጣ
ኑም ኃያል ነው፤ለጥበቡ ድንበር የለውም።
6እግዚአብሔር ትሑታንን ከፍ ከፍ እያደ
ረገ ያኖራቸዋል ፤ ክፉዎችን ግን አዋርዶ
ይጥላቸዋል።
7ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙር
ዘምሩለት ፤ ለአምላካችን በበገና እየታጀባ
ችሁ አዚሙለት። 8እርሱ ሰማዩን በደመ
ናት ይሸፍናል፤በምድርም ላይ ዝናብ ያዘን
ባል፤ለምለም ሣር በየተራራው ላይ እንዲበ
ቅል ያደርጋል። 9ለቍራ ጫጩቶችና ለከብ
ቶች በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ምግባቸውን
ይሰጣቸዋል።
10በፈረስ ኃይል፥በእግረኛም ጦር በሚ
ተማመኑ አይደሰትም ፤ 11እግዚአብሔር፥
በሚፈሩትና እምነታቸውን በማይለወጠው
ፍቅሩ ላይ በሚጥሉት ደስ ይለዋል።
12ኢየሩሳሌም ሆይ፥ለእግዚአብሔር ከፍ
ያለ ምስጋና አቅርቢ፤ጽዮን ሆይ፥አምላክ
ሽን እግዚአብሔርን አወድሺ፤ 13እርሱ የበ
ሮችሽን መቀርቀሪያ አጠንክሮልሻል፤በክል
ልሽ ውስጥ የሚኖረውንም ሕዝብሽን ባርኮ
ልሻል። 14በወሰኖችሽ ዙርያ ሰላምን ሰጥቶ
ሻል ፤ እጅግ ባማረ የስንዴ ምርት አጥግቦ
ሻል።
15ትእዛዙን ወደ ምድር ይልካል ፤
ቃሉም ፈጥኖ ይተላለፋል። 16አመዳዩን
እንደ ባዘቶ በመሬት ላይ ያነጥፈዋል፤ውር
ጩን እንደ አመድ ይበትነዋል። 17በረዶ
ውን እንደ ጠጠር እያስፈነጠረ ያወርደ
ዋል። የቍሩን ኃይል ማን ይቋቋመዋል?
18በትእዛዙ፥ሁሉም ይቀልጣል፤ነፋሱን ቀስ
ቅሶ ሲያነፍሰው ውሃው እየፈሰሰ ይወር
ዳል።
19ቃሉን ለያዕቆብ፥ሕጉንና ድንጋጌዎ
ቹን ለእስራኤል ሕዝብ ገለጠላቸው። 20ይህ
ንን ለሌሎች ሕዝቦች አላደረገውም፤ሕጉን
አልገለጠላቸውም።
ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 148

1ሃሌ ሉያ!
በሰማያት ያላችሁ እግዚአብሔርን አወ
ድሱት ፤ በላይ በአርያም ሆናችሁ

አወድሱት። 2 መላእክቱ ሁሉ አወድሱት፤
የሰማይ ሠራዊቱ ሁሉ አወድሱት። 3 ፀሐ
ይና ጨረቃ አወድሱት፤እናንት ብሩሃን ከዋ
ክብት ሁሉ አወድሱት። 4 እናንት ሰማየ
ሰማያት አወድሱት፤ከጠፈር በላይ ያላችሁ
ውሆች አወድሱት። 5 እነዚህ ሁሉ የእግዚአ
ብሔርን ስም ያወድሱ፥በእርሱ ትእዛዝ ተፈ
ጥረዋልና። 6 ለዘላለም በማይሻር ድንጋ
ጌው ፥ እንዳይናወጡ አድርጎ በየቦታቸው
መድቦአቸዋል።

7 በምድር ያላችሁ፥እግዚአብሔርን አወ
ድሱት፤እናንት ግዙፋን የባሕር ተንቀሳቃሾ
ችና የውቅያኖስ ጥልቀቶች ሁሉ፥ 8 መብረ
ቅና በረዶ፥አመዳይና ደመናት፥የጌታን ትእ
ዛዝ የምትፈጽሙ ዓውሎ ነፋሳት፥ 9 እናንት
ተራሮችና ኰረብታዎች ሁሉ፥የፍሬ ዛፎ
ችና ዝግባዎች ሁሉ፥ 10 የዱር አራዊትና
የቤት እንስሳት ሁሉ፥በደረታቸው የሚሳቡ
ፍጡሮችና በክንፋቸው የሚበሩ አዕዋፍ፥
11 የምድር ነገሥታትና አሕዛብ ሁሉ፥መሳ
ፍንትና የምድር ባለሥልጣኖች ሁሉ፥
12 ጎልማሶችና ልጃገረዶች፥ሽማግሎችና ሕፃ
ናት እግዚአብሔርን አወድሱት።

13 እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም
ያወድሱ፤ የእርሱ ስም ብቻውን ገናና
ነውና፤ ክብሩ ከምድርና ከሰማያት በላይ
ከፍ ብሏልና። 14 እርሱ የሕዝቡን ሥል
ጣን፥የቅዱሳኑንና የሚወደውን የእስራኤልን
ሕዝብ ውዳሴ ከፍ ከፍ አድርጓል።

ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 149

1 ሃሌ ሉያ!

ለእግዚአብሔር አዲስ ቅኔ ተቀኙታችሁ
ዘምሩለት፤ በቅዱሳኑ ጉባኤ መካከል
በዜማ አወድሱት።

2 የእስራኤል ሕዝብ በፈጣሪው እጅግ
ደስ ይበለው፤የጽዮን ልጆች በንጉሣቸው
ሐሤት ያድርጉ። 3 በከበሮና በበገና ታጅ
በው እየጨፈሩና እያሸበሸቡ ስሙን ያወ
ድሱ። 4 እግዚአብሔር በሕዝቡ ተደስቷል፤
ለተዋረዱት ቤዛነቱን አቀዳጅቷቸዋል።
5 ቅዱሳን ይህን ክብር ስላገኙ እጅግ ደስ
ይበላቸው፤በመኝታቸው ላይ በደስታ ይዘ
ምሩ።

6 በአንደበታቸው የእግዚአብሔርን ምስ
ጋና ለመናገር ይዘጋጁ፤በእጃቸው በሁለት
ፌት ስለት ያለው ሰይፍ ይያዙ፤ 7 በአሕዛብ
ላይ በቀልን፥በሕዝቡም ላይ ቅጣትን ይፈ
ጽሙ፤ 8 ንጉሦቻቸውን በሰንሰለት፥መኳንን
ቶቻቸውንም በእግር ብረት ይሰሩ፤ 9 በእነ
ዚህ ላይ ተጽፎ የተሰጠውን ፍርድ ያስፈ
ጽሙ። ይህም የቅዱሳኑ ሁሉ ክብርና ድል
ነውና።

ሃሌ ሉያ!

## መዝሙር 150

1 ሃሌ ሉያ!

እግዚአብሔርን በመቅደሱ አወድሱት።
የኀያልነቱ መገለጫ በሆኑት በሰማያት አወ
ድሱት። 2 በሥልጣኑ ስለ ፈጸማቸው ሥራ
ዎቹ አወድሱት። ከሁሉ በላይ የሆነውን
ታላቅነቱን አወድሱ። 3 በመለከት ድምፅ
አወድሱት፤በበገናና በመሰንቆ አወድሱት፤
4 በከበሮና በሽብሸባ አወድሱት፤ በክራርና
በእምቢልታ አወድሱት፤ 5 ድምፁ በሚያስ
ተጋባና በሚንሿሿ ጽናጽል አወድሱት።

6 እስትንፋስ ያለው ፍጡር ሁሉ እግዚአ
ብሔርን ያወድስ።

ሃሌ ሉያ!